# የተሻሻለው የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ደንብ

**ይህ ዕትም ከዚህ በፊት ያሉትን ዕትሞች የሚተካ ነው።** **ማሻሻያ ቁጥር** 8/2007

**ጥቅምት** 2007፣ **አዲስ አበባ**

ማውጫ

1. መግቢያ ..... 3
2. ትርጓሜ ..... 3
3. የምርት ገበያ ሥራ አመራር ..... 10
4. ስለምርት ገበያ አባልነት ..... 14
5. በምርት ገበያው ላይ ንግድ ማካሄድ ..... 28
5.7 ግብይት መሰረዝ ..... 48
6. ለደንበኛ ወይም ለራስ ስለመገበያየት ..... 48
7. ውሎች ..... 52
8. ስለማከማቻ መጋዘን አሰራር ..... 56
9. የማከማቻ መጋዘን አገልግሎት ደረሰኝ ..... 63
10. ክፍያና ርክክብ አፈፃፀም ..... 71
11. ርክክብ ..... 82
12. የክፍያና ርክክብ መፈጸሚያ ዋስትና ፈንድ ..... 84
13. የገበያ መረጃ ስርጭት ..... 86
14. የአባል የሥራ አካሄድ ደንብ ..... 87
15. ዲሲፕሊን እና አፈጻጸም ..... 92
16. የግልግል/የሽምግልና ዳኝነት፣ ዕርቅ እና የባለሙያ ውሳኔ ..... 97
17. ቁጥጥር ..... 110
18. የኃላፊነት ወሰን ..... 112
19. የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች ..... 112
20. ሚስጢር ስለመጠበቅ ..... 114
21. ደንብ ስለማሻሻል ..... 115
22. የደንቡ ድንጋጌዎች በተናጠል የሚታዩ ስለመሆናቸው ..... 115
23. ማስታወቂያዎች ..... 115
24. ስለ ደንቡ ተፈጻሚነት ..... 115

## 1. መግቢያ

1.1 የተሻሻለውን የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ደንብ ቁጥር 7/2005'ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

1.2 የኢትዮጵያ ምርት ገበያ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 550/1999 (ከዚህ በኋላ "የምርት ገበያ አዋጅ"ተብሎ ይጠቀሳል።) አንቀጽ 12 (10) መሠረት ይህን ማሻሻያ ደንብ አውጥቷል።

1.3 ይህ ደንብ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን (ከዚህ በኋላ "ባለሥልጣን"ተብሎ ይጠቀሳል።) በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 551/1999 አንቀጽ 6(3) በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ካጸደቀው በኋላ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ (ከዚህ በኋላ "የምርት ገበያ" በመባል ይጠቀሳል።) የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚወስነው ቀን ተፈጻሚ ይሆናል።

1.4 ይህ ደንብ በምርት ገበያው ወዲያውኑ በሚፈጸም ውል ላይ የሚደረግ ግብይት የሚመራበት ይሆናል። ደንቡ የምርት ገበያው በስራ ላይ ሲያውለው ወደፊት በሚፈጸም ውል ላይ የሚደረግ ግብይትም የሚመራበት ይሆናል።

1.5 ይህ ደንብ "ደንብ" ወይም "የተሻሻለው የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ደንብ ቁጥር 8/2007" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

1.6 ይህ ደንብ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 550/1999 እና የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 551/1999 ተጨማሪ ነው።

1.7 በዚህ ደንብ ድንጋጌዎችና በምርት ገበያው አዋጅ ወይም በባለስልጣኑ አዋጅ ድንጋጌዎች መካከል ልዩነት ሲኖር አዋጆቹ የምርት ገበያው ደንብ ተፈፃሚነትን ካልፈቀዱ በቀር ከሁለቱ አዋጆች የአንደኛው ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ያገኛሉ።

1.8 በዚህ ደንብ "የእሱ" ወይም "እሱ" በሚል አነጋገር የተገለጸው "ለእርሱ/ለእርሷ" ወይም "እሱ/እሷ" የሚለውን ይገልጻል።

## 2. ትርጓሜ

2.1 በዚህ ደንብ ከዚህ በታች በመጀመሪያው ረድፍ የተመለከቱት ቃላቶች ከተካተቱበት ሃሳቦች ጋር የሚቃረኑ ካልሆነ በቀር፣ በያንዳንዱ ቃል ትይዩ በሁለተኛው ረድፍ የተቀመጠው ትርጓሜ ይገልጻቸዋል፤

| ቃላት | ትርጓሜ |
|---|---|
| 2.1.1 በከለላ መንገድ መገበያየት | ሌላ ሰው ሕገ ወጥ ግብይት እንዲፈጽም ለማገዝ ታስቦበት ውድድር እንዳይኖር ለማድረግ መስማማት ነው፤ |

| | |
|---|---|
| 2.1.2 የግልግል/የሽምግልና ዳኛ ወይም የግልግል/የሽምግልና ዳኞች ጉባዔ | በቀረበለት የተከራካሪ ወገኖች ያለመግባባት ጉዳይ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ በምርት ገበያው የተሰየመ ገለልተኛ ወገን ነው፤ |
| 2.1.3 አመልካች | የግልግል ዳኝነቱ ጉዳዩን እንዲያይለት የሚያመለክት ሰው ነው፤ |
| 2.1.4 ተባባሪ አባል | በአገናኝ አባል አማካኝነት ለደንበኞቹ የሚነግድ ወይም ጉዳያቸውን የሚከታተል አባል ነው፤ |
| 2.1.5 የባለሥልጣኑ አዋጅ | የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 551/1999 ነው፤ |
| 2.1.6 የተፈቀደለት ተወካይ | ንግድን (ግብይትን) በተመለከተ አባልን የሚወክል በባለሥልጣኑ ዕውቅና ያገኘ ሰው ነው፤ |
| 2.1.7 ምርጥ የግዢ ትዕዛዝ | ከፍተኛ ዋጋ የተሰጠበት የግዢ ትዕዛዝ ነው፡፡ |
| 2.1.8 ምርጥ የሽያጭ ትዕዛዝ | ዝቅተኛ ዋጋ የተሰጠበት የሽያጭ ትዕዛዝ ነው፡፡ |
| 2.1.9 ቦርድ | በአዋጅ ቁጥር 550/1999 መሠረት የተቋቋመ የኢትዮጵያ የምርት ገበያ የዳይሬክተሮች ቦርድ ነው፤ |
| 2.1.10 ተቃራኒ አቋም መያዝ | አንድ አባል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በራሱ ስም ወይም የእርሱ ጥቅም ባለበት በሌላ ሰው ስም በምርት ገበያው መገበያያ መድረክ ግልጽ ባልሆነና ውድድር በሌለበት ሁኔታ ከደንበኛው ትዕዛዝ ተቃራኒ የሆነውን አቋም መያዝ ነው ፤ |
| 2.1.11ማዕከላዊ ማከማቻ | በምርት ገበያው የተደረጉ ግብይቶች እንደዚሁም በደረሰኞች አማካይነት የሚደረግ ርክክብ በእንጥልጥል ላይ እያለ የኤሌክትሮኒክስ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞችን በባላደራነት የማስቀመጥሥራን የሚያከናውን የምርት ገበያው ክፍል ነው፤ |

| | |
|---|---|
| 2.1.12 የክፍያ መፈጸሚያ ክፍል | የግብይቶችን የክፍያና ርክክብ አገልግሎት የሚሰጥና በምርት ገበያው ስም ለአባላት ለርክክብ ዋስትና የሚሰጥ በክፍያ ተቋምነት ዕውቅና ያገኘ የምርት ገበያው ክፍልነው፤ |
| 2.1.13 የክፍያ መፈጸሚያ ተቋም | የምርት ገበያው ወይም በባለስልጣኑ እውቅና ያገኘ የአገር ውስጥ ባንክ ወይም የክፍያ መፈጸሚያ ባንክ ወይም ተመሳሳይ የፋይናንስ ተቋም ነው፤ |
| 2.1.14 ምርት | ከሌላ አንድ ዓይነት ምርት ጋር መለዋወጥ የሚችል ምርት ነው፤ |
| 2.1.15 ውል | ለምርት ገበያ ግብይት ሲባል አንድን ምርት ለመግዛት ወይም ለመሸጥ ወጥ ሆኖ የተዘጋጀና የምርቱን መጠንና ዋጋ፣ ደረጃ፣ ተፈፃሚ የሚሆንበትንና የምርቱ ርክክብ የሚፈጸምበትን ቀን በዝርዝር የሚያትት ስምምነት ነው፤ |
| 2.1.16 ምርትን ከገበያ ማስወገድ | የምርትን በገበያ ውስጥ ያለውን ምርት በተመለከተ ለማሳሳት በምርት ገበያ ለሽያጭ ከቀረበ ምርት ውስጥ ከፍተኛ ፐርሰንቴጅ መግዛት እና/ወይም የምርቱን ዋጋ ያለአግባብ ካናረ በኋላ በትርፍ መሸጥ ነው፤ |
| 2.1.17 ግዢና ሽያጭን ስለማቻቻልና ስለማስታረቅ (ተቋራጭ ግብይት) | የአንድን ደንበኛ የግዢ ትዕዛዝ ከሌላ ደንበኛ የሽያጭ ትዕዛዝ በመገበያያ መድረክ ግልጽ ባልሆነና ውድድር በሌለበት ሁኔታ ማቻቻል ወይም ወድድር በሌለበት ሁኔታ ማስታረቅ ነው፤ይህ አሰራር የሚፈቀደው በዚህ ደንብ አንቀጽ 5.5.19.4 መሰረት ተፈጻሚ ከሆነ ብቻ ነው፤ |
| 2.1.18 ርክክብ | በዚህ ደንብ በተደነገገው መሠረት በማዕከላዊ ማከማቻው አማካይነት ለገዢው የባለቤትነት መብትን ማስተላለፍና ምርቱን ማስረከብ ነው፤ |
| 2.1.19 የተሰየመ የምርት ገበያ የዕቃ ማከማቻ ሠራተኛ | ምርቶችን ለመመዘን፣ ደረጃ ለማውጣትና ለመሰየም በሚያስችል መልኩ የመመዝገብና የማስተዳደር ሥራ የሚያከናውን እንዲሁም የምርት ገበያውን ምርት መቀበያ ደረሰኝ የሚሰጥ በምርት ገበያው የተመሰከረለትና በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ወይም በሚኒስቴሩ ለዚሁ ዓላማ በተወከለ ተቆጣጣሪ አካል የተመዘገበ ሶስተኛ ሰው ነው፤ |

| | |
|---|---|
| 2.1.20 የተሰየመ የምርት ገበያ የዕቃ ማከማቻ | በዚህ ደንብ መሠረት ምርቶች የተከማቹበት ወይም የተቀመጡበት ሶስተኛ ሰው በባለቤትነት የያዘውና የሚያካሂደው በዕቃ ማከማቻ ሥራ አስኪያጅ ሕጋዊ ይዞታና ብቸኛ ቁጥጥር ሥር ያለ ሕንፃና ሕንፃው የሚገኝበት ግቢና አጎራባች ቦታ ነው፤ |
| 2.1.21 ልዩ የቀጥታ ንግድ | አምራቾች ልዩ ምርቶችን በቀጥታ ለአለም አቀፍ ገዥዎች ወደ ውጭ የሚልኩበት ሁኔታ የሚመቻችበት ሥርዓት ነው፤ |
| 2.1.22 የኤሌክትሮኒክስ የዕቃዎች መቀበያ ደረሰኝ | ምርቶችን ስለመረከቡ የሚያሳይ /የሚያረጋግጥ/ በዕቃ ማከማቻው ቦታ በሥራ አስኪያጁ የሚሰጥ ሰነድ ነው፤ |
| 2.1.23 ኤሌክትሮኒክ ግብይት | በምርት ገበያው ኤሌክትሮኒክ ግብይት መድረክ የተፈጸመ ግብይት ነው፡፡ |
| 2.1.24 ኤሌክትሮኒክ ግብይት መድረክ | የተፈቀደላቸው ተወካዮች በአውቶሜትድ ስክሪን አማካኝነት ጨረታ የሚያካሂዱበት የመገበያያ ስርዓት ነው ፡፡ |
| 2.1.25 ኤልክትሮኒክ ግብይት ተወካይ | በምርት ገበያው ኤሌክትሮኒክ ግብይት መድረክ ላይ የግብይት ትዕዛዞች እንዲፈፅም የተፈቀደለት የአባል ተወካይ ነው፡፡ |
| 2.1.26 የምርት ገበያ የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ | ዕቃ ማከማቻው ለተረከበው ምርት ለምርት አስቀማጩ የባለቤትነት መብት የሚሰጥ /የሚያጎናፅፍ/ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው እንዲተላለፍ የተፈቀደ በማዕከላዊ ማከማቻ የሚሰጥ የኤሌክትሮኒክስ ምርት ገበያ ደረሰኝ ነው፤ |
| 2.1.27 ግብይት ፈጻሚ | ለሌሎች ወይም ለራሱ ሲል የምርት ገበያ ውሎችን በመግዛትና በመሸጥ ንግድ ሥራ የተሠማራ በባለስልጣኑ ዕውቅና ያገኘ ማንኛውም ሰው ነው፤ |
| 2.1.28 የምርት ገበያ አዋጅ | የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 550/1999 ነው፤ |

| | |
|---|---|
| 2.1.29 የወጪ ንግድ አገልግሎት ሰጪ | በልዩ የቀጥታ ንግድ ለሚሳተፉ አምራቾች ምትክ ሆኖ የወጪ ንግድ ዝግጅት አገልግሎት የሚሰጥና የሚያሳልጥ የምርት ገበያ አባል ነው፤ |
| 2.1.30 ተተኪ ምርት | በተፈጥሮ ወይም በተለመደው የንግድ አሠራር አንደኛው ክፍል ለሌላኛው ተመጣጣኝ ወይም ምትክ ተደርጎ የሚወሰድ ምርት ነው፤ |
| 2.1.31 ለወደፊት የሚፈጸም ውል | በተቆረጠ የወደፊት ቀን የምርት ርክክብ የሚፈጸምበት ምረትን ለመሸጥ ወይም ለመግዛት የሚደረግ የምረት ገበያ ውል ነው፤ |
| 2.1.32 የመገበያያ መድረክ ተወካይ | በመገበያያ መድረክ ላይ የግብይት ትዕዛዞችን እንዲፈፅም የተፈቀደለት አባል ወይም የተፈቀደለት ተወካይ ነው፤ |
| 2.1.33 ደረጃ መስጠት | እያንዳንዱን የምርት መደብ በመመርመር የተወሰነ የጥራት ደረጃ የሚያሟላ ሆኖ ሲገኝ በምርት ገበያው የወጣውን ደረጃ መስጠት ነው፤ |
| 2.1.34 የደረጃ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት | የምርት ገበያው ባወጣው የደረጃ መመዘኛ መሠረት በዕቃ ማከማቻ የተቀመጠ ምርትን የጥራት ደረጃ የሚገልጽ በእቃ ማከማቻ ሰራተኛ ለአስቀማጩ የሚሰጥ ሰነድ ነው፤ |
| 2.1.35 መመሪያ | ደንበኛ የምርት ገበያው ውል ለመግዛት ወይም ለመሸጥ ለአገናኝ አባሉ የሚያስተላልፈው የግዥ ወይም የሽያጭ መመሪያ ነው።” |
| 2.1.36 አባል | በምርት ገበያው የሚጠየቀውን መመዘኛ ያሟላና በባለሥልጣኑ በግብይት ፈጻሚነት ዕውቅና ያገኘ ሰው ነው፤ |
| 2.1.37 የአባልነት መቀመጫ | በምርት ገበያው የመገበያየት ቋሚ፤ የሚተላለፍና ብቸኛ መብት የሚሰጥ ወይም የሚያጐናጽፍ በምርት ገበያው መድረክ ላይ ለመነገድ የተሰጠ ቋሚ የሚተላለፍ ብቸኛ መብት ነው፤ |
| 2.1.38 ሚኒስቴር | የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድ ሚኒስቴር ነው፤ |
| 2.1.39 ትዕዛዝ | በምርት ገበያው ግብይት መድረክ ላይ የምርት ገበያ ውል ለመግዛት ወይም ለመሸጥ የግብይት ተወካይ የሚያስተላልፈው የግዥ ወይም የሽያጭ ትዕዛዝ ነው። |

| | |
|---|---|
| 2.1.40 የማዘዣ ቲኬት | የትእዛዞችና የግብይቶች ዝርዝር የሚመዘገብበት በምርት ገበያው የቅደም ተከተል ቁጥሮች የተሰጠውና በህትመት አስቀድሞ የተዘጋጀ ካርድ ነው፤ |
| 2.1.41 ያልተፈጸመ ግዴታ | አንድ ተዋዋይ ወገን በውል ከተጣሉበት ግዴታዎች ውስጥ የመፀሚያው ጊዜ ያለፈ ወይም ያልተፈፀመ ግዴታ ነው፤ |
| 2.1.42 ሰው | የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤ |
| 2.1.43 የጋራ ሂሳብ | የደንበኞችን የመግዢያ ገንዘብ ለማስገባት እና የሽያጭ ገንዘብን ለመቀበል በምርት ገበያው አገናኝ አባል የሚከፈት የባንክ ሂሳብ ነው፡፡ ይህ ሂሳብ የተለየ ሂሳብ የሌላቸውን ከአንድ በላይ የሆኑ ደንበኞችን የግብይት ግዴታዎችን ለመክፈል ያገለግላል፡፡ |
| 2.1.44 የአባላት መዝገብ | በምርት ገበያ የተመዘገቡ አባላት ስሞችንና ሌሎች ዝርዝሮችን የያዘ የመረጃ ማከማቻ /ዳታ/ ወይም መዝገብ ነው፤ |
| 2.1.45 መልስ ሰጭ ወይም ተጠሪ | የሚቀርብበት የመብት ጥያቄ ቢኖርም ባይኖርም እንድ አመልካች በግልግል ዳኝነት ማመልከቻ እንዲጠየቅለት የሚፈልገው ሰው ነው፤ |
| 2.1.46 ዋስትና ያለው አበዳሪ | ግዙፍነት ያለውን ንብረት በመያዣነት በመያዝ ገንዘብ የሚያበድር ግለሰብ ወይም ተቋም ነው፤ |
| 2.1.47 ተቀማጭ የዋስትና ገንዘብ | ለምርት ገበያው የክፍያና ርክክብ ዋስትና ፈንድ የሚዋጣ ለአባልነት የሚጠየቅ ተቀማጭ ገንዘብ ነው፤ |
| 2.1.48 የተለየ ሂሳብ | የአንድ ደንበኛን የመግዢያ ገንዘብ ለማስገባት እና የሽያጭ ገንዘብን ለመቀበል በምርት ገበያው አገናኝ አባል የሚከፈት የባንክ ሂሳብ ነው፡፡ ይህ ሂሳብ የአንድ ደንበኛን የግብይት ግዴታዎችን ለመክፈል ያገለግላል፡፡” |
| 2.1.49 የክፍያ መፈፀሚያ ባንክ | አባላት በምርት ገበያው የፈፀሙትን /ያደረጉትን/ ግብይቶች የሚያስፈጽም በባለሥልጣኑ በክፍያ መፈፀሚያ ተቋምነት እውቅና አግኝቶ በምርት ገበያው ተቀባይነት ያገኘ የሀገር ውስጥ ባንክ ነው፤ |
| 2.1.50 ልዩ ምርት | ባለው የተለየ ባህርይ በተለይም ምርቱ በተመረተበት መልከዐ ምድር ምክንያት ያለውን ጥራት ወይም የተሰጠውን የምስክር ወረቀት ጨምሮ በገበያ ካለው መደበኛ ምርት ብልጫ ያለው ምርት ነው፤ |

| | |
|---|---|
| 2.1.51 ወዲያዉኑ የሚፈፀም ውል | ግብይት በተፈፀመበት እለት ክፍያ የሚፈፀምበትና ግብይቱ በተፈፀመ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ የምርት ርክክብ የሚፈፀምበት /የሚከናወንበት/ የምርት ገበያው የመገበያያ ውል ነው፤ |
| 2.1.52 ያለማንም ጣልቃ ገብነት / በቀጥታ/ የሚካሄድ ግብይት | በመመሪያ/በተቀመጠው የቁጥጥር ሥርዓት/ እና በህግ የተቀመጡት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው፣ አገናኝ አባል መመሪያውን ወደ ምርት ገበያው የግብይት ስርዓት ደግሞ ማስገባት ወይም እርዳታ ማድረግ ሳያስፈልግ በኤሌትሮኒክ መንገድ የደንበኛ መመሪያን በቀጥታ ወደ ትዕዛዝ የመቀየር አሰራር ነው፡፡" |
| 2.1.53 የመገበያያ መድረክ | የመድረክ ተወካዮች በቃል በማስተጋባት ጨረታ የሚያካሂዱበት የመገበያያ ቦታ ወይም የምርት ገበያው ያዘጋጀው ሌላ የመገበያያ ሥርዓት ነው፤ |
| 2.1.54 የግብይት ተወካይ | የመገበያያ መድረክ ወይም የኤሌክትሮኒክ ግብይት ተወካይ ነው፡፡ |
| 2.1.55 የግብይት ክፍለ ጊዜ | በአንድ ውል ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ውሎች ላይ ግብይት የሚካሄድበት የተወሰነ ጊዜ ነው፤ |
| 2.1.56 የግብይት ሥርዓት | ተስማሚ በሆኑ በማናቸውም ዘዴዎች ስለዋጋ አሰጣጥ ወይም ስለሌሎች ጉዳዮች ለአባላት መረጃ የሚተላለፍበት እንዲሁም በምርት ገበያው የሚፈፀሙ ግብይቶች፣ ግብይት የሚፈፀምባቸው ምርቶች መጠንና ተዛማጅ የሆኑ ሌሎች የምርት ገበያው ማስታወቂያዎች የሚተላለፉበት በምርት ገበያው የተቀመጠ ሥርዓት ነው፤ |
| 2.1.57 አባልነትን ማስተላለፍ | የአባልነት መቀመጫን በሽያጭ፤ በስጦታ ወይም በሌላ በማናቸውም ዘዴ ማስተላለፍ ነው፤ |
| 2.1.58 የዕቃ ማከማቻ ሠራተኛ | በሚኒስቴሩ ወይም ለዚሁ ዓላማ በሚኒስቴሩ በተወከለ ሌላ ተቆጣጣሪ አካል የተመዘገበ ምርት ገበያ ወይም ሌላ ሶስተኛ ሰው ነው፤ |
| 2.1.59 የማስመሰል ግብይት | ምንም ዓይነት አደጋ በማያስከትልበት ወይም የተገበያዩን የገበያ አቋም በማይቀይርበት ሁኔታ ግዢዎችና ሽያጮች እንደተከናወኑ ለማስመሰል ግብይት መፈፀም ወይም ግብይት የተፈፀመ ማስመሰል ነው። |
| 2.1.60 የሥራ ማከናወኛ መሣሪያ | በምርት ገበያው የጸደቀ ማንኛውም የኤሌክትሮኒክ ግብይት ማካሄድ የሚቻልበት መሳሪያ ነው፡፡" |

# 3. የምርት ገበያ ሥራ አመራር

## 3.1 የዳይሬክተሮች ቦርድ

3.1.1 የዳይሬክተሮች ቦርድ የምርት ገበያውን የሥራ አመራር በበላይነት ይቆጣጠራል ።
3.1.2 ቦርዱ አስራአንድ አባላት ሲኖሩት ሊቀመንበሩን ጨምሮ ስድስቱ አባላት በሚኒስቴሩ ይሾማሉ፣ የተቀሩት አምስቱ በምርት ገበያው አባላት ይመረጣሉ።
3.1.3 የምርት ገበያው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ድምፅ የማይሰጥ የቦርድ አባል ይሆናል።
3.1.4 ሚኒስቴሩ የምርት ገበያው ተቆጣጣሪ አካል ይሆናል።
3.1.5 ሚኒስቴሩ ቢያንስ ከመንግስት ወገን ያልሆኑ ሁለት ገለልተኛ የቦርድ አባላትን ሊሾም ይችላል።
3.1.6 የምርት ገበያው አባላት የቦርዱ ዳይሬክተሮችን ለመምረጥ ጠቅላላ ጉባኤ ያካሂዳሉ።
3.1.7 የምርት ገበያው አባላት የሚመርጧቸው የቦርድ ዳይሬክተሮች በተለያዩ የምርት ዘርፍ በተመጣጠነ ሁኔታ ይሆናል።
3.1.8 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል የሥራ ዘመን ሦስት ዓመታት ይሆናል። የቦርድ ዳይሬክተሮች እስከ ሦስት የስራ ዘመን እንደገና ሊሾሙ ወይም ሊመረጡ ይችላሉ።
3.1.9 የቦርድ ዳይሬክተሮች ሥራቸውን ሳያቋርጡ እንዲያከናውኑ ለማድረግ የሁሉም የሥራ ዘመን በአንድ ጊዜ እንዲያበቃ አይደረግም።
3.1.10 የቦርዱ ዳይሬክተሮች ቦታ ክፍት በሚሆንበት ጊዜ ሥራውን የለቀቀው ዳይሬክተር በተሾመበት ወይም በተመረጠበት ሁኔታ ሌላ ሰው እንዲመርጡ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጉዳዩን ሚኒስቴሩ ወይም የምርት ገበያው አባላት እንዲያውቁት ያደርጋል።

## 3.2 የቦርዱ ሥልጣንና ተግባራት

3.2.1 ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤
3.2.1.1 የምርት ገበያውን ዋና ስራ አስፈፃሚ ይሾማል፣
3.2.1.2 የምርት ገበያውን የስራ አመራር በበላይነት ይቆጣጠራል፣

3.2.1.3 የምርት ገበያውን ድረጅታዊ አወቃቀር፤ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞችን ያፀድቃል፣
3.2.1.4 ለዋና ስራ አስፈፃሚ ተጠሪ የሆኑ የስራ ኃላፊዎችን ቅጥር፤ የስራ ምደባና ስንብት እንዲሁም ደመወዝና አበል ያፀድቃል፣
3.2.1.5 የምርት ገበያውን የስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የስነ ምግባር ደንብ ያፀድቃል፣
3.2.1.6 የምርት ገበያውን ድርጅታዊ ዕቅድና ግብ፤ የምርት ግብይት አገልግሎት ክፍያ አደረጃጀት እና የአደጋ ቁጥጥር አስተዳደር ስትራቴጂን ያፀድቃል፣
3.2.1.7 የተጣራ ትርፍ ለተወሰኑ ስራዎች ወይም ለኢንቨስትመንት እንዲውል መደረጉን ያፀድቃል፣
3.2.1.8 የምርት ገበያው ካፒታል እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ ለሚኒስቴሩ ሃሣብ ያቀርባል፣
3.2.1.9 የምርት ገበያው የሂሣብ መዝገብ በአግባቡ መያዙን ያረጋግጣል፣
3.2.1.10 ለምርት ገበያው ኦዲተሮች የሂሣብ መግለጫ ያቀርባል፣
3.2.1.11 በየሩብ ዓመቱ የፋይናንስና የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርቶች ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣

3.2.1.12 በባለስልጣኑ መጽደቅ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አባልነትን፣ የንግድን የክፍያና ርክክብ አፈጻጸምን፣በምርት ገበያውየሚከናወኑ የግብይት ውሎችን የሚመለከቱ የምርት ገበያውን ደንቦችና መመዘኛዎች ያወጣል፣ ያሻሽላል፣
3.2.1.13 በባለስልጣን በፀደቀው የምርት ገበያው የውስጥ ደንብ ላይ በተደነገገው መሠረት የምርት ገበያውን አዲስ አባል ይቀበላል፣ ከአባልነት ያግዳል ወይም ያሰናብታል፣
3.2.1.14 በምርት ገበያው የተዘረጋው የግልግል ዳኝነት ሥርዓት በአግባቡ መስራቱን ያረጋግጣል፣
3.2.1.15 የቦርዱን ጸሐፊ ከምርት ገበያው ሠራተኞች መካከል መርጦ ይመድባል ፣
3.2.1.16 የምርት ገበያው አስተዳደርን ለማቀላጠፍ የሚያግዙ የተለያዩ መምሪያዎችንና ክፍሎች ያቋቁማል እንዲሁም
3.2.1.17 የምርት ገበያውን በአግባቡ ለመምራት የሚያስፈልጉ የተለያዩ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል::

3.3 የምርት ገበያው ኮሚቴዎች

3.3.1 ቦርዱ ለምርት ገበያው አስተዳደር አስፈላጊ የሆኑ የምርት ገበያው ሠራተኞችን፣ አባላትንና ሌሎችን ያቀፈ ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል:: የኮሚቴዎቹ አባላት ቁጥር በቦርዱ ይወሰናል::
3.3.2 ቋሚ ኮሚቴዎቹ የሚከተሉትን የሚያካትት ሊሆን ይችላል፤
3.3.2.1 የግብይት ውሎች፣
3.3.2.2 ምርት ግብይት ማስፋፊያና ማበልጸጊያ፣
3.3.2.3 በጀት፣
3.3.2.4 የግብይት አፈፃፀም፣
3.3.2.5 የአባላት የግብይት አፈጻጸም፣
3.3.2.6 የሸማቾች ጥበቃ፣
3.3.2.7 የኢንቨስትመንትና የካፒታል ማጠናከሪያ /ማጎልበቻ/፣
3.3.2.8 የሰው ኃይል ሀብት እና
3.3.2.9 ሌሎች በገበያው ስራ አመራር አስፈላጊነታቸው የታመነባቸው።
3.3.3 የምርት ገበያው አማካሪ ኮሚቴ
ቦርዱ ለተወሰነ ምረት ወይም የምርት ዓይነቶች በቂ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችንና የምርት ገበያው ኃላፊዎች የሚኖሩበት የምርት ገበያው አማካሪ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል። ባለሙያዎቹ ምረት ገበያው አባላት ወይም ሌሎች በመስኩ ልዩ ሙያ ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ።
3.3.4 የኮሚቴዎቹ የስብሰባ ሥነ ሥርዓት
3.3.4.1 የእያንዳንዱ ኮሚቴ አንድ ሶስተኛው አባላት ወይም ሁለት አባላት የትኛውም ቢሆን የበለጠው ከተገኙ ምልዕተ ጉባዔ ይኖራል።
3.3.4.2 የምርት ገበያው ደንብ እንደተጠበቀ ሆኖ የኮሚቴው ስብሰባ የሚመሩበት ደንብ የቦርድ የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ይሆናል።

3.3.5 ኮሚቴዎቹን በተመለከተ ቦርዱ ያለው ስልጣን

ቦርዱ የኮሚቴው አባልነትን የማቋረጥ ወይም የማገድና ከአባልነት የማሰናበት ወይም ማንኛውንም ኮሚቴ የማፍረስ ስልጣን አለው።ቦርዱ የኮሚቴውን የውሳኔ ሃሳብ የማሻሻል፣ የማስተካከል፣ የመለወጥ ወይም በከፊል የመቀበል ስልጣን አለው።የኮሚቴው ሚና ቦርዱ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት እንዲያስችለው የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ ሲሆን ውሳኔውም በውሳኔ ሃሳብነት የሚወሰድ ነው።

3.4 የዳይሬክተሮች ቦርድ የስብሰባ ሥነ ሥርዓት

3.4.1 ቦርዱ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል።

3.4.2 አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም ቢያንስ አራት የቦርድ ዳይሬክተሮች ሲጠይቁ ወይም ዋና ስራ አስፈጻሚው ሲጠይቅ ሊቀመንበሩ ስብሰባ ይጠራል።

3.4.3 የቦርድ የስብሰባ አጀንዳ ለዳይሬክተሮች በቅድሚያ መድረስ ይኖርበታል።

3.4.4 አብዛኞዎቹ የቦርድ አባላት ከተገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይኖራል።

3.4.5 ቦርዱ ውሣኔ የሚያሳልፈው በድምፅ ብልጫ ይሆናል።

3.4.6 የሚከተሉት ጉዳዮች የሚወሰኑት በሁለት ሦስተኛ የቦርድ ዳይሬክተሮች ድምጽ ይሆናል፤

3.4.6.1 የምርት ገበያዉ የሚያስከፍላቸው ክፍያዎች፣

3.4.6.2 የተጣራ ትርፍን እንደገና ኢንቬስት የማድረግ፣

3.4.6.3 የዋና ሥራ አስፈጻሚ ሹመት፣

3.4.6.4 የምርት ግብይት ደንቦችን ማፅደቅ ወይም ማሻሻል፤እና

3.4.6.5 ሁለት ሦስተኛ ድምፅ የሚጠይቁ ሌሎች ጉዳዮች።

3.4.7 ቦርዱ እያንዳንዱን ስብሰባ በተመለከተ በስብሰባ ላይ በተገኙ የቦርድ አባላት የተፈረመ ቃለ ጉባዔ ይይዛል፤

3.5 የምርት ገበያው የስራ አመራር መዋቅር

3.5.1 የምርት ገበያው ራሱን የቻለና በባለሙያዎች የተዋቀረ አመራር ይኖረዋል።

3.5.2 በሚኒስቴሩ መፅደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ የምርት ገበያው የራሱ የሆነ የደመወዝ ስኬል ይኖረዋል።

3.5.3 የምርት ገበያው ሥራ አመራር መንግስት በምርት ገበያው ላይ ካለው ባለቤትነትም ሆነ ከምርት ገበያው አባልነት ጋር የሚያያዝ መሆን የለበትም።

3.5.4 ምርት ገበያው ሥራ አመራር አንድ ዋና የስራ አስፈፃሚ እና ቦርዱ አስፈላጊ ነው ብሎ የሚወስነውን ያህል የሥራኋላፊዎች ይኖሩታል፡፡

3.5.5 የምርት ገበያው ኃላፊዎች በቀጥታ ለምርት ገበያው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሪፖርት ያደርጋሉ።

3.5.6 በተጨማሪም፤ ቦርዱ በቅድሚያ እንዲጸድቅ በማድረግ፣ በዋና ሥራ አስፈጻሚ በየጊዜው የሚወሰነው መሠረት የምርት ገበያው የድጋፍ ሰጪ ጽ/ቤቶች ይኖሩታል።

3.6 የምርት ገበያ ድርጅታዊ መዋቅር

3.6.1 ቦርዱ የምርት ገበያውን ስራዎች ለማከናወን ልዩ ልዩ መምሪያዎችን በማንኛውም ጊዜ ሊያቋቁም ይችላል።

3.6.2 ምርት ገበያው የተለያዩ መምሪያዎች ይኖሩታል፡፡ እያንዳንዱ መምሪያ በምርት ገበያው የሥራ ኃላፊ ይመራል፡፡
3.6.3 የምርት ገበያው መምሪያዎች በሥራ አመራር የሥራ ክፍሎች ይደራጃሉ። የሥራ አመራሩ ክፍል መምሪያውን ለሚመራው ኃላፊ ተጠሪ በሆነ የመሥመር ሥራ አስኪያጅ ይመራል።
3.6.4 የምርት ገበያው አመራር በቦረዱ በማፀደቅ የምርት ገበያውን ድረጅታዊ መዋቅር እንደአስፈላጊነቱ ማሻሻል ይችላል።
3.6.5 የምርት ገበያው ድርጅታዊ አወቃቀሩ ላይ የሚያደርገውን ማሻሻያ በተቻል ፍጥነት ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

3.7 የምርት ገበያው የቢሮ ድጋፍ ሰጪ አካላት

3.7.1 የምርት ገበያው ከመማሪያዎች በተጨማሪ ቦርዱ አስፈላጊ ነው ብሎ የሚወስነውን ያህል የድጋፍ ሰጪ ጽ/ቤቶች ይኖሩታል፡፡
3.7.2 ድጋፍ ሰጪ ቢሮዎች ተጠሪነታቸው በቀጥታ ለዋና ስራ አስፈፃሚው ይሆናል።
3.7.3 የምርት ገበያው አመራር በቦርዱ በማፀደቅ የምርት ገበያውን ድጋፍ ሰጪ ቢሮዎች አወቃቀር እንደ አስፈላጊነቱ ማሻሻል ይችላል።

3.8 የምርት ገበያው ሠራተኞች ሥነ ምግባር

3.8.1 ማንኛውም የምርት ገበያው ሠራተኛ ምንም ዓይነት የንግድ ወይም የግል ጥቅም ከአባላት ወይም ደንበኞች ጋር አይመሰርትም።
3.8.2 በሌላ አኳኀን ካልተገለፀ በቀር በሥራ ክንዋኔ ሂደት በሠራተኞች እጅ የገቡ የፋይናንስ መረጃዎች በሚስጥር የሚያዙ ሆነው አስፈላጊ በሆነበት ወቅት ለሚመለከተው ኃላፊ፣ ክፍል ወይም ቢሮ ብቻ መግለፅ ይቻላል።
3.8.3 ማንኛውም የምርት ገበያው ሠራተኛ የአንድን ግለሰብ የገበያ ወይም የፋይናንስ አቋም የሚመለከት መረጃ ጨምሮ የሚያስፈልግ ካልሆነ በቀር የአንዱን ደንበኛ ስም ለሌላው ደንበኛ፣ ላልተፈቀደለት ሠራተኛ፣ላልተፈቀደለት ሰው ምስጥር ወይም ጠቃሚና በይፋ የማይገኝን መግለፅ፤ እንዲገለፅ መፍቀድ ወይም እንዲገለፅ ማድረግ አይችልም። ሆኖም የሚከተሉትን አያካትትም።
   3.8.3.1 ከዲሲፕሊን ወይም ሌላ መደበኛ የክስ ሂደት ጋር የተያያዘ ወይም
   3.8.3.2 ለተፈቀደለት የምርት ገበያው መምሪያ ተግባር ወይም
   3.8.3.3 ለቦርዱ ተግባራት ሥራ ወይም
   3.8.3.4 በፍርድ ቤት በታዘዘ ትዕዛዝ ወይም
   3.8.3.5 በጉዳዩ ላይ ሥልጣን ባለው የመንግስት አስተዳደር ወይም ሕግ አውጪ ለሚቀርብ ጥያቄ።
3.8.4 በዋና ስራ አስፈፃሚ ካልተፈቀደ በቀር ማንኛውም የምርት ገበያው ሠራተኛ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከ100 ብር በላይ የሆነ ስጦታ፣ የማካካሻ ክፍያ ወይም ሌላ አይነት ክፍያ ከማንኛውም አባል ወይም ከተባባሪው መቀበል አይችልም።

## 4. ስለምርት ገበያ አባልነት

### 4.1 የአባልነት ዓይነቶች (መደቦች)

4.1.1 የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚከተሉት ሁለት ዓይነት መደበኛ አባላት( ሀ እና ለ) እና ሁለት ዓይነት ልዩ አባላት(ሐ እና መ) ይኖሩታል።

ሀ. ተገበያይ አባል፣

ለ. አገናኝ አባል፣

ሐ. ውስን ተገበያይ አባል እና

መ. ውስን አገናኝ አባል።

4.1.2 ተገበያይ አባል የሚገበያየው በራሱ ስም ብቻ ነው።

4.1.3 አገናኝ አባል በራሱ ወይም በደንበኞች ስም መገበያየት ይችላል።

ሀ. አገናኝ አባል ተባባሪ አባል መሾም ይችላል።

ለ. በአገናኝ አባል የተሾመ ማንኛውም ተባባሪ አባል በባለሥልጣኑ ዕውቅና ማግኘትና ዕውቅናውም በምርት ገበያው መጽደቅ ይኖርበታል።

ሐ. ተባባሪ አባል የግብይት ትዕዛዝ በአገናኝ አባል በኩል ማስተላለፍ የሚችለው በደንበኞች ስም ብቻ ነው።

መ. አገናኝ አባል ተባባሪ አባሉ ለሚፈጽመው ግብይት ኃላፊ ነው።

4.1.4 ውስን ተገበያይ አባል መገበያየት የሚችለው በራሱ ስም ገገር-ብቻ ወይም ሻጭ-ብቻ በመሆን በባለስልጣኑ በጸደቀ ተለይቶ በተገለጸ አንድ አይነት ምርት ብቻ ነው።ሆኖም ቡና ላኪ ገገር-ብቻ ውስን ተገበያይ አባል በቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብይት አዋጅ ቁጥር 602/2000 መሰረት ተረፈ ምርት ቡናውን በምርት ገበያ መሸጥ ይችላል።ውስን ተገበያይ አባል ደንበኛ ሊኖረው አይችልም።

4.1.5 ውስን አገናኝ አባል መገበያየት ሚችለው በራሱ ስም እንዲሁም በደንበኛው ስም በባለስልጣኑ በጸደቀ አንድ አይነት ምርት በሻጭነት ብቻ ነው።

4.1.6 የምርት ገበያው የተቀላጠፈ የገበያ አሠራርን ታሳቢ በማድረግ ሌሎች የአባልነት መደቦችን ሊፈጥር ይችላል።

### 4.2 ለአባልነት መቀመጫ ብቁ ስለመሆን

4.2.1 ማንኛውም ሰው፣የንግድ ድርጅት፣የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም የኅብረት ሥራ ማኅበር በዚህ ደንብ የተመለከቱትን መመዘኛዎች ካሟላ አባል ለመሆን ይችላል።

4.2.2 ማንኛውም አባል፣ የንግድ ድርጅት፣ የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም የኅብረት ሥራ ማኅበር አንድ መቀመጫ ብቻ ይኖረዋል።

4.2.3 ኃላፊነቱ በተወሰነ የግል ማህበር ወይም በማንኛውም አይነት የሽርክና ማህበር ውስጥ ከአንድ በላይ የባለቤትነት ጥቅም ያለው ሰው ወይም በቦርድ አባልነት እያገለገለ የሚገኝ ባለአክሲዮን ወይም በአክሲዮን ማህበር ውስጥ ከ50% በላይ የአክሲዮኖች ድርሻ ያለው ባለአክሲዮን ወይም በተገባቢጦሹ በአንድ ወቅት ሁለት የተለያየ አባልነት ሊያገኝ አይችልም።

4.2.4 በሆልዲንግና ተነጣይ መልክ የተቋቋሙ ወይም በሕግ ወይም በተግባር የሚገናኙ የንግድ ድርጅቶች ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቶች በአንድ ወቅት ሁለት የተለያየ አባልነት ሊያገኙ አይችሉም።

4.2.5 ከላይ በንኡስ አንቀጽ 4.2.2፣4.2.3 እና 4.2.4 የተደነገገው ቢኖርም፣ ኃላፊነቱ በተወሰነ የግል ማህበር ወይም ማንኛውም አይነት የሽርክና ማህበር ውስጥ የባለቤትነት ጥቅም ያለው ወይም በቦርድ አባልነት እያገለገለ የሚገኝ ባለአክሲዮን ወይም በአክሲዮን ማህበር ውስጥ ከ50% በላይ አክሲዮኖች ያለው ባለአክሲዮን ወይም በተገላቢጦሹ ወይም በሆልዲንግና ተነጣይ መልክ የተቋቋሙ ወይም በሕግ ወይም በተግባር የሚገናኙ የንግድ ድርጅቶች ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሆነ ማንኛውም በምርት ገበያው በብቸኝነት ግብይት እንዲፈጸምባቸው በሕግ የተወሰኑ ምርቶች ግብይት የተሰማራ ውስን አባል የሚከተሉትን የሚያሟላ ከሆነ በአንድ ወቅት ሁለት የተለያየ አባልነት ሊያገኝ ይችላል፤

i. ባለቤትነታቸውንና የበላይ አመራራቸውን አወቃቀር በተመለከተ እንዲሁም የምርት ገበያው ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚጠይቃቸውን ነገሮች በተመለከተ የተሟላ መግለጫ ከሰጡ፣
ii. እርስ በእርሳቸው ወይም ደንበኞቻቸውን ወክለው ግብይት የማያካሂዱ ከሆነ፣
iii. የራሳቸው አገናኝ አባል ደንበኛ የማይሆኑ ከሆነ፣
iv. እርስ በእርሳቸው ለራሳቸው ወይም ለደንበኞቻቸው ሲገበያዩ ከተገኙ ከአባልነት እንደሚሰረዙ ማረጋገጫ ከሰጡ፣ እና
v. ለሁለቱም የንግድ መድበሎች አንድ የስራ አመራር የማይጠቀሙ ከሆነ።

4.3 የአባልነት መቀመጫ

4.3.1 የምርት ገበያ አባልነት በተወሰነ ጊዜያት፣ የውል ቃሎችና ቁጥር በቦርዱ ውሳኔ ለሽያጭ ይቀርባሉ። አዲስ የአባልነት መቀመጫዎች ወይም የአባልነት መደቦች በቦርዱ ይወሰናሉ።

4.3.2 አዲስ ወይም የተለቀቁ የአባልነት መቀመጫዎች ሽያጭ ስርዓት

4.3.2.1 የምርት ገበያው በአዲስ ወይም በተለቀቁ የአባልነት መቀመጫዎች ግዢ ለመሳተፍ ለሚፈልጉ ተጫራቾች ከሽያጩ ቀን በፊት አስራ አምስት ቀን ቀደም ብሎ በህዝብ ማስታወቂያ የጨረታ ተሳትፎ ጥሪ ማድረግ አለበት።

4.3.2.2 ማንኛውም ተጫራች የሚከተሉትን ሰነዶች ከጨረታው ቀን ሶስት ቀናት ቀደም ብሎ ማቅረብ አለበት፡

i. የጸና የንግድ ፍቃድ ቅጅ ፣
ii. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥርና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ከሆነም የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሰርተፊኬት፣
iii. የሽርክና ማህበር ከሆነ የጸና የንግድ ፍቃድ እና የሽርክና ስምምነት ሰነድ ቅጅ፣
iv. ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ወይም የአክሲዮን ማህበር ከሆነ የጸና የንግድ ፍቃድ እና የመመስረቻ ጽሁፉንና የመተዳደሪያ ደንቡን ቅጅ፣
v. የህብረት ስራ ማህበር ከሆነ የመመስረቻ ጽሁፉንና የመተዳደሪያ ደንቡን ቅጅ፣
vi. የመንግስት ልማት ድርጅት ከሆነ የማቋቋሚያ ህጉን፣ እና
vii. ተጫራቹ በጨረታው የሚሳተፈው በህጋዊ ወኪል ከሆነ የጸና የውክልና ስምምነት።

4.3.2.3 እያንዳንዱ ተጫራች የምርት ገበያው በሚወስነው መጠን የጨረታ ማስከበሪያ ጥሬ ገንዘብ ወይም የባንክ ዋስትና እንዲሁም ለአባልነት መቀመጫ የሚያቀርበውን ዋጋ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ ማቅረብ አለበት፡፡

4.3.2.4 የምርት ገበያው ለእያንዳንዱ የምርት ገበያ አባልነት መደብ የሚያቀርበውን መነሻ ዋጋ እንዲሁም የተጫራቾችን ስም ሳይጨምር ተጫራቾች ያቀረቧቸውን የግዢ ዋጋዎች የሚመዘገብበት መዝገብ ይይዛል፡፡

4.3.2.5 የምርት ገበያው ከላይ በንዑስ አንቀጽ 4.3.2.1 በሚወጣ ማስታወቂያ በሚጠቀሰው ቦታ፣ ቀንና ጊዜ ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት የጨረታውን ሰነድ ይከፍታል፡፡

4.3.2.6 አባልነትን የሚመለከቱ የደንቡ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የምርት ገበያው ያሉትን የአባልነት መቀመጫዎች ከፍተኛ ዋጋ ላቀረቡ ተጫራቾች ይሸጣል፡፡ በዚህ ዙር አሸናፊዎችን መለየት ካልተቻለ፣ የመጀመሪያው ዙር ጨረታ እንደተጠናቀቀ ሁለተኛው ጨረታ ወዲያውኑ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ መከናወን አለበት፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ የጨረታ አሸናፊዎችን ለመለየት ካልተቻለ አሸናፊነታቸው ሊለይ ያልቻሉትን ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት የምርት ገበያው በሚያካሂደው እጣ አሸናፊው ሊለይ ይችላል፡፡

4.3.2.7 ግልጽነትን ለማረጋገጥ እንዲቻል፣ የጨረታው ሂደት እንደተጠናቀቀ የምርት ገበያው የአባልነት መቀመጫዎች የተሸጡበት ዋጋ ታትሞ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

4.3.2.8 ከዚህ በላይ የተመለከቱት የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጾች፣ እንዲሁም ቅድሚያ አሰጣጡ በባለስልጣኑ መጽደቁ እንደተጠበቁ ሆነው፣ የምርት ገበያው ከጊዜ ወደ ጊዜ የአባልነት መቀመጫዎቹን ሽያጭ ለተለያዩ ቅድሚያ የሚሰጣቸው የገበያ ዘርፎች ሊመድብ ይችላል፡፡

## 4.4 የአባላት መብት

4.4.1 የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ተገበያይ አባል እና አገናኝ አባል በምርት ገበያው የመገበያያ ቋሚና የሚተላለፍ መብት የሚያጎናጽፍ የአባልነት መቀመጫ ይኖራቸዋል፡፡

4.4.2 ተገበያይ አባል እና አገናኝ አባል በዚህ ደንብ በተደነገገው መሠረት ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት በመረጧቸው ተወካዮች አማካይነት በምርት ገበያው አስተዳደር የመሳተፍ መብት አላቸው፡፡

4.4.3 የደንቡ አንቀጽ 4.1.4 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ውስን ተገበያይ አባል በምርት ገበያ የመግዛት-ብቻ ወይም የመሸጥ-ብቻ የመገበያየት መብት ይኖረዋል፡፡

4.4.4 የውስን አባል የአባልነት ጊዜ ለአንድ አመት ብቻ የሚቆይ ነው፡፡ የአባልነት ጊዜው መቆጠር የሚጀምረው አባሉ በምርት ገበያው ለመገበያየት ብቁ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

4.4.5 የውስን አባል በምርት ገበያው የመገበያየት መብት ለሶስተኛ ወገኖች ሊተላለፍ አይችልም፡፡

## 4.5 የአባልነት ግዴታዎች

4.5.1 ማንኛውም ተገበያይ አባል ያሉበትን የተጣራ የክፍያ ግዴታዎቹን በቀጥታለምርት ገበያው የመፈጸምና ለዚህም ሲባል ዕውቅና ባገኘ የክፍያ መፈጸሚያ ባንክ የባንክ ሂሳብ የመክፈት እንዲሁም በእርሱ ስም የክፍያ ትዕዛዞች ከምርት ገበያው ወደ ክፍያ መፈጸሚያ ባንክ እንዲተላለፍ መፍቀድ ይኖርበታል፡፡

4.5.2 ማንኛውም አገናኝ አባል የራሱንና የደንበኛውን የተጣራ የክፍያ ግዴታዎች ለምርት ገበያው በቀጥታ የመፈጸምና ለዚህም ሲባል ዕውቅና ባገኘ የክፍያ መፈጸሚያ ባንክ ለራሱና ለደንበኛው የባንክ ሂሳቦችን የመክፈት፣ ለደንበኞቹ የሚፈጽማቸውን ክፍያዎች ሪፖርት የሚያደርግበት ሥርዐት የመዘርጋት እንዲሁም የደንበኞቹን ጨምሮ በእርሱ ስም የክፍያ ትዕዛዞች ከምርት ገበያው ወደ ክፍያ መፈጸሚያ ባንክ እንዲተላለፍ መፍቀድ ይኖርበታል። ማንኛውም አገናኝ አባል በደንበኞቹ ጥያቄ መሠረት የተለየ የባንክ ሂሳብ ለእያንዳንዱ ደንበኛው መክፈት ይችላል።

4.5.3 ማንኛውም አባል በማናቸውም ጊዜ ለዚህ ደንብ ተገዢ መሆኑና የተፈቀደላቸው ተወካዮቹም ለዚህ ደንብ እና ለሌሎች የምርት ገበያው ደንቦች ተገዢ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

4.5.4 ማንኛውም አባል የተፈቀደለት ተወካዩ የዚህን ደንብ ማንኛውንም ድንጋጌ የሚተላለፍ ድርጊት መፈጸሙን እንዳወቀ ወዲያውኑ ለምርት ገበያው ማስታወቅ ይኖርበታል።”

4.5.5 ማንኛውም አባል የምርት ገበያው ኮሚቴ ወይም ሠራተኞች ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ የመተባበር ግዴታ አለበት።

4.5.6 ማንኛውም አባል ሀሰት ወይም አሳሳች መሆኑን የሚያውቀውን ወይም በምክንያታዊነት ሊያውቅ የሚገባውን መረጃ ለምርት ገበያው መስጠት የለበትም።

4.5.7 ማንኛውም አባል በተመደበለት የምርት ገበያ የመገበያያ ሥርዐት በመጠቀም ለሚያስተላልፈው ትዕዛዝ ሁሉ ኃላፊ ነው። በዚህ መሰረት ለተፈጸመው ግብይትም ተዋዋይ ወገን ይሆናል።

4.5.8 በዚህ ደንብ አንቀጽ 4.5.1፣4.5.2፣4.5.12 እና 4.5.14 ከተመለከተዉ በተጨማሪ፣ማንኛዉም አባል በምርት ገበያዉ በየጊዜዉ በሚወሰነዉ መጠንና ጊዜ በራሱ ወይም በደንበኛዉ ስም ለፈፀመዉ ለእያንዳንዱ ግብይት የግብይት አገልግሎት ክፍያ ይከፍላል።

4.5.9 ማንኛውም ክፍያ ፈጻሚ-ያልሆነ ገዢ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባል ያሉበትን የተጣሩ የክፍያ ግዴታዎች በምርት ገበያው አገናኝ አባል በኩል መፈጸም ይኖርበታል።

4.5.10 ክፍያ ፈጻሚ-ያልሆነ ገዢ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባል የክፍያ መፈጸሚያውን ገደብ ያካተተ የክፍያ መፈጸሚያ አገልግሎት ስምምነት ከአገናኝ አባሉ ጋር ማድረግ አለበት።

4.5.11 ክፍያ ፈጻሚ-ያልሆነ ገዢ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባል አገናኝ አባሉ ለሰጠው የክፍያ መፈጸም አገልግሎት የሚከፍለው ዋጋ ጣሪያ ከውሉ ዋጋ 0.5% ሊበልጥ አይችልም።

4.5.12 ክፍያ ፈጻሚ ገዢ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባል ያሉበትን የተጣሩ የክፍያ ግዴታዎቹን በቀጥታ ለምርት ገበያው የመፈጸምና ለዚህም ሲባል ዕውቅና ባገኘ የክፍያ መፈጸሚያ ባንክ የመግዣ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ የመክፈት እንዲሁም በእርሱ ስም የክፍያ ትዕዛዝ ምርት ገበያው ወደ ክፍያ መፈጸሚያ ባንክ እንዲያስተላልፍ ስልጣን መስጠት/መፍቀድ ይኖርበታል።

4.5.13 ሻጭ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባል የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሳብ በምርት ገበያ የክፍያ መፈጸሚያ ባንክ መክፈት ወይም በክፍያ መፈጸሚያ ባንክ ያለውን የባንክ ሂሳብ ለዚሁ ዓላማ መሰየም አለበት።

4.5.14 አገናኝ አባል ክፍያ ፈጻሚ-ያልሆነ ገዢ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባል ያሉበትን የተጣሩ የክፍያ ግዴታዎች ይፈጽማል።ለዚሁ ዓላማ አገናኝ አባሉ የተዋሃደ የክፍያ የመግዣ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ በምርት ገበያ የክፍያ መፈጸሚያ ባንክ መክፈት አለበት።

4.5.15 ክፍያ ፈጻሚ-ያልሆነ ገዢ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባል ላካሄደው የግዢ ግብይት በምርት ገበያ የወጡ የርክክብ ማስታወሻ እና የማንሻ ማስታወሻ የመቀበል እንዲሁም ተከታትሎ የማስፈጸም ሙሉ ኃላፊነት አለበት።

## 4.6 በአባልነት ስለመቀበል

### 4.6.1 የማመልከቻ ሥርዐት

4.6.1.1 ለአባልነት የሚያመለክት ማንኛውም ሰው ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ቅፅ ማመልከቻውን የምርት ገበያው በየጊዜው ከሚጠይቃቸው የግዴታ መፈጸሚያ ማረጋገጫ፣ መረጃና ሰነዶች ጋር በምርት ገበያው የተወሰነውን ክፍያ በመክፈል ለምርት ገበያው ማቅረብ ይኖርበታል።

4.6.1.2 ማመልከቻው አመልካቹ ወይም (አመልካቹ ድርጅት ከሆነ) ሕጋዊ ወኪሉ በዚህ ደንብና በምርት ገበያው ሌሎች ደንቦች የተደነገጉትን ለማክበር የተስማማ መሆኑን በምርት ገበያው በተዘጋጀው ቅፅ በመሙላት በፊርማው በማረጋገጥ የሚገባውን ግዴታ ያካትታል ።

4.6.1.3 የምርት ገበያው ማመልከቻውን በመመርመር አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ተጨማሪ መረጃ እንዲቀርብለት መጠየቅ ይችላል።

4.6.1.4 የምርት ገበያው ማመልከቻውን ውድቅ ካደረገው ውድቅ ያደረገበትን ምክንያት በጽሁፍ ማስፈር ይኖርበታል።ማመልከቻው ውድቅ ከተደረገ አመልካቹ ለቦርዱ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል። ቦርዱ አመልካቹ ለአባልነት ብቁ መሆን አለመሆኑን በአብላጫ ድምጽ ይወስናል።ዉሳኔዉም የመጨረሻ ይሆናል።

4.6.1.5 ምርት ገበያው ማመልከቻውን በሚመረምርበት ጊዜ የአመልካቹን ወይም የንግድ ድርጅት የሆነ እንደሆነ፣ የደርጅቱን ዳይሬክተሮች፣ ሸሪኮች፣ ሥራ አስኪያጆች፣ የስራ ኃላፊዎችንና የሠራተኞችን የሥልጠናና የልምድ ደረጃ ወይም የድርጅቱን ተአማኒነት እና የገንዘብ አቋም የማገናዘብ መብት አለው።

4.6.1.6 ምርት ገበያው የቀረበለትን መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በቦታው በመገኘት፣ ቃለ መጠይቅ በማድረግ፣ ሰነዶች እንዲረጋገጡ በማድረግና እንዳስፈላጊነቱ በሌሎች ዘዴዎች በመጠቀም መመርመር ይችላል።

4.6.1.7 አመልካቹ ማመልከቻው በሚታይበት ጊዜ በቦርዱ ወይም ጉዳዩን በሚያየው ኮሚቴ ፊት ለቃለ መጠይቅ ወይም ለፈተና መቅረብ ይኖርበታል።

### 4.6.2 ለአባልነት ብቁ የሚያደርጉ መመዘኛዎች

ማንኛውም ሰው፣ የንግድ ድርጅት፣ የልማት ድርጅት ወይም የኅብረት ሥራ ማኅበር ለአባልነት ብቁ ሊሆን የሚችለው የሚከተሉትን ካሟላ ነው፤

4.6.2.1 በባለሥልጣኑ በግብይት ፈጻሚነት ዕውቅና ካገኘ፤

4.6.2.2 እንደ አባልነት መደቡ ቢያንስ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ግዙፍነት የሌለዉ ወይም በእጅ የማይዳሰሱትን ንብረት በመቀነስ የሚገኘውን የተጣራ ንብረት ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ በባለሥልጣኑ ዕውቅና ባገኘ ኦዲተር የተመረመረ የፋይናንስ መግለጫ ካቀረበ፤

ሀ. ተገበያይ አባል ብር 500,000፣

ለ. አገናኝ አባል ብር 1,000,000።

4.6.2.3 የአባልነት መቀመጫ ክፍያ ብር 50,000 ከከፈለ፤

4.6.2.4 በባለስልጣኑ መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በምርት ገበያዉ ቦርድ የተወሰነውን የአባልነት ማስጠበቂያ የመጀመሪያ አመት ክፍያ ከከፈለ፤

4.6.2.5 በዚህ ደንብ በተመለከተው መሠረት እያንዳንዱ አባል በአባልነት ለሚቆይበት ጊዜ እንደ አባልነት መደቡ የግዴታ መፈጸሚያ ዋስትና ማቋቋሚያ የሚሆን ከዚህ በታች የተመለከተውን ከወለድ ነፃ የሆነ የዋስትና ተቀማጭ በጥሬ ገንዘብ ከከፈለ፤

ሀ. ተገበያይ አባል ብር 200,000፣

ለ. አገናኝ አባል ብር 300,000::

4.6.2.6 የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩንና የሚፈለግበት የታክስ ክፍያ እንደሌለ የሚያሳይ ማረጋገጫ ካቀረበ።የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥሩን መስጠት/ማቅረብ ይኖርበታል።

4.6.2.7 የሽርክና ማኅበር ከሆነ፣ የፀና የንግድ ፈቃዱንና የሽርክና ስምምነቱን፤

4.6.2.8 የአክሲዮን ማኅበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ከሆነ፣ የመመሥረቻ ጽሁፉንና የመተዳደሪያ ደንቡን ቅጂ ካቀረበ፤

4.6.2.9 የሕብረት ሥራ ማኅበር ከሆነ፣ የመመሥረቻ ጽሁፉንና የመተዳደሪያ ደንቡን ቅጂ ካቀረበ፤

4.6.2.10 የመንግሥት የልማት ድርጅት ከሆነ፣ የመቋቋሚያ ሕጉን ቅጂ ካቀረበ፤

4.6.2.11 በምርት ገበያው ነፃ ካልተደረገ በቀር ፣ስለምርት ግብይት የተዘጋጀውን የብቃት ማረጋገጫ ስልጠና ተከታትሎ ፈተናውን ካለፈ።

4.6.2.12 በምርት ገበያው የተቀመጠውን አነስተኛ ቴክኒካል መሠረተ ልማት

4.6.2.13 ማንኛውም ሰው፣ የንግድ ድርጅት፣ የመንግስት ልማት ድርጅት ወይም የኅብረት ሥራ ማኅበር ለክፍያ ፈጻሚ-ያልሆነ ገዢ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባልነት ወይም ለሻጭ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባልነት ብቁ ሊሆን የሚችለው የሚከተሉትን ካሟላ ነው፤

4.6.2.13.1 ተመላሽ የማይሆን የአባልነት ክፍያ 5000 ብር ከከፈለ፣

4.6.2.13.2 ተመላሽ የሚሆን ከወለድ ነጻ የሆነ የዋስትና ተቀማጭ 50,000 ብር ከከፈለ፣

4.6.2.13.3 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 4.6.2.1, 4.6.2.6, 4.6.2.7, 4.6.2.8, 4.6.2.9 ፣4.6.2.10 እና 4.6.2.11 ስር የተጠቀሱትን ሌሎች መስፈርቶች ካሟላ::

4.6.2.14 ማንኛውም ሰው፣ የንግድ ድርጅት፣ የመንግስት ልማት ድርጅት ወይም የኅብረት ሥራ ማኅበር ለክፍያ ፈጻሚ ገዢ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባልነት ብቁ ሊሆን የሚችለው የሚከተሉትን ካሟላ ነው፤

4.6.2.14.1 ተመላሽ የማይሆን የአባልነት ክፍያ 5000 ብር ከከፈለ፣

4.6.2.14.2 ተመላሽ የሚሆን ከወለድ ነጻ የሆነ የዋስትና ተቀማጭ 200,000 ብር ከከፈለ፣

4.6.2.14.3 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 4.6.2.1, 4.6.2.6, 4.6.2.7, 4.6.2.8, 4.6.2.9 ፣4.6.2.10 እና 4.6.2.11 ስር የተጠቀሱትን ሌሎች መስፈርቶች ካሟላ::

4.6.2.15 ማንኛውም ሰው፣ የንግድ ድርጅት፣ የመንግስት ልማት ድርጅት ወይም የኅብረት ሥራ ማኅበር ለውስን አገናኝ አባልነት ብቁ ሊሆን የሚችለው የሚከተሉትን ካሟላ ነው፤

4.6.2.15.1 ተመላሽ የማይሆን የአባልነት ክፍያ 5000 ብር ከከፈለ፣

4.6.2.15.2 ተመላሽ የሚሆን ከወለድ ነጻ የሆነ የዋስትና ተቀማጭ 100,000 ብር ከከፈለ፣

4.6.2.15.3 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 4.6.2.1, 4.6.2.6, 4.6.2.7, 4.6.2.8, 4.6.2.9፣4.6.2.10 እና 4.6.2.11 ስር የተጠቀሱትን ሌሎች መስፈርቶች ካሟላ።

4.6.3 የተፈጥሮ ሰው ያልሆኑ አባላት

4.6.3.1 ማንኛውም የንግድ ድርጅት፣የሽርክና ማህበር፣የሕብረት ሥራ ማኅበር ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅቱ፤

ሀ. በምርት ገበያዉ እንዲሳተፍ የሚፈቅድ በቦርድ ወይም በሌላ ተመሳሳይ አካል የተፈቀደበትን ውሳኔ ካላቀረበ፤

ለ. የሽርክና ማህበር ከሆነ፣በሽርክና ስምምነት የሽርክና ማህበሩ ወይም ሽሪኮች በምርት ግብይት እንዲሳተፍ ካልተፈቀደ፣አባል ሊሆን አይችሉም።

4.6.3.2 በሽርክና ውል፣ በመመሥረቻ ጽሁፍና በመተዳደሪያ ደንብ ላይ የሚደረግ ማሻሻያ ማሻሻያው በተደረገ በ 1 ወር ጊዜ ውስጥ በምርት ገበያው ተቀማጭ መሆን ይኖርበታል።

4.6.4 አባልነት ስለማግኘት

4.6.4.1 አመልካች አባል መሆን የሚችለው፤

ሀ. የምርት ገበያዉ በዚህ ደንብ በተመለከተው መሠረት ማመልከቻውን ለመቀበል የሚያስፈልገውን ሂደት ካጠናቀቀና ማመልከቻው ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ለአመልካቹ ሲያሳውቀው፤እና

ለ. አመልካቹ በዚህ ደንብ የተመለከቱትን ክፍያዎችና ተቀማጭ ገንዘቦች ከከፈለ፤ ነው።

4.6.4.2 አመልካቹ ማመልከቻው ተቀባይነት ማግኘቱ የምርት ገበያው የጽሑፍ ማስታወቂያ በደረሰው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ክፍያዎቹን ካልፈጸመና ገንዘብ ተቀማጭ ካላደረገ የአባልነት መቀበያው ጊዜ እንዳለፈ ይቆጠራል።

4.6.4.3 ማንኛውም አባል አግባብ ያለውን የባንክ ሂሳብ መክፈትን በተመለከተ በዚህ ደንብ በክፍያና በርክክብ አፈጻጸም ሥር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ካላሟላ በግብይት የመሳተፍ መብት አይኖረውም።

4.6.4.4 ምርት ገበያው የተቀበላቸውን አባላት ዝርዝር ለባለሥልጣኑ ማስታወቅ ይኖርበታል።

4.6.5 ስለክፍያዎች

4.6.5.1 አባላት ክፍያን በተመለከተ፣ የምርት ገበያው በተለያዩ የአባላት መደቦች ለሚገኙ አባላት የተለያዩ ደረጃዎች ያሏቸውን ክፍያዎች ለመወሰን ይችላል።

4.6.5.2 ክፍያ የሚፈጸመው በምርት ገበያው በሚወሰነው ቀን ይሆናል።

4.6.5.3 የአባላት ከአባልነት መታገድ ዓመታዊ የአባልነት ክፍያን አያስቀርም።

4.6.5.4 ዓመታዊ የአባልነት ክፍያውን መክፈል በሚገባው ቀን ያልከፈለ አባል፣ ምርት ገበያው ክፍያውን ለመፈጸም ተጨማሪ የአንድ ወር ጊዜ ካልፈቀደለት በቀር፣ ከአባልነት ይታገዳል።

4.6.5.5 ክፍያው መከፈል ከሚገባው ወይም የተራዘመው ቀን ካበቃበት ቀን ጀምሮ በ አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ግዴታውን ያልፈጸመ አባል፣ ምርት ገበያው አባልነቱን እንዲቋረጥ ማድረግና ከአባሉ የሚፈለጉ ክፍያዎችንና ወለዶችን ተከታትሎ ማስከፈል ይችላል።

## 4.7 አባልነትን እና የመገበያየት መብትን ስለማገድ

### 4.7.1 የመገበያየት መብትን ወዲያውኑ ለማገድ የሚያስችሉ ሁኔታዎች

የአባል የመገበያየት መብቶች በማናቸውም ጊዜ ከሚከተሉት ምክንያቶች አንዱ ሲከሰት ወዲያውኑ ይታገዳል፤

4.7.1.1 አባሉ የክፍያ ግዴታውን ሳይወጣ ሲቀር፤

4.7.1.2 በምርት ገበያው የተፈጸሙ ግብይቶችን የሚመለከቱ ግዴታዎችን ጨምሮ፣ አባሉን ማገዱን ወይም የአባሉን የባንክ ሂሳብ መዘጋቱን የሚገልጽ ማስታወቂያ ከአባል የክፍያ መፈጸሚያ ባንክ ለምርት ገበያው ከደረሰው፤

4.7.1.3 አባሉን ወይም ንብረቱን በተመለከተ ንብረት አጣሪ፣ የንብረት አስተዳዳሪ ወይም ሥራ አስኪያጅ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሹም ከተሾመ ወይም አባሉ ከከሰረ፣ክፍያ መክፈል ካቆመ ወይም የዕዳ መክፈያው ጊዜ ሲደርስ ካልከፈለ፤

4.7.1.4 የምርት ገበያው የመክፈያውን ጊዜ ካላራዘመለት በቀር፣አባሉ በዚህ ደንብ ቁጥር 4.6.5 የተመለከተውን ክፍያና ይህን ደንብ መሠረት አድርገው የሚነሱ የፋይናንስ ግዴታዎቹን መክፈል በሚገባዉ ጊዜ ካልከፈለ፤

4.7.1.5 አባሉ በዚህ ደንብ መሠረት በግልግል ዳኞች የተላለፈበትን ውሳኔ ካልፈጸመ፤

4.7.1.6 የምርት ገበያው አባል የሆነ የምርት ገበያው ቦርድ አባል ለራሱ ወይም ለደንበኛው ትዕዛዝ የሚቀበልበትንና የሚፈጽምበትን ሁኔታ ሳይጨምር ፤ለምርት ገበያው ሰራተኛ ወይም የሥራ ኃላፊ፣ ለክፍያ መፈጸሚያ ባንክ ሰራተኛ ወይም ዳይሬክተር፣ ለዕቃ ማከማቻ መጋዘን ሰራተኛ ወይም ዳይሬክተር፣ ለሌላ መደበኛ አባል ወይም ለዚሁ መደበኛ አባል ሰራተኛ፣ ውስን አባሉ ሊገበያይ በሚችልበት ምርት ለውስን አባሉ ወይም ለዚሁመ ውስን አባል ሰራተኛ፣ ለባለሥልጣኑ ሰራተኛ ወይም የቦርድ አባል እንዲሁም ለሌላ ማንኛውም የምርት ገበያ የቦርድ አባል በምርት ገበያው ግብይት እየተደረገባቸው የሚገኙ ወይም ለግብይት የተዘረዘሩ ምርቶችን በተመለከተ ትዕዛዝ መቀበል ወይም መፈጸም፤

4.7.1.7 የአባልነት መስፈርትን በተመለከተ የተደረገ መጭበርበርን የምርት ገበያው ከደረሰበት፤

4.7.1.8 ጉቦ፣ ሰነዶችን ወደ ሀሰተኛነት የመቀየር እና የተጭበረበረ መረጃ መስጠትን በመሳሰሉ የሙስና ተግባራት ከተሰማራ፡፡

4.7.1.9 በደንቡ ድንጋጌዎች መሰረት በተለየ ሁኔታ ካልታየ በስተቀር፤ የምርት ገበያው በዚህ ደንብ ወይም በሌላ አግባብ ባለው ደንብ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ከግዴታው ነጻ ካላደረገው በቀር፣ በምርት ገበያው በተሰጠው የችሮታ ጊዜ (ካለ) ይኸው የችሮታ ጊዜ ካበቃ በኋላ በዚህ ደንብ ውስጥ የተመለከቱትን ሌሎች ግዴታዎቹን ካልተወጣ፤

4.7.1.10 ከደንቡ ንዑስ አንቀጽ 4.7.1.1 እስከ 4.7.1.8 ስር የታገደ አባል በምርት ገበያው ደንብ በሚወሰነው መጠን የገንዘብ መቀጮ እንዲከፍል ሊደረግ ይችላል፤

4.7.1.11 አባሉ ውሳኔውን እንዲያውቅ በተደረገ በአስር የስራ ቀናት ውስጥ በደንቡ ንዑስ አንቀጽ 4.7.1.9 ስር የተጣለበትን መቀጮ ካልከፈለ ክፍያው ሙሉ ለሙሉ ተከፍሎ እስኪጠናቀቅ ድረስ እገዳው እንዲቀጥል መደረግ አለበት፤

4.7.2 እንደአስፈላጊነቱ የመገበያየት መብትን ለማገድ የሚያስችሉ ሁኔታዎች

4.7.2.1 በምርት ገበያው የሚወሰዱ ሌሎች እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም አባል ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ ከአባልነት ሊታገድ ይችላል፤

ሀ. የአባሉ የተጣራ ንብረት በማናቸውም ጊዜ በምርት ገበያው የመገበያያ ደንብ ከተመለከተው መነሻ ወርዶ ከተገኘ፤

ለ. የሽርክና ማኅበር ከሆነ የአባሉ ሽሪክ ወይም የተፈጥሮ ሰው ካልሆነነ ዳይሬክተሩ ወይም ሌላ ሹም ከከሰረ፤

ሐ. ከምርት ገበያው ግብይት ጋር በተያያዘ ማንኛውንም ምርት ከገበያ ካስወገደ ወይም ለማስወገድ ከሞከረ፤

መ. በምርት ማስቀመጥ ወይም በርክክብ ወቅት የምርትን ጥራትና መጠን በተመለከተ ካሳሳተ ወይም ለማሳሳት ከሞከረ፤

ሠ. የምርት ገበያውን የመረጃ ቴክኖሎጂ ስርዓት፣ የሶፍት ዌር አሰራር፣ ዳታ እና መሳሪያዎች ተዓማኒነት በማንኛውም ሁኔታ አደጋ ላይ በሚጥል ተግባር ከተሰማራ፤

ረ. ከምርት ገበያው ፈቃድ ወይም ስምምነት ሳያገኝ ከምርት ገበያው ንግድ፣ አባልነት፣ ክፍያና ርክክብ አፈጻጸም፣ በማከማቻ መጋዘን ስለተቀመጠ ምርት፣ ቅኝት፣ የደንበኞች መረጃ እና ፋይናንስ የተገናኙና ከተጠቀሰው ውጭ ያሉትንም ጨምሮ ለሕዝብ ይፋ ያልሆኑ የምርት ገበያውን መረጃ እጁ ካስገባ ወይም በእጁ ለማስገባት ከሞከረ፤

ሰ. አባሉ በፍርድ ቤት፣ በምርት ገበያው ወይም በባለሥልጣኑ የምርት ገበያውን ወይም የባለሥልጣኑን የውስጥ ደንብ ተላልፎ መገኘቱ ከተረጋገጠ፤ወይም

ሸ. አባሉ በፍርድ ቤት በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ።

4.7.2.2 አንድ አባል በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.7.2.1 መሰረት የታገደ ከሆነ በዚህ ደንብ በተደነገገው መሰረት በሚወሰነው መጠን ተገቢውን መቀጮ ሊከፍል ይችላል፡፡

4.7.2.3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4.7.2.2 የተመለከተውን መቀጮ አባሉ ወሳኔውን እንዲያውቅ በተደረገ በ 10 ቀናት ጊዜ ውስጥ አለመክፈል ወዲያውኑ መታገድን ሊያስከትል ይችላል። አባሉ አስቀድሞ የታገደ ከሆነ፣ ክፍያው ሙሉ ለሙሉ ተከፍሎ እስከተጠናቀቀ ድረስ እገዳው እንደፀና ይቆያል።

4.7.2.4 ወዲያውኑ እገዳ የሚያስከትል የክፍያ ግዴታ አለመወጣትን የሚመለከት ካልሆነ በቀር፣ አባሉ የታገደ እንደሆነ፣ እገዳው ተፈጻሚ የሚሆነው የምርት ገበያው የእገዳውን ውሳኔ ለአባሉ ካስታወቀ ከ 24 ሰዓት በኋላ ነው።

4.7.2.5 በምርት ገበያው አስተያየት አባሉ የግዴታ መፈጸሚያው ጊዜ ካለፈ በኋላ በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን ግዴታዎች ለማሟላት ተገቢውን ጥረት አድርጓል ብሎ ካመነ፣ ግዴታው ካበቃበት ቀን አንስቶ ግዴታውን እንዲያሟላ 10 ተጨማሪ የሥራ ቀናት ይሰጠዋል፣ በተፈቀደለት ጊዜ ውስጥ ግዴውን ካላሟላ ይኸው ጊዜ እንዳበቃ እገዳው ይጸናል።

4.7.3 ከአባልነት የመታገድ ውጤቱ

4.7.3.1 የአባል የመገበያየት መብት፣ አገናኝ አባል ከሆነ በአባሉ ስም የመገበያየት መብቱን ጨምሮ የአባሉ የአባልነት መብት ለታገደበት ጊዜ በሙሉ ይቋረጣል።

4.7.3.2 ከአባልነት መታገድ አባሉ በዚህ ደንብ ወይም በሌላ ደንብ መሠረት የተሰጠውን መመሪያ ወይም የተጣለበትን ገደብ የማክበር ችሎታዉን ወይም ግዴታዉን አይነካም ወይም የዚህ ወይም የሌላ ማንኛውም ደንብ ተፈጻሚነት አያግደውም።

4.7.4 የመገበያየት መብት እገዳን ስለማንሳት

4.7.4.1 በዚህ ደንብ አንቀጽ 4.7.1.2 የአባል የመገበያየት መብት የታገደ እንደሆነ፣ የክፍያ መፈጸሚያ ባንኩ የተሰጠው የእገዳ ትዕዛዝ መነሳቱን ለምርት ገበያው በጽሁፍ እንዳሳወቀ እገዳው ይነሳል።

4.7.4.2 የምርት ገበያው በተለየ ሁኔታ በራሱ ስልጣን ካልወሰነ በቀር፣የአባል የመገበያየት መብት በዚህ ደንብ አንቀጽ 4.7.1.3 መሠረት የታገደ እንደሆነ፣በአባሉ ላይ ተፅዕኖ የሚያደርጉና ዕዳ የመክፈል አቅም እንዳይኖረው የሚያደርጉ ከንብረት ማጣራት፣ ከንብረት ጥበቃና የመጠባበቂያ ስምምነት ወይም ሌሎች ከመክሰር ሂደት ጋር የተያያዙ ሥነ ሥርዐቶች ከተፈጸሙና አባሉ በጥሩ አቋም ላይ የሚገኝ መሆኑ ከታወቀ እገዳው ይነሳል።

4.7.4.3 የአባል የመገበያየት መብት በዚህ ደንብ አንቀጽ 4.7.2.1 (ሀ) መሠረት የታገደ እንደሆነ፣አነስተኛው የተጣራ ንብረት መጠንን የሚገልጽ መግለጫ ለምርት ገበያው እንደደረሰ እገዳው ይነሳል።

4.7.4.4 የአባል የመገበያየት መብት በዚህ ደንብ አንቀጽ 4.7.2.1(ሰ) መሠረት የታገደ እንደሆነ፣አባሉ ግዴታውን ያሟላ መሆኑን በማሳየት ቦርዱን ሲያሳምን እገዳው ይነሳል።

4.8 የአባልነት መቀመጫን ስለማስተላለፍ

4.8.1 መቀመጫን የማስተላለፍ መብት

4.8.1.1 ይህ ደንብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም ተገበያይ አባል እና አገናኝ አባል የአባልነት መቀመጫቸውን በምርት ገበያው ተቀባይነት ላገኘ አባል የማስተላለፍ መብት አላቸው።

4.8.1.2 የምርት ገበያው አንድ አባል አባል ከሆነበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሦስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ አባልነቱን እንዳያስተላልፍ በምርት ገበያው ግዴታ ተጥሏል።

4.8.1.3 ማናቸውም የአባልነት ማስተላለፍ የሚከተሉት ካልተሟሉ በቀር አይጸናም፤

ሀ. የማስተላለፍ መብት የተገደበበት ጊዜ ካላበቃ፤

ለ. አስተላላፊው ከምርት ገበያው የሚፈለግበትን ገንዘብ በሙሉ ካልከፈለ፤

ሐ. አስተላላፊው ከደንበኞቹ በሚሰጠው ትህዛዝ መሠረት በደንበኞች ስም ያሉ (የተያዙ) ግዴታዎች መሟላታቸው ካልተረጋገጠ እና

መ. አባሉ ካልታገደ።።

4.8.2 የማስተላለፍ ሥርዐት፣የአባልነት መቀመጫን ለጨረታና ለግዢ ስለማቅረብ

4.8.2.1 የምርት ገበያው ለእያንዳንዱ ምርት ገበያ የአባልነት መደብ የአባልነት መብታቸውን ለመሸጥ የሚፈልጉ አባላት የሚያቀርቡት የጨረታ የሽያጭ ዋጋዎች እንዲሁም አባልነት እንዲተላለፉላቸው የሚፈልጉ ሰዎች የሚያቀርቡት የግዢ ዋጋዎች የሚመዘገብበት መዝገብ ይይዛል፡፡

4.8.2.2 የምርት ገበያው በመዝገብ ላይ የሚመዘግበው የጨረታ የሽያጭና የግዢ ዋጋዎች ያቀረቡትን አባላት ሳይሆን ዋጋዎቹን ብቻ ነው፡፡

4.8.2.3 አንደኛው ወገን በመዝገብ ላይ ያለውን የወቅቱን የጨረታ ወይም የሽያጭ ዋጋ ለመቀበል የሚፈልግ የሆነ እንደሆነ፣ ለምርት ገበያው ያስታውቃል፣ ምርት ገበያውም አግባብነት ያለውን የተጫራቾች ወይም የሻጮች ዝርዝን ይሰጠዋል፡፡

4.8.2.4 ጨረታው ወይም ሽያጩ ተቀባይነት ካገኘ አባልነቱ የተላለፈበት ዋጋን ያካተተ ተዋዋይ ወገኖቹ የተፈራረሙበትን የማስተላለፊያ ውል ቅጂዎች ለምርት ገበያው ያቀርባሉ፡፡

4.8.2.5 ምርት ገበያውም አባልነት የተላለፈበትን ዋጋ ታትሞ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

4.8.3 የማስተላለፍ ሥርዐት፤ ስለተላለፈለት ሰው

4.8.3.1 አባልነት የሚተላለፍለት ሰው በዚህ ደንብ አንቀጽ 4.6.2 እና 4.6.3 የተመለከቱትን ለአባልነት የሚያበቁ መመዘኛዎችን መሟላት ይኖርበታል፡፡

4.8.3.2 በዚህ ደንብ አንቀጽ 4.6.1 መሠረት አባልነት የተላለፈለት ሰው ማመልከቻው ተቀባይነት ካገኘ በኋላ፣ የጨረታ ዋጋው ላመለከተበት መደብ እንዲመዘገብለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

4.8.4 አባልነትን በማስተላለፍ ስለማግኘት

አባልነት የሚተላለፍለት ሰው አባልነት የሚያገኘው፤

4.8.4.1 የምርት ገበያው በዚህ ደንብ አንቀጽ 4.6.1 እና 4.6.2 መሰረት በአባልነት ለመቀበል የሚታለፍባቸውን ሥርዐቶች ካጠናቀቀና ማመልከቻው ተቀባይነት ማግኘቱን ምርት ገበያው በጽሁፍ እንዳስታወቀው፣

4.8.4.2 የምርት ገበያው በዚህ ደንብ አንቀጽ 4.8.2.4 የተመለከተውን የውል ቅጂ እንደተቀበለ ነው፡፡

4.8.5 በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ሥነ ሥርዐት፤

ሀ. በአንድ ድርጅት ሥር ባሉ ተቀጥያ ድርጅቶች መካከል በሚደረግ ማስተላለፍ ወይም

ለ. የሽርክና ማኅበር ከሆነ፣ ለማኅበሩ ሽሪክ ወይም አብዛኛው ድርሻ በሽሪኩ ባለቤትነት ለተያዘ ድርጅት የሚደረግ ማስተላለፍ፤ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

4.8.6 ከአባልነት መቀመጫ ሽያጭ ከሚገኘው ገንዘብ ላይ ሻጭ ለምርት ገበያው የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፡፡ በባለስልጣኑ መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህ ክፍያ መጠን በምርት ገበያዉ ቦርድ በየጊዜው ይወሰናል፡

## 4.9 አባልነትን ስለማቋረጥ

### 4.9.1 አባልነትን ስለማቋረጥ

4.9.1.1 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.7.1 እና 4.7.2 ስር የተመለከቱትን ድርጊት ከፈጸመ፣ መፈጸም የሚገባውን ሳይፈጽም ከቀረ ወይም ድንጋጌውን ተላልፎ ከተገኘ ቦርዱ እንዳስፈላጊነቱ አባልነት እንዲቋረጥ ሊወስን ይችላል፡፡

4.9.1.2 ምክንያት ካልቀረበና ምክንያቱም በምርት ገበያው ተቀባይነት ካላገኘ በስተቀር፣ ማንኛውም አባል ተቀማጭ የዋስትና ገንዘብ ካልከፈለና አባልነቱ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ ባለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ በምርት ገበያው መገበያየት ካልጀመረ ወይም ለተወሰነ ጊዜ ከተገበያየ በኋላ በተከታታይ ለሶስት ወራት ያህል መገበያየት ካቋረጠ የሚሰጠው የሶስት ወራት ማስታወቂያ ጊዜ እንዳበቃ የምርት ገበያው አባልነቱን ማቋረጥ አለበት፡፡

4.9.1.3 በንዑስ አንቀጽ 4.9.1.2 ስር የተጠቀሰው ማስታወቂያ ለአባሉ የሚሰጠው ለአንድ ጊዜ ብቻ መሆን አለበት፡፡

### 4.9.2 የግዴታ ቀጣይነት

ከአባልነት መልቀቅ አባሉ ለምርት ገበያው፣ ለክፍያ መፈጸሚያ ባንክ ወይም ለሌላ ማናቸውም አባል ከእንቅስቃሴው ወይም ከአባልነቱ በመነጨ ያለበትን ግዴታ ወይም ኃላፊነት አይቀንሰውም፣ አባሉ ግዴታውን ሙሉ ለሙሉ እስካልተወጣ ድረስ ተጠያቂነቱ የጸና ይሆናል።

### 4.9.3 ክፍያዎች ተመላሽ የማይሆኑ ስለመሆኑ

4.9.3.1 አባል ሲታገድ ወይም አባልነት ሲቋረጥ ለምርት ገበያው የተከፈለ የአባልነት ማስጠበቂያ ክፍያ ተመላሽ አይሆንም።

4.9.3.2 አንድ አባል አባልነቱ ሲቋረጥ ወይም ሲታገድተቀማጭ ገንዘቡን መጀመሪያ ባስቀመጠበት ዋጋ እንዲሁም የአባልነት መቀመጫ ክፍያውን መጀመሪያ በገዛበት ዋጋ ወይም በወቅቱ የገበያ ዋጋ አነስተኛ የሆነው ተመላሽ ይደረግለታል።

### 4.9.4 የአባልነት እገዳን ወይም ማቋረጥን ስለማስታወቅ

4.9.4.1 አባልነት ሲታገድ ወይም ሲሰረዝ የምርት ገበያው ለአባሉ ማስታወቂያ እንዲደርሰው ያደርጋል፤ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያለው ሌላ የሕዝብ ማታወቂያም ያወጣል፤ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘውም እንደሁኔታው ስለአባሉ መታገድ ወይም ስለአባልነቱ መቋረጥ በሕዝብ ማስታወቂያ እንዲገለጽና ሌሎች ሰዎች እንዲያውቁ ማድረግ ይችላል።

4.9.4.2 የምርት ገበያው እንደሁኔታው ስለማንኛውም አባል ከአባልነት መታገድ ወይም አባልነት መቋረጥ እና አባሉን በተመለከተ በቀጣይነት ስለተወሰዱት እርምጃዎች ለባለሥልጣኑ ያሳውቃል።

4.9.4.3 የምርት ገበያው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4.9.4.1 መሠረት በሚወጣ ማናቸውም ማስታወቂያ አግባብ ያለውን ውሳኔ ለመስጠት መነሻ የሆኑትን ምክንያቶች ታትመው እንዲወጡ ያደርጋል።

## 4.10 ስለአባላት ሆኖ ሥራ ስለሚያከናውን ሰው

### 4.10.1 የተፈቀደለት ተወካይ

4.10.1.1 ማንኛውም አባል ግብይቱን በተመለከተ በተፈቀደለት ተወካይ (ዮች) የመወከል መብት አለው።

4.10.1.2 የተፈቀደለት ተወካይ የግብይት ተወካይ ወይም ሌላ ተወካይ ሆኖ ሊሰየም ይችላል፡፡

4.10.1.3 የተፈቀደለት ተወካይ ለመሾም የሚፈልግ ማንኛውም አባል የምርት ገበያውን ይሁንታ ለማግኘት ማመልከት አለበት። የምርት ገበያው ስለ ተወካዩ አሿሿም፣አሠራር እና ውክልናው ስለሚቋረጥበት ሁኔታ መመሪያ ያወጣል።

4.10.1.4 የተፈቀደለት ተወካይ ለመሆን የሚያበቁ መመዘኛዎች አንድ ሰው የተፈቀደለት ተወካይ ለመሆን የሚችለው፤

ሀ. በባለሥልጣኑ በግብይት ፈጻሚነት ዕውቅና ካገኘ፣

ለ. ከስልጠናው ነጻ እንዲሆን በምርት ገበያው ካልተወሰነ በቀር፣ ስለምርት ግብይት ስልጠና ተከታትሎ ፈተናውን ካለፈ እና

ሐ. የተሾመበትን ደብዳቤ ከአባሉ ካቀረበ ነው።

4.11 ደንብን ስለ ስለማክበርና የደንብ መጣስን ስለማሳወቅ

ማንኛውም አባል፤

4.11.1 በማናቸውም ጊዜ ይህንን ደንብና ሌሎች የምርት ገበያ ደንቦችን ማክበርና ተወካዮቹም ማክበራቸውን ማረጋገጥ፣

4.11.2 የዚህን ደንብ ድንጋጌና ሌላ የምርት ገበያውን ደንቦች ወይም በምርት ገበያው ከሚካሄዱ ግብይቶች ጋር ተያያዥነት ያለው ሕግ በራሱ ወይም በተወካዮቹ ተጥሶ ሲገኝ ለምርት ገበያው ወዲያውኑ ማሳወቅ እና

4.11.3 ተቆጣጣሪ አካል በእርሱ ላይ ምርመራ እያካሄደ ወይም ክስ የመሠረተ መሆኑን እንዳወቀ ለምርት ገበያው ማሳወቅ ይኖርበታል።

4.12 ትብብርና ግንኙነት ስለመመሥረት

4.12.1 አባሉ የምርት ገበያው ወይም ምርመራውን በምትኩ እንዲያከናውንለት የምርት ገበያው የሾመው ሰው ወይም ሰዎች የግብይቱንና የገንዘብ አቋሙን በተመለከተ በራሱ ወይም በደንበኛው ስም የሚገኝ ሂሳብን በሚመረምሩበት ጊዜ መተባባር ይኖርበታል።

4.12.2 የምርት ገበያው የክፍያ መፈጸሚያ ባንክ ማንኛውንም አባል በተመለከተ በእጁ የሚገኝን ማናቸውንም መረጃ እንዲሰጠው ለመጠየቅ ይችላል፤ በአባሉ ላይ ምርመራ እንዲያካሂድ ወይም ምርመራውን የሚያከናውን ሰው እንዲሾም መጠየቅ ይችላል። እያንዳንዱ አባል የምርት ገበያው ለክፍያ መፈጸሚያ ባንኩ የሚያቀርበውን ጥያቄ እንዲፈጸም በዚህ ደንብ ውክልና ሰጥቶታል።

4.12.3 የምርት ገበያው ስለ ራሱ አሰራር ወይም ስለ አንድ አባል የሥራ እንቅስቃሴ እና ያልፈጸማቸው ግዴታዎችን አስመልክቶ በባለሥልጣኑ መረጃ ሲጠየቅ ማቅረብ ይኖርበታል።

4.12.4 በዚህ ደንብና በሌሎች አግባብ ባላቸው ደንቦች ወይም መተዳደሪያ ደንቦች ካልተመለከተ ወይም ሕግ ካላስገደደ በቀር፣ የምርት ገበያው አባላቱንና በአባለቱ መፈጸም የሚገባቸውን ግዴታዎች የሚመለከቱ መረጃዎችን በሚስጥር መያዝ ይኖርበታል። የምርት ገበያው የያዘውን መረጃ ለሌላ ሰው መግለጽ የሚችለው በዚህ ደንብና በሌሎች ደንቦች፣የመተዳደሪያ ደንብ ወይም በሕግ የተፈቀደ ሲሆን ወይም ከዚህ በላይ የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ ደንብ

የተጣለበትን ግዴታ ለመፈጸም ወይም ተግባራቱን ለማከናወን በተለይም ለኢንሹራንስ ድርጅቶች፣ ለክፍያ መፈጸሚያ ባንክ ወይም በምርት ገበያው ለተሰየመ የዕቃ ማከማቻ መጋዘን መረጃውን እንዲሰጥ ሲጠየቅ ነው።

4.12.5 እያንዳንዱ አባል በባለሥልጣኑ ወይም በምርት ገበያው ሲጠየቅ በምርት ገበያው የወጣውን ይህንን ደንብና ሌሎች ደንቦች እንዲሁም በባለሥልጣኑ የወጡ መመሪያዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ (ለመቆጣጠር ወይም ለመከታተል) በማናቸውም ጊዜ ባለሥልጣኑ ወይም ምርት ገበያው ቢሮው እንዲገባ (ምርት ገበያው ወይም የምርት ገበያው ሠራተኞች ወደ ቢሮው እንዲገቡ) መፍቀድ ይኖርበታል።

4.13 የውጭ አስተዳዳሪዎችን ስለማሳወቅ

ማንኛውም አባል ከዚህ በታች ከተመለከቱት ውስጥ አንዱ ከተፈጸመ ለምርት ገበያው ወዲያውኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፤

4.13.1 የአባሉን ንብረት በተመለከተ ንብረት አጣሪ ኮሚሽነር ወይም ባላደራ ሲሾም ወይም

4.13.2 የሽርክና ማኅበር ከሆነ የአባሉ ሽሪክ ሲከስር።

4.14 የአነስተኛ የተጣራ ንብረት መጠንን ስለመጠበቅ

እያንዳንዱ አባል፤

4.14.1 የተጣራ ንብረቱ መጠን (ግዙፍነት የሌለዉ ወይም በእጅ የማይዳሰሰው ንብረት ተቀንሶ የሚገኘውን) በማናቸውም ጊዜ በምርት ገበያው ከተወሰነው አነስተኛ የንብረት መጠን ያነሰ አለመሆኑን ማረጋገጥ፤

4.14.2 የተጣራው የንብረት መጠን (ግዙፍነት የሌለዉ ወይም በእጅ የማይዳሰሰው ንብረት ተቀንሶ የሚገኘውን) በምርት ገበያው ከተወሰነው አነስተኛ የንብረት መጠን ያነሰ እንደሆነ ወዲያውኑ ለምርት ገበያው ማሳወቅ፤

4.14.3 እያንዳንዱ የበጀት ዓመት ባበቃ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ በምርት ገበያው በተዘጋጀው ቅጽ መሠረት በተመሰከረላቸው ኦዲተሮች የተመረመረ የሂሳብ መግለጫ ማቅረብ፤ ይኖርበታል።

4.15 የሂሳብ መዝገቦች ስለመያዝ

4.15.1 እያንዳንዱ አባል፡-

ሀ. የየራሱን ግብይትና የፋይናንስ አቋም በትክክል መመዝገብና ማስረዳት እና

ለ. የምርት ገበያ አባሉ ይህን ደንብና ሌሎች የምርት ገበያውን ደንቦች ማክበሩን ለማረጋገጥ የሚያስችለውን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርበታል።

4.15.2 እነዚህ መዝገቦች በቀላሉና በአግባቡ ኦዲት ሊደረጉ በሚችሉበት ፎርምና ቦታ መያዝ አለባቸው።

4.16 ተፈጻሚ የሚሆኑ ሕጎችን ስለማክበር

እያንዳንዱ አባል የምርት ገበያውንና የባለሥልጣኑን አዋጆች እንዲሁም አግባብነት ያላቸዉን ሌሎች ሕጎች ማክበር ይኖርበታል።

## 5. በምርት ገበያው ላይ ንግድ ማካሄድ

### 5.1 የመገበያያ መድረክ

በምርት ገበያው የሚደረግ ግብይት በምርት ገበያው የመገበያያ መድረክ ፣ የምርት ገበያው በሚያዘጋጀዉ የኤሌክትሮኒክ መገበያያ ወይም የምርት ገበያው በሚያፀድቀው ሌላ ተመሳሳይ መድረክ ላይ ይሆናል።

### 5.2 የመገበያያ ቀናትና ሰዓታት

የመገበያያ መድረኩ በምርት ገበያው ለሚወሰኑ ሰዓታት ለግብይት ክፍት ይሆናል።

5.2.1 የመገበያያ ቀናት

5.2.1.1 በምርት ገበያው በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በቀር፣ በምርት ገበያው የሚደረግ ግብይት ከሕዝብ የበዓል ቀናት ውጪ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ይሆናል።

5.2.1.2 የዳይሬክተሮች ቦርድ ባለስልጣኑ እንዲያጸድቀው በማድረግ በንዑስ አንቀፅ 5.2.1.1 የተደነገገው ተፈጻሚ የማይሆንበት ልዩ ሁኔታ መወሰን ይችላል። እንደዚህ ዓይነት ልዩ ዉሳኔ መወሰኑን የምርት ገበያው አባላት እንዲያውቁት መደረግ አለበት።

5.2.1.3 ልዩ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ምክንያቱ በጽሁፍ ተመዝግቦ የምርት ገበያው ማኔጅመንት (በተቻለ ፍጥነት ለቦርዱ በማሳወቅ) በማንኛውም ውል ወይም በሁሉም ውሎች የሚደረግን ግብይት ከአንድ የግብይት ቀን በላይ መዝጋት ይችላል።

ሀ. ሆኖም አመቺ በሆነ መንገድ ከተቻለ ግብይቱ ከመዘጋቱ በፊት ወይም ካልተቻለ ግብይቱ ከተዘጋ በኋላ ወዲያው ባለስልጣኑ እንዲያውቀው ካልተደረገ በምርት ገበያ የሚደረግ ግብይት ሊዘጋ አይችልም። በዚህ አንቀጽ ውስጥ ማሳወቅ የሚለው ቃል መጀመሪያ በስልክ በማስከተል በደብዳቤ፣ በፋክስ፣ ወይም በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ማሳወቅ ማለት ነው።

ለ. ሆኖም የምርት ገበያው ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ውጭ በምርት ገበያዉ የሚደረግ ግብይት በማናቸውም ጊዜ ከሦስት ተከታታይ የግብይት ቀናት በላይ መዝጋት አይችልም።

ሐ. ሆኖም መዝጋቱን አስመልክቶ መረጃ ለባለስልጣኑ ተላልፎ ከሆነ፤ የምርት ገበያው ቦርድ/ ማኔጅመንት የባለስልጣኑ ውሳኔ እስኪደርስ ድረስ ባለስልጣኑ ባይፈቅድም ግብይቱን በተከታታይ ሦስት ቀናት ለሚበልጥ ቀጣይነት ላለው ማናቸውም ጊዜ ሊዘጋው ይችላል።

5.2.2 የተወሰኑ የግብይት ሰዓታት

የምርት ገበያው በገበያው ለተዘረዘረው ለእያንዳንዱ ውል የመገበያያ ሰዓታትን በመወሰን ማሳወቅ አለበት፡:

### 5.2.3 ኤሌክትሮኒክ የግብይት ክፍለ ጊዜ

የኤሌክትሮኒክ የግብይት ክፍለ ጊዜ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፤

ሀ. ቅድመ መክፈቻ የግብይት ክፍለ ጊዜ - ትዕዛዝ ማስገባት ይጀመራል፣ የገቡ ትዕዛዞች መሰረዝ ይቻላል፣ ግብይት አይፈቀድም፤

ለ. መሰረዝ የማይቻልበት ቅድመ መክፈቻ ክፍለ ጊዜ - ትዕዛዝ ማስገባት ይቻላል ነገርግን ትዕዛዝ መሰረዝ ወይም ማሻሻል አይቻልም፣ ግብይት አይፈቀድም፤

ሐ. ክፍት የግብይት ክፍለ ጊዜ — የተላኩ ትዕዛዞች የሚዛመዱበት የግብይት ክፍለ ጊዜ ነው፣ በዚህ ክፍለጊዜ ትእዛዙ ከመፈጸሙ በፊት ትእዛዝ ማስገባት፣ ማሻሻል እና መሰረዝ ይቻላል፤

መ. ግብይት ማቆም — የምርት ገበያውን ግብይት ታአማኒነት እና ጤናማነት ለመጠበቅ ወይም ለሌላ የደህንነት ምክንያት ሲባል ግብይቱ ከመጠናቀቁ/ከመዘጋቱ በፊት ግብይትን ማቆም ነው። በዚህ ጊዜ የሚፈቀደው ትዕዛዝን መሰረዝ ብቻ ነው።

ሠ. ዝግ የግብይት ክፍለ ጊዜ — ትዕዛዝ ማስገባት፣ ማሻሻል ወይም መሰረዝ የማይቻልበት ዝግ የግብይት ክፍለ ጊዜ ነው፤

ረ. ማጠናቀቂያ እና መሰናጃ ክፍለ ጊዜ —— ግብይቱ ከተጠናቀቀ/ካበቃ በኋላ ገበያው ዝግ ሆኖ የሚቆይበት እና አባላትም ትዕዛዝ ማስገባት፣ ማሻሻል፣ ማየት ወይም መሰረዝ የማይችሉበት ጊዜ ነው። በዚህ ጊዜ ምርት ገበያው የተለያዩ የቢሮ ስራዎችን ማጠናቀቅና እስከ እለት ድረስ ብቻ የሚጸና ትእዛዝ ከሲስተም ማውጣት የመሳሰሉትን የጥገና ስራዎች ያከናውናል።

ሰ. ሌሎች ምርት ገበያው የሚጨምራቸው ክፍለ ጊዜዎች።

## 5.3 የግብይት ስርዓት

ግብይቱ ምርት ገበያው በሚወስነው አኳኋንና የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በመገበያያ መድረክ ድምጽን በማስተጋባት ወይም በኤሌክትሮኒክ ግብይት መድረክ ላይ ተወዳዳሪነትን በሚጋብዝ ሁኔታ ይካሄዳል። ግብይቱ የምርት ገበያው በሚወስነው አኳኋንና ጊዜ መሠረት በኤሌክትሮኒክ የግብይት ስርዓት የሚደረግ መገበያየትን ይጨምራል።

### 5.3.1 ወደመገበያያ መድረክ የመግባት ፈቃድ

5.3.1.1 ወደ መገበያያ መድረክ የመግባት ፈቃድ

ሀ. ወደ መገበያያ መድረኩ እንዲገቡ የሚፈቀድላቸው የመድረክ ተወካዮች፣ ወይም በንዑስ አንቀፅ 5.3.1.4 መሠረት የተፈቀደላቸው እንግዶች እና የተፈቀደላቸው የምርት ገበያው ሠራተኞች ብቻ ናቸው።

ለ. በምርት ገበያው የመገበያያ መድረክ ላይ በቃል በማስተጋባት የንግድ ስራ ማከናወን የሚችለው የመድረክ ተወካይ ብቻ ነው።

ሐ. አባሉ የታገደ ከሆነ የመድረክ ተወካዩ ወደ ግብይት መድረኩ እንዲገባ አይፈቀድለትም።

5.3.1.2 በመገበያያ መድረኩ ላይ ምንም ዓይነት ተንቀሳቃሽ የመገናኛ መሣሪያዎችን መያዝ አይፈቀድም።

5.3.1.3 የመለያ ባጅ

ማንኛውም የመድረክ ወኪል ወይም የምርት ገበያ ሰራተኛ በምርት ገበያው የተዘጋጀ የመለያ ባጅ ሁል ጊዜ በግልፅ በሚታይ ቦታ ላይ ሳያንጠለጥል ወደ መገበያያ መድረኩ እንዲገባ አይፈቀድለትም።

5.3.1.4 የእንግዳ ባጆች

ሀ. የደህንነት መምሪያው በአባሉ አመልካችነት ወይም የምርት ገበያው በሚያዘው መሰረት በራሱ አነሳሽነት እንግዳ ወደ መገበያያ መድረኩ እንዲገባ የሚያስችል የእንግዳ ባጅ ሊሰጥ ይችላል።

ለ. ማንኛውም የአባል እንግዳ በመገበያያ መድረኩ ላይ ከአባሉ ጋር መሆን ያለበት ሲሆን በዚህ ደንብ መሠረት ለአንድ አባል የተደነገጉ የመድረክ ሥነ-ምግባሮችን ሁሉ ማክበር አለበት። አባላት በእንግዶቻቸዉ ለሚፈጸሙ የግብይት ደንቦች ጥሰት እና የገንዘብ ቅጣቶች ተጠያቂዎች ናቸው።

ሐ. ማንኛውም የባለስልጣኑ ኦፊሴላዊ ተወካይ ለሌላ ዓላማ ሳይሆን በባለስልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት እንዲያስችለው ጉብኝት የሚያደርግ ከሆነ በማንኛውም ጊዜ ወደ መገበያያ መድረኩ መግባት ይችላል። በመገበያያ መድረኩ ላይ እያለም የምርት ገበያው ሠራተኛ አብሮት መኖር አለበት።

መ. ሕጋዊ ውክልና የተሰጣቸው ፕሬሶች በምርት ገበያው የኮሙኒኬሽን መምሪያ በፅሁፍ ሲፈቀድላቸው ከምርት ገበያው ሠራተኛ ጋር በመሆን ወደ መገበያያ መድረኩ መግባት ይችላሉ።

5.3.2 ወደ ኤሌክትሮኒክ መገበያያ መድረክ የመግባት ፈቃድ

ሀ. የተፈቀደላቸው ሰዎች ብቻ አባላትን ወክለው ወደ ኤሌክትኖኒክ መገበያያ መድረክ መግባት ይችላሉ፤

ለ. ማንኛውም ሰው ኤሌክትኖኒክ ግብይት ተወካይ መሆን የሚችለው፡

i. በግብይት ፈጻሚነት ዕውቅና ካገኘ፣
ii. በምርት ግብይት በኤሌክትኖኒክ ግብይትና ምርት ገበያው በሚጠይቃቸው ሌሎች የብቃት ማረጋገጫ ስልጠናዎች የወሰደና ፈተናውን በሚገባ ያለፈ እና
iii. በአባሉ የተሰጠ የሹመት ደብዳቤ ካቀረበና ይህም በምርት ገበያው ከጸደቀ ነው፡፡

ሐ. ደንበኛ በኤልክትሮኒክ መገበያያ መድረክ ላይ መመሪያ ማስገባት የሚችለው

i. አባል እና ደንበኛው የአባልና ደንበኛ ውል ስምምነት ከተዋዋሉ፣
ii. ደንበኛው በምርት ገበያው የሚዘጋጅ የደንበኛ ኤልክትሮኒክ ግብይት ስልጠና ከተሳተፈ፣
iii. አባሉ ለደንበኛው ትክክለኛ የምርት ገበያው ኤሌክትሮኒክ የግብይት የተገልጋይ መለያ ቁጥር ከሰጠው፣
iv. አባሉ ለደንበኛው የክፍያና ግዴታ መፈጸሚያ የተለይ ሂሳብ ከከፈተ እና
v. ደንበኛው በምርት ገበያው ግብይት መፈጸም የሚችለው ዕውቅና ካለው ነው፡፡

መ. የሁሉም ደንበኞች መመሪያበሚመለከተው አባል መመርመር ይኖርበታል፡፡ አንድ ደንበኛ መመሪያ ሲያስገባ፣ ሲያሻሽል ወይም ሲሰርዝ አባሉ አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት ጨምሮ በኤልክትሮኒክ የግብይት መድረክ ለሚገቡ የደንበኛ መመሪያዎችን በተመለከተ ከግብይት ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ማንኛውም ጉዳዮች ኃላፊነት አለበት፡፡

ሠ. አባል መመሪያ በቀጥታ የማስተላለፍ ሂደት ተጠቃሚ እንዲሆን ከፈቀደለት ደንበኛ በስተቀር የእያንዳንዱን ደንበኛ መመሪያ ያጸድቃል ወይም ይሰርዛል፡፡ አባል ካለበቂ ምክንያት የደንበኛውን መመሪያ ይዞ ማቆየት የተከለከለ ነው፡፡

ረ. የደንበኛው መመሪያ የምርት ገበያውን ህግ ካልጣሰ ወይም ደንበኛው ካልጠየቀው በስተቀር አባል የደንበኛውን መመሪያ መሰረዝ አይችልም፡፡ አባል መመሪያ ከሰረዘ ወዲያው ለደንበኛው እና ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

ሰ. የራሳቸውን መመሪያ ማስገባት ለተፈቀደላቸው ደንበኞች፣ የክፍያ ፈጻሚ ያልሆነ አባል እና የኤሌክትሮኒክ ግብይት ተወካይ የቀጥታ ግንኙነት እንዲያገኙ ማድረግን ጨምሮ ሁሉም ወደኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ ለሚደረጉ ግንኙነቶች በሙሉ በግንኙነት ውስጥ ለሚደረጉት እንቅስቃሴዎች ኃላፊነት የሚወስደው ክፍያ ፈጻሚ አባል ዋስትና ይሰጣል።

ሸ. በኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ አማካኝነት ወይም መድረኩን በመጠቀም የተፈጸሙ የህግ ጥሰቶችን በተመለከተ ለሚደረጉ ምርመራዎች አባላት ለምርት ገበያው አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት አለባቸው፡፡ የዚህ አይነቱ ድጋፍ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ሳይወስን ሰነድ ማቅረብን፣ ጥያቄዎችን መመለስን እና/ወይም በአካል ቀርቦ ማስረዳትን የሚያጠቃልል ሆኖ ድጋፉ እንደተጠየቀ ወዲያውኑመፈጸም አለበት፡፡

ቀ. የኤሌክትሮኒክ የግብይት ተወካይ ወይም የራሱን መመሪያ የሚያስገባ ደንበኛ የውሎችን ህልውና ጤናማነት ወይም ተፈላጊነት አደጋ ላይ ከጣለ ወይም የምርት ገበያውን ደንብ ከጣሰ ወይም በምርመራ ጊዜ ለመተባበር ፈቃደኛ ካልሆነ ወደኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ የመግባት መብታቸውን የምርት ገበያ ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል፡፡ ይህ ሁኔታ ሲፈጠር ምርት ገበያው ለአባሉ/ለወኪሉ ወይም ለደንበኛው እና ለባለስልጣኑ ውሳኔውን እና ለምን ይህ ውሳኔ እንዳስተላለፈ ያሳውቃቸዋል፡፡

በ. የኤሌክትሮኒክ ግብይት ተወካይ ወይም የራሱን መመሪያ የሚያስገባ ደንበኛ የኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ህግ መጣሳቸውን አባሉ እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው እና አስፈላጊውን እርምጃ ሳይወስድ ሲቀር አባሉ የምርት ገበያውን አደጋ ላይ የሚጥል ስራ እንደፈጸመ ይቆጠራል፡፡

5.3.3 የኤሌክትሮኒክ ግብይት ተርሚናል የሥራ ማከናመኛ መሣሪያ ተጠቃሚን መለየት

ሀ. ምርት ገበያው ህግን መሰረት በማድረግ እያንዳንዱ የኤሌክትሮኒክ የግብይት ተወካይ እና የራሱን መመሪያ የሚያስገባ ደንበኛ የሚለዩበትን ሁኔታ ይወስናል፣

ለ. እያንዳንዱ ተጠቃሚ የራሱ መለያ ቁጥር ይኖረዋል፡፡ የኤሌክትሮኒክ ግብይት ተወካይ እና የራሱን መመሪያ የሚያስገባ ደንበኛ የተጠቃሚ መለያ ምዝገባ ሁልጊዜ የጸና እና ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ የአባሉ ኃላፊነት ነው፡፡

ሐ. እያንዳንዱ የኤሌክትሮኒክ የግብይት ተወካይ እና የራሱን መመሪያ የሚያስገባ ደንበኛ ኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረኩን ለመጠቀም ልዩ መለያ ቁጥር መጠቀም አለበት፡፡ ኤሌክትሮኒክ ግብይት ተወካይ ወይም የራሱን መመሪያ የሚያስገባ ደንበኛ ከተጠቃሚው ውጭ ሌላ ሰው የእሱን መለያ ቁጥር ተጠቅሞ ትዕዛዝ ወይም መመሪያ እንዲያስገባ መፍቀድ የለበትም፡፡

መ. ምርት ገበያው በአንድ ጊዜ የኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ የሚጠቀሙትን የኤሌክትሮኒክ ግብይት ተወካዮች ወይም የራሳቸውን መመሪያ የሚያስገቡ ደንበኞች ብዛት ሊገድብ ይችላል፡፡

ሠ. ምርት ገበያው የአካውንት ስርዓት አስተዳደርን በተመለከተ የአሰራር ስርዓት በማውጣት ለሚመለከታቸው የኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ ተጠቃሚዎች ያሰራጫል፡፡

5.3.4 የኤሌክትሮኒክ ግብይት ድጋፍ

የምርት ገበያው ኤሌክትሮኒክ የግብይት ስርዓት ቁጥጥር ክፍል ለአባላት እና ኤሌክትሮኒክ የግብይት ተወካዮች ድጋፍ እና ለሚከሰቱ ችግሮችም መፍትሄ ይሰጣል፡፡ ምርት ገበያው በተወሰነ ጊዜ ለዚሁ ጉዳይ በተመደበ ስልክ ወይም በሌላ የኤሌክትሮኒክ መንገድ ድጋፍ ሊሰጥ ይችላል፡፡ የራሳቸውን መመሪያ የሚያስገቡ ደንበኞች ከምርት ገበያው ጋር ግንኙነት ማድረግ የሚችሉት በአባል ወይም ኤሌክትሮኒክ የግብይት ተወካይ አማካኝነት ነው፡፡

5.3.5 ፋንተም ትዕዛዝ ወይም መመሪያ

ሀ. ፋንተም ትዕዛዝ ወይም መመሪያ ማለት 1) የምርት ገበያው የግብይት ስርዓት በጉድለት፣ በብልሽት ወይም በቸልተኝነት ምክንያት ወይም 2) የገባው መረጃ (ለምሳሌ ያህል ውል፣ መጠን ወይም ዋጋ) ከኤሌክትሮኒክ የግብይት ተወካይ ወይም የራሱን መመሪያ የሚያስገባ ደንበኛ እውቅና ውጭ በምርት ገበያው የግብይት ስርዓት ወይም አገልግሎት ላይ በተከሰተ ጉድለት፣ ብልሽት ወይም ቸልተኝነት ምክንያት ሲቀየር ነው::

ለ. ምርት ገበያው የግብይት ስርዓት ውስጥ ፋንተም ትዕዛዝ/ መመሪያ መግባቱ ወይም እየገባ ስለመሆኑ ወይም ስለመፈፀሙ አሳማኝ ምክንያት ሲኖር ምርት ገበያ ለጉዳት የተጋለጡ ግብይቶችን በተመለከተ ግብይት መዝጋት፣ የሽያጭ እና የግዥ ትዕዛዞችን መሠረዝ እና/ወይም አዲስ የሚገቡ የሽያጭ እና የግዥ ትዕዛዞችን ማገድን ጨምሮ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

ሐ. በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በፋንተም ትዕዛዝ/መመሪያ ምክንያት የተፈጸሙ ግብይቶች ከዕለታዊ የዋጋ ተመን ውጪ ተፈጽመው ከሆነ ምርት ገበያው ግብይቶቹ እንደሚሰረዙ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡ በዚህ አንቀፅ መሰረት ለተሰረዘ ግብይት የምርት ገበያው ምንም አይነት ተጠያቂነት ወይም ለግብይት ተሳታፊዎች ኃላፊነት የለበትም፡፡

መ. በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በፋንተም ትዕዛዝ/መመሪያ ምክንያት የተፈጸሙ ግብይቶች በዕለታዊ የዋጋ ገደብ ውስጥ የተፈጸሙ ቢሆንም የምርት ገበያውን ህልውናና ጤናማ አሰራር አደጋ ላይ የሚጥሉ ከሆነ ምርት ገበያው ግብይቶቹን መሰረዝ አለበት፡፡

ሠ. በምርት ገበያው የግብይት መድረክ የተፈጸመ ፋንተም ትዕዛዝ/መመሪያ ካልተሰረዘ ከፋንተም ትዕዛዝ ተቃራኒውን የያዘው ተገበያይ ምርት ገበያውን ተጠያቂ ሊያደርገው አይችልም፡፡ ካለፈቃዱ በፋንተም ትዕዛዝ ምክንያት ለተገበያየ ሰው ምርት ገበያው ተጠያቂ ይሆናል፡፡ ለዚህ ሰው የምርት ገበያው ተጠያቂነት በተሸጠበት ዋጋ እና ሊሸጥ ይችልበት የነበረው ዋጋ መካከል ያለውን የዋጋ ልዩነት ብቻ መሆን አለበት፡፡

## 5.4 የግብይት ደንቦች

### 5.4.1 የግብይት ክፍለ ጊዜ መክፈቻ ጥሪ

5.4.1.1 እያንዳንዱ በቃል የማስተጋባት የግብይት መድረክ ክፍለ ጊዜ ሲጀምር በምርት ገበያው በይፋ በተገለፀው የመክፈቻ ጊዜ ሰሌዳ መሠረት አንድ የመክፈቻ ጥሪ መደረግ አለበት፡፡

5.4.1.2 ምርት ገበያው እያንዳንዱ የኤልክትሮኒክ ግብይት ክፍለጊዜ መቼ እንደሚከፈት በየጊዜው በቅድሚያ ያሳውቃል

### 5.4.2 የግብይት ክፍለ ጊዜ መዝጊያ ጥሪ

5.4.2.1 በቃል የማስተጋባት የግብይት ክፍለ ጊዜ ከመዘጋቱ በፊት ያለው የአንድ ደቂቃ ጊዜ ለእያንዳንዱ የግብይት ክፍለ ጊዜ እንደመዝጊያ ጊዜ ይቆጠራል።የግብይት መድረኩ ተቆጣጣሪ የመዝጊያ ጊዜው ሲጀምር የመጀመሪያውን የመዝጊያ ጥሪ እንዲሁም የግብይት ጊዜው ሲያበቃ የመጨረሻውን የመዝጊያ ጥሪ ማሰማት አለበት።

5.4.2.2 ምርት ገበያው እያንዳንዱ የኤሌክትሮኒክ ግብይት ክፍለጊዜ መቼ እንደሚዘጋ በየጊዜው በቅድሚያ ያሳውቃል፡፡

5.4.3 ዕለታዊ የዋጋ ገደብ

5.4.3.1 ለእያንዳንዱ ውል ካለፈው ዕለት ከተሰጠው የመጨረሻ መዝጊያ ዋጋ ከፍ ወይም ዝቅ ሊል በሚችል ውኸቀት መገበያየት ይፈቀዳል።

5.4.3.2 በግብይት ክፍለ ጊዜው ውስጥ ምንም ግብይት ካልተፈፀመ የመዝጊያ ዋጋው በመጨረሻ የተመዘገበው ዋጋ መሆን አለበት።ሆኖም በመጨረሻ የተመዘገበው ዋጋ አምስት ቀን ወይም ከዚያ በላይ ከቆየ የምርት ገበያው ተገቢ ነው ብሎ በገመተው መጠን የዋጋ ገደብ ሊያስቀምጥ ይችላል።

5.4.3.3 የተለየ ሁኔታ ባጋጠመ እና ምክንያቱ በጽሁፍ ተመዝግቦ ከተያዘ፣ የምርት ገበያው ማኔጅመንት፣በተቻለ ፍጥነት ለቦርዱ በማሳወቅ፣ የአንዱን ውል ዕለታዊ የዋጋ መጠን ሊለውጥ ይችላል።

5.4.4 የመክፈቻ ዋጋ

5.4.4.1 የእያንዳንዱ ውል መጀመሪያ የተገለፀ ወይም የቀረበ የጨረታ ግዢ ወይም ሽያጭ ዋጋ በእያንዳንዱ ውል ውስጥ እንደተጠቀሰው ለዕለቱ በተወሰነው የዋጋ ገደብ ውስጥ መሆን አለበት።

5.4.4.2 የውሉን የገበያ ዋጋ የሚያቋቁሙ ወይም የሚለውጡ ተከታይ ጨረታዎች ወይም ሽያጮች ላይ የሚደረግ ጭማሪ ዕለታዊውን የዋጋ ገደብ መብለጥ የለበትም።

5.4.5 የመዝጊያ ዋጋ

5.4.5.1 ውሎች መዝጊያ ዋጋ የሚሰላበትን ቀመር የምርት ገበያው የስራ አመራር በየጊዜው ይወስናል፡፡ ምርት ገበያው ይህንን ውሳኔውን ለምርት ገበያው ቦርድ እና ለባለስልጣኑ በተቻለ ፍጥነት ያሳውቃል፡፡”

5.4.6 ዕለታዊ የአቋም ወሰን

5.4.6.1 ዕለታዊ የአቋም ወሰን አንድ አባል በአንድ የግብይት ክፍለ ጊዜ እንዲገዛ ወይም እንዲሸጥ የሚፈቀድለት በእያንዳንዱ ውል ውስጥ የተገለፀ ከፍተኛው መጠን ነው።

5.4.6.2 የተለየ ሁኔታ ሲፈጠር እና በጽሁፍ ተመዝግቦ በሚያዝ ምክንያት፣ የምርት ገበያው ማኔጅመንት፣በተቻለ ፍጥነት ለዳይሬክተሮች ቦርድ በማሳወቅ፣ በአንድ የግብይት ክፍለ ጊዜ ውስጥ የነበረውን ዕለታዊ የአቋም ወሰን መለወጥ ይችላል።

## 5.5 የግብይትና የግብይት መድረክ አሠራሮች

5.5.1 በግብይት መድረኩ ጨረታዎችና የግዥ ዋጋዎች

በግብይት መድረኩ የሚደረጉ የጨረታዎችና ለውሎቹ የተሰጡ ዋጋዎች የጨረታ ጊዜና ሽያጭ

5.5.1.1 በተፈቀደው የግብይት ሰዓት ወቅት ለተሳታፊዎች በቃል በማስተጋባት ለሁሉም የመድረክ ተወካዮች መድረስ በሚችል መልኩ በውድድር፣ በይፋና በሚሰማ መልኩ መከናወን አለበት።

5.5.1.2 የሽያጩ መጠን ካልተገለፀ አንድ ውል እንደሆነ የሚቆጠር ሲሆን መጠኑን ያልገለፀዉ የመድረክ ተወካይ ቢያንስ አንድ ውል እንዲቀበል ይገደዳል።

5.5.1.3 ጨረታው፣ ግዢ ወይም ሽያጭ ያቀረበው የመድረክ ተወካይ ላቀረበው ጨረታ ግዢ ወይም ሽያጭ ወይም የጨረታ ግዢ ወይም ሽያጭ ክፍል የጠራውን ዋጋ ለተቀበለ የመጀመሪያ የመድረክ ተወካይ ክፍት መሆን አለበት።

5.5.1.4 ጨረታው ግዢ ወይም ሽያጩን ያቀረበው የመድረክ ተወካይ ወይም አባል ላቀረበው ጨረታ ወይም ሽያጭ ወይም የጨረታ ወይም የሽያጭ ክፍል የጠራውን ዋጋ የተቀበለ የመጀመሪያ የመድረክ ተወካይ ወይም አባል ላይ አስገዳጅ ይሆናል።

5.5.1.5 ወዲያውኑ ተቀባይነት ካላገኘ እንደተተወ ይቆጠራል።

5.5.1.6 በአማርኛ ቋንቋ መከናወን አለበት።

5.5.2 በኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ የሽያጭ እና የግዥ ጥያቄ

5.5.2.1 ትዕዛዝ ማስገባት

ሀ. በምርት ገበያው የኤሌክትሮኒክ ግብይት ማካሄድ የሚቻለው በተፈቀዱ የኤሌትሮኒክስ ግብይት ስራ ማከናወኛ መሳሪያዎች አማካኝነት ብቻ ነው፡፡

ለ. በኤሌትሮኒክስ ግብይት መሳተፍ የሚችሉት ሰርተፍኬት የተሰጣቸው ኤሌክትሮኒክ የግብይት ተወካዮች ወይም የራሳቸውን መመሪያ የሚያስገቡ ደንበኞች ብቻ ናቸው፡፡

ሐ. እያንዳንዱ ኤሌክትሮኒክ የግብይት ተወካይ ወይም የራሱን መመሪያ የሚያስገባ ደንበኛ በምርት ገበያው የሚሰጥ እና ወደ ኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ ለመግባት የሚያስችል ልዩ መለያ ቁጥር ይሰጠዋል፡፡ መመሪያ ወይም ትዕዛዝ ወደ ኤሌክትሮኒክ መገበያያ መድረክ ማስገባት የሚችለው በምርት ገበያው የሚዘጋጀው የተጠቃሚ መለያ ቁጥር የተሰጠው ሰው ብቻ ነው፡፡

መ. መመሪያ ወይም ትዕዛዝ ለማስገባት ቢያንስ የሚከተሉት መረጃዎች ያስፈልጋሉ፡

i. የተሰጠ መለያ ቁጥር፤
ii. የአባል መለያ ቁጥር፤
iii. ዋጋ፤
iv. ብዛት፤
v. የግብይት አይነት (የገዥ ወይም የሻጭ)፤
vi. የሚጸናበት ጊዜ፤
vii. ቀርብበት ቦታ፤ እና
viii. የምርት መረጃ ናቸው፡፡

ምርት ገበያው የሚጠየቀውን አነስተኛ መረጃ በየጊዜው ሊቀይር ይችላል፡፡

ሠ. ውስን ተገበያይ አባል በተፈቀደለት (ገዢ-ብቻ ወይም ለሻጭ-ብቻ ) አቋም በኩል በኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ ትእዛዝ እንዲያስገባ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

ረ. በዚህ ደንብ ንዑስ አንቀፅ 5.5.7.2 የተቀመጠው ቢኖርም የኤሌክትሮኒክ የግብይት ተወካይ የተቀበለው ወደ ኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ በቀጥታ መግባት የሚችል መመሪያን በተመለከተ ከላይ ከተገለጸው

መረጃ ውጭ ሌላ ተጨማሪ ሪከርድ እንዲያዝ አይጠበቅም፡፡ ይሁንና ኤሌክትሮኒክ የግብይት ተወካይ የተቀበለው መመሪያ በቀጥታ ወደ ኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ ማስገባት የማይቻል ከሆነ መመሪያውን እና የተመደበለትን ሂሳብ፣ ቀን፣ መመሪያው የተሰጠበትን ጊዜ ጨምሮ የተሰጠውን መመሪያ በጽሁፍ መያዝ አለበት፡፡ መመሪያው መፈጸሚያው ጊዜ ሲደርስ ወደ ኤሌክትሮኒክ የግብይት ስርዓት ውስጥ መግባት አለበት፡፡ የራሱን መመሪያ የሚያስገባ ደንበኛ ይህን አይነት መረጃ መያዝ ግዴታ የለበትም፡፡

5.5.2.2 ትእዛዝ የሚጸናበት ጊዜ

.

ሀ. እስከሚሰረዝ ድረስ የሚጸና ትዕዛዝ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ካልተፈጸመ ወይም ትእዛዙ ከእለቱ የዋጋ ገደብ ውጪ በመሆኑ ምክንያት ካልተሰረዘ ሲስተሙ ትእዛዙን ከምን ያህል ቀናት በኋላ መሰረዝ እንዳለበት የምርት ገበያው ይወስናል፡፡

ለ. ምርት ገበያው እስከ እለት ድረስ ብቻ የሚጸና ትዕዛዝ የሚቆይበትን ከፍተኛውን ቀን ይወስናል፡፡ ይህ ትዕዛዝ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ሳይፈጸም ከቀረ ወይም ትዕዛዙ ከእለቱ የዋጋ ገደብ ውጪ ከሆነ ትዕዛዙን ሲስተሙ ይሰርዘዋል፡፡"

5.5.3 ግብይቶች

ኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ ከተሳታፊዎች ማንነት በስተቀር የተፈጸሙ ግብይቶችን ዝርዝር መረጃ በሙሉ ለተገበያዮች እንዲታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡ የተከናወኑ ግብይቶች በሙሉ በተከናወኑበት ዕለት በክፍያና ርክክብ መመሪያ መሠረት ክፍያ እንዲፈፀም ለምርት ገበያው የክፍያ መፈፀሚያ ተቋም መቅረብ አለባቸው።

5.5.4 ከዕለታዊ የዋጋ ገደብ ውጪ የተከናወኑ ሽያጮች

ከዕለታዊ የዋጋ ገደብ ውጪ የተከናወኑ ግብይቶች በሙሉ ውድቅ ይደረጋሉ፡፡ የዚህ አይነትግብይቶች በምርት ገበያው ሪፖርት መደረግ የለባቸውም።

5.5.5 የአፈፃፀም ዋስትና መስጠት

5.5.5.1 ማንኛውም በምርት ገበያው ላይ ምርት ወይም ውል ለመግዛት ወይም ለመሸጥ መመሪያ የተቀበለ አባል በግልጽም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ መመሪያው የሚፈጸምበት ሁኔታ ላይ ዋስትና ለመስጠት አይችልም።አባሉ በቃል የማስተጋባት ወይም በኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረኩ ላይ በጨረታ የተከናወነ ወይም የተፈፀመ ግብይትን ብቻ ሪፖርት ማድረግ አለበት።

5.5.5.2 ይህ ድንጋጌ በስህተት ወይም ትዕዛዙን በአግባቡ ባለመፈፀም የደረሰ ጉዳትን ወይም ኪሳራን ለመሸፈን ወይም ለመጋራት እንዳያስችል ተደርጎ መተርጐም የለበትም፡፡

5.5.6 የግብይት ተወካዮች ምርት ገበያው ቅጥር ግቢ ስለመገኘት
የግብይት ተወካይ ወይም መመሪያ ማስገባት የተፈቀደለት ደንበኛ ሊሳተፍበት ያሰበው ግብይት የመጀመሪያ የግብይት ክፈለ ጊዜ ከመከፈቱ ከግማሽ ሰዓት አስቀድሞ በምርት ገበያው ቅጥር ግቢ ውስጥ በአካል መገኘት አለበት።

5.5.7 የደንበኛ መመሪያ መዝገብ

5.5.7.1 ሁሉም የደንበኛ የግዥ ወይም የሽያጭ መመሪያ በስልክ አማካኝነት መሆን አለባቸው። እያንዳንዱ የስልክ ጥሪ ከአንድ አመት ላላነሰ ጊዜ ተመዝግቦ ይያዛል።

5.5.7.2 አባል ወይም ኤሌክትሮኒክ የግብይት ተወካይ ሁሉንም የደንበኛ የግዥ ወይም የሽያጭ መመሪያ ከአስር አመት ላላነሰ ጊዜ በጽሁፍ መዝግቦ ይይዛል፡፡ ይህ የጽሁፍ መዝገብ የሚከተሉትን መረጃ ይይዛል፡- የደንበኛ መለያ ቁጥር፣ የመመሪያው ዝርዝር(ዋጋ፣ መጠን፣ የግብይት አይነት (ግዥ ወይም ሽያጭ)፣ የሚጸናበት ጊዜ እና የመመሪያው አይነት) ፣ የግብይቱ አይነት እና መመሪያው የተሰጠበት ትክክለኛ ጊዜ ናቸው፡፡ ምርት ገበያው የጽሁፍ መዝገቡን በየተወሰነ ጊዜ ኦዲት ሊያደርግ ይችላል፡፡ ምርት ገበያው ተለዋጭ የደንበኛ መመሪያ መከታተያ ስርዓት ከዘረጋ ይህንን ስርዓት በጽሁፍ መዝገቡ ፋንታ አባላት ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

5.5.7.3 በቃል በማስተጋባት በሚደረግ የመገበያያ መድረክ ለመገበያየት ለአባል የሚደረጉ ወይም ከደንበኛ በስልክ የተሰጡ መመሪያዎች በሙሉ በጽሁፍ ለመቀበል እንዲቻል ቀደም ሲል በቁጥር ቅደም ተከተል በምርት ገበያው ተዘጋጅተው በታተሙ የትዕዛዝ ትኬቶች ላይ መያዝ አለባቸው። እያንዳንዱ የትዕዛዝ ቲኬት ቀን ያለውና ትዕዛዙ እንደተሰጠ ሰዓቱ የታተመበት ሆኖ የሚከተሉትን መመዝገብ አለበት፡-

ሀ. የአባል መለያ ቁጥር፣
ለ. የተፈቀደለት ተወካይ መለያ ቁጥር (ካለ)፣
ሐ. የደንበኛ መለያ ቁጥር (ካለ)፣
መ. በመጨረሻው ደቂቃ የሚለካ ጊዜ፣
ሠ. ለግብይት የቀረበው የሽያጭ ወይም የግዢ መጠን፣
ረ. የትዕዛዝ ዋጋ፣
ሰ. የግብይት አይነት (ሽያጭ ወይም ግዥ) እና
ሸ. የትእዛዝ አይነት (ገበያ፣ ገደብ)።

5.5.7.4 እያንዳንዱ የመድረክ ተወካይ የትዕዛዝ ትኬቱን ሲሞላ የማይሰረዝ ቀለም መጠቀም ያለበት ሲሆን በመጀመሪያ የሞላውን መረጃ ሳይደልዝ/ሳያጠፋ ወይም በማንኛውም መልኩ እንዳይታይ ሳያደርግ በተሳሳተው መረጃ ላይ አንድ መስመር አግድም በመሰረዝ ማንኛውንም ስህተት ለማስተካከል ይችላል።

5.5.7.5 እያንዳንዱ በቃል ማስተጋባት የመገበያያ መድረክ ላይ ግብይት መፈፀም የሚፈልግ የመድረክ ተወካይ የትዕዛዝ ትኬቱን ከሞላ በኋላ የተሞላውን ትኬት በግብይት መድረኩ ላይ እንዲፈጽምለት በተመደበለት የምርት ገበያ ሠራተኛ በኩል ለመድረክ ተወካዩ ማስተላለፍ አለበት።

5.5.8 በቃል የማስተጋባት ግብይት አፈጻጸም

5.5.8.1 እያንዳንዱ በግብይት መድረኩ ላይ ውል የሚገዛ ወይም የሚሸጥ የመድረክ ተወካይ ከግብይቱ ጋር የተያያዘ መረጃ ለመያዝ በአባሉ ወይም በተፈቀደለት ወኪል የተሞላና በንዑስ አንቀጽ 5.5.6.2 ሥር የተዘረዘሩትን መረጃዎች የያዘ የትዕዛዝ ትኬት መጠቀም አለበት።

5.5.8.2 በመድረክ ተወካዮች መካከል በዋጋ ላይ ስምምነት ሲደረስ እያንዳንዱ ተወካይ የስምምነቱን ዋጋ፣ መጠንና ከእሱ ጋር ግብይት ያከናወነውን ተቃራኒ የመድረክ ተወካይ የመለያ ቁጥር መሙላት አለበት።

5.5.8.3 እያንዳንዱ የመድረክ ተወካይ በግብይት መድረኩ ላይ ከተቃራኒ የመድረክ ተወካይ ጋር የተፈፀሙ ግብይቶችን ሁሉ ተቃራኒ የመድረክ ተወካዩን ወዲያውን በማስፈረም ማረጋገጥ አለበት።

5.5.8.4 የትዕዛዝ ትኬቱ ከአንድ በላይ ከሆኑ ተቃራኒ የመድረክ ተወካዮች ጋር ሊፈጸም ይችላል። በዚህ ጊዜ የትዕዛዝ ትኬቱ መጠን፣ ዋጋ፣ የእያንዳንዱ የተቃራኒ የመድረክ ተወካይ መለያ ቁጥር እና ፊርማመያዝ አለበት።

5.5.8.5 እያንዳንዱ የመድረክ ተወካይ ግብይቱንና ተያያዥ መረጃዎችን ካረጋገጠ በኋላ እያንዳንዱ የተሟላ የትዕዛዝ ትኬት ላይ የግዜ ማህተም ማድረግ አለበት።

5.5.8.6 በግብይት ክፍለ ጊዜው መጨረሻ ላይ ሳይሟላ የቀረ የትዕዛዝ ትኬት ካለ የቀረው የትዕዛዝ ትኬት ዋጋ የማይኖረው ሲሆን በሚቀጥለው ቀን እንደገና መሰጠት አለበት።

5.5.9 መመሪያ የማጽደቅ ቅደም ተከተል

ሀ. መመሪያ የሚጸድቅበት የቀደምትነት መስፈርት ጊዜ ነው ፡፡

ለ. ኤሌክትሮኒክ የግብይት ተወካይ የራሱን መመሪያ የማስገባት መብት የሌለውን ደንበኛ መመሪያ በተቀበለበት ቅደም ተከተል ወደ ኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ ያስገባል፡፡ በቂ እና ተገቢነት ባለው ምክንያት ወዲያው ወደ ኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ መግባት ያልቻለ መመሪያ ወደ ሲስተሙ በተቻለ ፍጥነት በቀረበበት ቅደም ተከተል መሰረት መግባት አለበት፡፡

ሐ. ከላይ የተቀመጠው ጠቅላላ ድንጋጌ ቢኖርም አባላት በእጃቸው ያሉትን መመሪያዎች በሙሉ ሳያስገቡ የራሳቸውን ትዕዛዝ ወደ ኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ ማስገባት አይችሉም፡፡

5.5.10 ትዕዛዝ ማዛመድ

ሀ. ምርት ገበያው ተመሳሳይ ወይም የተለያዩ የትዕዛዝ ማዛመጃ ደንቦችን መሰረት በማድረግ ከአንድ በላይ የትዕዛዝ መዝገቦችን ጎን ለጎን ወይም በተለያየ ጊዜ ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ምርት ገበያው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም ጊዜ የማንኛውንም ውል ትዕዛዝ የማዛመጃ ደንብ የማስተካከል ወይም የመለወጥ መብት አለው፡፡ የዚህን አይነት ማስተካከያዎች ወይም ለውጦች ከመተግበሩ በፊት ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ያሳውቃል፡፡

ለ. ከላይ የተቀመጠው ጠቅላላ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ትዕዛዝ የሚዛመድበት መንገድ የሚከተለው ገጽታ ይኖረዋል፣

i. ትዕዛዝ በዋጋ - ጊዜ ቅድመ ተከተል መሰረት በማድረግ ይዛመዳል፣
ii. ምርጥ የግዥ ትዕዛዝ ከምርጥ የሽያጭ ትዕዛዝ ጋር ይዛመዳል፣
iii. ሁለት የተለያዩ ዋጋ ያላቸው ትዕዛዞች ከተዛመዱ ግብይቱ መጀመሪያ በገባው ዋጋ ይፈጸማል፡፡

5.5.11 የኤሌክትሮኒክ ግብይት መመሪያ እና ትዕዛዝ ማስተካከል እና መሰረዝ

ሀ. የኤሌክትሮኒክ የግብይት ተወካይ ትዕዛዝ ከመፈጸሙ በፊት ትዕዛዙን ማስተካከል ወይም መሰረዝ ይችላል፡፡

ለ. የራሱን መመሪያ የሚያስገባ ደንበኛ መመሪያው ከመፈጸሙ በፊት መመሪያውን ማስተካከል ወይም መሰረዝ ይችላል፡፡

ሐ. ማንኛውም አይነት ትዕዛዝ ወይም መመሪያ ማስተካከል ቀድሞ የመፈጸም ተራ ላይ ተጽእኖ ሊያመጣ የሚችል አዲስ ሰአት ያስከትላል፡፡

5.5.12 በግብይት መድረኩ ላይ የተከናወኑ ግብይቶች መዝገብ

5.5.12.1 በግብይት መድረኩ ላይ ውል የገዛ ወይም የሸጠ እያንዳንዱ የመድረክ ተወካይ የመጀመሪያውን የተሞላና የጊዜ ማህተም የተደረገበት የትዕዛዝ ትኬት ቅጂ በግብይት መዝጋቢው እንዲመዘገብ እና ትኬቱ ከተሞላ ምርት ገበያው በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግብይት እንዲፈፀም ማስተላለፍ አለበት።

5.5.12.2 ሻጭ የመድረክ ተወካዮች እያንዳንዱ ሪፖርት ያደረጉትን ግብይት መመዝገቡን መፈፀሙንና በምርት ገበያው መሰራጨቱን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው።

5.5.13 ተያያዥና ተከታታይነት ያላቸውን ኤሌክትሮኒክ ኦዲት አስፈላጊነት

ምርት ገበያው ትዕዛዝ ማስገባት፣ ማሻሻል እና መሰረዝን ጨምሮ ሁሉንም አግባብነት ያላቸውን ተያያዥና ተከታታይ የኤሌክትሮኒክ ትዕዛዞችን ያካተተ ግልጽ የኦዲት መከታተያ ይኖረዋል፡፡ ይህ ኤሌክትሮኒክ ኦዲት መከታተያ ቢያንስ ለአስር አመት ላላነሰ ጊዜ መያዝ አለበት፡፡

5.5.14 በግብይት መድረኩ ላይ የተከናወኑና የተመዘገቡ ግብይቶችን ማረጋገጥ

እያንዳንዱ በግብይት መድረኩ ላይ ሽያጭ ወይም ግዥ የሚያስፈፅም የመድረክ ተወካይ ከምርት ገበያው ቅጥር ግቢ ከመውጣቱ በፊት የአባላት ግብይቶች ለክፍያና ርክክብ አፈፃፀም መተላለፋቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት። የክፍያ መፈፀሚያ

ተቋሙ የእያንዳንዱን ምርት መደብ ግብይት ክፍለ ጊዜ ሲያበቃ ለመድረክ ተወካዮ የማስታረቂያ ሪፖርት መስጠት አለበት።

5.5.15 ኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ ላይ የተፈጸሙ እና የተመዘገቡ ግብይቶችን ማረጋገጥ

ሀ. ኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ ስርዓት ለኤሌክትሮኒክ የግብይት ተወካይ እና የራሱን መመሪያ ለሚያስገባ ደንበኛ የማስታረቂያ ሪፓርት መስጠት አለበት፡፡ የማስታረቂያ ሪፓርት ይዘት እና መቼ እንደሚሰጥ ምርት ገበያው በየጊዜው ሊወስን ይችላል፡፡

ለ. ምርት ገበያው የተዛመዱ እና የተፈጸሙ ግብይቶችን መመርመር አለበት፡፡

5.5.16 ተቀባይነት ያላቸው የግብይት ትዕዛዞች

የሚከተሉት ትዕዛዞች በመገበያያ መድረኩ እና በኤሌክትሮኒክስ መገበያያ መድረክ ተፈፃሚ ለመሆን ተቀባይነት አላቸው።

5.5.16.1 የሚከተሉት ትዕዛዞች በቃል በማስተጋበት እና በኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ ተፈፃሚ ለመሆን ተቀባይነት አላቸው።

ሀ. የገበያ ትዕዛዝ

የገበያ ትዕዛዝ ማለት በተገኘ ምርጥ ዋጋ ለመግዛት ወይም ለመሸጥ የሚሰጠ ትዕዛዝ ነው።

ለ. ዋጋው የተገደበ ትዕዛዝ

ዋጋው የተገደበ ትዕዛዝ ማለት በተወሰነ ዋጋ (የተገደበ ዋጋ) ወይም በተሻለ ዋጋ ለመግዛት ወይም ለመሸጥ የሚሰጥ ትዕዛዝ ነው።

5.5.16.2 የሚከተሉት የተገደበ ትዕዛዝ አይነቶች ኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ ላይ ቢፈጸሙ ተቀባይነት አላቸው፡፡

ሀ. ሁሉንም የማዘዝ ወይም የመተው ትዕዛዝ - ትዕዛዙን በአንድ ጊዜ ሙሉ ለሙሉ የመፈጸም ወይም ሙሉ ለሙለ የሚተው ትዕዛዝ፤

ለ. የእለት ትዕዛዝ - ካልተሰረዘ በስተቀር ትዕዛዙ በተሰጠበት ቀን ብቻ የሚፈጸም ትእዛዝ፤ .

ሐ. ለእለቱ ብቻ የሚጸና ትዕዛዝ - በትእዛዙ ላይ የተጠቀሰው እለት እስከሚያበቃበት ድረስ ለመፈጸም ዝግጁ የሆነ ትእዛዝ፤ ፡.

መ. እስከሚሰዝ ድረስ የሚጸና ትዕዛዝ - እስከሚሠረዝ ጊዜ ድረስ ለመፈጸም ዝግጁ የሆነ ትእዛዝ፤

ሠ. በባለስልጣኑ መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ የገበያውን ፍላጎት መሰረት አድርጎ ሌሎች የግብይት ትዕዛዝ አይነቶችን የምርት ገበያው ሊጨምር ይችላል፡፡

5.5.17 ለግብይት ሰነዶች ኃላፊነት ስለመውሰድ

5.5.17.1 በቃል የማስተጋባት መገበያያ መድረክ እና የኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ ላይ ግብይት የሚፈፅም አባል ለራሱና ለደንበኛው ጥቅም ሲባል ግብይት የተደረገባቸው የትዕዛዝ ትኬቶችን ወይም ኤሌክትሮኒክ ግብይት ትዕዛዝ የማረጋገጫ ሪፓርት ሁሉ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋትና ጠብቆ ማቆየት አለበት።

5.5.17.2 ግብይቱ ቢፈፀምም ባይፈፀምም እያንዳንዱ አባል በቁጥር ቅደም ተከተል ለተቀመጡት ለሁሉም የትዕዛዝ ትኬቶች ኃላፊነት አለበት።

5.5.17.3 የትዕዛዝ ትኬቶች ቅጂዎች ለሚከተሉት ዓላማዎች ያገለግላሉ፡-

ሀ. የመጀመሪያው ቅጂ - ለምርት ገበያው ስርዓት፣

ለ. ሁለተኛ ቅጂ - ለመድረክ ተወካይ እና

ሐ. ሦስተኛ ቅጂ - ለደንበኛ (ተፈጻሚነት ካለው)።

5.5.17.4 አባላት ግብይት ያልተፈፀመባቸውን ጨምሮ በድምጽ ማስተጋባት ግብይት እና የኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ የትዕዛዝ ትኬቶች ወይም ኤሌክትሮኒክ ግብይት ትዕዛዝ የማረጋገጫ ሪፓርት ቅጂ ለአስር አመት መያዝ አለባቸው።

5.5.17.5 በቦርዱ በፀደቀዉ ሥነ-ሥርዓት መሠረት በድምጽ በማስተጋባት እና ኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ ትዕዛዝ ትኬቶች ወይም ኤሌክትሮኒክ ግብይት ትዕዛዝ የማረጋገጫ ሪፓርት በምርት ገበያው የህግ ማስከበሪያ መምሪያ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰቡ ይችላሉ።

5.5.18 ሪፖርት ያልተደረጉ ወይም በትክክል ሪፖርት ያልተደረጉ ግብይቶች

5.5.18.1 ማንኛውም የግብይት ተወካይ በአግባቡ የተደረገ ግብይት ወይም ትዕዛዝ በትክክል ሪፓርት አልተደረገም ወይም የደንበኛው ትዕዛዝ ሪፓርት በአግባቡ አልተደረገም ብሎ ሲያምን በተቻለ ፍጥነት ለምርት ገበያው የግብይት ክፍለ ጊዜ ተቆጣጣሪ ወይም የተመደበ የምርት ገበያው ሰራተኛ ማሳወቅ አለበት፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይህ የግብይት ተወካይ ጉዳዩን እንዳወቀ ወይም ማወቅ ከነበረበት ጊዜ አንስቶ በትክክል ሪፓርት ባለመደረጉ ወይም በአግባቡ ሪፓርት ባለመደረጉ ሊደርስ የሚችል ማንኛውንም አይነት ኪሳራ ለመቀነስ አስፈላጊ እና ተገቢ የሆነ እርምጃ ወዲያውኑ መውሰድ አለበት፡፡

5.5.18.2 ምርት ገበያው በቅድሚያ የግብይት ስርዓት ወይም አገልግሎት ይህን የተሳሳተ ሪፓርት ሊያደርግ እንደሚችል ገልጾ ትክክለኛውን የግብይት ሪፓርት እንዴት ሊገኝ እንደሚችል በማስታወቂያ አሳውቆ ከሆነ ለዚህ በትክክል ሪፓርት ባልተደረገ ግብይት ምክንያት ለሚደርስ ኪሳራ ኃላፊነት የለበትም፡፡

5.5.15.3 የምርት ገበያው የግብይት ክፍለ ጊዜ ተቆጣጣሪ ወይም የተመደበ የገበያው ሰራተኛ ማረሚያ ወይም ማስተካካያዎችን ከተቻለ በግብይቱ ክፍለ ጊዜ አልያም ስህተቱን በሚያረጋግጥ መረጃ ላይ በመመርኮዝ የግብይቱ ክፍለ ጊዜ ካለቀ በኋላ ስህተቱን ወይም ግድፈቱን የማረም ስልጣን አለው።

5.5.18.4 የምርት ገበያው የማሻሻያ ወይም የማስተካከያ ጥያቄ ዝርዝርን፣ ጥያቄውን ያቀረበውን የግብይት ተወካይ ስምና ማሻሻያው ወይም ማስተካከያውን ያፀደቀውን የግብይት ክፍለ ጊዜ ተቆጣጣሪ ጨምሮ ሁሉንም የማሻሻያ ወይም የማስተካከያ ዝርዝር ይይዛል።

### 5.5.19 ትዕዛዝ በማስተናገድ ወቅት የሚከሰቱ ስህተቶች ወይም ግድፈቶች

#### 5.5.19.1 በጉድለት የሚፈፀም ስህተት

የግብይት ተወካይ በደንበኛው የተሰጠውን መመሪያ ሳይፈፅም ከቀረ ወይም ለምሳሌ የታዘዘውን ያህል ባለመግዛት ወይም ባለመሸጥ ደንበኛውን በማስተናገድ ሂደት ስህተት ከሠራ እና መመሪያው ሊያገኝ ከሚገባው ዋጋ ጋር እኩል በሆነ የገበያ ዋጋ ሊፈፀም ካልቻለ የግብይት ተወካዩ ለደንበኛው እና ለግብይት ክፍለ ጊዜ ተቆጣጣሪው ማሳወቅ አለበት። በመቀጠልም ከሚከተሉት እርምጃዎች አንዱን መውሰድ አለበት፡-

ሀ. መመሪያውን በሚቀጥለው የግብይት ቀን በገበያ ዋጋ መፈፀምና ስህተቱ ባይፈጠር ኖሮ ደንበኛው ሊያገኝ የነበረው ዋጋ የተሻለ ከነበረ የደንበኛውን ሂሳብ ማስተካከል፣

ለ. ተቃራኒ ድንጋጌ ቢኖርም እንኳ ስህተቱ ባይከሰት ኖሮ ትዕዛዙ ያገኝ ከነበረው ዋጋ ጋር እኩል ከሆነ የተቃራኒውን ቦታ ወስዶ ዋጋውን መቀበል፣

ሐ. በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ደንበኛው ስህተቱ ባይከሰት ኖሮ ሊያገኝ ይችል ከነበረው ዋጋ ያነሰ ሊያገኝ አይችልም

መ. ማንኛውም ከላይ በንዑስ አንቀጽ (ለ) መሠረት የተፈፀመ ግብይት ግብይቱ በተከናወነበት ዕለት ከታች በአንቀጽ 5.5.19.4 ስር በተዘረዘሩት ሥነ-ሥርዓቶች መሠረት ለህግ ማስከበሪያ መምሪያ ሪፖርት መደረግ አለበት።

#### 5.5.19.2 "መግባባት የሌለበት ግብይት"

ሀ. ግብይት የፈፀሙ ሁለት የመድረክ ተወካዮች መጠንና ዋጋን ጨምሮ በግብይቱ መሠረታዊ ድንጋጌዎች ላይ ወይም አንዱ የመድረክ ተወካይ ግብይቱን መቀበል ካልቻለ (በሌላ አገላለፅ "መግባባት የሌለበት ግብይት" ሲከሰት)፣ ክፍያ የሚፈጸመው ሁለቱም የመድረክ ተወካዮች በግብይቱ መሠረታዊ ድንጋጌዎች ላይ ሲስማሙ ብቻ ነው።

ለ. መግባባት ላይ ካልተደረሰ ግብይቱ ውድቅ ይሆናል።

ሐ. ግብይቱ ውድቅ ከተደረገ፣ የመድረክ ተወካዩ ለደንበኛው በማሳወቅ ከሚከተሉት እርምጃዎች አንዱን መውሰድ ይችላል፡-

   i. ትዕዛዙን በዚያኑ ዕለት ወይም በሚቀጥለው የግብይት ቀን በገበያ መፈፀምና ስህተቱ ባይከሰት ኖሮ ደንበኛው የተሻለ ዋጋ ያገኝ ከነበረ የደንበኛውን የባንክ ሂሳብ ማስተካከል፣

   ii. (ተቃራኒ ድንጋጌ ቢኖርም እንኳ) ስህተቱ ባይከሰት ኖሮ ትዕዛዙ ያገኝ ከነበረው ዋጋ ጋር እኩል በሆነ ዋጋ የትዕዛዙን ተቃራኒ ቦታ መቀበል ወይም መውሰድ ፣

መ. በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ደንበኛው ስህተቱ ባይከሰት ኖሮ ያገኝ ከነበረው የከፋ ዋጋ ላይቀበል ይችላል።

5.5.19.3 ስህተቶችን ወይም ግድፈቶችን የማስተካከያ ሥነ-ሥርዓት

ሀ. ግድፈት ያለበት ወይም መግባባት የሌለባቸው ግብይቶች በ15 ደቂቃ ውስጥ መፍትሔ ካገኙ በኋላ የግብይት ተወካዩ የሚከተሉትን ዝርዝሮች በግልፅና በትክክል የሚያሳይ የግብይት ማስተካከያ ደረሰኝ (ከዚህ በኋላ "ደረሰኝ" ተብሎ የሚጠራ) ማዘጋጀት ወይም እንዲዘጋጅ ማድረግ አለበት፡-

i. ስህተቱ ወይም ግድፈቱ የተከሰተበት ቀን ፣

ii. የግብይት ተወካዩን መለያ ቁጥር፣

iii. የተቃራኒ የግብይት ተወካዩን የመለያ ቁጥር (ካለ) ፣

iv. (1) በግብይት ተወካዩ የተመዘገበው ግብይት (2) መግባባት የሌለበት ግብይት ሲሆን በተቃራኒ የግብይት ተወካይ የተመዘገበ ግብይት ዝርዝር፣ (3) የግብይት ተወካዩ ከደንበኛው መመሪያ ተቃራኒ አቋም የያዘበት ተቋራጭ ግብይት፣

v. ደረሰኙ የተዘጋጀበት ቀን ፣

vi. ደረሰኙን ያዘጋጀው ግለሰብ ፊርማ እና

vii. የምርት ገበያው የሚጠይቀው ተጨማሪ መረጃ ።

ለ. ደረሰኙ እንደተሞላ የመድረክ ተወካዩ የትዕዛዝ ቲኬቱን ቅጂ ከደረሰኙ ጋር በማያያዝ ደረሰኙንና የግብይት መዝገቡን ለግብይቱ ክፍለ ጊዜ ተቆጣጣሪ ያስተላልፋል። ተቆጣጣሪውም ሰነዶቹ የተሟሉ መሆኑንና ደረሰኙ መፈረሙን መርምሮ በማረጋገጥ አንዱን ቅጂ ለምርት ገበያው ማስቀረት አለበት።

ሐ. የምርት ገበያው ተወካይ ደረሰኙን ከፈረመ በኋላ የመድረኩ ተወካይ ቀሪዎቹን የደረሰኝ ቅጂዎች እንደሚከተለው ያቀርባል፡-

i. የላይኛውን ቅጂ ለግብይት መዝጋቢው ያቀርባል፤ ግብይት መዝጋቢው ደረሰኙ ላይ የጊዜ ማህተም በማድረግ መቀበሉን ያረጋግጣል።

ii. መግባባት በሌለበት ግብይት ጊዜ ሁለተኛው ቅጂ ለተቃራኒ የመድረክ ተወካይ ይሰጣል።

iii. የመድረክ ተወካዩ ደረሰኙን ለአስር ዓመታት መያዝ አለበት።

5.5.19.4 የምዝገባ መስፈርቶች

ሀ. አንድ የግብይት ተወካይ በትዕዛዝ ቲኬት ላይ ስህተትን ለማስታረቅ ሲል ከደንበኛው መመሪያ ተቃራኒ አቋም የወሰደበትን የተቻቻለ ወይንም የታረቀ ግዢና ሽያጭን በማሻሻያነት እንዲያስገባ አይገደድም። ነገር ግን ማንኛውም ስህተትን ለማጣጣት የተደረገ የተቻቻለ ወይንም የታረቀ ግዢና ሽያጭን በአንቀፅ 5.5.7 እና 5.5.8 ከተገለፀው የትዕዛዝ ቲኬት ስርዓት ጋር በሚጣጣም መልኩ መመዝገብ እና ከተቋራጭ ግብይቱ በኋላ

ከተፈፀመ፣ የምርት ገበያው በሚጠይቀው መልኩ በግልፅ ተለይቶ ይቀመጣል።

ለ. ለምርት ገበያው የሚቀርብ የግብይት ዳታ በተለይ የመድረክ ተወካዩ ስህተቶችን ለማስታረቅ ያደረጋቸውን ማናቸውም ተቋራጭ ግብይት መለየት አለበት። ተቋራጭ ግብይትን ለማጣጣት የተያዘ የግብይት ዳታ የማጣጣት ግብይቱ የሚከፈልበትን የባንክ ሂሳብ ማሳየት አለበት።

ሐ. መግባባት ከሌለበት ግብይት ጋር በተያያዘ ማንኛውም የመድረክ ተወካይ በሌላ አባል / የመድረክ ተወካይ ላይ የሚያነሳው ማንኛውም የይገባኛል ጥያቄ በእያንዳንዱ አባል/ የመድረክ ተወካይ የትዕዛዝ ቲኬት ጀርባ ላይ መመዝገብ አለበት። የመድረክ ተወካዮቹ መግባባት ያልተደረሰበትን ግብይት ለመመዝገብ የጊዜ ማህተም የተደረገበት የተፃፈ የትዕዛዝ ቲኬት መጠቀም አለባቸው።

መ. ማስተካከያዎች

መግባባት ከሌለበት ግብይት ወይም ከስህተት ጋር የተያያዘ አለመግባባት ላይ የተሰጠ መፍትሄ አባሉ ወይም የግብይት ተወካዩ በሌላ የግብይት ተወካይ ወይም ደንበኛ ላይ ማስተካከያ ማድረግን የሚጠይቅ ከሆነ ማሻሻያው በቼክ ወይም በባንክ ለባንክ ዝውውር መደረግ አለበት።

ሠ. የግብይት ድንጋጌዎች እንዳይሻሻሉ የተቀመጠ ክልከላ

በዚህ ደንብ በተለየ ሁኔታ ካልተቀመጠ በስተቀር፣ ማንኛውም አባል ወይም የግብይት ተወካይ ስህተትን ለማረም ወይም መግባባት የሌለበት ግብይትን ለማስተካከል የግብይቱን ድንጋጌዎች መለወጥ የለበትም።

ረ. የግልግል ዳኝነት

ከስህተት ወይም መግባባት ከሌለበት ግብይት ጋር በተያያዘ የሚነሱ አለመግባባቶች በዚህ ደንብ አንቀፅ 16 መሠረት በግልግል ዳኝነት መፍትሄ መስጠት የተጠበቀ ይሆናል።

### 5.5.20 ኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ መስተጓጎል

ምርት ገበያው ባለብዙ አማራጭ የአሠራር ዘዴዎች፤ የመደበኛ ሥራ ማስቀጠያ እና የአደጋ ማገገሚያ ዕቅድ በመጠቀም ኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ ስርዓት ጉድለት እንዳይኖር ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ ከፍተኛ ኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ ስርዓት መስተጓጎል ከተከሰተ ምርት ገበያው የግብይት ሰዓትን ማራዘም፣ መደበኛው የግብይት ክፍለጊዜ ሲጠናቀቅ ሌላ የግብይት ክፍለጊዜ በተመሳሳይ ቀን መክፈት ወይም ሌላ የመገበያያ አማራጭ ማቅረብ አለበት፡፡ ይህ ውሳኔ የገበያውን ደህንነት ከግንዛቤ ያስገባ መሆን አለበት፡፡

## 5.6 ልዩ የቀጥታ ንግድ

አግባብ ባላቸው ሕጎች ድንጋጌ በቀጥታ ምርታቸውን ለውጭ ገበያ የመላክ መብት የተሰጣቸው የልዩ ምርት አምራቾች በምርት ገበያው ልዩ የቀጥታ ንግድ አገልግሎት አማካኝነት ከአለም አቀፍ ገዥዎች ጋር ሊገበያዩ ይችላሉ::

ልዩ የቀጥታ ንግድ አገልግሎት በአምራቾች እና በአለም አቀፍ ገዥዎች መካከል የሽያጭ ውልን ለማስፈጸም የታለመ ሳይሆን ትክክለኛው የገበያ ዋጋ የሚታወቅበትን ሁኔታ የማመቻቸት እና ገበያውን የማቀናጀት ዓላማን መሰረት ያደረገ ነው:: በምርት ገበያው ልዩ የቀጥታ ንግድ ጨረታ ከተከናወነ በኋላ አለምአቀፍ የሽያጭ ውል በቀጥታ በአምራቹ እና በአለም አቀፍ ገዥው መካከል ይፈጸማል::

5.6.1 በልዩ የቀጥታ ንግድ ለመሳተፍ ብቁ ስለመሆን

በልዩ የቀጥታ ንግድ ለመሳተፍ የሚችሉት ዋና ዋና ተዋንያን:-

5.6.1.1 ገበሬዎች፣ የሕብረት ስራ ማህበራት፣ የግል ባለሀብቶች እና መንግስታዊ አምራች የልማት ድርጅቶች የመሳሰሉት የልዩ ምርት አምራቾች እና

5.6.1.2 አለም አቀፍ የምርት ገዥ ወይም ህጋዊ ተወካዩ ናቸው፡፡

5.6.2 ልዩ የቀጥታ ንግድ ምርትን ስለማከማቸት

5.6.2.1 በልዩ የቀጥታ ንግድ መሳተፍ የሚፈልግ አምራች ምርቱን ለዚሁ ተብሎ በተመደበ መጋዘን ማከማቸትና ለምርቱ ልዩ ደረጃ የተሰጠዉ መሆን ይኖርበታል::

5.6.2.2 ምርቱ የቅድመ ወጪ ንግድ ወይም ድህረ ወጪ ንግድ ዝግጅት ልዩ ደረጃ ያገኘ ሊሆን ይችላል::

5.6.2.3 ሻጩ ምርቱን በምርት ገበያው በተመደበ የማከማቻ መጋዘን ማስቀመጥና ልዩ የቀጥታ ንግድ ምርት የማከማቻ መጋዘን ደረሰኝ ያገኘ መሆን ይኖርበታል::

5.6.2.4 ለማከማቸት የሚቻለው አነስተኛ መጠን 30 ከረጢት ወይም በምርት ገበያው በሚወሰነው መጠን መሰረት ይሆናል::

5.6.2.5 የምርት ገበያው የምርቱን ጥራት፣ የአምራቹን ማንነት እና የምርቱን ልዩ ባህርያት የሚገልፅ ልዩ የቀጥታ ንግድ ምርት የማከማቻ መጋዘን ደረሰኝ ለአስቀማጩ ይሰጣል::

5.6.2.6 ለልዩ የቀጥታ ንግድ የሚቀርብ ምርትን የመመዝገብና የማስተዳደር ስራ ሲከናወን እያንዳንዱ ምርት በአምራቹ ማንነት ተለይቶ መከማቸት ይኖርበታል::

5.6.3 በልዩ የቀጥታ ንግድ ጨረታ ለመሳተፍ ብቁ ስለሚያደርጉ ሁኔታዎች

5.6.3.1 የምርት ገበያው አስፈላጊ ነው ብሎ ባመነበት አስቀድሞ በተገለፀ ጊዜ በልዩ ምርት አምራቾችና አለም አቀፍ ገዥዎች መካከል ልዩ የቀጥታ ንግድ በመደበኛነት ያከናውናል::

5.6.3.2 የተለየ አሰራር ለመከተል መፈለጉን ለምርት ገበያው ካላሳወቀ በቀር የልዩ ምርት አምራቹ የወጪ ንግድ አገልግሎት የሚሰጠው ሶስተኛ ወገን መሰየም ይኖርበታል:: ለልዩ የቀጥታ ንግድ ጨረታ ብቁ ለመሆን አምራቹ የወጪ ንግድ አገልግሎት ስምምነት በምርት ገበያው ማስመዝገብ ይኖርበታል::

5.6.3.3 አምራቹ በጨረታው ክፍለ ጊዜ በሌላ ሰው መወከል ከፈለገ የወኪሉን ማንነት ማመልከትና የውክልና ውሉን ማያያዝ ይኖርበታል::

5.6.3.4 የምርት ገበያው ከጨረታው አስቀድሞ ብቁ በሆኑ አምራቾች ለልዩ የቀጥታ ንግድ ጨረታ የቀረበውን የምርት መጠን መደብ(ሎት) እንዲሁም የምርቱን ብዛት፣ የአምራች ማንነት፣ ምርቱ የተመረተበት አካባቢ፣ የምርቱ መጠን፣ ደረጃ፣ ሌሎች የምርቱን ልዩ ባህርያት እና የተሰየመውን የወጪ ንግድ አገልግሎት ሰጪ ይፋ ማድረግ ይኖርበታል::

5.6.3.5 የጨረታው ክፍለ ጊዜ ይፋ መደረጉን ተከትሎ ምርት ገበያው በልዩ የቀጥታ ንግድ ክፍለ ጊዜ ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸውን አለም አቀፍ ገዥዎች ቅድመ ምዝገባ ማድረግ ይኖርበታል:: ገዥው የንግድ ድርጅቱን የተመለከተ መረጃ እንዲሰጥ እና ለጨረታዉ ክፍለ ጊዜ በሌላ ሰው መወከል ከፈለገ የወኪሉን ማንነት እንዲገልፅ እና የውክልና ውልም እንዲያይዝ መደረግ ይኖርበታል::

5.6.3.6 የገዥ ምዝገባ ፍጻሜ ተከትሎ የምርት ገበያው የምርቱን ናሙና በሚቀርብለት ጥያቄ መሰረት ለሚፈልጉ ገዥዎች መላክ እና ልዩ የቀጥታ ንግዱ ጨረታ ከሚካሄድበት ጊዜ ቀደም ብሎ ምርቱን ባለበት ቦታ ተገኝተው እንዲመረምሩ መፍቀድ ይኖርበታል::

5.6.3.7 የምርት ገበያው ልዩ የቀጥታ ንግድ ጨረታ ክፍለ ጊዜው ከመጀመሩ በፊት ቅድመ ምዝገባ ያደረጉትን ገዥዎች ማንነት ይፋ ማድረግ አለበት::

5.6.4 ልዩ የቀጥታ ንግድ ጨረታ ሂደት ሥነ-ሥርዓት

5.6.4.1 በልዩ የቀጥታ ንግድ ጨረታ ለመሳተፍ የሚፈቀድላቸው ብቁ የሆኑ አምራቾች እና ቅድመ ምዝገባ ያደረጉ ገዥዎች እና/ወይም ወኪሎቻቸው ብቻ መሆን አለባቸው::

5.6.4.2 ጨረታው በምርት ገበያው አማካኝነት ገዥና ሻጭ ወይም ወኪሎቻቸው በሚሳተፉበት በቃል በማስተጋባት ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በመገበያያ መድረክ ላይ መደብ በመደብ (በሎት) መካሄድ ይኖርበታል::

5.6.4.3 የእያንዳንዱ መደብ (ሎት) ግብይት እንዳበቃ ምርት ገበያው የተጫራች ወገኖችን ማንነት፣ የተስማሙበትን ዋጋ እና የምርት መጠን መዝግቦ በመያዝ የልዩ የቀጥታ ንግድ ክፍለ ጊዜ ማጠቃለያ ሪፖርት አዘጋጅቶ ይፋ ማድረግ ይኖርበታል::

5.6.4.4 በልዩ የቀጥታ ንግድ የጨረታ ክፍለ ጊዜ ስምምነት ላይ የተደረሰበት ዋጋ እና የምርት መጠን በሁለቱ ወገኖች ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል፡፡

5.6.4.5 አምራቹ ወይም የወጪ ንግድ አገልግሎት ሰጪው ልዩ የቀጥታ ንግድ ጨረታ በተከናወነ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ በብሔራዊ ባንክ የተመዘገበ አለም አቀፍ የሽያጭ ውል ቅጂ ለምርት ገበያው ማቅረብ አለባቸው::

5.6.4.6 በተመዘገበው የሽያጭ ውል ላይ የተመለከተው ዋጋ፣ የምርት መጠን ወይም የርክክብ ሁኔታ በልዩ የቀጥታ ንግድ የጨረታ ክፍለ ጊዜ ከተደረገው የስምምነት ሁኔታ(ቃሎች) የተቀየረ ሆኖ ከተገኘ ምርት ገበያው የሃሰት ጨረታ እንደሆነ በመቁጠር ስለሁኔታው ይፋ ማድረግ ይኖርበታል::

5.6.5 ልዩ የቀጥታ ንግድ የውል ቃሎችና ሁኔታዎች

5.6.5.1 በልዩ የቀጥታ ንግድ የጨረታ ክፍለ ጊዜ የሚደረጉ የዋጋ ስምምነቶች ለውጭ ገበያ በሚቀርብ የምርት መጠን ኤፍ.ኦ.ቢ./FOB/ ወደብ እና ለመጓጓዝ ዝግጁ በሆነ ምርት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡

5.6.5.2 ምርት ገበያው ከኤፍ.ኦ.ቢ. የመጨረሻ ዋጋ ቢያንስ 85 ከመቶ ለአምራቹ መድረሱን ማረጋገጥ ይኖርበታል::

5.6.5.3 የምርት ገበያው የሚፈለገው አነስተኛ የአምራች ድርሻ መጠን መስፈርት መሟላቱን የሚያሳይ ደጋፊ ማስረጃ አግባብነት ካላቸው ወገኖች እንዲቀርብለት መጠየቅ አለበት፡፡

5.6.5.4 በእያንዳንዱ ልዩ የቀጥታ ንግድ የጨረታ ክፍለ ጊዜ የተደረሰባቸው በአለም አቀፍ የሽያጭ ውል ላይ የተጠቀሱ ዋጋዎችን እና የምርት መጠኖች ክትትል ተደርጎባቸው በምርት ገበያው ይፋ መደረግ ይኖርባቸዋል::

5.6.5.5 የምርት ገበያው የተከማቸውን ልዩ ምርት ጥራት፣ መጠንና ርክክብ በተመለከተ ለሻጩ ወይም ለወጪ ንግድ አገልግሎት ሰጪው ዋስትና ይሰጣል:: ሆኖም በአምራቹና በአለም አቀፍ ገዥው መካከል የተደረገው አለም አቀፍ የሽያጭ ውል አፈፃፀም አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት የሚገዛ ይሆናል::

5.6.5.6 የምርት ገበያው የአምራቹን ምርት ወደ ውጭ ገበያ የመላክ ልምድ መሰረት በማድረግ ከግዴታ ነጻ ካላደረገው በቀር፣ ልዩ የቀጥታ ንግድ ተሳታፊ አምራቾች ሁሉ በምርት ገበያው የፀደቀ የተሸጠውን ምርት አለም አቀፍ ገዥው እስኪረከብ ድረስ ያሉትን ኃላፊነቶች በሙሉ ያካተተ የወጪ ንግድ አገልግሎት ሰጪ ስምምነት እንዲገቡ የምርት ገበያው መጠየቅ አለበት::

5.6.5.7 ከልዩ የቀጥታ ንግድ ጨረታ ክፍለ ጊዜ የሚመነጩ ሁሉም አለም አቀፍ የሽያጭ ውሎች አምራቹና የወጪ ንግድ አገልግሎት ሰጪው ያደረጉትን የአሰራር ስምምነት ማጣቀስ ይኖርበታል፡፡ የአሰራር ስምምነቱ የወጪ ንግድ አገልግሎት ሰጪው ማንነት፣ ሚና እና ኃላፊነቶች የሚዘረዘሩበት ይሆናል፡፡

5.6.5.8 ገዥዎች ለልዩ የቀጥታ ንግድ የግልፅነት ድንጋጌ ተፈጻሚነት ያላቸውን ፈቃደኝነት በቅድመ ምዝገባ ጊዜ ሊገልፁ ይችላሉ:: የግልጽነት ድንጋጌው ለገበሬው ስለሚደርስ ክፍያ እና ለወጪ ንግድ አገልግሎት ሰጪው ስለሚከፈል የአገልግሎት ዋጋ የሚገለጽበት ይሆናል፡፡

5.6.5.9 በአንቀጽ 5.6.5.8 ስር የተጠቀሰው ሁኔታ ሲኖር ገዥው በልዩ የቀጥታ ንግድ ጨረታ ክፍለ ጊዜ ለመክፈል ከተስማማበት ዋጋ በተጨማሪ የተወሰነ የግልፅነት ክፍያ መፈጸም አለበት:: የምርት ገበያው የግልፅነት ክፍያውን መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ መወሰን እና አስቀድሞ ይፋ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

5.6.6 ልዩ የቀጥታ ንግድ ምርት ስለማስረከብ

5.6.6.1 ልዩ የቀጥታ ንግድ ጨረታ ክፍለ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ አምራቹ ምርቱን ከተመደበው መጋዘን የሚያነሳበትን ቀን እና ምርቱን የሚረከበውን ወኪል ማንነት ማመልከት ይኖርበታል::

5.6.6.2 አምራቹ ልዩ የቀጥታ ንግድ ጨረታ ከተከናወነበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሶስት የሥራ ቀናት ውስጥ ምርቱን ለማንሳት ማስቀጠር አለበት::

5.6.6.3 የሽያጭ ውል ከተፈጸመ የምርት ገበያው የመጋዘን አገልግሎት፣ የሙያ እና የግብይት አገልግሎት ክፍያ በአምራቹ ወይም በተሰየመ ወኪሉ አማካኝነት እንደተፈጸመ እንዲሁም አለም አቀፍ ገዥው የግብይት አገልግሎት እና ሌሎች የአገልግሎት ክፍያዎች እንደፈፀመ የምርት ገበያው ምርቱን መልቀቅ ይኖርበታል::

5.6.6.4 አምራቹ ልዩ የቀጥታ ንግድ ጨረታ ከመከናወኑ በፊት ወይም ከተጠናቀቀ በኋላ ስምምነት የተደረገበት ሽያጭ ሳይፈጸም ከቀረ ምርቱን በማናቸውም ጊዜ ለማንሳት ይችላል:: በዚህ ጊዜ የምርት ገበያው የመጋዘን እና የሙያ አገልግሎት ክፍያ በአምራቹ ወይም በወኪሉ እንደተከፈለው ምርቱን ያለምንም ቅጣት ለአምራቹ መልቀቅ ይኖርበታል፡፡

5.7 ግብይት መሰረዝ

5.7.1 የተፈጸሙ ግብይቶችን ህልውናና ጤናማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል እና ለህዝብ ይፋ የተደረጉ የግብይት መረጃ ከነባራዊ የገበያ ሁኔታ ጋር የማይጣጣም ከሆነ ይህን ለማስተካከል ምርት ገበያው ግብይቶችን ሊሰርዝ ይችላል፡፡ ይህ እርምጃ ሊወሰድ የሚችለው የምርት ገበያውን የግብይት መድረክ አግባብ ባልሆነ ወይም በተሳሳተ አጠቃቀም ወይም በሲስተም መበላሸት ምክንያት ግብይት የሚያናጉ ሁኔታዎችን ለማስተካከል ነው፡፡ የገበያውን ህልውና እና ጤናማነትን የሚያናጉ ግብይቶችን ምርት ገበያው ሊሰርዛቸው ይችላል፡፡ ግብይት ለመሰረዝ የተወሰኑ ውሳኔዎች በሙሉ ለምርት ገበያው ቦርድ እና ለባለስልጣኑ ወዲያውኑ ሪፓርት ይደረጋሉ፡፡

5.7.2 ከላይ በተቀመጠው አንቀጽ ምክንያት ኪሳራ ደርሶብኛል የሚል ሰው ግብይቱ በተሰረዘ በአምስት ቀናት ውስጥ ለምርት ገበያው ማሳወቅ አለበት፡፡ በጊዜ ያልቀረበ አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡

# 6. ለደንበኛ ወይም ለራስ ስለመገበያየት

6.1 ለደንበኛ ስለተደረገ ግብይት ኃላፊነት

አባል እና የአባሉ የግብይት መድረክ ተወካይ የደንበኛውን መመሪያ ከማስተናገድ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች እና አፈጻጸም በትጋት መከታተል አለባቸው፡፡ በትጋት አለመከታከል አንደቸልተኝነት ይቆጠራል፡፡

6.2 መዝገብ መያዝ

አባላት በምርት ገበያው የተፈቀዱ በሁሉንም ውሎች ላይ የተደረጉ ግብይቶቻቸውን በመዝገብ መያዝ አለባቸው። አባላት በምርት ገበያው ለሚፈፅሟቸው ግብይቶች የራሳቸውን ግብይት እና የደንበኞቻቸውን ግብይቶች መዝገብ ለየብቻ መያዝ አለባቸው። አባላት ለእያንዳንዱ ደንበኞቻቸው ትዕዛዝ የተቀበሉበትን ጊዜና ቀን፣ የተፈፀሙ ዝርዝር ትዕዛዞችንና የሂሳብ መዝገቦች የያዘ መዝገብ ለአስር ዓመት በመያዝ በቦርዱ ወይም/እና በባለሥልጣኑ በተፈለገ ጊዜ ማቅረብ አለባቸው።

6.3 የግብይት አሠራሮች

6.3.1 ከደንበኛ አስቀድሞ መገበያየት

ሀ. እያንዳንዱ አባል እና የግብይት ተወካይ ከደንበኛው ትዕዛዝ አስቀድሞ ግብይት መፈፀም ክልክል ነው። የኤሌክትሮኒክ ግብይት ተወካይ የደንበኛውን መመሪያ ወደኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ ሳያስገባ የራሱን ትዕዛዝ አስቀድሞ ማስገባት ክልክል ነው፡፡

ለ. እያንዳንዱ አባል እና የግብይት ተወካይ ከደንበኛው የምርት ወይም ውልና ግዥ ወይም ሽያጭ መመሪያ ጋር አንድ አይነት ምርት ወይም ውል በገበያ ዋጋ ወይም በተወካይ በራሱ ስም ወይም የአባሉ ጥቅም ባለበት ተገበያይ ስም ተገዝቶ የሚያልቅ ከሆነ የግብይት ተወካዩ ጥቅም ባለበት ማንኛውም ሰው ስም ምርቱን ወይም ውሉን መግዛት ወይም መሸጥ የተከለከለ ነው።

6.3.2 ትዕዛዞቹን ስለ መግለፅ

በባለስልጣኑ ወይም በምርት ገበያው ስልጣን የተሰጠው ተወካይ ሲጠይቅ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም አባል ወይም የግብይት ተወካይ የሌላን ሰው የሽያጭ ወይም የግዥ መመሪያ ማሳወቅ ክልክል ነው፡፡ ማንኛውም አባል ወይም የመድረክ ተወካይ ሌሎችና እነዚህ መረጃዎችን እንዲገልጽለት ማግባባት ወይም ማስገድድ የለበትም፡፡

6.3.3 ተቃራኒ አቋም ስለ መያዝ

ማንኛውም አባል እና የግብይት ተወካይ ከሌላ ግለሰብ ጋር ባለው ቅርበት የተነሳ የተገለፁለትን ትዕዛዞች በተመለከተ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የተቃራኒ ወገንን አቋም መያዝ የተከለከለ ነው።

6.3.4 አስቀድሞ የተመቻቸ ሽያጭ

እያንዳንዱ አባል እና የግብይት ተወካይ ቀደም ብሎ የተመቻቸ ማንኛውም ሽያጭ ወይም ግዥ ከማድረግ ተከልክሏል።

6.3.5 ግብይቶችን ስለመመደብ

እያንዳንዱ የግብይት ተወካይ ግብይቶችን በባንክ ሂሳብ መመደብ ተከልክሏል።

6.3.6 ትዕዛዝ ማዘግየት ወይም መተው

እያንዳንዱ አባል እና የግብይት ተወካይ ለሌላ ሰው ጥቅም ሲባል የአንድን ሰው ትዕዛዝ በሙሉ ወይም በከፊል ከገበያ ማስወጣት ወይም መተው ተከልክሏል።

6.3.7 ከመዝጊያ ደወል በኋላ መገበያየት

እያንዳንዱ የመድረክ ተወካይ የመዝጊያ ደወል ከተደወለ በኋላ በግብይት መድረኩ ላይ ግብይት መፈፀም የተከለከለ ነው።

6.3.8 የተፈፀሙ ግብይቶችን ማሳወቅ

ማንኛውም በቃል በማስተጋባት በተከናወነ ግብይት ላይ የተሳተፈ የመድረክ ተወካይ ግብይቶቹ የተፈፀሙበትን ዋጋ ለግብይት መዝጋቢው ወይም ለግብይት መድረኩ ተቆጣጣሪ ሳያሳውቅ መቅረት የለበትም።

6.3.9 ፍትሀዊ የግብይት መርሆች

እያንዳንዱ የመድረክ ተወካይ አሳሳች የሽያጭ ዘዴዎችን ከማድረግ መቆጠብን ጨምሮ ከፍትሃዊነትና ርትዓዊነት መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ የትዕዛዝ አፈፃፀሙን መከፋፈል አለበት፡፡

6.4 የተከለከሉ ግብይቶች

6.4.1 አባላት ወይም የግብይት ተወካዮች ለራሳቸው ወካይ ለሌላ ሰው ደግሞ ተወካይ መሆን አይችሉም፡፡

ማንኛውም አባላት ወይም የግብይት ተወካይ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን አውቆና ፈቅዶ ወካይና ተወካይ ሆኖ መስራት አይችልም፡፡

6.4.2 የማስመሰል ግብይት፣ ተቋራጭ ግብይት፣ የከለላ መንገድ ግብይት ወይም እውነተኛ ያልሆነ ግብይትየማስመሰል ግብይት፣ ተቋራጭ ግብይት፣ የከለላ መንገድ ግብይት ወይም እውነተኛ ያልሆነ ግብይት ባህሪይ ያላቸው ግብይቶች አካል መሆን ወይም አፈፃፀማቸውን ማረጋገጥ ይህን ድንጋጌ የሚጥስ ይሆናል ።

6.4.3 አንድ አባል ወይም የግብይት ተወካይ የተቋራጭ ግብይትን ትክክለኛ ባህርያት ለመደበቅ ስም በመስጠት እና ሁለት ተቃራኒ ግብይቶችን በማጣጣም የሚፈጥረው የተመቻቸ ግብይት ይህን ድንጋጌ የሚቃረን ይሆናል፡፡

6.4.4 የሀሰት ዋጋ

ማንኛውም ግብይት አንድን እውነተኛና ትክክለኛ ያልሆነ ዋጋ ሪፖርት ለማድረግ ወይም ለመመዝገብ ጥቅም ላይ የዋለ ከሆነ የዚህ ግብይት አካል መሆን ወይም ይህንኑ ግብይት ማረጋገጥ ይህን ድንጋጌ ይቃረናል።

6.4.5 ጎጂ ድርጊቶች

አንድ አባል ወይም የግብይት ተወካይ የምርት ገበያውን ጥቅምና የምርት ግብይቱን መልካም ስም የሚጐዳ ድርጊት ፈፅሞ ከተገኘ ወይም ከፍትሃዊና ርትዓዊ የግብይት መርሆዎች ጋር የማይጣጣም ድርጊት ከፈፀመ ይህን ደንብ እንደጣሰ ይቆጠራል፡፡

6.4.6 ተዛማጅ ግብይቶች

6.4.6.1 ተዛማጅ ግብይቶች በቃል በማስተጋባት ጨረታ

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ካልተሟሉ በስተቀር አንድ የመድረክ ተወካይ በአንድ ጊዜ የሁለት የተለያዩ ደንበኞችን የግዥና የሽያጭ ትዕዛዞች በእጁ በመያዝ እነዚህን ሁለት ትዕዛዞች በገበያ ዋጋ በቀጥታ ካገበያየ ይህን ደንብ እንደጣሰ ይቆጠራል፡፡

6.4.6.1.1 በግብይት መድረኩ የፀና የተዛማጅ ግብይት ለመፈፀም ትዕዛዞቹ በመጀመሪያ ደረጃ ቢያንስ ሁለት ጊዜ ተመሳሳይ ዋጋ በመድረኩ ተሰጥቷቸው በጨረታ ወይም ለሽያጭ በይፋና በውድድር ቀርበው ጨረታውም ሆነ ሽያጩ በሌላ

የመገበያያ መድረክ ተወካይ ተቀባይነት ካላገኙ ትዕዛዙ በቀጥታ ተፈፅሞ ወዲያው የተዛመደው መጠን መገለፅ አለበት ። ይህ ዓይነት ግብይት የመድረክ ግብይቱ ተቆጣጣሪ በአካል በተገኘበት መፈፀም አለበት።

6.4.6.1.2 የፀና የተዛማጅ ግብይት የሚፈፅም የመገበያያ መድረክ ተወካይ ይህንኑ በአግባቡ በተሞላ የትዕዛዝ ቲኬቱ ላይ በግልፅ ማስፈር አለበት። የትዕዛዝ ቲኬቱ ግብይቱ ሲፈፀም ተሞልቶ ወዲያውኑ ለግብይት መድረኩ ተቆጣጣሪ ለማጣራት፣ የጊዜ ማህተም ለማድረግና ለአጭር ፊርማ መቅረብ አለበት።

6.4.6.1.3 ትዕዛዞችን የሚቀበለው ወይም የሚፈፅመው የመገበያያ መድረክ ተወካይ ከአገናኝነት ውጪ በግብይቱ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የራሱ ጥቅም ሊኖረው አይችልም።

6.4.6.1.4 የምርት ገበያው የግብይቱን ቀን፣ ዋጋ፣ መጠን፣ ምርት፣ በማን እንደተፈፀመና በትክክል የተፈፀመበትን ጊዜ የሚያመለክት እያንዳንዱን የፀና ተዛማጅ ግብይት የቋሚ መዝገቡ አካል ማድረግ አለበት።

6.4.6.2 ኤሌክትሮኒክ ተዛማጅ ግብይቶች

"በኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ ላይ አንድ የኤሌክትሮኒክ የመድረክ ተወካይ በአንድ ጊዜ የሁለት የተለያዩ ደንበኞችን የግዥና የሽያጭ መመሪያ በተመሳሳይ ጊዜ ካስገባ ወይም በኤልክትሮኒክ መገበያያ መድረክ ላይ መመሪያ ማስገባት የሚችሉ የአንድ አባል ሁለት ደንበኞች የግዥና የሽያጭ መመሪያዎችን ወደኤሌክትሮኒክ የግብይት መድረክ ካስገቡ ሲስተሙ በቀጥታ ሊያገበያያቸው ይችላል።

6.5 የተከለከሉ የግብይት አሰራሮች

ማንኛውም አባል ወይም የግብይት ተወካይ ግብይቱ የተፈጸመው፤

ሀ. በምርት ገበያው ሰራተኛ ወይም ስራ አስፈፃሚ፣

ለ. በክፍያ መፈጸሚያ ባንክ ሠራተኛ ወይም ዳይሬክተር፣

ሐ. በዕቃ ማከማቻ መጋዘን ሠራተኛ ወይም ዳይሬክተር፣

መ. በሌላ መደበኛ አባል ወይም የዚሁ መደበኛ አባል ሰራተኛ ወይም

ሠ. ውስን አባሉ ሊገበያይ በሚችልበት ምርት ውስን አባል ወይም የዚሁ ውስን አባል ሠራተኛ ወይም

ረ. በባለስልጣኑ ሠራተኛ ወይም የቦርድ አባል ወይም ለእርሱ ተወካይ መሆኑን ካወቁ ወይም ምክንያታዊ ጥንቃቄ በመውሰድ ማወቅ የሚኖርባቸዉ ከሆነ በምርት ገበያው ግብይት እየተደረገባቸው ያሉ ወይም ለግብይት የተዘረዘሩ ምርቶችን አስመልክቶ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ትዕዛዝ መቀበል ወይም መፈፀም ተከልክለዋል።

6.6 ሌሎች የተከለከሉ ድርጊቶች

አባል ወይም የግብይት ተወካይ ከማንኛውም ትዕዛዝ/ መመሪያ ወይም ውል ጋር በተያያዘ ለሌላ ሰው ወይም በሌላ ሰው ስም ሲሰራ የሚከተሉትን መፈጸም የለበትም:

ሀ. ማታለል፡- የወከለውን ሰው ማታለል፣ ማጭበርበር፣ ወይም ለማታለል ወይም ለማጭበርበር መሞከር፣

ለ. በሀሰት ሪፓርት ማድረግ፡- ለወከለው ሰው በፍቃደኝነት የተሣሣተ ሪፖርት ወይም ቃል መስጠት፣ወይም ማስመዝገብ ወይም ለዚህ ምክኒያት ሆኖ መገኘት፣

ሐ. ሆነ ብሎ ማጭበርበር ፡- በማንኛውም ዘዴ ከትዕዛዝ ወይም ከውል፣ ትዕዛዙን ወይም ውሉን ከመፈፀም፣ ለወከለው ሰው ከውሉ ወይም ከትዕዛዝ ጋር በተያያዘ ማንኛውንም የውክልና ተግባር ለመፈፀም ፈቅዶ ማጭበርበር ወይም ለማጭበርበር መሞከር፣

መ. የራስን ጥቅም ማስቀደም፡- ትዕዛዝን ወደጐን በመተው የራስን ጥቅም ማስቀደም፣ ትዕዛዙን ከሌላ ሰው/ዎች/ ትዕዛዞች ጋር በማጣጣት ማሟላት፣ አውቆና ፈቅዶ በሌላ ሰው የተሰጠን የሽያጭ ትዕዛዝ ገዥ መሆን፣ የግዥ ትዕዛዝ ሲሰጥ ራስን ሻጭ ማድረግ፣ ወይም እንደዚህ ዓይነት ተግባር በሚፈፅሙ ሰዎች ወይም ግንኙነት ካላቸው ሰዎች ጋር አውቆ መገበያየት፣

ሠ. ማስገደድ፡- ከአባላት ወይም ከሌሎች ሰዎች ጋር ማንኛውንም ዓይነት የማስገድድ ወይም የማስገድድ ሙከራ ጥፋተኛ መሆን፣ ማንኛውንም የማጭበርበር፣ የሙስና፣ ኢ-ንግዳዊ ወይም ሸፍጠኛ የንግድ አሠራር ላይ መሣተፍ፣

ረ. አሳሳች መሆን፡- የምርቶችን ዋጋ ማሳሳት ወይም ለማሳሳት መሞከር፣

ሰ. ምርትን ከገበያ ማስወገድ፡- ገበያውን በበቂ ሁኔታ ተቆጣጥሮ በምርት ገበያው የሚገበያዩ ምርቶችን ዋጋ ለማዛባት ምርትን ከገበያ ማስወገድ ወይም ለማስወገድ መሞከር፣

ሸ. የተሳሳተ መረጃ ማሰራጨት ፡- የገበያ ፍላጎትን፣ የቀረቡ ዋጋዎችን ወይም የምርት ዋጋዎችን በተመለከተ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች ዜና፣ መረጃ ወይም ወሬ ማሰራጨት

ቀ. የውስጥ አዋቂ መረጃ ተጠቅሞ ግብይት መፈጸም፡- ለሌሎች ተገበያዮች ወይም ለህዝብ ይፋ ያልሆነ የውስጥ አዋቂ መረጃን መሰረት አድርጎ መገበያየት፣ እና

በ. የምርት ተፈላጊነት ላይ ሰውሰራሽ ተጽዕኖ ማድረግ - ሰው ሰራሽ ተፈላጊነት ለማመላከት አሳሳች ግብይት መፈጸም

## 7. ውሎች

7.1 ውል ማለት በምርት ገበያው ቦርድ በተጀመሩ ምርቶች እና በምርት ገበያው ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ለግብይት በተለይ የፀደቁ ሁሉንም ዓይነት ውሎች የሚያካትት ነው።

7.2 የምርት ገበያው ከተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ ፈቃድ ያገኘላቸውን የምርት ውሎች አስመልክቶ የውሎቹን ይዘት የመጨረሻ ቅርጽ የማስያዝ እና/ወይም የማሻሻል ስልጣን የዳይሬክተሮች ቦርድ ይሆናል።

7.3 አባላት ግብይት መፈፀም ያለባቸው በዳይሬክተሮች ቦርድ በተገለፀውና በተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ በፀደቀው የውል ዓይነት ብቻ መሆን አለበት።

7.4 በምርት ገበያው እንዲፈፀሙ የተፈቀዱ የውል ግብይቶች ሁሉ በምርት ገበያው በተፈቀደው አኳኋን ብቻ መፈፀም አለባቸው።

7.5 አባላት ትዕዛዝ ሲመዘግቡ ትዕዛዙ የራስው ወይም የደንበኛቸው እንደሚሆን በግልፅ ማሰቀመጥ አለባቸው። ትዕዛዙ ለደንበኛው ወይም በደንበኛው ስም የሚፈጸም ከሆነ የደንበኛውን የመለያ ቁጥር መግለጽ አለበት።

7.6 አንድ አባል ለደንበኛው ውል ከመፈፀሙ በፊት ከደንበኛው ጋር በምርት ገበያው በተደነገገው ስርዓትና ቅፅ መሠረት የፅሁፍ ስምምነት መፈራረም አለበት።

7.7 በምርት ገበያው የተፈቀዱ የውል ግብይቶች በሙሉ በክፍያ ማስፈፀሚያ ተቋም መመዝገብ ፣መጣራት እና መፈጸም ያለባቸው ሲሆን ፣ በዚህ ደንብ/የውስጥ ደንብ የሚገዙ ይሆናል።

7.8 የምርት ገበያው አባላት በግብይት መድረኩ ላይ ለደንበኞቻቸው ለፈጸሙት ለእያንዳንዱ ግብይት የግብይት ካርድ ማውጣት አለባቸው። እነዚህ የትዕዛዝ ቲኬቶች በምርት ገበያው በተዘጋጀው ቅፅ መሠረት ብቻ መዘጋጅት አለባቸው። አባላት በምርት ገበያው የግብይት ስርዓት መሠረት ላልተፈፀሙ ማናቸውም ግብይት የትእዛዝ ቲኬት መስጠት የለባቸውም።

7.9 በምርት ገበያው አባላት የተፈጸመ ማንኛውም ውልን አስመልክቶ ተገቢውን ክፍያ፣ ግብርና ቀረጥ ሁሉ ለሚመለከተው የመንግስት አካል በቀጥታ መክፈል የአባላት ኃላፊነት ነው።

7.10 በምርት ገበያው ለግብይት በተፈቀዱ ምርቶች ላይ የተፈፀሙ የውል ግብይቶች ብቻ ተቀባይነት እንዳላቸው የሚቆጠሩት አባሉ ለግብይቱ የሚሆን በቂ ተቀማጭ በመግዢያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ያለው ሲሆን ነው።

7.11 የምርት ገበያው ለግብይት የተፈቀዱ ውሎች ዝቅተኛ የዋጋ ጭማሪ እንቅስቃሴ መጠን፣ የግብይት መለኪያና ዋጋ የሚጠራው በዚህ ድንጋጌ ለዚያ ውል በተቀመጠው ድንጋጌና ውሉ ለተደረገበት ምርት በተሰጠው ደረጃ መሠረት መሆን አለበት።

7.12 በባለሥልጣኑ በቅድሚያ መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ በምርት ገበያው ላይ ለተፈቀዱ ውሎች የአቋም ገደብ የመወሰን፣ የመለየትና የማሻሻል መብት የቦርዱ ይሆናል። እንደዚህ ዓይነቱ የአቋም ገደብ እንደየአባልነት ክፍሎች እና/ወይም ከአባል አባል ሊለያይ የሚችል ሲሆን ቦርዱ ለዚህ የአቋም ገደብ ልዩ ሁኔታ ድንጋጌ ሊያወጣ ይችላል። የአቋም ገደብና ልዩ ሁኔታ ድንጋጌ በምርት መደቡና በውል መፈፀሚያ ወር ድንጋጌ ላይ በግልፅ መቀመጥ አለበት።

7.13 በምርት ገበያው የተፈቀዱ ውሎችን አስመልክቶ ቦርዱ የዋጋ ወሰን የመተመን፣የመለየትና የማሻሻል መብት አለው። እንደዚህ ዓይነቱ የዋጋ ተመን ለአንድ ቀን ወይም ለተወሰነ ጊዜ የዋጋ ወለልና ጣሪያ መወሰንን ሊያካትት ይችላል። የዋጋ ወሰን ተፈጻሚነት በእያንዳንዱ ምርት መደብ ወይም ውል በሚመለከቱ ድንጋጌዎች ውስጥ በየጊዜው እንዲገለፅ ይደረጋል። የምርት ገበያው ያደረገውን ማናቸውንም የዋጋ ወሰን ማሻሻያ በሃያ አራት ሰዓት ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት።

7.14 የምርት ገበያው አባላት የሚከፍሉትን የግብይት ክፍያ፣ የማወራረጃ ክፍያና ሌሎች ክፍያዎች የመወሰንና የማስከፈል መብት አለው።

7.15 የምርት ገበያው አባላት ደንበኞቻቸውን የሚያስከፍሏቸውን ከፍተኛና ዝቅተኛ የግብይት ክፍያ፣ የማወራረጃ ክፍያ እና የሌሎች ክፍያዎችን መጠን የመወሰን መብት አለው።

7.16 የሁሉም የምርት ግብይት ውሎች ርክክብ ምርት ገበያው ባፀደቀውና በሰየመው አንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ መጋዘኖች የሚፈፀም መሆን አለባቸው።

7.17 በአንድ ምርት ወይም የምርት መደቦች ላይ ከተፈፀመ የውል ግብይት ጋር በተያያዘ የሚደረጉ የምርት ግብይት ድንጋጌዎችንና የርክክብ አኳኋን የመወሰን፣ በግልጽ የማስቀመጥና የማሻሻል መብት የቦርዱ ነው።

7.18 ቦርዱ መጠንን፣ አስተሻሸግን፣ የማቅረቢያ ቦታን፣ የማከማቻ መጋዘኖችን ጥራትና የአቅርቦት ቅናሽና ጭማሪ ድንጋጌዎችን፣ የጨረታ ጊዜን፣ ማረጋገጥንና የጨረታና የሽያጭ ዋጋዎችን ድንጋጌዎች የመወሰን፣ በግልጽ የማስቀመጥና የማሻሻል መብት አለው::

7.19 አባላት የምርት ገበያው በምርት ገበያው ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ያስጸደቃቸው ውሎች ውስጥ ብቻ መግባት ሊኖርባቸው ይችላል::

7.20 የምርት ገበያው አባላት ውል ውስጥ የሚገቡት በምርት ገበያው በወጡ ድንጋጌዎች ውስጥ በተደነገጉት ሁኔታዎችና በዚሁ መሠረት በወጡ ማስታወቂያዎች መሠረት ብቻ መሆን አለበት።

7.21 ማንኛውም አባል በምርት ገበያው ድንጋጌዎች መሠረት በዚያ ውል ላይ መገበያየት ሳይጀመር ወይም በዚያ ውል ላይ መገበያየት ካበቃ በኋላ ውል ውስጥ መግባት የለበትም።

7.22 ማንኛውም በቦርዱ ተቀባይነት ባላገኘ ውል እና የመደብ ዝርያዎች የሚገበያይ የምርት ገበያ አባል ተጠያቂ ይሆናል፣ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድበታል።

7.23 የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 7.12 እና 7.13 እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የውሎች ይዘት ማሻሻያ ውጤት የሚኖረው ለባለሥልጣኑ የተሰጠው የአስር ቀን ማስታወቂያ ጊዜ ካለፈ በኋላ ነው። በተሰጠው የአስር ቀን ማስታወቂያ ጊዜ ውስጥ ባለሥልጣኑ በጽሁፍ ምክንያቱን በመግለጽ የቀረበው የውል ይዘት ማሻሻያ ስራ ላይ እንዳይውል ሊያደርግ ይችላል።

7.24 በምርት ገበያው ግብይት የሚደረግበትን ውል ለማዘጋጀት ወይም ለማሻሻል የምርት ገበያው የሚከተለውን ስርዓት መከተል አለበት፤

7.24.1 የግብይት አሰራር ክፍል የአንድን ምርት መመዘኛ እና ደረጃ ለማውጣት ወይም ለማሻሻል የሚያስፈልጉ ትንታኔዎችን በጽሁፍ በማዘጋጀት የደረሰበትን መደምደሚያ ለዚሁ ምርት ተብሎ ለተቋቋመው የቴክኒክ አማካሪ ጉባኤ (ከዚህ በኋላ "አማካሪ ጉባኤ" እየተባለ ይጠቀሳል) ማቅረብ አለበት፡፡

7.24.2 አማካሪ ጉባኤው የሚከተሉትን አባላት ማካተት አለበት፡፡

ሀ. ከምርት ገበያው የተወከሉ ሁለት የምርት የቴክኒክ ባለሙያዎች (አንደኛው የአማካሪ ጉባኤው ሰብሳቢ ይሆናል)፣

ለ. የኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን የሚወክል አንድ የቴክኒክ ባለሙያ፣

ሐ. የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር የሚወክል አንድ የቴክኒክ ባለሙያ፣

መ. በምርት ገበያው ዋና ስራ አስፈጻሚ የሚሰየም የሌላ አግባብነት ያለው ተቋም አንድ የቴክኒክ ባለሙያ፡፡

7.24.2.1 የአማካሪ ጉባኤው እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

7.24.2.2 ከአባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፡፡

7.24.2.3 የአማካሪ ጉባኤው ውሳኔዎች በስብሰባው በተገኙ አባላት በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፡፡ ሆኖም ድምጽ እኩል በኩል የተከፈለ ከሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

7.24.2.4 የአማካሪ ጉባኤው የምርት መመዘኛ ለማውጣት ለሚያስፈልግ ጊዜ ወይም በጊዜያዊነት ለተከታይ ማሻሻያዎች አገልግሎት ይሰጣል፡፡

7.24.2.5 የአማካሪ ጉባኤው የምርት ደረጃ እና ክፍፍልን ቴክኒካዊ ጉዳዮች በተመለከተ ለግብይት አሰራር ክፍል በጽሁፍ የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ አለበት፡፡

7.24.3 የግብይት አሰራር ክፍል ከአማካሪ ጉባኤው በተሰጠው ቴክኒካዊ የውሳኔ ሃሳብ ላይ የገበያ ትንታኔ በማከናወን የግብይት ውል ረቂቅ ማዘጋጀት አለበት፡፡

7.24.4 የግብይት ውል ረቂቁ ለዚሁ ውል ተብሎ ለሚደራጀው የኢንዱስትሪ ምክክር ኮሚቴ መቅረብ አለበት፡፡

7.24.5 በምርት ገበያው ዋና ስራ አስፈጻሚ መደበኛ ጥሪ የሚዋቀረው የኢንዱስትሪ ምክክር ኮሚቴ የሚከተሉትን አባላት ማካተት አለበት፡፡

ሀ. አምራቾችን እና ነጋዴዎችን ከሚወክሉ ሕጋዊ እውቅና ካላቸው የንግድ ወይም የኢንዱስትሪ ማህበራት ወይም ሌሎች ድርጅቶች የተውጣጡ አስር ወይም ከአስር የሚበልጡ የምርቱ ሻጮች ተወካዮች፣

ለ. ላኪዎችን፣ ነጋዴዎችን እና አዘጋጆችን ከሚወክሉ ሕጋዊ እውቅና ካላቸው የንግድ ወይም የኢንዱስትሪ ማህበራት ወይም ሌሎች ድርጅቶች የተውጣጡ አስር ወይም ከአስር የሚበልጡ የምርቱ ገገርዎች ተወካዮች፣

ሐ. ከላይ በተመሳሳይ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) እና (ለ) ስር ተጨማሪ ተወካዮች ካሉ ተመጣጣኝ መሆን አለባቸው፣ እና

መ. ሕጋዊ እውቅና ያላቸው የኢንዱስትሪ ማህበራት ወይም ወካይ ተቋማት ከሌሉ የግብይት ማስፋፊያ ክፍል የንግድ ዘርፉን በመተንተን አግባብነት ላለው ተወካይ በምርት ገበያው ዋና ስራ አስፈጻሚ ጥሪ እንዲደረግ ለውሳኔ ማቅረብ አለበት፡፡

7.24.6 የደንቡ ንዑስ አንቀጽ 7.24.5 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የንግድ ወይም የኢንዱስትሪ ማህበራት ተወካዮች ምርጫ የሚከናወነው የማህበራቱን አባላት ድምጽ መሰረት በማድረግ መሆን አለበት፡፡

7.24.7 የኢንዱስትሪ ምክክር ኮሚቴ ብቸኛ ዓላማ ረቂቅ ውሉን መመርመር እና የጽሁፍ አስተያየት ለምርት ገበያው መስጠት ይሆናል፡፡

7.24.8 የግብይት አሰራር ክፍል ከሚመለከታቸው የምርት ገበያው መምሪያዎች ጋር በመመካከር እንዲሁም ከአማካሪ ጉባኤው እና ከኢንዱስትሪ ምክክር ኮሚቴ ያገኘውን አስተያየት በመጠቀም ውሉን የመጨረሻ ቅርጽ በማስያዝ ከሕግ አንጻር እንዲፈተሽ ለሕግ ማስከበሪያ መምሪያ ማቅረብ አለበት፡፡

7.24.9 የሕግ ማስከበሪያ መምሪያ የመጨረሻ ቅርጽ የያዘውን ውል ለምርት ገበያው ቦርድ ውሳኔ ማቅረብ አለበት፡፡

7.24.10 የሕግ ማስከበሪያ መምሪያ የምርት ገበያውን ቦርድ ይሁንታ ካገኘ በኋላ ውሉን እንዲያጸድቀው ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን መላክ አለበት፡፡

7.24.11 የምርት ገበያው ለባለስልጣኑ እንዲጸድቅ ከሚልከው ውል ጋር ውሉን አስመልክቶ የተደረገ ጥናት አጭር መግለጫ እንዲሁም የአማካሪ ጉባኤ እና የኢንዱስትሪ ምክክር ኮሚቴ ከውሉ ጋር በተያያዘ የሰጡትን አስተያየት ያካተተ አጠቃላይ ሪፖርት አባሪ አድርጎ ማቅረብ አለበት፡፡

7.24.12 የተሻሻለው ደንብ አንቀጽ 7 አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 7.24 ስር የተቀመጡት ድንጋጌዎች ቀደም ሲል የጸደቁ ውሎችን ለማሻሻልም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

7.24.13 ማንኛውም ፍላጎቱ ያለው የምርት ገበያው አባል የውል ማሻሻያ ሃሳቡን በንዑስ አንቀጽ 7.24.5 መሰረት ለሚቋቋመው የኢንዱስትሪ ምክክር ኮሚቴ ማቅረብ ይችላል፡፡ የኢንዱስትሪ ምክክር ኮሚቴ በበኩሉ አግባብነት አለው ብሎ ያመነበትን ማናቸውንም የማሻሻያ ሃሳብ ለምርት ገበያው ለማቅረብ ይችላል፡፡

7.24.13.1 የኢንዱስትሪ ምክክር ኮሚቴ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው ውሳኔው በደረሰው በአምስት ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለምርት ገበያው ለማቅረብ ይችላል:: የምርት ገበያው ይግባኙ በ□ረሰ□ በአምስት ቀናት ውስጥ በ□□ባኙ ላይ ውሳኔ መስጠት አለበት::

**7.24.13.2** የምርት ገበያው በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው ውሳኔው በደረሰው በሰላሳ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን ለማቅረብ ይችላል::

**7.24.13.3** ባለስልጣኑ ከላይ በንዑስ አንቀጽ **7.24.13.2** መሰረት በቀረበለት ይግባኝ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል::

# 8. ስለማከማቻ መጋዘን አሰራር

8.1 *ለተሰየመ የምርት ገበያ ማከማቻ መጋዘን ሠራተኛ ማረጋገጫ ስለመስጠት*

*ማንኛውም የማከማቻ መጋዘን ሠራተኛ ለምርት ግብይቱ ዓላማ የተሰየመ የምርት ገበያ ማከማቻ መጋዘን ሠራተኛ መሆኑን ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፤*

8.1.1 *አግባብነት ባለው አካል የተሠጠ የፀና የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ፣*
8.1.2 *ከማከማቻ መጋዘን አገልግሎት ጋር የተያያዙ የምርት ገበያውን ደንቦች መቀበል፣*
8.1.3 *የማከማቻ መጋዘኑ ያለበት ቦታ/በቂ መንገድ፣ ቴሌኮሚኒኬሽን እና የትራንስፖርት መሣሪያዎች ወዘተ መኖር/እና የማከማቻ መጋዘን ዕቃዎች /ሚዛን፣ የጥራት ቁጥጥር አገልግሎት፣ የብቃት አስተዳደር ወዘተ/ አመቺነት እና*
8.1.4 *ከግብር ነፃ መሆኑን የሚያሳይ የፀና የምስክር ወረቀት እና የግብር መለያ ቁጥር ማቅረብ፣*

8.2 *ምርትን በማከማቻ መጋዘን ስለማስቀመጥ*

8.2.1 *ምርቱን በምርት ገበያው ለመሸጥ የፈለገ ማንኛውም አባል ወይም ደንበኛ፤ ወይም የአባሉ ወይም የደንበኛው ተወካይ ወይም ማንኛውም ሰው (ከዚህ በኋላ "አስቀማጭ" ተብሎ ይጠቀሳል።) በምርት ገበያው በተሰየመ ማከማቻ መጋዘን ውስጥ ምርቱን ከግብይቱ ቀን በፊት ባለው የመጨረሻ የግብይት ቀን ከቀኑ* 11፡00 *ሰዓት ድረስ ማስቀመጥ አለበት።*

8.2.2 *ስለማጣራት*

*ማከማቻ መጋዘኑ ምርቱን ለመቀበል የሚያስችለውን ሥነ ሥርዓት መፈፀም ከመጀመሩ በፊት ምርቱ ስላለው ተቀባይነት፣ የአስቀማጩን ማንነት( የአባልነት መታወቂያ እና ውክልና መኖሩንወዘተ) ማጣራት አለበት።*

8.2.3 *የምርት ገበያው የማከማቻ መጋዘን በደንቡ ንኡስ አንቀጽ* 8.2.2 *ስር ካለበት ግዴታ በተጨማሪ የግብርና እና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ባወጣቸው ደንቦች እና መመሪያዎች መሰረት የአቅርቦት ቡና እና ተረፈ ምርት ቡናን የሚመለከት መረጃ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ያቀርባል።*

## 8.3 ስለተሰየሙ ማከማቻ መጋዘኖች

8.3.1 የምርት ገበያው ለምርት ገበያው ንግድ የሚቀርቡ ምርቶች የሚከማቹባቸውን እና ርክክብ የሚፈፀምባቸውን እንደዚሁም የምርት ገበያው በየጊዜው በሚወስነው መሠረት ምርት ክምችትን የሚያመቻቹ የተሰየሙ መጋዘኖችን መለየት ይኖርበታል።

8.3.2 የተሰየሙ ማከማቻ መጋዘኖች ስለሚፈጽሙት ሥነ-ሥርዓትና ሂደት
የምርት ገበያው እያንዳንዱ የተሰየመ ማከማቻ መጋዘን ሊፈፅም የሚገባውን ሂደቶች፣ ሥነ-ሥርዓቶች እና ተግባራት በየጊዜው መወሰን አለበት። ከተሰየሙ የማከማቻ መጋዘኖች ጋር የተያያዙ ሂደቶች፣ ሥነ-ሥርዓቶች እና ተግባራት በግልጽ የተቀመጠ የግዴታ አፈፃፀም ሂደት ክፍል ተደርገው ይቆጠራሉ።

8.3.3 ስለ ተሠየመ ማከማቻ መጋዘን አገልግሎት
በእቃ ማከማቻ ደረሰኝ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 372/96 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተሰየሙ የምርት ማከማቻ መጋዘኖች የሚከተሉትን አገልግሎቶች መስጠት ይኖርባቸዋል፡-

8.3.3.1 በንግድ ልውውጡ ሂደት የሚቀርቡ ምርቶች በምርት ገበያው በተወሠነው መሠረት የሚቀመጡበትን ቦታ መወሰን፣ የምርት ገበያው ምርትን በማከማቻ መጋዘን ስለማስቀመጥ በየጊዜው የሚያወጣቸውን መመዘኛዎች ማሟላት ፤

8.3.3.2 የምርት ናሙና መውሰድ ፣ ደረጃ ማውጣት እንደዚሁም የምርት ደረጃ ሠርተፍኬት መስጠት ፤

8.3.3.3 ምርቶቹን መመዘን እንደዚሁም የሚዛን ትኬት መስጠት ፤

8.3.3.4 በወረቀት የተፃፈ የምርት ርክክብ የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ለአስቀማጩ መስጠት ፤

8.3.3.5 የደረጃ ዝርዝር መመዘኛን መሠረት በማድረግ ምርትን ማስቀመጥ ፤

8.3.3.6 በዚህ ደንብና የምርት ገበያው በተጨማሪነት በሚያወጣቸው መመሪያዎች የተደነገጉ ሥነ ሥርዓቶችን ተከትሎ የጥራት ቁጥጥር ማድረግ እንደዚሁም የንብረት ምዝገባ ሥርዓትን ማስተዳደር ፤

8.3.3.7 በዕቃ ርክክብ ደረሰኝ መሠረት የማከማቻ መጋዘን ቆይታ ጊዜያቸው ካልተጠናቀቀ ምርቶች ጋር እንዳይቀላቀሉ ለማድረግ የቆይታ ጊዜያቸው ያበቃ ምርቶችን መለየትና በተለየ ቦታ ማስቀመጥ።

8.3.4 ስለተሰየሙ ማከማቻ መጋዘኖች ግዴታዎች

8.3.4.1 በዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 372/1996 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የተሰየመ መጋዘን የምርት ገበያውን ፍላጎት በሚያሟላ ሁኔታ የሚከተሉትን መፈጸም አለበት።

ሀ. የተከማቹ ምርቶችን አስመልክቶ በምርት ገበያው ተቀባይነት ያገኘ (የፀደቀ) ወጥና ደረጃውን የጠበቀ የምርት መግለጫንና መለኪያን መጠቀም ፣

ለ. የምርት ገበያው ለተወሰነ ምርት በተለይ ወይም በተወሰነ ጎራ ለሚመደቡ ምርቶች በጠቅላላው የሚያወጣቸውን የማከማቻ መጋዘን ደንቦችን ማክበር፣

ሐ. ምርቱ በማከማቻ መጋዘን በሚቆይበት ጊዜ ደረጃውና መጠኑ ሳይጓደል መጠበቁን የሚያረጋግጡ እርምጃዎች መወሰዳቸውንና ጥንቃቄ መደረጉን ማረጋገጥ፣

መ. በምርት ገበያው በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት በማከማቻ መጋዘን የተቀመጡ ምርቶች የኤሌክትሮኒክስ ዳታ ዝርዝርን መያዝ።

8.3.4.2 የምርት ገበያው በግልጽ መስማማቱን ካልገለጸ በስተቀር የማከማቻ መጋዘኑ በይዞታው (በስሩ) ያሉትን ምርቶች ለሶስተኛ ሰው በዳረጎት ማሳለፍ ፣ ማዛወር እና ለሶስተኛ ሰው መልቀቅ ክልክል ነው። ይሁንና የማከማቻ መጋዘኑ ምርቶቹን በመጋዘን ውስጥ ወደ መደበላቸው ቦታዎች የማዛወር መብት አለው።

8.3.5 በማከማቻ መጋዘን ውስጥ በተቀመጡ ምርቶች ላይ ስለሚደረግ ቁጥጥር

የምርት ገበያው በራሱ ወይም በሶስተኛ ሰው አማካኝነት በማናቸው ጊዜ በማከማቻ መጋዘን ውስጥ ባሉ ምርቶች ወይም በማከማቻ መጋዘን ውስጥ ባሉ መሣሪያዎች ላይ በጠቅላላው ቁጥጥር የማድረግ ወይም በምርት ገበያው የተደነገጉ የማከማቻ መጋዘን ደንቦች መከበራቸውን የመመርመር መብት አለው።

8.4 በማከማቻ መጋዘን ምርትን ስለመረከብ

8.4.1 በምርት ገበያው ማከማቻ መጋዘን ውስጥ ምርት እንዲከማች ርክክብ ከመደረጉ በፊት የሚከተሉት ተግባራት ይከናወናሉ ፣

8.4.1.1 ምርትን ለመረከብ እንዲያመች የማስቀመጫ ቦታ እንደዚሁም ተዛማጅነት ያላቸው እንደ አየር መተላለፊያ፣ ምርቱ የተቀመጠበት ቦታ ክትትል የማድረግ አቅምና የመሳሰሉት ጉዳዮች ግምት ውስጥ በማስገባት ማከማቻ መጋዘኑ እና አጎራባች ቦታዎችን ማደራጀት፣

8.4.1.2 በማከማቻ መጋዘን እንዲቀመጡ በቀረቡና ደረሰኝ በሚቆረጥላቸው ምርቶች እንዲሁም ከረጢቶችና መጠቅለያዎች ሁኔታ ላይ የመጀመሪያ ምርመራ ማድረግ ፣

8.4.1.3 በምርት ገበያው የናሙና አወሳሰድ ሥርዓት መሠረት ወካይ ናሙና መውሰድ፣

8.4.1.4 በምርት ገበያው የምርት ደረጃ መመዘኛ መሠረት የደረጃ ትንተና ማካሄድ ፣የደረጃ ሪፖርት ቅፅ መሙላት፣

8.4.1.5 ምርትን መዝኖ የሚዛን ትኬቱን በትክክል መሙላት፣

8.4.1.6 ምርትን (ከተሽከርካሪዎች ላይ) ማውረድ፣

8.4.1.7 መጋዘን እንዲቀመጥ የቀረበው ምርት ሁኔታ በማከማቻ መጋዘን በተቀመጡ ምርቶች ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር ከሆነ የማከማቻ መጋዘኑ ሥራ አስኪያጅ ምርቱን ያለመረከብ ፣

8.4.1.8 ምርቱ በማከማቻ መጋዘን ውሰጥ እንዲቀመጥ የቀረበውን ጥያቄ ያልተቀበለበትን ምክንያት ለምርቱ አቅራቢ በፅሑፍ ማሳወቅ።

8.5 ስለ ናሙና አወሳሰድና ደረጃ አወጣጥ

8.5.1 ናሙና የሚወስደው ሰው ምርቱን በዓይን መፈተሽ፣ የምርቱን ዓይነትና የምርቱን ከረጢት (መያዣ) መለየት፣ እንዲሁም ወካይ ናሙና መውሰድ ይኖርበታል።

8.5.2 ከላይ በአንቀጽ 8.5.1. የሚወሰደው ናሙና ለሶስት ይከፈላል። የመጀመሪያው የደረጃ ትንታኔ ለማካሄድ ያገለግላል ( የሥራ ናሙና )፤ ሁለተኛው ደህንነቱ በተጠበቀ ዕቃ ውሰጥ ይቀመጣል፤ ሶስተኛው ለአስቀማጩ ይሰጣል።

8.5.3 የምርት ጥራት ተቆጣጣሪ የደረጃ ውጤትን ለአስቀማጩ ማሳወቅ አለበት። አስቀማጩ በውጤቱ ከተስማማ የምርት ጥራት ተቆጣጣሪ ለአስቀማጩ የደረጃ ሠርትፍኬት መስጠት ይኖርበታል።

8.5.4 ናሙናው ከተወሰደበት ቀን ጀምሮ እስከ 20 ቀን ድረስ ደህንነቱ በተጠበቀ እቃ ውስጥ መቀመጥ ይኖርበታል።

8.5.5 በማከማቻ መጋዘን የሚቀመጡ ምርቶችን ደረጃ መስጠት የሚችሉት የተመሠከረላቸው የምርት ደረጃ መዳቢዎች (አውጪዎች) ብቻ ይሆናሉ።

8.5.6 የምርት ደረጃ የማውጣት ተግባር ትክክለኛና ወካይ ናሙናን መሠረት አድርጎ፣ በምርት ገበያው የፀደቀ የደረጃ አወጣጥ ሥነ ሥርዓትን ተከትሎ እና እውነተኛ የደረጃዎች አመዳደብን ለመወሰን በሚያስችል ሁኔታ የሚከናወን ይሆናል።

8.5.7 የምርት ገበያው የምርት ደረጃዎች አወጣጥና ናሙና አወሳሰድ መመዘኛዎችን በየጊዜው ሊያወጣ እና ሊያሻሽል ይችላል።

8.5.8 አስቀማጩና የማከማቻ መጋዘኑ ሥራ አስኪያጅ ያልተስማሙ ከሆነ ወይም ምርቱ ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረ ከሆነ ይግባኝ ማቅረብ እንዲቻል እና የምርት ገበያው ደረጃ መዳቢው ዝቅተኛ መመዘኛ ማሟላቱን ለመቆጣጠር እንዲችል ናሙናው (በአግባቡ የተለየ) እርጥበት በማያስገባና ደህንነቱ በተጠበቀ ማስቀመጫ ውሰጥ ቢያንስ ለ20 የሥራ ቀናት ተጠብቆ መቆየት አለበት።

8.5.9 የምርት ገበያ የሚሰጠው የደረጃ ሠርተፍኬት፣ ኦሪጅናል፣ ግልባጭ ወይም ሌላ ቅጅ ስለ መሆኑ ፣ ምርቱ ስለተቀመጠበት መጋዘን ስም እና ስለሚገኝበት ቦታ፣ ስለ ምርቱ ደረጃ፣ ሠርትፍኬቱ ስለተሠጠበት ቀን እና የተመሠከረለት የምርት ደረጃ መዳቢ ፊርማን የመሳሰሉ መረጃዎችን መያዝ አለበት።

8.6 ደረጃን ለመወሰን ስለሚያገለግሉ መሳሪያዎች

8.6.1 ማናቸውም ናሙና የመውሰጃ ፣ የክብደት መለኪያ፣ የምርት ደረጃ መወሰኛ መሣሪያዎች ትክክለኛነታቸው ሊረጋገጥና የተመረቱበት ፋብሪካ በሠጠው አስተያየትና የዋስትና ጊዜ መሠረት መጣራትእና መጠበቅ አለባቸው።

8.6.2 ሁሉም የደረጃ መወሰኛ መሳሪያዎች በተገቢው ሁኔታ መያዝና መጠበቅ ይኖርባቸዋል።

8.6.3 የላቀ ደህንነትን እና ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ እያንዳንዱ ማከማቻ መጋዘን ውስጥ ደረጃ ለመወሰን አገልግሎት የሚሰጡ መሣሪያዎችየኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት (ከዚህ በኋላ የኢተምድ ተብሎ የሚጠቀስ) ተመርምረው እና ትክክለኛነታቸው ተረጋግጦ የምስክር ወረቀት ያገኛሉ።

8.7 የክብደት አመዛዘን ሥነ-ሥርዓት

8.7.1 የመመዘኛ መሳሪያ አጠቃቀም

መዛኙ ምርቱን መርምሮ፣ የክብደት መለኪያ መሣሪያውን ወይም የምድር ሚዛኑን ትክክለኛነት አረጋግጦ እንዲሁም የምርቱን ክብደት ወስኖ ለማከማቻ መጋዘኑ ሥራ አስኪያጅ የክብደት /የመጠን ሰርተፊኬት መስጠት ይኖርበታል።

8.7.1.1 ምርቱን ከተሽከርካሪ ጋር የሚመዘን ከሆነ ምርቱን በማውረድ የተራገፈውን ተሽከርካሪ ክብደት መዝኖ የተሽከርካሪውን ክብደት ከጠቅላላው ክብደት ላይ በመቀነስ የምርቱን የተጣራ ክብደት ይወስናል።

8.7.1.2 መጠን ወሳኝ ባለሙያው ወይም መዛኙ የሚዛን ትኬቱን በመሙላትና በመፈረም የማከማቻ መጋዘኑ ስራ አስኪያጅ እንዲፈርምበት እንደዚሁም አስቀማጩ ማረጋገጫ እንዲሰጥበት ማቅረብ ይኖርበታል።

8.7.2 ተቀባይነት ያለው ጠቅላላ ክብደት እና ጭማሪ ክምችት

8.7.2.1 ከቡና በስተቀር ለሌሎች ምርቶች ዝቅተኛው የተፈቀደ ክምችት 50 ኩንታል ይሆናል። በተከታይ የሚቀርብ ክምችትም በ50 ኩንታል ብዜት ወይም በውል ላይ እንደ ስታንዳርድ የተወሰነው የክምችት መጠን ይሆናል።

8.7.2.2 በምርት ገበያ ማከማቸት የሚቻለውን አነስተኛ የቡና መጠን የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚያጸድቀው ውል ድንጋጌዎች መሰረት ይወሰናል።

8.7.3 የሚፈቀድና ከግምት የማይገባ የምርት ክብደት ጭማሪ /ጉድለት
በባለስልጣኑ መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከፍተኛው የተፈቀደ የምርት ክብደት ጉድለት/ጭማሪ ገደብ መጠን   በምርት ገበያው ይወሰናል፡፡።

8.8 ስለ ክምችት ጊዜ ማብቃት

8.8.1 ለባለስልጣኑ በቅድሚያ ማሳወቁ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የምርት ገበያው ለእያንዳንዱ የምርት አይነት አግባብነት ያለው የማከማቻ መጋዘን ደረሰኝ ማብቂያ ጊዜን ይወስናል፤ የማብቂያ ጊዜውንም በየጊዜው ማሻሻል ይችላል።

8.8.2 ማንኛውም አስቀማጭ በዚህ የተወሰነ ጊዜ ውስጥ ምርቱን ከማከማቻ መጋዘን እንዲያወጣ ወይም እንዲሸጥ ይጠበቃል።

8.8.3 ስለ ማከማቻ መጋዘን አገልግሎት ማብቂያ ሥነ-ሥርዓት

8.8.3.1 የማከማቻ መጋዘኑ ሠራተኛ የማከማቻ መጋዘን አገልግሎት ማብቂያ ጊዜን የሚያራዝም ሁኔታ ሲያጋጥም የማብቂያ ጊዜው ከመጠናቀቁ ከ2 ሣምንታት በፊት የፅሑፍ ማስታወቂያ ማውጣት አለበት።

8.8.3.2 ምርቱ በማከማቻ መጋዘን አገልግሎት ማብቂያ ቀን ያልተሸጠ ወይም ከማከማቻ መጋዘኑ ያልወጣ ከሆነ የማከማቻ መጋዘኑሠራተኛ የምርት ገበያው በወሰነው መሠረት ቅጣት መጣል አለበት።

8.8.3.3 የማከማቻ መጋዘን ደረሰኝ የማብቂያ ጊዜ በመጠናቀቁ የሚጣለው ቅጣት ተጠራቅሞ ከተከማቸው የምርት ዋጋ በላይ ከሆነ ማከማቻ መጋዘኑ የተከማቸውን ምርት ሊሸጠው ይችላል፡፡

8.8.3.4 የማከማቻ መጋዘን ደረሰኝ የማብቂያ ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ሁለት የፅሁፍ ማስታወቂያ ለአስቀማጩ መሰጠት አለበት፡፡ የመጀመሪያው ማስታወቂያ የሚሰጠው የማከማቻ መጋዘን ደረሰኝ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ በመጀመሪያ ቀን ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ክምችቱ ከመሸጡ ሁለት ቀናት ቀድሞ ይሆናል፡፡

8.9 ምርትን ከማከማቻ መጋዘን ስለማውጣት

8.9.1 ተፈጻሚነት ባለው ሕግ ካልተከለከለ በስተቀር በምርት ገበያው ሽያጭ ሳይፈጸም በማከማቻ መጋዘን የተቀመጠ ምርት ከማከማቻ መጋዘን ሊወጣ ይችላል።

8.9.2 በምርት ገበያው የሚፈፀም ሽያጭ ሳይኖር ምርቱን ከማከማቻ መጋዘን ማውጣት ያስቀጣል።

8.9.3 በምርት ገበያው ሽያጭ ከተፈጸመ በኋላ የተከማቸው ምርት ለርክክብ ከማከማቻ መጋዘን ሊወጣ ይችላል።

8.10 ለመጋዘን ናሙና ወሳጅ፣ መዛኝ፣ ደረጃ መዳቢ ስለሚሰጥ የምስክር ወረቀት፣

8.10.1 የምርት ገበያው ማከማቻ መጋዘን የሚያከማቻቸውን ምርቶች በአግባቡ እንዲይዙ ችሎታ ያላቸውንና ብቁ የሆኑ ናሙና ወሳጆች ፣ደረጃ መዳቢዎች፣ መዛኞች ወዘተ ብቻ መቅጠር አለበት።

8.10.2 የእነዚህ ሠራተኞች የብቃትና የስልጠና ደረጃ በምርት ገበያው ይረጋገጣል።

8.10.3 ምርት ገበያው በናሙና ወሳጅነት፣ ደረጃ መዳቢነት እና መዛኝነት የተቀጠሩ ሰዎችን ሠርተፊኬት ለሕዝቡ በግልፅ በሚታይ ቦታ ማስቀመጥ ይኖርበታል።

8.10.4 የተመሠከረለት ናሙና ወሳጅ፣ ደረጃ መዳቢ ወይም መዛኝ አገልግሎት መስጠት ባቆመ ጊዜ፣የማከማቻ መጋዘኑ ሥራ አስኪያጅ ሁኔታው በተከሰተ በ24 ሰዓታት ውስጥ ለምርት ገበያው የማስታወቅ ኃላፊነት አለበት።

8.10.5 አስፈላጊውን የብቃት መመዘኛ ማሟላታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለናሙና ወሳጅ፣ ለደረጃ መዳቢ እና መዛኝ በምርት ገበያው የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ /የምስክር ወረቀት/ በየአመቱ የሚታደስ ይሆናል።

## 8.11 ስለ ንብረት ቆጠራ አመራር

8.11.1 በማከማቻ መጋዘን ያሉ ምርቶች የአስቀማጩን ምንነት ግምት ውስጥ ሳያስገቡ የተሰጣቸውን ደረጃና ማከማቻ መጋዘን የገቡበትን ቀን መሠረት በማድረግ ብቻ በማከማቻ መጋዘን ይቀመጣሉ::

8.11.2 ወደ መጋዘን የሚገቡት ምርቶች የምርት ገበያው ባወጣው ደንብ መሠረት በ50 ወይም በ100 ኪሎ ግራም ክብደት ተደራጅተው በኀሮኘሊን ከረጢት መጠቅለል ይኖርባቸዋል::

8.11.3 በቀረጢት የተጠቀለሉ ምርቶችን በማከማቻ መጋዘኑ በፀደቁ ቦታዎች የመደርደር ሥራ በምርት ገበያው ተቀባይነት ባገኙ አሠራሮችና ሥነ-ሥርዓቶች መሠረት መከናወን ይኖርበታል::

8.11.4 ማንኛውም የማከማቻ መጋዘን እነኝህን ተሞክሮዎች እና ሥነ-ሥርዓቶች መከተሉን ማረጋጥ ይኖርበታል።

8.11.5 ማንኛውም የማከማቻ መጋዘን በማከማቻ መጋዘን ውስጥ ያሉ ምርቶች ዝርዝርን የያዘ አግባብነት ያለው የሥራ እንቅስቃሴ መዝገብ በየጊዜው ማደራጀትና ተቀባይነት ባለው ቦታ ማስቀመጥ ያለበት ሲሆን ይኸም በተለይ፤

8.11.5.1 በምርት ገበያው የተዘጋጀ ቅፅን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ዕለታዊ የአቋም መዝገብን፣

8.11.5.2 የምርት ገበያው ቅፅ የሚያዘውን ተጠቀሞ የሚዘጋጅ የሚዛን ትኬት ቅጅን እና የደረጃ ሰርተፊኬት ቅጅን፣

8.11.5.3 ተቀባይነት ያለው አቅራቢን በመጠቀም የተቀባይ ቁጥጥርንና ርጭትን የያዘ መዝገብን፣

8.11.5.4 በምርት ገበያው የወጣን ቅፅ በመጠቀም የማከማቻ መጋዘን ውስጥ ባሉ ምርቶች ላይ የተከናወነን የአይን ፍተሻና ክትትል የያዘ የአስተዳደር መዝገብን እና

8.11.5.5 ሁሉም አግባብነት ያላቸው መረጃዎች በማከማቻ መጋዘኑ ስራ አስኪያጅ መደበኛ የሥራ ቦታ መቀመጥ / መያዝ ይኖርባቸዋል። እነዚህ መዝገቦች በየጊዜው ተዘጋጅተው የምርት ገበያውና አግባብነት ያለው ተቆጣጣሪ አካል ሊያገኛቸው በሚችል ቦታ መጠበቅ ይኖርባቸዋል።

8.11.6 ምርቱን በማከማቻ መጋዘን ውስጥ የማከማቸትና ከመጋዘኑ የማውጣት አሠራር መጀመሪያ የገባ መጀመሪያ ይወጣል /መገመይ/ የሚለውን መርህ የተከተለ ይሆናል።

8.11.7 ማንኛውም የማከማቻ መጋዘን ምርትን ለማስቀመጥ ተፈፃሚ የሚሆኑ ደንቦችንና የግዴታ ሰነዶችን ህዝብ በሚያያቸው እና በሚደርስባቸው ግልጽ በሆኑ ቦታዎች ማስቀመጥ ይኖርበታል።

8.11.8 ማንኛውም በከረጢት የተጠቀለለ ምርት ሁሉም ምርቶች ላይ ለመድረስ እንደዚሁም የምርት ምርመራን፣ ናሙናን፣ ቆጠራን ወይም ርጭትን ለማፋጠንና ለማመቻቸት በሚረዳ መልኩ ሊቀመጥ / በግድግዳው መካከል 2 ሜትር ፤ በከረጢቶች መካከል 1 ሜትር / ይገባል።

8.11.9 የማከማቻ መጋዘኑ ስራ አስኪያጅ ከመጋዘኑ ስታንዳርድ አቅም በላይ ማከማቸት የለበትም። ይሁንና መጋዘኑ ከተረጋገጠለት /ከተመሠከረለት አቅም በላይ ምርቶችን ይዞ በተገኘ ጊዜ ሁኔታውን ምርት ገበያው አስቀድሞ እንዲያውቀው እና ጊዜያዊ የማከማቻ ቦታን ሥራ ላይ ከማዋሉ በፊት እንዲያፀድቀው ሊደረግ ይገባል።

8.11.10 በቀዳዳ ወደ ማከማቻ መጋዘኑ የሚገባ የውሃ ፍሳሽ መገታት ይኖርበታል። ጥንቃቄ ማድረጉ ሳይጓደል የተከማቸው ዕቃ እርጥበት ካዘለ ዕቃው ከሌሎች ተለይቶ ሊቀመጥ የሚገባው ሲሆን ይህንንም የምርት ገበያው ወዲያውኑ እንዲያውቀው መደረግ አለበት።

8.11.11 አግባብነት ባለው የመንግሥት አካል የተከለከለ ዕቃ በማንኛውም ጊዜ በማከማቻ መጋዘን ማስቀመጥ የተከለከለ ነው።

8.11.12 ማከማቻ መጋዘኑ የተመሰከረለትን ምርቶች ለማስቀመጥ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች፣ ለተከለከሉ ዕቃዎች መገልገያ ጥቅም ላይ መዋል የለባቸውም።

8.11.13 እያንዳንዱ ማከማቻ መጋዘን የገባውን የእሳት አደጋ መከላከያ እና የቁጥጥር መመዘኛ ኢንሹራንስ ፖሊሲ እንደዚሁም የምርት ገበያው በፅሑፍ ያስቀመጣቸውን የውሳኔ ሀሳቦች ማክበር ይኖርበታል።

8.11.14 እያንዳንዱ የማከማቻመጋዘን ለፀደቀ የክምችት ቦታ እና ለተቀለፈ የናሙና ሳጥን የ24 ሠዓት የደህንነት ጥበቃ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት ።

8.12 በተባዮችና አጥፊ እንሰሳት ላይ የሚደረግ ቁጥጥር

8.12.1 የማከማቻ መጋዘን ሰራተኛ ተባዮችንና አጥፊ እንሰሳትን የማከማቻ መጋዘኑ ከሚገኝበት አካባቢ ለማራቅ ማናቸውንም አስፈላጊ እርምጃ መውሰድ ያለበት ሲሆን እርምጃው በመጋዘኑ የሚገኙ ምርቶች አለመበከላቸውን ለማረጋገጥ በሚያስችል ሁኔታ የታቀደ መሆን ይኖርበታል። የማከማቻ መጋዘኑ አመራር የቁጥጥር ዘዴውን እንደዚሁም ምርመራ የተከናወነበትን ወይም የተበላሸው የተላከበትን ቀን በሠነድ ላይ ማስፈር አለበት።

8.12.2 በተቻለ መጠን ምግብነት ያላቸው ሽርፍራፊ ነገሮችን የማከማቻ መጋዘን አገልግሎት ከሚሰጥበት አካባቢ ማራቅ/ውጪ ማድረግ ይገባል።

8.12.3 በማከማቻ መጋዘኑ አካባቢ ያሉ ሁሉም አትክልቶች ከመጋዘኑ መሠረት ቢያንስ በ3 ሜትር መራቅ አለባቸው። የማከማቻ መጋዘኑ አስተዳደር የቁጥጥር ዘዴንና ቀኑን በመዝገብ ማስፈር አለበት።

8.12.4 የማከማቻ መጋዘን አስተዳደሩ አእዋፍ ማከማቻ መጋዘኑ ካለበት አካባቢ እንዲርቁ እና ወደ ማከማቻ መጋዘኑ እንዳይገቡ ለመከላከል ማንኛውንም አስፈላጊ እርምጃ መውሰድ ያለበት ሲሆን ይህም ጥልፍልፍ ሽቦን ከመስኮት፣ቬንትሌር እና ከማንኝውም ቀዳዳ በላይ መትከልን ያካትታል።

8.12.5 ሁሉም ዓይነት እንስሳትና አእዋፍ ከማከማቻ መጋዘኑ እና አካባቢው መወገድ አለባቸው።

8.12.6 የማከማቻ መጋዘኑ ሥራ አስኪያጅ በማከማቻ መጋዘኑ ውስጥ ያለው ምርት ከተባይ ነፃ ሆኖ መቀመጡን ለማረጋገጥ ማንኛውንም አስፈላጊ እርምጃ መወሰድ አለበት። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የኬሚካል ርጭት አለማቀፍ የእውቅና ደረጃውን ጠብቆ መከናወን ያለበት ሲሆን ሥራው በሠለጠኑ ባለሞያዎች ወይም በተመሠከረላቸውና በምርት ገበያው ተቀባይነት ባገኙ የተባይ ተቆጣጣሪ / የፈሳሽ ርጭት ኩባንያዎች ብቻ ሊከናወን ይገባል።

8.12.7 የማከማቻ መጋዘኑን ከተባይ ለመጠበቅ ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ የዕፅዋት ጥበቃና ተቆጣጣሪ መምሪያ እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የተቀበላቸው ፀረ ተባይ መድሀኒቶች ብቻ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ይደረጋል። ዚንክ ፎስፈረስን የያዘ ፀረ-አጥፊ እንሰሳት መድሀኒት በማከማቻ መጋዘን ውስጥ ጥቅም ላይ መዋል የለበትም ።

8.13 *ንፅህና*

8.13.1 *ማከማቻ መጋዘኑ በማንኛውም ጊዜ የእሳት አደጋን ከሚያባብሱ ወይም በማከማቻ መጋዘኑ የተቀመጡ ምርቶች አያያዝን ከሚያሰናክሉ ገለባ፣ ጥራጊ ወይም የዕቃ ክምችት ነፃ መሆንና ንፅህናውም በበቂ ሁኔታ መጠበቅ ይኖርበታል።*

8.13.2 *የጣሪያ መደርደሪያዎችን ወይም አቧራ የሚስቡ ቦታዎችን ጨምሮ ሁሉንም የማከማቻ መጋዘን ክፍሎችንና ስትራክቸሮችን የሚሸፍን በጽሁፍ የተዘጋጀ የዘወትር የፅዳት ፕሮግራም ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል። የፅዳት ፕሮግራሙ ወለሎች በማንኛውም ጊዜ ንፁህና ደረቅ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ መሆን አለበት።*

8.13.3 *ማንኛውም የመጫኛና የማውረጃ መሳሪያ ለታቀደው አገልግሎት የሚስማማ እና አዘውትሮ ንጽህናው የተጠበቀ መሆን ይኖርበታል።*

8.13.4 *አቧራን ለመቀነስ ማንኛውም አስፈላጊ እርምጃ መወሰድ አለበት። ቁጥጥር የሚደረግበት መንገድ /ዘዴው / አቧራ የሚፈጠርበትን ሁኔታ የሚቀንስ መሆን አለበት። ከመደርደሪያዎች ፣ ከብርሃን መስጫ መሳሪያዎች ወዘተ... ላይ የተጠረገው አቧራ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ከፀደቀ ስፍራ ላይ መወገድ ይኖርበታል።*

8.13.5 *በፀደቀ የክምችት ሥፍራ ላይ የተቀመጠ ምርት ከብክለት ነፃ መሆን ይገባዋል።*

8.13.6 *የማከማቻ መጋዘኑ አመራር ችግሮችን ለመለየት አስፈላጊው የጊዜ የሚሰጠው ሲሆን የእርምት እርምጃ በወሰደም ጊዜ የጽሁፍ ሪፖርት ማቅረብ አለበት።ወዲያውኑ መታረም ያለባቸው ችግሮችን አስመልክቶ የምርት ገበያው ሠራተኛ የማስተካከያ እርምጃ ሪፖርት /ማ.እ.ሪ./ ማቅረብ ያለበት ሲሆን የማከማቻ መጋዘን አስተዳደር ለችግሮቹ እንዴት እልባት እንደሰጠ በሁለት የሥራ ቀናት ውስጥ የጽሁፍ ሪፖርት ለምርት ገበያው ማቅረብ አለበት።*

8.14 ስለ *መድን*

8.14.1 *የምርት ገበያው ማከማቻ ግዙፍነት ላላቸው የሥራ ማስኬጃ መሳሪያዎች/ዕቃዎች መድን የመግዛት ግዴታ አለበት።*

8.14.2 *የማከማቻ መጋዘን ሠራተኛ በማከማቻ መጋዘን ለተቀመጡ ምርቶች መድን የመግዛት ግዴታ አለበት።*

## 9. የማከማቻ መጋዘን አገልግሎት ደረሰኝ

9.1 *የዕቃዎች ርክክብ ማስታወሻ መስጠት*

9.1.1 *የማከማቻ መጋዘኑ ከአስቀማጩ ጋር ስምምነት ፈጽሞና የሚዛን ትኬትና በደረጃ ሰርተፍኬት ላይ ፈርሞ ምርቱን ይረከባል።*

9.1.2 *የአስቀማጩ ፊርማ በምርት ገበያው ሕግ በጠቅላላው እንደዚሁም በማከማቻ መጋዘኑ፣ በምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻ እና በክፍያ መክፈያ ተቋም ደንቦች በተለይ ለመገዛት ስምምነት ለመደረሱ ማስረጃ እንደሆነ ይቆጠራል።*

9.1.3 *የማከማቻ መጋዘኑ የዕቃዎች ርክክብ የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ማውጣትና የተፈረመበትን ግልባጭ ለአስቀማጩ ወይም ለተወካዩ መስጠት ይኖርበታል።*

9.1.4 በከፊል ለሚደረግ እያንዳንዱ ምርት ክምችት ይህንኑ የሚያመለክት የእቃ ርክክብ ቮውቸር ይሰጣል።ለሻጩ ወይም ለወኪሉ የተሟላ የእቃዎች ርክክብ ደረሰኝ የሚሰጠው ሙሉ በሙሉ ምርቱ ሲከማች ብቻ ነው።

9.1.5 በማከማቻ መጋዘኑ የዕቃ ርክክብ የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ በኤሌክትሮኒክስ እና በህትመት መልክ መያዝና ምርቱ ተቀማጭ በሆነበት ቀን ወደ ማዕከላዊ የምርት ገበያ ማከማቻ መጋዘን መተላለፍ አለበት።

9.1.6 የዕቃ ርክክብ የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ በምርት ገበያው ማዕከላዊ የማከማቻ መጋዘን ለሚወጣው የማከማቻ መጋዘን የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ቅድመ ሁኔታ ነው።

9.1.7 የዕቃ ርክክብ የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ በማከማቻ መጋዘን ያለን ምርት አስመልክቶ እንደ ተላላፊ፣ ተዘዋዋሪ ወይም የሕግ መብት ባለቤትነት ማረጋገጫ ሠነድ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም።

9.2 የማከማቻ መጋዘን የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝን ስለማውጣት

9.2.1 የምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻ የመጋዘን ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝን ለማውጣት፣ የደረሰኙን ቅጂ ለማተም፣ ሕጋዊ መብትን ለማስተላለፍ እና ደረሠኙን ለመሠረዝ ብቸኛ ሥልጣን የተሠጠውና ኃላፊነትን የወሰደ አካል ይሆናል።

9.2.2 በምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻ የሚወጣው የመጋዘን ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ በማከማቻ መጋዘን ከተቀመጠው ምርት የሚመነጭ ሕጋዊ መብትን የሚወክል ይሆናል።

9.2.3 የማከማቻ መጋዘን የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ በምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻ አማካኝነት በምርት ገበያው ግብይት ውስጥ ተላላፊና ተዘዋዋሪ ሰነድ ሆኖ ያገለግላል።

9.2.4 የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ገንዘብ ለማግኘት በመያዣነት ሊያገለግል ይችላል።

9.2.5 የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ በምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻ መመሪያዎች/ሥነ ሥርዓቶች/ መሠረት የማከማቻ መጋዘን በሚል ስያሜ የወረቀት ደረሠኝ ሆኖ ሲጠየቅ ሊላክ ይችላል።

9.3 የማዕከላዊ ማከማቻ ተግባር

የምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻ የሚከተሉትን አገልግሎቶች ይሰጣል።

9.3.1 የማከማቻ መጋዘን የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ማዘጋጀት እና ማጽደቅ፣

9.3.2 የሚፈለጉ የመጋዘን የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ዳታዎችን ማረምና መያዝ፣

9.3.3 የአስቀማጮች ዝርዝርን የያዘ መዝገብ መያዝ፣

9.3.4 የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ በመጠቀም በምርት ገበያው ላይ የተፈጸሙ ግብይት ውሎችን ርክክብ ማድረግ፣

9.3.5 የርክክብ ማስታወሻ፣የማንሻ ማስታወሻ እና የማከማቻ መጋዘን ደረሰኝ የማብቂያ ጊዜን መቆጣጠር፣

9.3.6 የማከማቻ መጋዘን የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ዋጋ እንዳይኖራቸው ማድረግ ወይም መሰረዝ፣

9.3.7 የአባላትና ደንበኛ አቋም ሪፖርት ማዘጋጀት እና እንዲዘጋጅ መፍቀድ፣

9.3.8 ከማከማቻ መጋዘን ደረሰኝ ጊዜ ማብቃት፣ዘግይቶ ከመረከብ እና በምርት ገበያው የተፈጸመ ሽያጭ ሳይኖር ምርትን ከማከማቻ መጋዘን ከማውጣት ጋር የተያያዙ ቅጣቶችን ማስተዳደር እና

9.3.9 በየቀኑ ዘገባዎችን ማጣጣም።

## 9.4 የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ አፈጣጠር /አወጣጥ/ /አዘገጃጀት/ሥነ-ሥርዓት

9.4.1 የማከማቻ መጋዘን የዕቃዎች ርክክብ ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ከፈጠረ/ካዘጋጀ / በኋላ የማከማቻ መጋዘን የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ እንዲዘጋጅ ጥያቄ የማቅረቢያ መዝገብን ለምርት ገበያው ማዕከላዊ የማከማቻ መጋዘን ደረሰኝ ማስቀመጫ ማስረከብ አለበት ።

9.4.2 የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ በነጠላ የዳታ ደህንነት ሰርቨር ውስጥ መቀመጥ ይኖርበታል። ዳታው ያለፈቃድ እንዳይደረስበት፣ ላልተፈለገ ዓላማ እንዳይውል ወይም እንዳይወድም ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል።

9.4.3 ሳይፈቀድ ዳታ የሚጠለፍበት ወይም የሚሠረቅበትን አጋጣሚ ለማስወገድ የሚተላለፍበት መንገድ በኢንክራይፕድ /በልዩ የሚስጥር ኮድ/ እንዲሆን መደረግ አለበት።

9.4.4 በምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻ መጋዘን የዳታ መጠባበቂያ ሥርዓት ውስጥ የተከማቸው ዳታ በምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻን በብቸኝነት በሚቆጣጠረው የተለየ ስፍራ ተጠብቆ መቆየት ይኖርበታል። የምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻ ከሥራው ጋር የተያያዙ ዳታዎች ባልተፈቀደላቸው ሠዎች እንዳይደረስባቸው በቂ የጥበቃ ሥርዓት መዘርጋቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

9.4.5 የምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻ በእያንዳንዱ ዝርዝር ሒሳብ ወይም በአስቀማጩ ባለቤትነት ማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ውስጥ ለተደረጉ ለውጦች የግብይት መለያንና የኦዲት መከታተያ እንዲኖር የሚያስችሉ በቂ እርምጃዎችን መወሰድ ይኖርበታል።

9.4.6 የማዕከላዊ ማከማቻ ሥራ አስኪያጅ ወይም እርሱ የወከለው ሰው የመጋዘን ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ለማዘጋጀት ስልጣን /ውክልና / ለመስጠት እንደዚሁም የደረሰኙን ባለቤትነት ለማስተላለፍ ብቸኛ ኃላፊነት እና ሥልጣን ይኖራቸዋል።

9.4.7 የመጋዘን አገልግሎት የኤሌክትሮኒክስ ደረሠኝ መሠረት አድርጎ የተፈጠረበትን /የተዘጋጀበትን/ የዕቃ ርክክብ የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ማስታወሻ ቁጥርን በውስጡ የያዘ ልዩ /የመለያ / ቁጥር ሊኖረው ይገባል።

9.4.8 የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ የዕቃ ርክክብ ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ያወጣውን ማከማቻ መጋዘን ለመለየት የሚያስችል ሊሆን አይገባም።

9.4.9 በምርት ገበያው ላይ የሽያጭ ትዕዛዝ ለማቅረብ የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ቁጥር አስፈላጊ ነው።

## 9.5 የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ በመያዣ ስለመስጠት

9.5.1 የምርት ገበያው በሚያወጣው የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ በመያዣ መስጠትን በተመለከተ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ሥርዓት አዋጅ ቁ. 372/1996፣ በባንክ በመያዣ ስለተያዘ ንብረት የወጣ አዋጅ ቁ. 97/ 1990 እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው አዋጆች ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

9.5.2 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 9.5.1 አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በምርት ገበያው የሚወጣ የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ በመያዣ መስጠትን በተመለከተ የሚከተሉት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

9.5.2.1 ስለብድር ጥያቄ ማመልከቻ እና ስለማበደር

ሀ. በምርት ገበያው የማከማቻ መጋዘን የተቀመጠ ምርት ባለቤት የሆነ ሰው የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ወይም የአባላት/የደንበኛ አቋም ሪፖርትን መሰረት በማድረግ ለምርት ገበያው የክፍያ መፈጸሚያ ባንክ የብድር ጥያቄ ማመልከቻ ለማቅረብ ይችላል፡፡ የብድር ጥያቄ ማመልከቻው አግባብነት ባለው ባንክ ተፈጻሚ የሆነን ሥነሥርዓት ተከትሎ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

ለ. የቀረበው የብድር ጥያቄ ትንተና ከመጀመሩ በፊት የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙ ዋጋ ያለው ስለመሆኑ፣ የብድር ጥያቄ ያቀረበው ሰው በባለቤትነት የያዘው ስለመሆኑ እና ቀደም ብሎ በመያዣ ያልተያዘ ስለመሆኑ የምርት ገበያው እንዲያጣራ ባንኩ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ መረጃዎቹ ትክክለኛ ሆነው ከተገኙ የምርት ገበያው ስለማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙ አስፈላጊውን ዝርዝር መልሶ ይልካል፡፡

ሐ) ባንኩ የብድር ጥያቄውን ትንተና ካከናወነ በኋላ የምርት ገበያውን የኤሌክትሮኒክ መያዣ መጠየቂያ ቅጽ ሞልቶ በመፈረም በብድር ጥያቄው ማመልከቻ የተካተተውን መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ለምርት ገበያው መላክ አለበት፡፡የምርት ገበያው የኤሌክትሮኒክ መያዣ መጠየቂያ ቅጹ ላይ በመመስረት በማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ላይ ለባንኩ መያዣ ይሰጣል፡፡

መ. የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ላይ አንድ ጊዜ መያዣ ከተሰጠ ይህንኑ ለማመልከት 'በመያዣ የተያዘ' የሚል ምልክት ይደረግበታል፡፡ ባንኩ ምርቱ እንዳይሸጥ የተጣለው ገደብ እንዲነሳ ካላሳወቀ ወይም ከመያዣ-ነጻ ካልሆነ የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙ ለሽያጭ ሊቀርብ ወይም ከማከማቻ መጋዘን ሊወጣ አይችልም፡፡

ሠ. መያዣው ከተሰጠ የምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻ የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙን ትክክለኛነት እና መያዣውን በማረጋገጥ አግባብነት ላለው ባንክ የመያዣ ማረጋገጫ ሪፖርት ወዲያውኑ መላክ አለበት፡፡ የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙ ላይ ስህተት ከተገኘ ወይም አስቀድሞ በመያዣ ተይዞ ከሆነ የምርት ገበያው ምክንያቱን በመግለጽ 'የአቁም ምልክት' ለባንኩ ማስተላለፍ አለበት፡፡ ስህተቱ ካልተስተካከለ ወይም አዲስ የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መረጃ ካልተሰጠ በስተቀር በማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙ ላይ የተጀመረው የብድር መስጠት ሂደት አይቀጥልም፡፡

ረ. የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙ በመያዣ እንደተሰጠ የምርት ገበያው ወዲያውኑ 'የማይሸጥ' የሚል ምልክት የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙ ላይ በማድረግ በአባላት/የደንበኛ አቋም ሪፖርት እና በመያዣ መመዝገቢያና እንቅስቃሴ ዝርዝር ላይ ማመልከት አለበት፡፡

ሰ. በኤሌክትሮኒክ የሚወጣው የመያዣ መመዝገቢያና እንቅስቃሴ ዝርዝር በማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙ የተመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮችን በሙሉ ያካተተ እና በሚከተለው ሁኔታ በቡድን የተቀመጠ መሆን አለበት፡፡

i. መሸጥ የማይችሉ በመያዣ የተያዙ የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኞች፣
ii. መሸጥ የሚችሉ በመያዣ የተያዙ የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኞች፣
iii. በመያዣ የተያዙና መያዣ የተሰጠው ሰው መብቱን እያስከበረባቸው ያሉ በመያዣ የተያዙ የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኞች፣
iv. በመያዣ የተያዙ እና ባለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ (በከፊል ወይም በሙሉ) የተሸጡ የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኞች፣
v. በመያዣ የተያዙ ሆነው ባለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ ከማከማቻ መጋዘን ምርት የወጣባቸው የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኞች፣እና
vi. ባለፉት ሰባት ቀናት ከመያዣ ነጻ የተደረጉ የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኞች፡፡

ሸ. ብድሩ ተከፍሎ እስኪጠናቀቅ ድረስ የምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻ የምርት ገበያውን የመያዣ መመዝገቢያና እንቅስቃሴ ዝርዝር ለባንክ በየዕለቱ መላክ አለበት፡፡

ቀ. የምርት ገበያው ለአበዳሪው ባንክ የመያዣ ማረጋገጫ ሪፖርት ከሰጠ በኋላ በብድርና የመያዣ ስምምነት ውስጥ በሚገለጸው ጊዜና ዝርዝር መሰረት ብድሩ ሊጸድቅ እና ለማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙ ባለቤት ብድር ሊሰጥ ይችላል፡፡

በ. የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝን መሰረት በማድረግ ባንኩ የሰጠው ብድር መክፈያ ቀን ከማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙ ማብቂያ ጊዜ በፊት ብድሩን ለማስመለስ በቂ ጊዜ መስጠት አለበት፡፡

ተ. አንድ ተበዳሪ በአንድ ባንክ የተለያዩ ቅርንጫፎች ወይም በተለያዩ ባንኮች በርካታ የብድር የባንክ ሂሳብ ሊኖረው ይችላል፡፡ በርካታ የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኞች ለአንድ የብድር የባንክ ሂሳብ በመያዣነት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ሆኖም በማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ የተመለከተውን የምርት መጠን በከፊል መያዣ መስጠትም ሆነ ከመያዣ ነጻ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

ቸ. ከባንኩ ጋር የሚደረግ ግንኙነት በሙሉ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጥቅም ላይ ሊውል በሚችል በእጅ የሚሰራ መጠባበቂያ ሂደት ባለው ደህንነቱ በተጠበቀ የኤሌክትሮኒክ ዘዴ በመጠቀም መሆን አለበት፡፡

ኀ. በመያዣ ሊሰጡ የሚችሉት የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኞች አንድ መደብ ወይም ከዛ በላይ ምርት የሚወክሉት ብቻ ናቸው፡፡

9.5.2.2 ከመያዣ ነጻ ስለማድረግ

ባንኩ ከምርት ገበያው ማእከላዊ ማከማቻ ጋር በሚከተሉት ሁኔታዎች ከመያዣ ነጻ የማድረግ ሥነስርዓት በኤሌክትሮኒክ ሊጀምር ይችላል፡፡

ሀ. በመያዣ የተሰጠው ምርት (የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ) ሳይሸጥ ተበዳሪው ብድሩን በጥሬ ገንዘብ ከከፈለ፣

ለ. የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙን እንደመያዣ ሆኖ መቀጠል ባንኩ ካልፈለገ፡፡

9.5.2.3 ስለሽያጭ እና ክፍያ

ሀ. ተበዳሪው እና ባንኩ የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙን ለመሸጥ ከተስማሙ በኋላ የምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻ መያዣው ለሽያጭ መቅረብ እንዳይችል የተደረገበትን ሁኔታ እንዲያነሳ እና ለክፍያ መፈጸሚያ ክፍል የብድር ሂሳቡን ዝርዝር እንዲሰጥ ባንኩ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ትዕዛዝ ማስተላለፍ አለበት፡፡

ለ. መያዣው ለሽያጭ መቅረብ እንዳይችል የተደረገበት ሁኔታ የተነሳ ስለመሆኑ ባንኩ ለተበዳሪው ማሳወቅ አለበት፡፡ ይህ ሁኔታ በምርት ገበያው የአባላት/የደንበኛ አቋም ሪፖርት እና በመያዣ መመዝገቢያና እንቅስቃሴ ዝርዝር ላይ መመልከት አለበት፡፡

ሐ. በመቀጠል ተበዳሪው በመያዣ የተሰጠውን የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ በምርት ገበያ ለመሸጥ ይችላል፡፡ የምርት ገበያው የክፍያ መፈጸሚያ ክፍል ሽያጩን ተከትሎ የምርት ገበያውን ክፍያና አግባብነት ያለውን ግብር ከቀነሰ በኋላ ቀሪውን ገንዘብ በቀጥታ ወደ ባንኩ የብድር ሂሳብ ገቢ ያደርጋል፡፡ የምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻም የባለቤትነት መብት ወደ ገዢው ማስተላለፍ አለበት፡፡

መ. በምርት ገበያው የተሸጠውን በመያዣ ተሰጥቶ የነበረ የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ክፍያ የምርት ገበያው ለባንኩ ወዲያውኑ ለማስተላለፍ እንዲችል ባንኩ የተበዳሪውን ስም፣ የምርት ገበያውን የደንበኛ መታወቂያና የብድር ሂሳብ ቁጥር ያካተተ የተበዳሪውን የብድር ሂሳብ ዝርዝር መያዣው ለሽያጭ መቅረብ እንዳይችል የተደረገበት ሁኔታ እንዲነሳ ከሚቀርብ ጥያቄ ጋር ለምርት ገበያው የክፍያ መፈጸሚያ ክፍል መስጠት አለበት፡፡

ሠ. በመያዣ የተሰጠው የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ሽያጭ ክፍያ ከምርት ገበያው እንደተላለፈለት ባንኩ በሁለት የስራ ቀናት ውስጥ ማናቸውንም ከደረሰኙ ጋር የተያያዘ ተከፋይ ቀሪ ገንዘብ ለተበዳሪው መስጠት አለበት፡፡

9.5.2.4 ስለዋስትና አፈጻጸም

ሀ. ተበዳሪው የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙን በመሸጥ ዕዳውን በመክፈያ ጊዜው መክፈል ካልቻለ ባንኩ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ሥርዓት አዋጅ ቁ. 372/1996፣ በባንክ በመያዣ ስለተያዘ ንብረት የወጣ አዋጅ ቁ. 97/ 1990 እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የአገሪቱ ሕጎች መሰረት በማድረግ በመያዣው ላይ መብቱን ለማስከበር የሚከተሉትን ሂደቶች ያካተተ እንቅስቃሴ ሊጀምር ይችላል፡፡

i. ከክፍያው ጊዜ አንድ ቀን በኋላ ዋስትናውን ለማስከበር በመያዣ የተሰጠውን ምርት የመሸጥ ሃሳቡን ባንኩ የአምስት ቀን ሕጋዊ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ለተበዳሪው ያሳውቃል፣

ii. ተበዳሪው በንዑስ አንቀጽ (i) ስር በተሰጠው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ውስጥ የሚጠበቅበትን ክፍያ ካልፈጸመ በማስጠንቀቂያው ላይ የተገለጸው የክፍያ ጊዜ ካለፈ ከአስራ አምስት ቀን በኋላ ባንኩ የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙን ለመሸጥ ይችላል፣

iii. ባንኩ ዋስትናውን ለማስከበር መወሰኑን ለምርት ገበያው እንዳሳወቀ እና ለምርት ገበያው የተላከው የዋስትና መብት ማስከበሪያ ሕጋዊ ማስጠንቀቂያ ስርዓት የተከተለ መሆኑ እንደታወቀ (የትዕዛዙ ትክክለኛነት ተጣርቶ) የምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻ ባንኩ ምርቱን እንዲሸጥ ወይም እንዲያወጣ መፍቀድ አለበት፣

iv. ባንኩ መብቱን ለማስከበር መያዣውን ለመሸጥ እንደወሰነ የምርት ገበያው የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙን የማብቂያ ጊዜ በአርባ ቀን ማራዘም አለበት፡፡ የምርት ገበያው መደበኛ የጥራት ዋስትና ጊዜ ለዚህ የችሮታ ጊዜም መቀጠል ይኖርበታል፣

v. በንዑስ አንቀጽ (iv) ድንጋጌ ስር የተሰጠው የአርባ ቀን ተጨማሪ ጊዜ እንዳበቃ የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙ ማብቂያ ጊዜ ተራዝሞ ከመሸጡ ወይም ከመውጣቱ በፊት ባንኩ መደበኛውን የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ማብቂያ ቅጣት መክፈል አለበት፡፡

ለ. ዋስትናውን በማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙ ላይ ለማስከበር መወሰኑን ባንኩ ለምርት ገበያው እንዳሳወቀ የምርት ገበያው በተመሳሳይ ቀን በመያዣ የተሰጠውን የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ በማገድ ጥያቄውን ማረጋገጥ ወይም ውድቅ ማድረግ አለበት፡፡ ሂደቱ ስርዓት ባለመከተሉ (ትዕዛዙ ትክክለኛ ባለመሆኑ) ጥያቄው ውድቅ ከተደረገ የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙ በመያዣ እንደተያዘ በተበዳሪው

ለግብይት እንዲቀርብ የሚደረግበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ የባንኩ ጥያቄ ተቀባይነት ካገኘ ደግሞ ማዕከላዊ ማከማቻ የባለቤትነት መብት ሳያዞር የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙ ዋስትና እየተከበረበት መሆኑን በማመልከት ለባንኩ የመሸጥ ወይም የማውጣት መብት መስጠት አለበት፡፡

ሐ. ባንኩ በደንበኝነት በአገናኝ አባል አማካይነት በመያዣ የተሰጠው የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ በምርት ገበያው በከፊል ወይም በሙሉ ለመሸጥ ይችላል፡፡ ሽያጩ ካልተከናወነ ተገቢውን የማከማቻ አገልግሎት ክፍያና ቅጣት ከከፈለ በኋላ ባንኩ ከምርት ገበያው መጋዘን ምርቱን የማውጣት አማራጭ አለው፡፡

መ. የዚህ ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌ (ሐ) ቢኖርም፣ በምርት ገበያው መድረክ ብቻ ግብይት እንዲካሄድባቸው የተወሰኑ ምርቶችን ባንኩ እንዲያወጣ አይፈቀድለትም፡፡

ሠ. ከገበያ ዋጋ ጋር በማነጻጸር የብድር መጠን መተመንና ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የማስተካከያ እርምጃዎች የመውሰድ ጉዳይ የባንኩ እና የተበዳሪው ብቻ ነው፡፡ የምርት ገበያው በዚህ ጉዳይ መሳተፍ የለበትም፡፡

## 9.6 የአፈጻጸም ዋስትና

9.6.1 የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ባለቤት ወይም የምርት ገበያው አባል የሆነ ወኪሉ በምርቱ ርክክብ ወይም ምርቱ በሚወጣበት ወቅት ለሚታይ ማናቸውም የመጠን ወይም የጥራት መጓደል በምርት ገበያው ላይ ያላቸውን ቅሬታ ለማቅረብ ይችላሉ፡፡

9.6.1.1 የምርት ገበያው በአፈጻጸም ዋስትናው ምርቱን በማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙ ላይ በተጠቀሰው የክብደት መጠን እና የጥራት ደረጃ መሰረት ለማስረከብ ወይም እንዲወጣ ለማድረግ ዋስትና ሰጥቷል፡፡

9.6.1.2 ማናቸውንም በእርጥበት መጠን መቀነስ ምክንያት የሚመጣ ማስተካካያ ማድረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ የምርት ገበያው በማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙ ላይ በተጠቀሰው የክብደት መጠን እና የጥራት ደረጃ መሰረት ምርቱን ማስረከብ ካልቻለ የምርት ገበያው ለማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኙ ባለቤት ካሳ መክፈል አለበት፡፡ የካሳው መጠንም የምርቱ ርክክብ የሚፈጸም ከሆነ ምርቱ የተሸጠበት ዋጋ፣ ምርቱ የሚወጣ ከሆነ ደግሞ በወቅቱ ተቀባይነት ባለው የገበያ ዋጋ ሆኖ የምርት ገበያው የአገልግሎት ክፍያ፣ ግብርና ሌሎች ማስተካከያዎች ከተቀናነሱ በኋላ የሚገኘው መጠን ይሆናል፡፡

9.6.1.3 በምርት ገበያው ዋስትና የተሰጠው የምርት መጠን በእርጥበት መቀነስ ምክንያት የሚደረግ ማስተካከያን ግምት ውስጥ ያስገባል፡፡

9.6.2 የአፈጻጸም ዋስትና ጥያቄ እንደሚከተለው መስተናገድ አለበት፡፡

9.6.2.1 አቤቱታ አቅራቢ የጥያቄውን ባህሪ በመግለጽ አቤቱታውን ለምርት ገበያው የአባላት ክፍል በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፡፡

9.6.2.2 የምርት ገበያው ተገቢውን ምርመራ በማድረግ እያንዳንዱን አቤቱታ መቀበል ወይም ውድቅ ማድረግ አለበት፡፡

9.6.2.3 አቤቱታው ተቀባይነት ካገኘ የምርት ገበያው አቤቱታው በቀረበ አስር የስራ ቀናት ውስጥ ለአቤቱታ አቅራቢው ካሳ መክፈል አለበት፡፡

9.6.2.4 የምርት ገበያው የርክክብ መጠን ጉድለትን በተመለከተ ለባለስልጣኑ በየወሩ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

9.6.3 የምርት ገበያው በአፈጻጸም ዋስትና ስር ያሉበትን ግዴታዎች ለመወጣት የሚከተሉትን የሚጨምር የተለያዩ ዘዴዎች ሊኖሩት ይችላል፡፡

9.6.3.1 የጉዳትና የንብረት መድን ዋስትና፣

9.6.3.2 የታማኝነት ዋስትና መድን ወይም

9.6.3.3 የማከማቻ መጋዘን ደረሰኞች ካሳ ፈንድ፡፡

9.7 የማከማቻ መጋዘን ደረሰኞች ካሳ ፈንድ

9.7.1 ከማከማቻ መጋዘን ደረሰኝ የአፈጻጸም ዋስትና ጋር በተያያዘ የሚነሱ ኃላፊነቶችን ለመሸፈን የምርት ገበያው የካሳ ፈንድ ማቋቋም አለበት፡፡

9.7.2 የዳይሬክተሮች ቦርድ የካሳ ፈንድ የሚተዳደርበትን ሥርዓት በተለይም በምርት ገበያው ስለሚደረግ መዋጮ መጠን እና በካሳ ፈንድ የተቀመጠው ገንዘብ ወጪ ስለሚደረግበት ሁኔታ በየጊዜው ሊወስን ይችላል፡፡

9.7.3 ለካሳ ፈንድ መዋጮ ስለማድረግ እና ስለማጠራቀም

9.7.3.1 የምርት ገበያው ከሚያስከፍለው ጠቅላላ የመጋዘን አገልግሎት እና ከስራው ጋር በተያያዘ ከሚያገኘው ክፍያ/ገንዘብ ውስጥ በየወሩ መጨረሻ የተወሰነ ፐርሰንት ለካሳ ፈንድ መዋጮ ማድረግ አለበት፡፡ የሚደረገው መዋጮ ፐርሰንት በቦርዱ መጽደቅ አለበት፡፡

9.7.3.2 መንግስት ለካሳ ፈንዱ በየጊዜው መዋጮ ማድረግ ይችላል፡፡

9.7.3.3 የምርት ገበያው ስለሚያደርገው ተጨማሪ መዋጮ መጠን እና ስለመዋጮው ዘዴ መወሰን ይችላል፡፡

9.7.4 ስለመዋጮው ዓይነት እና ሂሳብ

የምርት ገበያው በጥሬ ገንዘብ ወይም በሌላ ዓይነት ወይም ዘዴ ለካሳ ፈንዱ መዋጮ ሊያደርግ ይችላል፡፡ የምርት ገበያው የሚያደርገው መዋጮ የክፍያ ማስፈጸሚያ ክፍሉ በሚያዘጋጀው የካሳ ፈንድ ሂሳብ ገቢ ተደርጎ በየዓመቱ ኦዲት መደረግ አለበት፡፡

9.7.5 የካሳ ፈንዱን ኢንቨስት ማድረግ

የካሳ ፈንዱ ወለድ በሚያስገኝ የባንክ ሂሳብ እንዲቀመጥ ሊደረግ ወይም የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚወስነው መሰረት ኢንቨስት ሊደረግ ይችላል፡፡ ፈንዱን ኢንቨስት በማድረግ የተገኘ ጥቅም እንደገና ፈንዱ ውስጥ መግባት አለበት፡፡

9.7.6 የዳይሬክተሮች ቦርድ በየጊዜው በሚወስነው መሰረት የካሳ ፈንዱ የሚከተሉትን ለሚጨምር አገልግሎት ሊውል ይችላል፡፡

9.7.6.1 የካሳ ፈንዱን ለማቋቋምና ለማስተዳደር የወጡ ወጪዎችን ለመሸፈን፣

9.7.6.2 ከማከማቻ መጋዘን ደረሰኝ ጋር በተያያዘ የምርት ገበያው ያለበትን የአፈጻጸም ዋስትና ለማሟላት በጊዜያዊነት ለመጠቀም እና

9.7.6.3 የምርት ገበያው በየጊዜው በሚወስነው መሰረት ከማከማቻ መጋዘን ደረሰኝ ጋር ለተያያዙ አገልግሎቶች የሚወጡ ማናቸውንም ወጪዎች ለመሸፈን፡፡

9.7.7 የምርት ገበያው በካሳ ፈንዱ ውስጥ የተቀመጠውን ጥሬ ገንዘብ ወይም ማናቸውም ሌላ ተቀማጭ በሙሉ ለማስያዝ፣ መያዥውን ለማደስ፣ ወለድ አግድ ለመግባት፣ ለማስተላለፍ፣ የዋስትና መብት ለማቋቋም ወይም ለማዛወር ይችላል፡፡

9.8 ስለ አስቀማጩ ሒሳብ

ማዕከላዊ ማከማቻ ለእያንዳንዱ አስቀማጭ የተለየ ሒሳብ /መዝገብ/ መያዝ አለበት።

9.8.1 የምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻ የመጋዘን ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ እንዲፈጠር/እንዲዘጋጅ/ የቀረበ ጥያቄን ሲቀበል፤

9.8.1.1 የአስቀማጭ ሒሳብ መክፈትና ሒሳቡን ለአዲሱ አስቀማጮች ገቢ ማድረግ ወይም፤

9.8.1.2 ሂሳቡን አስቀድሞ ለነበረ አስቀማጭ ገቢ ማድረግ ይኖርበታል።

9.8.2 ማዕከላዊ ማከማቻ ከማከማቻ መጋዘኑ የቀረቡ ጥያቄዎችን ወይም ከክፍያ ማስፈፀሚያ ተቋም የቀረቡ መመሪያዎችን በመቀበል በኋላም ይህንኑ የምርት ገበያው ያወጣውን ደንብ ተከትሎ ለአስቀማጩ በማረጋገጥ ከአስቀማጩ ሒሳብ የወጣ ወይም የገባ የመጋዘን ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ዝውውርን የሚያሳይ መዝገብ መያዝ ይኖርበታል።

9.8.3 በአስቀማጩ ሒሳብ ገቢ የሚደረግ ገንዘብ ማከማቻ መጋዘኑ ወይም ክፍያ መፈፀሚያ ተቋሙ በኤሌክትሮኒክስ ወይም በማንኛውም መልክ ባቀረበው ጥያቄ ወይም በተሰጠው መመሪያ ሊደገፍ ይገባል።

9.9 ስለ መዛግብት

9.9.1 የምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻ የሚከተሉትን መዛግብቶች እና ሰነዶች መያዝ አለበት።

9.9.1.1 የዕቃ ርክክብ የኤሌክትሮኒክስ ማስታወሻ፣ የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ፣ የርክክብ ማስታወቂያ ፣የማንሻ ማስታወሻ እና የእቃዎች መረከቢያ ማስታወሻ መዛግብት፣

9.9.1.2 የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ የተላለፈለት፣ ያስተላለፈው ሰው ስምና ዝውውሩ የተፈፀመበት ቀናት የሚያሳዩ መዛግብት ፣

9.9.1.3 ከማከማቻ መጋዘኑ እና ክፍያ ማስፈፀሚያ ተቋሙ ወይም ለማከማቻ መጋዘኑ እና ለክፍያ መፈፀሚያ ተቋሙ የተላኩ ወይም የቀረቡ ጥያቄዎች እና ትእዛዞች የሚመለከት መዛግብት ፣

9.9.1.4 የአስቀማጮች ዝርዝርን የያዘ መዝገብ፣

9.9.1.5 ከቅጣት እና ከክፍያ ጋር የተያያዙ ሰነዶች እና

9.9.1.6 በቦርድ ዳይሬክተሮች ሊወሰኑ የሚችሉ ሌሎች አስፈላጊ መዛግብት።

9.9.2 የምርት ገበያው ማዕከላዊ ማከማቻ መዛግብትንና ሠነዶችን ቢያንስ ለአስር ዓመታት ማቆየት / መጠበቅ / አለበት።

## 10. ክፍያና ርክክብ አፈፃፀም

10.1 የምርት ገበያው የክፍያ ተቋም

10.1.1 የምርት ገበያው የክፍያ መፈፀሚያ ተቋም ተግባራት በዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም በዋናው ሥራ አስፈፃሚ የሚመራ ይሆናል። የዳይሬክተሮች ቦርድ ተስማሚ ሆኖ ሲያገኘው ለዋናው ሥራ አስፈጻሚ ወይም ለሌላ ማንኛውም ክፍያ ፈፃሚ ባንክ ተጨማሪ ሥልጣን ወይም ሀላፊነት በየጊዜው ሊሰጥ ይችላል።

10.1.2 በምርት ገበያው የተደረጉ ውሎች ተጣርተው ክፍያና ርክክብ በምርት ገበያው የክፍያ መፈጸሚያ ተቋም ሊፈጸምባቸው የሚገባ ሲሆን እንዳስፈላጊነቱ በግብይቱ ደንብ ወይም ሕግን ተከትሎ ባለሥልጣኑ በሚሰጠው መመሪያ ወይም ትዕዛዝ መሠረት መጠናቀቅ / መሠረዝ / ይኖርባቸዋል።

## 10.2 የክፍያ መፈጸሚያ ተቋም ዋስትና

10.2.1 በምርት ገበያው በየጊዜው የሚወሰኑ የተወሰኑ ምርቶችን የሚመለከቱ እንደዚሁም በዚህ ደንብ መሠረት በምርት ገበያው ግብይት ክፍያቸው ስለሚፈጸም ውሎች አከፋፈል በተመለከተ የምርት ገበያው የክፍያ መፈጸሚያ ተቋም በአባላት ላይ ስላለ የተጣራ የገንዘብ ግዴታ እንደዚሁም ስለምርቱ ጥራት እውነተኛነት እና ርክክብ ወይም በምርት ገበያው ላይ ስለተደረገ ግብይት ለአባላቱ ዋስትና እንደሠጠ ይቆጠራል።

10.2.2 አባላት ለደንበኞቻቸው ወይም ክፍያ ለሚፈጽሙላቸው የምርት ገበያው አባላት ላለባቸው ግዴታዎች የምርት ገበያው ዋስትና እንደሰጠ ሊቆጠር አይችልም።

## 10.3 ክፍያ ፈጻሚ አባላት

ሁሉም ተገበያይ አባላት፣አገናኝ አባላት እና ክፍያ ፈጻሚ ገዢ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባላት ክፍያ ፈጻሚ አባላት ናቸው።

10.3.1 ሁሉም ተገበያይ አባላት፣አገናኝ አባላት እና ክፍያ ፈጻሚ ገዢ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባላት ክፍያ የመፈጸም ግዴታ ያለባቸው አባላት ናቸው።የምርት ገበያውን የክፍያ መፈጸሚያ ተቋም የክፍያ አፈጻጸም፣ የርክክብ እና የዋስትና አፈጻጸም አገልግሎት ቀጥተኛ ተጠቃሚለመሆን የሚችሉት እነርሱ ብቻ ናቸው።

10.3.2 በምርት ገበያው ግብይት የተፈፀመባቸው ውሎች በሙሉ በምርት ገበያው መረጋገጥና በዚህ ደንብ መሠረት በተወሰነው አኳኋን ክፍያቸው እንዲፈፀም ለአባላት በዳረጎት ይተላለፋሉ።

10.3.3 በምርት ገበያው የሚከናወኑ ግብይቶችን በተመለከተ ማንኛውም አባል በአባሉና በደንበኛው መካከል የተደረሰ የፀና ስምምነት ሣይኖር ውሎችን ሊፈፅም ፣ሊከፍል ወይም ሊዘጋ አይችልም። የስምምነቱ ቅጅ ለምርት ገበያው መሰጠት አለበት። ከዚያ በኋላ ስምምነቱ እስኪያበቃ ድረስ አባሉ በግዴታ መፈፀሚያ ተቋሙ ካለው ሂሣብ የደንበኛውን ውል መፈፀም፣መዝጋት ወይም ማጣራት አለበት።

10.3.3.1 ማንኛውም ሰው በአንድ የምርት መደብ ከአንድ በላይ ለሆኑ አባላት ደንበኛ መሆን የለበትም።

10.3.3.2 ክፍያ መፈጸም የማይችል ገዢ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባል በምርት ገበያ ያካሄደውን ግብይት ክፍያ ለመፈጸም ከአንድ በላይ ክፍያ ፈጻሚ አባል ደንበኛ ለመሆን አይችልም።

10.3.3.3 አገናኝ አባል ከደንበኞች ወይም ክፍያ ከሚፈጽምላቸው ደንበኞች ዝርዝር ውስጥ የተሰረዘ ወይም የተጨመረ ሲኖር ለምርት ገበያው በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል።

10.3.4 ክፍያ ፈጻሚ አገናኝ አባል ተቀባይነት ያለው የክፍያ መፈጸሚያ አገልግሎት ስምምነት ከማድረጉ በፊት ክፍያ መፈጸም የማይችል ገዢ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባልን የመግዢያ ገንዘብ የማስገባት ግዴታ የሚመለከት ክፍያ ለመፈጸም አይችልም።የስምምነቱ አንድ ቅጂ ለምርት ገበያው ይሰጣል።ከዚህ በኋላ ስምምነቱ እስኪቋረጥ ድረስ ክፍያ መፈጸም የማይችለው ገዢ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባል ለገባቸው ውሎች አገናኝ አባሉ በክፍያ ተቋም ካለው ሂሳብ ክፍያ ይፈጽማል።

## 10.4 ስለ ክፍያ መፈፃሚያ ባንኮች

10.4.1 ስለተሰየሙ ክፍያ መፈፃሚያ ባንኮች

የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም ዋና ሥራ አስፈጻሚ በዚህ ደንብ መሠረት ገንዘብ የማሰባሰብን፣ የገንዘብ ልውውጥን ፣መረጃ መጋራትን እና ሌሎች እምርታ ያላቸው

አገልግሎቶችን የሚሰጡ እና የሚያመቻቹ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ሀገር በቀል ባንኮችን የክፍያ መፈፃሚያ ባንክ አድርጎ መሰየም ይኖርበታል።

10.4.2 ተገበያይ አባላት፣አገናኝ አባላት እና ክፍያ ፈጻሚ ገገር-ብቻ ውስን ተገበያይ አባላት ክፍያ መፈጸሚ ባንክ ሆነው ከተሰየሙ በአንደኛው በመረጃ መረብ የተገናኘ የባንክ ቅርንጫፍ ውስጥ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የባንክ ሂሳቦች መክፈት ይኖርባቸዋል።የተጠቀሱት አባላት በምርት ገበያው በሚጠየቀው መሰረት የራሳቸውን እና የደንበኞቻቸውን ገንዘብ፣የራሳቸውን እና የክፍያ መፈጸሚያ ገንዘብ የመለየትን ጨምሮ የባንክ ሂሳቦችን እንቅስቃሴ በተመለከተ በምርት ገበያው የሚተላለፉ ትእዛዞችን ማክበር ይኖርባቸዋል።ከሚመለከታቸው የባንክ ሂሳቦች የሚፈለገውን ገንዘብ የምርት ገበያው ወጪ በማድረግ ክፍያዎችን ለመሸፈን እንዲችል የተጠቀሱት አባላት በባንክ ሂሳቦቻቸው ውስጥ በቂ ገንዘብ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል።ሻጭ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባላት በክፍያ መፈጸሚያ ባንክ ማንኛውም ቅርንጫፍ የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሳብ መክፈት አለባቸው። ክፍያ መፈጸም የማይችሉ ገገር-ብቻ ውስን ተገበያይ አባላት የመግዢያ ገንዘብ የማስገባት ግዴታቸውን በአገናኝ አባል በኩል የሚወጡ በመሆኑ የክፍያ መፈጸሚያ የባንክ ሂሳብ መክፈት አይጠበቅባቸውም።

10.4.2.1 የተገበያይ አባል ሂሣብ

ሀ. ለምርት ገበያው የመግዢያ ገንዘብ ማስገቢያ(ፔይ ኢን) የባንክ ሂሣብ ለራሳቸው የሚገበያዩ አባላት የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ የመግዦያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ መክፈት አለባቸው፡-

i. አባሉ የመግዥያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሒሳብ ሕጋዊ ባለቤት መሆን፣

ii. ለምርት ገበያው ከአባሉ የባንክ ሂሣብ ያለ ቅድመ ሁኔታ ከባንክ ሂሣቡ ላይ ክፍያ እንዲፈጸም የመጠየቅ ብቸኛ ሥልጣን የሚሰጥ የውክልና ሠነድን መፈረም፣

iii. የደንቡ አንቀጽ 10.6.4 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አባሉ ከባንክ ሂሣቡ እንዲያወጣ የማይፈቀድለት መሆኑ፣

iv. ምርት ገበያው የተጣራ ኤሌክትሮኒክስ ሂሳብ ወደ ባንክ የመላክ ሥልጣን እንዲኖረው መፈቀድ፣

v. ምርት ገበያው ከባንክ ሂሣብ የዕዳ ክፍያ እንዲፈፀም የኤሌክትሮኒክስ ትዕዛዝ ለመስጠት የሚያስችለው ሥልጣን መኖር፣

vi. ከዚህ የባንክ ሒሳብ ተከፋይ ለማድረግ የሚያስችሉ ቼኮችን ማውጣት የማይቻል መሆን እና

vii. ከዚህ የባንክ ሂሳብ ተከፋይ የሚያደርጉ የክሬዲት ወይም የዴቢት ካርድማውጣት የማይቻል መሆን።

ለ. የአባላት የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ(ፔይ አውት) የባንክ ሒሳብ ለራሳቸው የሚገበያዩ አባላት የሚከተሉት ሁኔታዎችን የሚያሟላ የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሳብ መክፈት አለባቸው።

i. አባሉ የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሣብ ሕጋዊ ባለቤት መሆን፣

ii. ምርት ገበያው ለባንክ ሂሣቡ የኤሌክትሮኒክስ የገቢ ተከፋይ ትዕዛዝ ለመላክ ሥልጣን መኖር፣

iii. አባሉ የዴቢት ተከፋይ ለመጠየቅ ብቸኛ መብት ያለው መሆን፣

iv. አስፈላጊ ሲሆን ቼክ መስጠት ስለመቻሉ እና

v. የአባል የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሣብ አስቀድሞ ያለ የደንበኛ የባንክ ሂሣብ ሊሆን መቻሉ።

10.4.2.2 የአገናኝ አባላት የባንክ ሂሣብ

ከላይ ከተገለጸው የተገበያይ የባንክ ሂሣብ በተጨማሪ ለራሱና ለሌሎች የሚገበያይ አገናኝ አባል ለደንበኞች ገንዘብ ማስቀመጫ ብቻ የሚያገለግል የሚከተለውን የባንክ ሂሣብ መክፈት አለበት።

ሀ. የደንበኛ የመግዢያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሣብ

ለሌሎች የሚገበያዩ አባላት ቢያንስ አንድ የደንበኞቻቸው የመግዢያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሣብ መክፈት አለባቸው። ይኸም ደንበኞቻቸው የግዢ ገንዘብ የሚያስተላልፉበት ሂሳብ የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ መሆን አለበት ።

i. አባሉ የመግዢያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሣብ ሕጋዊ ባለቤት መሆን፣
ii. ለምርት ገበያው ያለ ቅድመ ሁኔታ የወጪ ክፍያ ለመጠየቅ ብቸኛ መብት የሚሰጥ ውክልና ሠነድ በአባሉ መፈረም፣
iii. የደንቡ አንቀጽ 10.6.4 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አባሉ ከባንክ ሂሣብ ገንዘብ ለማውጣት የማይፈቀድለት መሆን፣
iv. የምርት ገበያው የተጣራ ኤሌክትሮኒክስ ሂሳብ ስሌት ወደ ሂሳቡ ለማስገባት የሚያስችለው ውክልና መኖር፣
v. የምርት ገበያው የኤሌክትሮኒክስ የተከፋይ ወጪ መጠየቂያ ትዕዛዝ ወደ ሂሣቡ ለመላክ የሚያስችለው ውክልና መሰጠት፣
vi. ከሂሣቡ ተከፋይ ሊሆን የሚችል ቼክ መስጠት የማይቻል ስለመሆኑ እና
vii. ከባንክ ሂሣቡ ተከፋይ የሚሆን የክሬዲትና ዴቢት ካርድ ማውጣት አለመቻሉ።

ለ. የደንበኛው የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሳብ

ስለሌሎች የሚገበያዩ አባላት የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሟሉ ቢያንስ አንድ የደንበኛ የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሳብ መክፈት አለባቸው።

i. አባሉ የደንበኛ የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ ሂሳብ ሕጋዊ ባለቤት መሆን፣
ii. የምርት ገበያው የኤሌክትሮኒክስ ተከፋይ ገቢ ትዕዛዝ ለመስጠት ውክልና መኖር፣
iii. አባሉ ተከፋይ ወጪ ለመጠየቅ ብቸኛ መብት ያለው መሆን፣
iv. አስፈላጊ ሲሆን ቼክ መስጠት ስለመቻሉ እና
v. አባሉ የደንበኛ የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሁሳብ ውስጥ ያለን ገንዘብ ወዲያውኑ ለደንበኞች በባንክ ሂሳባቸው ውስጥ በማስገባት ማከፋፈል አለበት ፡፡

ሐ. የክፍያ መፈጸሚያ የመግዢያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ

ክፍያ መፈጸም በማይችሉ ገዢ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባላት ምትክ ክፍያ የሚፈጽሙ አገናኝ አባላት የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ የተጠቀሱት ገዢ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባላት የመግዢያ ገንዘብ ሚያስገቡበት የባንክ ሂሳብ መክፈት አለባቸው።

i. ክፍያ ፈጻሚው ተገበያይ አባል የክፍያ መፈጸሚያ የመግዢያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ ህጋዊ ባለቤት መሆን፣
ii. ለምርት ገበያው ከክፍያ ፈጻሚው አገናኝ አባል የባንክ ሂሳብ ያለቅድመ ሁኔታ ክፍያ እንዲፈጸም የመጠየቅ ብቸኛ ስልጣን የሚሰጥ የውክልና ሰነድ መፈረም፣

iii. የደንቡ አንቀጽ 10.6.4 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አባሉ ከክፍያ መፈጸሚያ የባንክ ሂሳብ እንዲያወጣ የማይፈቀድለት መሆኑ፣
iv. የምርት ገበያው የተጣራ ኤሌትሮኒክስ ሂሳብ ሚዛን ለክፍያ መፈጸሚያ የመግዢያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ የመላክ ስልጣን እንዲኖረው መፍቀድ፣
v. የምርት ገበያው ከባንክ ሂሳብ ክፍያ እንዲፈጸም የኤሌትሮኒክስ ትእዛዝ ለመስጠት የሚያስችለው ስልጣን መኖር፣
vi. ከዚህ የክፍያ መፈጸሚያ የመግዢያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ ተከፋይ ለማድረግ የሚያስችሉ ቼኮችን ማውጣት የማይቻል መሆን እና
vii. ከዚህ የክፍያ መፈጸሚያ የመግዢያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ ተከፋይ የሚያደርጉ የክሬዲት ወይም የዴቢት ካርድ ማውጣት የማይቻል መሆን።

ሐ. የክፍያ መፈጸሚያ የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሳብ
ክፍያ መፈጸም በማይችሉ ገገር ብቻ ውስን ተገበያይ አባላት ምትክ ክፍያ የሚፈጽሙ አገናኝ አባላት የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ያልተጠቀሙበትን የመግዣ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ ውስጥ የሚገኝ የግዢ ገንዘብ አገናኝ አባላት የሚያዛውሩበት የክፍያ መፈጸሚያ የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሳብ መክፈት አለባቸው፡፡
i. አገናኝ አባሉ የክፍያ መፈጸሚያ የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ ሂሳብ ሕጋዊ ባለቤት መሆን ፣
ii. የምርት ገበያው የኤሌክትሮኒክስ ተከፋይ ገቢ ትዕዛዝ ለመስጠት ውክልና ያለው መሆኑ፣
iii. አገናኝ አባሉ ተከፋይ ወጪ ለመጠየቅ ብቸኛ መብት ያለው መሆን፣
iv. አስፈላጊ ሲሆን ቼክ መስጠት ስለመቻሉ እና
v. አገናኝ አባሉ ከምርት ገበያ ከሚሰበሰብ የክፍያ መፈጸሚያ የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ያለን ገንዘብ ለደንበኞች የሚያከፋፍል መሆኑ።

10.4.3 የአባላት ባንክ ሂሣብ መክፈቻ ሂደት

10.4.3.1 አባላት ከላይ በተመለከተው መስፈርት መሠረት በሚፈጽሙበት ጊዜ የሚከተሉትን ሂደቶች መከተል ይኖርባቸዋል፡-
ሀ. በምርት ገበያው አባል መሆናቸው መጽደቅ አለበት፣
ለ. አባላት የሚከተሉትን በተመለከተ ምርጫቸውን ለምርት ገበያው ያሳውቃሉ፣
i. የምርት ገበያ ክፍያ መፈጸሚያ ባንክ፣
ii. ለተገበያይ አባላት፣ለአገናኝ አባላት እና ለክፍያ ፈጻሚ ገዢ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባላት በመረጃ መረብ የተገናኘ ቅርንጫፍ ባንክ ወይም ለውስን አገናኝ አባላት እና ለሻጭ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባላት ደግሞ በክፍያ መፈጸሚያ ባንክ ማናቸውም ቅርንጫፍ፡፡

10.4.3.2 በምርት ገበያው አባል መሆኑ የጸደቀ መሆኑን ለተመረጠው የክፍያ መፈጸሚያ ባንክ የሚገልጽ የምርት ገበያ የድጋፍ ደብዳቤ አባሉ ከምርት ገበያው ሊያገኝ ይገባል ፡፡ የምርት ገበያው ዋናውን ቅጅ ለክፍያ መፈጸሚያ ባንኩየምርት ገበያ የክፍያ ማስፈጸሚያ ቡድን መስጠት አለበት፡፡

10.4.3.3 አባላት የሚከተሉትን ሰነዶች ለተመረጠው የክፍያ መፈጸሚያ ባንክ መስጠት እና የባንክ ሂሣብ ለመክፈት ሌሎች የባንኩን ፎርማሊቲዎች ማሟላት አለባቸው፡፡
ሀ. የምርት ገበያ የድጋፍ ደብዳቤ ፣
ለ. አባላት ያለ ቅድመ ሁኔታ ለምርት ገበያው የሠጡት ውክልና፣
ሐ. የመለያ ካርድ ማረጋገጫ እና
መ. ሌሎች በክፍያ መፈጸሚያ ባንኩ የሚጠየቁ ሰነዶች፡፡

10.4.3.4 የውክልና ስልጣኑ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፤
ሀ. ቅድመ ሁኔታን ያላስቀመጠ፣
ለ. አባላት በክፍያ መፈጸሚያ ባንኮች ያላቸውን የባንክ ሂሣብ ቁጥሮች የምርት ገበያው ከክፍያ መፈጸሚያ ባንኮች ለመቀበል መብት ያለው መሆኑን፣
ሐ. የምርት ገበያው ከክፍያ መፈፀሚያ ባንኩ የአባላት የመግዣያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሣብ ገንዘብ ለማውጣት እንደዚሁም የክፍያ መፈፀሚያ ባንኩ ከአባላት ሂሳብ ላይ ለምርት ገበያው እንዲከፈል በተጠየቀው መሠረት ገንዘቡ በክፍያ መፈፀሚያ ባንክ ውስጥ ወዳለው የምርት ገበያው የክፍያ መፈጸሚያ ባንክ ሂሣብ እንዲዛወር የክፍያ መፈፀሚያ ባንኩን ለመጠየቅ ብቸኛ መብት ያለው መሆኑን፣
መ. የምርት ገበያው ስለሁሉም የመግዣያ ገንዘብ ማስቀመጫ የባንክ ሂሣቦች የተሠሩ የወጪና ገቢ ስሌቶችን ለመጠየቅ መብት ያለው መሆኑን፣
ሠ. በአባላት የመግዣያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሣቦችገንዘብ የገባበት፣የወጣበት እና የንዘቡን መጠን የመሳሰሉ መረጃዎችን የምርት ገበያው ከክፍያ መፈፀሚያ ባንክ ለመጠየቅ መብት ያለው መሆኑን እና
ረ. የክፍያ መፈጸሚያ ባንኩ አባላትን አስመልክቶ በእጁ ያለውን መረጃ እንዲሰጠው ለመጠየቅ የምርት ገበያው መብት ያለው መሆኑ እና በአባላት ላይ ክትትል ለማድረግ ወይም ክትትል የሚያደርግ ሰው ለመወከል የምርት ገበያው ያለውን መብት አስመልክቶ በግልጽ መደንገግ አለበት፡፡

10.4.4 የተሰየመው የክፍያ መፈጸሚያ ባንክ ከምርት ገበያው ወይም ከክፍያ መፈጸሚያ ተቋም የተሰጠውን ትእዛዝ ስለመፈጸም
የተሰየመው ክፍያ ፈፀሚ ባንክ በምርት ገበያው ወይም በክፍያ መፈጸሚያ ተቋም ሲታዘዝ በምርት ገበያው ወይም በክፍያ መፈጸሚያ ተቋሙ የባንክ ሂሳብ ወጪና ገቢ ያደርጋል።እንዲሁም ለተወከለበት የአባላት ክፍያ ሂሳብ ተመሳሳይ ድርጊት ይፈፀማል።

10.4.5 ክፍያ መፈጸሚያ ባንኩ የአባላትን ሂሣብ ዝርዝር ሁኔታን ለምርት ገበያው ማሳወቅ ይኖርበታል።

10.4.6 የክፍያ መፈጸሚያ ባንኩ አቋምን ስለሚያሳውቅበት ሁኔታ
አባላት ያለባቸውን ገንዘብ የመክፈል ግዴታ ካላቸው የመግዣያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ ለመወጣት የገንዘብ እጥረት ካጋጠመ ክፍያ መፈፀሚያ ባንኩ ስለሁኔታው ለምርት ገበያው የክፍያ መፈጸሚያ ክፍል ስራ አስኪያጅ በጋራ በተስማሙበት የመገናኛ መንገድ ማሳወቅ ይኖርበታል።

10.4.7 ስያሜ ስላገኘ ግንኙነት
እያንዳንዱ ክፍያ መፈፀሚያ ባንክ የምርት ገበያውን የባንክ ሂሣብ ከመክፈትና ክፍያን ከመፈጸም ጋር በተያያዙ ጉዳዮች እንደ አባል አገናኝ የሚያገለግል መሰየም ይኖርበታል።

10.4.8 በተሰየመ ክፍያ መፈፀሚያ ባንክ ውስጥ ስላሉ የምርት ገበያው የክፍያና ግዴታ መፈጸሚያ ሂሣቦች በውል ላይ የተመለከተን ክፍያ ወይም ግዴታ ለመፈጸም የሚደረግ

የገንዘብ ዝውውርን አስመልክቶ ለተወሰኑ አባላት ወይም ደንበኞች በተቃራኒው ካልተደነገገ በቀር፣ ማንኛውም አባል ወይም የአባላትን መብት መሠረት አድርጐ ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው በምርት ገበያው ክፍያና ግዴታ የመፈጸሚያ ሂሣብ ወይም ሌሎች በግዴታ ማስፈሚያ ሥር ባሉ የባንክ ሂሣቦች ውስጥ ያለን ገንዘብ አስመልክቶ መብት ወይም ጥቅም አይኖረውም ወይም እንዳለው አይቆጠርም።

10.4.9 በርካታ የባንክ ሂሳቦች

ተገበያይ አባላት፣ አገናኝ አባላት እና ክፍያ ፈጻሚ ገገር-ብቻ ውስን ተገበያይ አባላት የክፍያ መፈጸሚያ ባንኮች ውስጥ ከአንድ በላይ የመግገርያ ገንዘብ ማስገቢያ እና የሽያች ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሳብ ሊከፍቱ ይችላሉ፡፡

10.4.10 የተለየ የባንክ ሂሳብ እንዲከፈትለት የጠየቀ ደንበኛ የሌሎች ደንበኞች የግብይት ግዴታዎችን ለመክፈል የተከፈተውን የጋራ የባንክ ሂሳብ መጠቀም አይችልም፡፡ የደንበኛ የተለየ የባንክ ሂሳብ የጋራ የባንክ ሂሳብ የግብይት ግዴታዎችን ለመክፈል መጠቀም አይቻልም፡፡

10.4.11 ለራሱ ወይም ለደንበኛው ከአንድ በላይ የባንክ ሂሳብ የከፈተ አባል የግብይት ግዴታዎችን ክፍያ ከመግኘያ ገንዘብ ማስገቢያ (ፔይ ኢን) የባንክ ሂሳብ የሚቀነስበትን ቅደም ተከተል ሊወስን ይችላል፡፡”

10.5 የየዕለት የክፍያ እና ግዴታ አፈፃፀም

10.5.1 ስለ ቅድመ ንግድ የአባላት ተቀማጭ ገንዘብ

10.5.1.1 አባላት ግብይት ከሚያካሂዱበት ቀን በፊት ባለው የመጨረሻ የገበያ ቀን ከቀኑ 9፡30 ድረስ የምርት ገበያ የግገር ገንዘብን በመግገርያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ ገቢ ማድረግ አለባቸው።በተጨማሪም የወጪ ገበያ ቡና ገገር በግብይቱ ቀን ከጥዋቱ 4፡00 ድረስ የግገር ገንዘብን በመግገርያ ገንዘብ ማስገቢ የባንክ ሂሳብ ገቢ ማድረግ አለባቸው።

10.5.1.2 አባላት የንግድ ሥራ እንዲያከናውኑ የሚፈቀድላቸው በመግገርያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሣብ ውስጥ ባላቸው የምርት ገበያ የግዥ ገንዘብ መጠን ብቻ ይሆናል።

10.5.1.3 በመግገርያ ገንዘብ ማስገቢ የባንክ ሂሳብ ውስጥ በቂ ገንዘብ የሌላቸው አባላት ግገር ሊፈጽሙ አይችሉም።

10.5.1.4 ክፍያ ፈጻሚ አገናኝ አባል ክፍያ መፈጸም ለማይችል ገገር-ብቻ ውስን ተገበያይ አባል ክፍያ መፈጸም የሚፈቀድለት በክፍያ መፈጸሚያ የመግገርያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ባለው የምርት ገበያ የግገር ገንዘብ መጠን ብቻ ይሆናል።

10.5.2 የክፍያ ተቋም ከሁሉም ግብይት የሚመነጩ ክፍያዎችን መፈጸም ያለበት ስለመሆኑ

10.5.2.1 የክፍያ መፈጸሚያ ተቋሙ ተዛማጅ ከሆኑ ግብይቶች የሚመነጩ ክፍያዎች ተፈጻሚ ማድረግ ያለበት ሲሆን በክፍያ አፈፃፀም አባሉ ለክፍያ ተቋሙ ባለበት የተጣራ ዕዳ መጠን ብቻ የምርት ገበያውን ምትክነት መቀበል ይኖርበታል።

10.5.2.2 የግዥ ወይም የሽያጭ ትዕዛዝ ተዛማጅ ግብይት የሚሆነው በንግድ ሥርዓት ውስጥ የተያያዘ ሲሆንና ሌሎች ግምት ውስጥ ከሚገቡ ጉዳዮች አንፃር የክፍያ መፈጸሚያ ተቋሙ ትዕዛዙን ዋጋ አልባ ሆኖ ካላገኘው ነው።

10.5.2.3 የክፍያ መፈጸሚያ ተቋም ውሉ ተዛማጅ ሆኖ ካገኘው አባላቱ በማንኛውም ምርት ውል ላይ ላለባቸው የተጣራ የገንዘብ ዕዳ በሙሉ ተቃራኒ ወገን ሆኖ በምትክነት ይገባል።

10.6 ድኅረ ግብይት የክፍያ አፈፃፀም

10.6.1 የአባላት የተጣራ ግዴታ መግለጫ

10.6.1.1 የክፍያ መፈፀሚያ ተቋሙ በአባላት የተፈጸመ ግብይትንና በክፍያ መፈጸሚያ ተቋም የተዛመደን ግብይት መሠረት በማድረግ የክፍያ መፈጸሚያ ክፍል የአባላትን የተጣራ ግዴታ መግለጫ ማዘጋጀትና ከግብይቱ ቀን ቀጥሎ ባለው የገበያ ቀን ከጥዋቱ 1:30 ላይ እያንዳንዱ አባል ስለ መግገርያ ገንዘብ ማስገቢያ እና የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሣቦች አስመልክቶ ያለበትን ግዴታ ለአባላቱ ማሳወቅ አለበት።በአባላት የተጣራ ግዴታ ላይ የተሰጠው መግለጫ በአባላት ላይ አስገዳጅነት አለው።

10.6.1.2 ተገበያይ አባላት፣አገናኝ አባላት ፣ክፍያ ፈጻሚ ገገር-ብቻ ውስን ተገበያይ አባላት እና ሻጭ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባላት በእያንዳንዱ የግብይት ቀን ማግስት በሚገኝ የግብይት ቀን የክፍያ መፈጸሚያ ክፍል የሚሰጠውን የተጣራ የግዴታ መግለጫ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው።

10.6.2 ድህረ ንግድ ክፍያ አፈፃፀም

10.6.2.1 ስለ ገንዘብ ዝውውር

የክፍያ መፈጸሚያ ክፍል ስለ አባላት የመግገርያ ገንዘብ ከአባላት የመግገርያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ ወይም ተፈጻሚ የሚሆን ከሆነ ከአባላት ደንበኛ የመግገርያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ ወይም ከአባላት የክፍያ መፈጸሚያ የመግገርያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ የተጣራ የሽያጭ ክፍያ/ግዴታ ከግብይቱ ቀን ቀጥሎ ባለው የገበያ ቀን ከጥዋቱ 2:00 እስከ 3:00 ድረስ በወጪ ተከፋይ መያዝ አለበት።

10.6.2.2 የምርት ገበያው ከግብይቱ ቀን በኋላ ባለው የግብይት ቀን ከጥዋቱ 5:00 እስከ 6:00 ባለው ጊዜ ውስጥ አባላት ያለባቸውን የተጣራ የሽያጭ ግዴታ/ክፍያን ወደ ተገበያይ አባላት እና አገናኝ አባላት ወይም ተፈጻሚ የሚሆን ከሆነ ወደ አገናኝ አባላት ደንበኞች ወይም ወደ ውስን አገናኝ አባላት ወይም ወደ ሻጭ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባላት የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሳቦች ገቢ ማድረግ አለበት።

10.6.2.3 ክፍያ መፈጸሚያ ተቋም የአባላት የተጣራ የግዴታ መግለጫን መሠረት አድርጎ ከንግዱ ቀን ቀጥሎ ባለው የሥራ ቀን የአባላት ደንበኞች የርክክብ ማስታወቂያን ማዘጋጀትና ለምርት ገበያው ንግድ የሚሆኑ ምረቶችን ለማስረከብ በማከማቻ መጋዘን ጨረታ ላይ ለሚሳተፉ እያንዳንዳቸው አባላት ወይም ደንበኞች መስጠት አለበት። የርክክብ ማስታወቂያው በአባላትና ደንበኞች ላይ አስገዳጅነት አለው።

10.6.3 በክፍያ አፈፃፀም ላይ ስለሚደረጉ ማስተካከያዎች

በአባላት የሚፈፀሙና ተዛማጅ መሆናቸው በክፍያ መፈጸሚያ ተቋም የተለዩ ውሎች በክፍያ አፈፃፀም ሂደት አማካኝነት በየእለቱ በአባላቱ ሳይፈፀሙ በቀሩ ውሎች ወይም ሳይከፈሉ በቀሩ ሌሎች ዕዳዎች ክፍያ አፈፃፀም ይገዛሉ/ ሊገዙ ይችላሉ። እንዲህ ዓይነቱ የማስተካከያ የክፍያ አፈፃፀም የሚከተሉትን ልዩነቶች ያጠቃልላል።

ሀ. የክብደት ልዩነት (የገገርና ሻጭ የገቢ ወጪ ተከፋይ)፣

ለ. የቦታ ልዩነት(የገገር ወጪ ተከፋይ እና የሻጭ ገቢ ተከፋይ)፣

ሐ. የመጋዘን አገልግሎት ክፍያ (የገገር ወጪ ተከፋይ)፣

መ. የመጋዘን ቁጥጥር ክፍያ (የገገር ወጪ ተከፋይ)፣

ሠ. በንኡስ አንቀጽ (ሐ) እና (መ) ከተጠቀሱት ውጭ የሆኑ የመጋዘን አገልግሎት ክፍያዎች ፣

ረ. የምርት ገበያ ግብይት ክፍያ (የገዢ ወጪ ተከፋይ የሻጭ ገቢ ተከፋይ)፣
ሰ. ተፈጻሚ የሆነ ግብር የገቢ እና ወጪ ተከፋይ፣
ሸ. የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ፋይናንስ ክፍያ(የገዢ ወጪ ተከፋይ) እና
ቀ.የእስፖርት መዋጮዎች (ፈቃደኛ የሆኑ ቡና ነጋዴዎች ብቻ ወጪ ተከፋይ)፡፡

10.6.4 ከመግቢያ ገንዘብ ስለማውጣት

10.6.4.1 ተገበያይ አባል ወይም አገናኝ አባል ወይም ክፍያ ፈጻሚ ገዢ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባል የምርት ገበያው ከአባላት ወይም ከደንበኛ የመግቢያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ ወደ አባላት ወይም ደንበኛ ሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሳባቸው ገንዘብ እንዲያዛውርላቸው የማውጫ ቅጽ በመሙላት መጠየቅ ይችላሉ።

10.6.4.2 የምርት ገበያው የክፍያ መፈጸሚያ ክፍል ጥያቄውን በተቀበለ 48 ሰዓታት ውስጥ ገንዘቡን ከአባሉ ወይም ከደንበኛው የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ለማውጣት እንዲቻል ዝግጁ ማድረግ አለበት።

10.6.4.3 ክፍያ መፈጸም የማይችል ገዢ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባል በአገናኝ አባል ክፍያ መፈጸሚያ የመግቢያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ያስገባውን ገንዘብ ማውጣት ከፈለገ፣ ጥያቄው ለምርት ገበያ መቅረብ የሚችለው በአገናኝ አባሉ ብቻ ይሆናል።የምርት ገበያው በ48 ሰዓታት ውስጥ በአገናኝ አባሉ የክፍያ መፈጸሚያ የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ገንዘቡን ማዛወር እና አገናኝ አባሉም ገንዘቡን ክፍያ መፈጸም ለማይችለው ገዥ-ብቻ ውስን ተገበያይ አባል መስጠት አለበት።

10.6.4.4 የአባላት ወይም ከደንበኛ የመግቢያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሳብ ገንዘብ ለማውጣት ለሚቀርቡ ጥያቄዎች የምርት ገበያው ገንዘብ የሚያዛውረው በተመሳሳይ ባንክ ውስጥ በተከፈተ አግባብነት ያለው የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ የባንክ ሂሳብ ብቻ ይሆናል፡፡ የምርት ገበያው ለባንክ በሚያስተላልፈው ትዕዛዝ ውስጥ "የመግቢያ ገንዘብ ማውጣት" የሚል ማካተት አለበት፡፡

10.6.5 በክፍያ መፈጸሚያ ክፍል የተሰበሰቡ የተለያዩ ክፍያዎችን ሪፖርት ስለማድረግ እና ስለማስተላለፍ፡፡

የምርት ገበያው የክፍያ መፈጸሚያ የባንክ ሂሳብ ከክፍያ መፈጸሚያ ክፍል የሂሳብ መዝገብ ጋር በየወሩ መጨረሻ እንዲታረቅ መደረግ አለበት፡፡ በዚሁ መሰረት የሚከተሉት አይነት ሪፖርቶች እና ዝውውሮች በክፍያ መፈጸሚያ ክፍል መከናወን አለባቸው፡፡

ሀ. ሻጭ ከገዢ የሚሰበስበው የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የተርን ኦቨር ታክስ በሻጭ የተጣራ ግዴታ ውስጥ መካተት አለበት፣

ለ. የምርት ገበያው የክፍያ መፈጸሚያ ክፍል ከምርት ገበያው የክፍያ መፈጸሚያ የባንክ ሂሳብ የሰበሰበውን የቅድሚያ ገቢ ግብር ወደ ምርት ገበያው ኮርፖሬት የባንክ ሂሳብ በየወሩ ማዛወር አለበት፣

ሐ. የክፍያ መፈጸሚያ ክፍል ከምርት ገበያው የክፍያ መፈጸሚያ የባንክ ሂሳብ የሰበሰበውን የግብይት ክፍያ፣ የመጋዘን ቁጥጥር ክፍያ፣ የመጋዘን አገልግሎት ክፍያ፣ ሌሎች የመጋዘን ክፍያዎች፣ በምርት ገበያው ክፍያዎች ላይ የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የእስፖርት መዋጮዎች በሙሉ ወደ ምርት ገበያው ኮርፖሬት የባንክ ሂሳብ በየወሩ ማስገባት አለበት እና

መ. የክፍያ መፈጸሚያ ክፍል "ከወጪ ገበያ ቡና ላይ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ" እና አጠቃላይ "የቅድሚያ ገቢ ግብር" አግባብነት ያለው ዳታ የኤሌክትሮኒክ ቅጂ ለምርት ገበያው የፋይናንስ መምሪያ በየወሩ ማቅረብ አለበት፡፡ የፋይናንስ መምሪያ የዳታውን ቅጂ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

10.6.6 በክፍያ መፈጸሚያ ክፍል የሚፈጸም ድህረ ክፍያ አፈጻጸም ማስተካከያዎች

በአባላት ተፈርመው በክፍያ መፈጸሚያ ክፍል የተዛመዱ እና ክፍያ የተፈጸመባቸው ውሎች በሚከተሉት ምክንያቶች ድህረ ክፍያ አፈጻጸም ማስተካከያ ይደረግባቸዋል፡፡

i. ከአፈጻጸም ዋስትና ጋር ለተያያዙ አቤቱታዎች/የመብት ጥያቄዎች፣
ii. ከተገቢው መጠን በላይ በማሳለፍ የሚደረግ ርክክብ፣ ወይም
iii. የክፍያ ስህተቶችን ጨምሮ ለሌሎች በክፍያ አፈጻጸም ላይ የሚደረጉ ማስተካከያዎች፤

የክፍያ መፈጸሚያ ክፍል ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች እንዳስፈላጊነቱ የገቢ እና/ወይም ወጪ ተከፋይ ገንዘብ ማስታወሻ በማዘጋጀት የድህረ ክፍያ አፈጻጸም ማስተካከያ በአስር የስራ ቀናት ውስጥ ማድረግ አለበት፡፡

10.7 ስለዘገባዎች

ሀ. የምርት ገበያው በአባላቱ የተከናወኑ የንግድ ተግባራትን አስመልክቶ የተጣራ የግዴታ አፈፃፀም ሪፖርት ተዛማጅ የሆነ የርክክብ ማስታወቂያ ሪፖርትን ጨምሮ ዕለታዊ ሪፖርት ለአባላቱ መላክ አለበት። ሪፖርቶቹ በምርት ገበያው አባላት ላይ አስገዳጅነት ይኖራቸዋል።
ለ. የምርት ገበያው አባላት ምርት ገበያው በጊዜው ከአባላቱ የሚፈልጋቸውን ሪፖርቶች ለምርት ገበያው መሰጠት አለባቸው።
ሐ. ባለሥልጣኑ በሚደነግገው መሠረት የምርት ገበያው አባላት እነዚህን ሪፖርቶች ይሰጣሉ/ ያቀርባሉ።
መ. የአባሉን የፋይናንስ ጥንካሬ የሚጎዳ ውስጥ የሚጥል ወይም ለምርት ገበያው መልካም ጥቅም አባሉ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያለው ነገር በሚፈጠር ጊዜ አባሉ ለምርት ገበያው ማሳወቅ አለበት።
ሠ. ተወካዮቻቸውን ጨምሮ ሁሉም የምርት ገበያው አባላት የሂሣብ መዛግብትን፣ መዝገቦችን፣ መግለጫዎችንና ሌሎች ሪኮርዶችን በህትመት ወይም በኤሌክትሮኒክ መንገድ መያዝ አለባቸው። እነዚህ ሰነዶችና ሪኰርዶች ቢያንስ ለአስር ዓመታት ያህል በመልካም አያያዝ ተጠብቀው መቆየት አለባቸው። እነዚህ ሰነዶችና ሪኰርዶች በሙሉ ለምርመራ በተፈለጉ ጊዜ ለምርት ገበያው መሰጠት አለባቸው።
ረ. እያንዳንዱ የምርት ገበያ አባል ኦዲት ለመደረግና ለመመርመር ዝግጁ መሆን አለበት፤ በምርት ገበያው ውሣኔ መሠረት ሁሉንም የሂሣብ መዛግብት፣ ሰነዶች፣ ሪኮርዶች፣ ፋይሎችና ሌሎች መረጃዎች ሲፈለጉ መስጠት ይኖርበታል። የኦዲትና የምርመራ ሥራዎች የምርት ገበያው አባል ለደንበኛው ምርት ግብይት አቅራቢነቱ፣ ከፋይነቱ፣ የክፍያ አገልግሎት ሰጪነቱ በራሱ በቀጥታና በሌላ አባል አማካኝነት ምርት ግብይት እንቅስቃሴው ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ መወሰን አለባቸው።
ሰ. የምርት ግብይቱን ወይም ትዕዛዙን አስመልክቶ ወይም በእነሱ መነሻነት አለመግባባት ወይም የሃሳብ ልዩነት በአባሉ ሪፖርት እና በምርት ገበያው ሪፖርት መካከል ከተፈጠረ በምርት ገበያው ሪኰርድ ያለው ሪፖርት የመጨረሻ ሆኖ በአባላት ላይ ገዢና ተፈፃሚ ይሆናል።

## 10.8 ክፍያ ሳይፈፀም ስለመቅረት

10.8.1 አንድ አባል ከምርት ግብይቱ ቀን በኋላ ባለው የገበያ ቀን ከጥዋቱ 3፡00 ድረስ ለምርት ገበያው ተከፋይ የሚሆን ግዴታውን ካልተወጣ የሚከተሉት ተግባራዊ ይሆናሉ።

ሀ. የአባሉ የመገበያየት መብቶች ወዲያውኑ ይታገዳሉ፣

ለ. በምርት ግብይቱ ቀን ወደ ተገዡ የማከማቻ መጋዘን ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኞች የባለቤትነት መብቶችን ማስተላለፍ እና የተያያዥ ምርቶች ርክክብ ይታገዳሉ፣

ሐ. ክፍያ መፈጸሚያ ባንኩ ለምርት ገበያው በሰጠው የመረጃ ስህተት ምክንያት ኃላፊ ከሆነ፣የሚፈጠሩ የገንዘብ እጥረቶችን ከግብይቱ ቀን በኋላ ባለው የገበያ ቀን ከጥዋቱ 4፡30 ድረስ ያስተካክላል። በዚህን ጊዜ አባሉ በባንኩ በተፈጠረው ስህተት ተባባሪ እንዳልሆነ የምርት ገበያው የህግ ማስከበሪያ መምሪያ ካመነ የአባሉ የግብይት መብቶች እና የመብት መተላለፎች ተፈፃሚነት እንዲቀጥል ይደረጋል፣

መ. ከላይ በንኡስ አንቀጽ 10.8.1(ሐ) የተመለከተው ተፈፃሚ የማይሆን ከሆነ፣ የክፍያ መፈጸሚያ ክፍሉ አባሉ ግብይቱ ከተካሄደበት ቀን ቀጥሎ ባለው የገበያ ቀን ከጥዋቱ 3፡00 ድረስ በራሱ አግባብነት ያለው የመግዢያ ገንዘብ ማስገቢያ የባንክ ሂሣብ የጐደለውን ገንዘብ እንዲያስገባ ሊጠይቀው ይችላል። አባሉ ይህን የሚፈፅም ከሆነና የምርት ገበያው የህግ ማስከበሪያ መምሪያ ከተፈቀደው መጠን በላይ በተፈጸመው ግብይት ላይ ተባባሪ አለመሆኑን ከተረዳ የመገብየት መብቱና የመብት ማስተላለፍ መብቱ እንደገና ተፈፃሚነት ያገኛል፣

ሠ. ንዑስ አንቀጽ 10.8.1 /መ/ ከተሟላ፣ የክፍያ መፈጸሚያ ክፍሉ የክፍያ መፈጸሚያ ባንኩን ከመግዢያ ገንዘብ ማስቀመጫ የባንክ ሂሣብ ከአባሉ የሚፈለገውን ክፍያ ወደ ክፍያ መፈጸሚያ ክፍሉ ሂሣብ እንዲያስተላለፍ ያዘዋል። ያልተከፈለ ቀሪ/ካለ/፣ በንዑስ አንቀጽ 10.8.1 /ረ/ ቀጥሎ በተመለከተው ሁኔታ ለጉድለቱ የማካካሻ ክፍያ ይሆናል፣

ረ. አባሉ በምርት ገበያው ውሣኔ የተጣለበትን የክፍያ ዕዳ በሙሉ ከነ መቀጫው በአሥር የሥራ ቀናት ውስጥ ካልከፈለ ምርት ገበያው የሚከተሉትን እርምጃዎች ይወስዳል።

i. የአባሉን የምርት ግብይት መብት ማቋረጥ፣

ii. የአባሉ የማከማቻ መጋዘን የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ሂሣብን በማጣራት ገንዘቡን ወጪ ለተደረገ የክፍያና ርክክብ መፈፀሚያ ዋስትና ፈንድ እንዲከፈል ማድረግ፣

iii. የምርት ገበያው የአባሉን የማከማቻ መጋዘን የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ከአባሉ የመጀመሪያ ዋጋ በላይ ካጣራው የምርት ገበያው ትርፍ ገንዘቦችን ወደ ክፍያ ዋስትና ገንዘብ ያስገባቸዋል።

iv. የምርት ገበያው የአባሉን የማከማቻ መጋዘን የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ከአባሉ የመጀመሪያ ዋጋ ባነሰ ካጣራው ምርት ገበያው የሚከተሉትን ይፈፅማል።

ሀ. የአባሉን የዋስትና ተቀማጭ ገንዘብ ከክፍያና ርክክብ ዋስትና ፈንድ መጠቀም፣

ለ. የአባሉን መቀመጫ ለጨረታ /ሐራጅ ማቅረብ እና

ሐ. የጐደለውን ገንዘብ ለማስመለስ /ለመተካት በፍርድ ቤት ክስ መመስረት።

ሰ. አንድ አባል ክፍያ ባለመፈፀም ከታገደ የምርት ገበያው የህግ ማስከበሪያ መምሪያ ምርመራውን እስከሚያጠናቅቅ ድረስ የአባሉ የግብይት መብት ታግዶ ይቆያል። አባሉ የማጭበርበር ተግባር የፈፀመ አለመሆኑ በህግ ማስከበሪያ መምሪያ

ከተረጋገጠ በግብይት መብቶቹ መጠቀሙን የሚቀጥል ሲሆን ከዚህ ውጭ ከሆነ ግን የግብይት መብቶቹና አባልነቱ ይቋረጣል።

10.8.2 የሽያጭ ገንዘብ መቀበያ ሂደት ከግብይት ቀን በኋላ ባለው የገበያ ቀን ከጥዋቱ 5፡00 የሚጀመር በመሆኑ ክፍያን አለመፈጸም ዋስትና በተሰጠው የአባላት የመክፈል ግዴታ ላይ ውጤት አይኖረውም።

## 11. ርክክብ

11.1 በመጋዘን የተቀመጡ ምርቶች ርክክብ

11.1.1 በመጋዘን ዉስጥ የተከማቹ ምርቶችን ገዢው ወይም ወኪሉ በአካል እንዳለ ለመወሰድ ሲፈልግ፣ በማዕከላዊ ማከማቻ የተሰጠውን የርክክብ ማስታወሻ በማቅረብ በምርት ገበያ የተገበየውን ምርት ለመረከብ ጥያቄ ያቀርባል። በዚህን ጊዜ ግብይቱ በተደረገ በአሥር ቀናት ውስጥ ምርቱን ያነሣል።

11.1.2 በምርት ገበያው የሚዘጋጀው የእቃ ማንሻ ማስታወሻ የማንሻውን ቀን፣ ጊዜ፣ የተወካይ ስም፣ የስልክ ቁጥር፣ የመታወቂያ ቁጥርና አይነት፣ የሹፌር ስም፣ መንጃ ፈቃድ እና የተሽከርካሪ ታርጋ ቁጥር ማመልከት አለበት። የእቃ ማንሻ ማስታወሻው በአባሉ ወይም በተወካዩ ተፈርሞ ለማእከላዊ ማከማቻ መቅረብ አለበት።በእቃ ማንሻ ማስታወሻው ላይ የተጠቀሰው ሰው ምርቱን ማንሳት ካልቻለ አባሉ ሹፌሩን የሚመለከተውን መረጃ እና የተሽከርካሪውን የታርጋ ቁጥር በማእከላዊ ማከማቻ ደስክ የርክክብ ማስታወሻ በማስተካከል ለመቀየር ይችላል። ምርቱ ከማከማቻ መጋዘን በሚነሳበት ወቅት ገዢው ወይም ወኪሉ ወቅታዊና አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ይዞ መገኘት አለበት።

11.1.3 ማእከላዊ ማከማቻው የማንሻ ማስታወሻውን በኤሌትሮኒክስ መንገድ ለሚመለከተው መጋዘን ይልካል/ያስተላልፋል።

11.1.4 ማንኛውም አባል የተለየ ሁኔታ አጋጥሞ ከምርት ገበያ የገዛው ምርት በተወሰነ የምርት ገበያው መጋዘን ውስጥ ባለመኖሩ ምክንያት መረከብ ካልቻለ በተመሳሳይ የርክክብ ማዕከል ክልል ውስጥ ካለ መጋዘን ወይም ከሌላ የርክክብ ማዕከል ተመሳሳይ ምርት እንዲረከብ ማዕከላዊ ማከማቻ የርክክብ ማስታወሻውን ሊቀይርለት ይችላል። የተቀየረው የማከማቻ መጋዘን ከርክክብ ማዕከሉ ክልል ውጭ ያለ የማከማቻ መጋዘን የሆነ እንደሆነ በርክክብ ቦታው ለውጥ ምክንያት የደረሰውን ወጪ የምርት ገበያው ይሸፍናል።

11.1.5 የመለያ ሰነዶችን ትክክለኛነት ካረጋገጠ እና የማንሻ ማስታወሻዎችን ከተቀበለ/ከተረከበ በኋላ የማከማቻ መጋዘኑ ሥራ አስኪያጅ ምርቶቹን ለገዢው ወይም ለወኪሉ ያስረክባል። በተጨማሪም የማከማቻ መጋዘኑ ሥራ አስኪያጅ በገዢ ወይም በወኪሉ የቀረበውን የርክክብ ማስታወሻ ቅጂ ትክክለኛነት መመርመር አለበት።

11.1.6 በምርት ርክክቡ ጊዜ ለሚፈጠሩ መዘግየቶች የመጋዘኑ ኃላፊ ተጠያቂ ከመሆኑም ባሻገር በምርት ገበያው የዲስኘሊን እርምጃዎች ሊወሰድበት ይችላል።

## 11.2 የዕቃዎች መረከቢያ ማስታወሻ

11.2.1 መጋዘኑ የየዕለቱን የምርት ግብይት ውሎ በተለይም የምርት ግብይቱ ከመጀመሩ በፊት የነበረውን የእያንዳንዱን አባል የምርት አይነትና መጠን በቀኑ ውስጥ የገዛውና፣ የሸጠው ምርት አይነትና መጠን እንዲሁም እያንዳንዱ አባል በግብይት መጨረሻ የሚኖረውን ምርት አይነትና መጠን (balance) የሚያሳይ መረጃ ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት ማስተላለፍ አለበት።

11.2.2 የመጋዘኑ ሥራ አስኪያጅ በገዢው ወይም በወኪሉ የቀረበለትን የርክክብ ማስታወሻ ወይም የማንሻ ማስታወሻ ከተቀበለና መርምሮ ካረጋገጠ በኂላ ምርቱን ያስረክባል። ስራ አስኪያጁ ምርቱን ካስረከበ በኂላ ገዢውን ወይም ወኪሉን አስፈርሞበት የዕቃዎች መረከቢያ ማስታወሻ ይሰጠዋል።

11.2.3 በከፊል ለሚደረግ እያንዳንዱ የእቃ/ምርት ማንሳት ይህንኑ የሚያመለክት የእቃዎች መረከቢያ ቮውቸር ይሰጣል።ለገዢ ወይም ለወኪሉ የተሟላ የእቃዎች መረከቢያ ማስታወሻ የሚሰጠው ሙሉ ለሙሉ ርክክቡ ሲፈጸም ብቻ ነው።ግብይት በተደረገበት ውል የማስረከቢያ ጊዜ ውስጥ ምርቱ ሙሉ ለሙሉ መነሳት አለበት።

11.2.4 ማከማቻ መጋዘኑ ኤሌክትሮኒክስ የዕቃዎች መረከቢያ ማስታወሻ ማዘጋጀትና ታትመው የተፈረሙ ቅጂዎችን ለገዥው ወይም ለወኪሉ መስጠት አለበት።

11.2.5 ማከማቻ መጋዘኑ የዕቃዎች መረከቢያ ማስታወሻውን ለማዕከላዊ ማከማቻ በኤሌክትሮኒክስ ማስተላለፍ አለበት።

## 11.3 ዘግይቶ በመረከብ ወይም ጭራሽ አለመረከብ ሳቢያ የሚከሰቱ ቅጣቶች

11.3.1 ገዢው ወይም ሕጋዊ ተወካዩ በውሉ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የገዛውን ምርት ካልወሰደ ማእከላዊ ማከማቻ ዘግይቶ የመረከብ ቅጣት ያስከፍላል። ቅጣቱ ተፈጻሚ የሚሆነው ሳይነሳ በቀረው ከፊል ምርት ላይ ብቻ መሆን ይኖርበታል።

11.3.2 ዘግይቶ የመረከብ ቅጣት በየቀኑ የሚታሰብ ይሆናል።

11.3.3 ዘግይቶ የመረከብ ቅጣቱ በማከማቻ መጋዘኑ ደረሰኝ የተጠቀሰውን የምርት መቀበያ ቀነ ገደብ ጊዜ እስኪያበቃ ድረስ ይቀጥላል።

11.3.4 የማከማቻ ደረሰኙ የተጠቀሰውን የምርት ርክክብ ቀነ ገደብ ጊዜ አብቅቶ የተከማቹት ምርቶች ካልተወሰዱ፣ ማከማቻ መጋዘኑ የተከማቸውን ምርት እንደገና ደረጃ የማውጣትና ዘግይቶ የመረከብ ክፍያዎችን መሰብሰብ አለበት።

11.3.5 ዘግይቶ የመረከብ ቅጣቱ ተጠራቅሞ ከተከማቸው የምርት ዋጋ በላይ ከሆነ ማከማቻ መጋዘኑ የተከማቸዉን ምርት ይሸጠዋል።

11.3.6 ማከማቻ መጋዘኑ የመረከቢያ ጊዜውእንዳለቀና የተከማቸዉን ምርት ከመሸጡ ሁለት ቀናት አስቀድሞ ሁለት ማስጠንቀቂያዎችን በጽሁፍ ለገዢው ይሰጠዋል።እነዚህም ማስጠንቀቂያዎች የሚሰጡት አንደኛዉ ማርፈድ እንደተጀመረ ሲሆን ሌላኛዉ ደግሞ ክምችቱ ከመሸጡ ሁለት ቀናት ቀድሞ ይሆናል።

11.3.7 ገዥው ወይም ወኪሉ ዘግይቶ መረከብ የሚችለው በማዕከላዊ ማከማቻው አሠራር ሥርዓት መሠረት የተጠራቀመውን የቅጣት ክፍያ በኤሌክትሮኒክስ ለማዕከላዊ ማከማቻው ከከፈለ በኂላ ብቻ ይሆናል።

## 12. የክፍያና ርክክብ መፈጸሚያ ዋስትና ፈንድ

12.1 የምርት ገበያው የክፍያና ርክክብ መፈጸሚያ ዋስትና ፈንድ ማቋቋም ያለበት ስለመሆኑ

12.1.1 ምርት ገበያው የክፍያና ርክክብ መፈጸሚያ ዋስትና ፈንድ ማቋቋም ይኖርበታል፡፡

12.1.2 የዳይሬክተሮች ቦርዱ የክፍያና ርክክብ መፈጸሚያ ዋስትና ፈንድ የሚተዳደርበትን ሥርዓት በተለይ እያንዳንዱ አባል የዋስትና ፈንዱ የሚያስቀምጠው ገንዘብ ወይም የሚያደርገው መዋጮ መጠን፣የሚቀመጠው ገንዘብ ወይም የሚደረገው መዋጮ የሚደረግበትን ስርዓት፣ሁኔታ፣ አኳኃንና ዓይነት፣ በፈንዱ የተቀመጠው ገንዘብ የሚመለስበትና መዋጮው የሚቀርበትን ሁኔታ፣ ለአገልግሎት የሚከፈለውን ክፍያ፣ በአግባቡ ባለመፈጸም የሚከሰቱ ቅጣቶችንና የዲሲፕሊን እርምጃዎችን የሚያካትቱ መስፈርቶች፣ ሥነ-ሥርዓት እና ሁኔታዎች በየጊዜው ሊወሰን ይችላል፡፡

12.2 ለክፍያና ርክክብ መፈጸሚያ ዋስትና መዋጮ ማድረግና ማጠራቀም

12.2.1 እያንዳንዱ አባል የዳይሬክተሮች ቦርድ በየጊዜው በሚወሰነው መሠረት መዋጮ ማድረግና ዝቅተኛውን ከወለድ ነጻ የሆነ ተቀማጭ ለክፍያና ርክክብ መፈጸሚያ ዋስትና ፈንዱ ማቅረብ ይጠበቅበታል። የክፍያና ርክክብ መፈጸሚያ ዋስትና ፈንዱ በምርት ገበያው መያዝ አለበት። በክፍያና ርክክብ መፈጸሚያ ዋስትና ፈንዱ ውስጥ ያለው ገንዘብ በነዚህ ደንቦች ፣ማስታወቂያዎች እንዲሁም በዚሁ መሠረት በየጊዜው በሚወጡ ትዕዛዞች መሠረት ጥቅም ላይ መዋል አለበት።

12.2.2 መንግስት ለክፍያና ርክክብ መፈጸሚያ ዋስትና ፈንዱ መዋጮ ማድረግ ይችላል።

12.2.3 የዳይሬክተሮች ቦርድ እያንዳንዱ አባል እና ወይም የአባላት መደቦች በተጨማሪ ሊያዋጣ (ጡት) የሚገባውን መዋጮ መወሰን ይችላል።

12.2.4 ምርት ገበያው አግባብ ባላቸው ደንቦች በየጊዜው በሚደነገገው መሠረት የግብይት ክፍያዎችን ለመፈጸም በተከተለው ተያዥነት ህጋዊ አቻ ሆኖ እስከ ተንቀሳቀሰበት መጠን ድረስ የፋይናንስ ክፍያ ዋስትና መሰጠት አለበት።

12.2.5 አባላት ያስቀመጡት የደህንነት ተቀማጭ መጠን የዳይሬክተሮች ቦርድ በየጊዜው በሚያወጣቸው መስፈርቶች መሠረት ተመላሽ ይደረጋል። ። በአባል የተቀመጠ ወይም የተከፈለ ገንዘብ ተመላሽ የሚደረገው ገንዘቡ ትርፍ ከሆነ እና አባሉ መክፈል ያለበት በማንኛውም የክፍያ መፈጸሚያ ባንክ ተጨባጭ ወይም ሊከሰት የሚችል ሃላፊነት ወይም የይገባናል ጥያቄ ከሌለ ነው።

12.3 የመዋጮ ወይም ተቀማጭ ዓይነት

የዳይሬክተሮች ቦርድ በየጊዜው የሚወስናቸው ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ በራሱ ውሳኔ አባላት ለክፍያና ርክክብ መፈጸሚያ ዋስትና ፈንድ የሚያዋጡት መዋጮ ወይም የሚሰጡት ተቀማጭ በጥሬ ገንዘብ ወይም በሌላ ዓይነት ወይም ዘዴ እንዲሆን ሊፈቀድ ይችላል።

12.4 የክፍያና ርክክብ መፈፀሚያ ዋስትና ፈንዱን ኢንቬስት ማድረግ

የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚወስነው መሠረት በክፍያና ርክክብ መፈፀሚያ ፈንዱ ውስጥ ያሉ ገንዘቦች ወለድ ባለው የምርት ገቢያው የባንክ ሂሳብ ውስጥ ማስቀመጥ ወይም ኢንቬስት ማድረግ ይቻላል። ፈንዱን ኢንቬስት በማድረግ የተገኘ ወለድ እንደገና ፈንዱ ውስጥ መግባት አለበት።

12.5 የክፍያና ርክክብ መፈፀሚያ ዋስትና ፈንዱን ማስተዳደርና መጠቀም

12.5.1 የክፍያና ርክክብ መፈፀሚያ ዋስትና ፈንዱ በነዚህ ድንጋጌዎችና የዳይሬክተሮች ቦርዱ በየጊዜው በሚያወጣቸው መስፈርቶች መሠረት ግልጋሎት ላይ የሚውል ሲሆን ይህም፡-

12.5.1.1 የክፍያና ርክክብ መፈፀሚያ ዋስትና ፈንዱን ለማቋቋምና ለማስተዳደር የወጡ ወጪዎችን መሸፈን፣

12.5.1.2 በምርት ገበያው ድንጋጌዎች በሚቀመጠው መሠረት የአባልነት የክፍያና ርክክብ ግዴታዎችንና ጉድለቶችን ለማሟላት ፈንዱን በጊዜያዊነት መጠቀምን፣

12.5.1.3 በምርት ገበያው ድንጋጌዎች ሊቀመጥ በሚችለው መሠረት ከግብይት ክፍያና ርክክብ አካሄዶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ የምርት ገበያውን ማንኛውም እዳዎችንና ኪሳራዎችን ለመሸፈን፣

12.5.1.4 አባሉ አባልነቱን ሲያቋርጥ በምርት ገበያው ድንጋጌዎች መሠረት ያሉትን ሁሉንም እዳዎች ከከፈለ በኋላ ቀሪውን ለአባሉ ለመመለስ፣ እና

12.5.1.5 በዳይሬክተሮች ቦርድ በየጊዜው ሊወሰን በሚችለው መሠረት ማንኛውም ሌሎች ወጪዎች ለመሸፈን ሊውል ይችላል።

12.5.2 ምርት ገበያው በክፍያና ርክክብ መፈፀምያ ዋስትና ፈንድ የተቀመጠው ገንዘብ የማስያዝ፣ መያዣውን የማደስ፣ ወለድ አግድ የመግባት፣ የማስተላለፍ፣ ዋስትና የመፍጠር፣ ክፍያና ርክክብ መፈፀሚያ ዋስትና ፈንዱ ውስጥ ያለውን ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለሌላ ሰው ማስተላለፍ፣ ወይም በአባል ፈንታ ለምርት ገበያው የተላለፈን ማንኛውም ሰነድ ወደ ክፍያና ርክክብ መፈፀሚያ ዋስትና ፈንዱ የማዛወር ሙሉ ስልጣን አለው።

12.6 የክፍያ ግዴታዎችን ባለመወጣት ወቅት ወይም ግዴታዉን ያልፈጸመ ወገን ሲያሳዉቅ ስለሚኖር አጠቃቀም

12.6.1 በምርት ገበያው ድንጋጌዎች ሊደነገግ በሚችለው መሠረት አንድ አባል ከግብይት በሚመነጩ በምርት ገበያው የሚፈፀሙ ክፍያዎችንና ርክክቦችን መወጣት ሲያቅተው ወይም አንድ አባል ግዴታውን ያልተወጣ መሆኑ ሲገለፅ የምርት ገበያው የክፍያ ክፍል አስቀድሞ በቦርዱ በሚፀድቅ የአባሉን የክፍያ ርክክብ መፈፀሚያ ዋስትና ፈንድና ሌሎች ገንዘቦች እንዳስፈላጊነቱ ግዴታውን ለማሟላት በሚከተለው ቅደምተከተል መሠረት መጠቀም ይቻላል፡-

12.6.1.1 ግዴታውን ያልተወጣው አባል የከፈለው ማንኛውም የቅድመ ግብይት ተቀማጭ /የደንበኛ ቅድመ ግብይት ተቀማጭን ሳይጨምር/ መጠን ወይም የክፍያና ርክክብ ግዴታን ለመወጣት የተቀመጠ ወይም በምርት ገበያው የተያዘ ገንዘብ፣

12.6.1.2 ግዴታውን ባልተወጣው አባል እንደተጨማሪ ተቀማጭ በምርት ገበያው ዘንድ የቀመጠ ማናቸውም ገንዘብ፣

12.6.1.3 የአባሉን የአባልነት መብት በሐራጅ በማቅረብ በመሸጥ የሚገኝ ትርፍ ካለ እንደአስፈለጊነቱ ከሐራጁ ወይም ከሽያጩ ጋር የተያያዙ ወጪዎችን በመቀነስ፣

12.6.1.4 በምርት ገበያው ወይም በክፍያ ክፍሉ ሊሰጥ በሚችለው መሠረት የክፍያና ርክክብ መፈፀሚያ ዋስትና ፈንዱን ኢንቨስት በማድረግ ወይም በመሸጥ የሚገኙ ወይም የቅጣት ክፍያዎች፣ ወለድ ወይም ሌላ ገቢ ካለ፣

12.6.1.5 በክፍያና ርክክብ መፈፀሚያ ዋስትና ፈንዱ ውስጥ ባላቸው ተቀማጭ ተመጣጣኝነት ሁሉም የአባል ክፍሎች ያስቀመጡት መጠባበቂያ። የዳይሬክተሮች ቦርዱ አስፈላጊ ነው ብሎ በሚያምነው ጊዜ ውስጥ አባላት የጐደለውን መጠን በክፍያና ርክክብ መፈፀሚያ ዋስትና ፈንዱ ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል።

12.6.1.6 የክፍያና ርክክብ መፈፀሚያ ዋስትና ፈንዱን ኢንቨስት በማድረግ የሚገኝ ትርፍ ካለ እና

12.6.1.7 በመንግስት ለክፍያና ርክክብ መፈፀሚያ ፈንዱ የተደረጉ መዋጮዎች።

12.6.2 የዳይሬክተሮች ቦርዱ በተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ በማፀደቅ የክፍያና ርክክብ መፈፀሚያ ዋስትና ፈንዱን የአጠቃቀም ቅደም ተከተል በጊዜው በራሱ ፈቃድ ሊለውጥ ይችላል።

12.7 ተጨማሪ መዋጮ ወይም ተቀማጭ የማድረግ ግዴታ

12.7.1 በአንቀፅ 12.6.1.5 ውስጥ በተጠቀሰው መሠረት አንድ አባል በእርግጥ ካዋጣው ወይም ካስቀመጠው ተቀማጭ ላይ እንደየመጠኑ ተመጣጣኝ ክፍያ ከተጣለና በውጤቱም አባሉ በክፍያና ርክክብ መፈፀሚያ ዋስትና ፈንዱ ውስጥ የሚቀረው መዋጮ ወይም ተቀማጭ ከሚፈለገው መዋጮ ወይም ተቀማጭ በታች ሆኖ ከተገኘ አባሉ በዳይሬክተሮች ቦርዱ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በፈንዱ ውስጥ የጐደለውን መዋጮ ወይም ተቀማጭ ማሟላት አለበት።

12.7.2 በምርት ገበያው ድንጋጌዎች በተደነገገው መሠረት መዋጮ ወይም ተቀማጭ እንዲያደረግ የሚጠበቅበት አባል ይህን ሳይፈፅም ቢቀር፣ የዳይሬክተሮች ቦርዱ በየጊዜው በሚወሰነው መሠረት ሊከፈል በሚገባው ገንዘብ ላይ ወለድ መጣል እና የገንዘብ ቅጣትን ጨምሮ ተገቢውን የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወስድ ይችላል። አባሉ ከላይ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች መሠረት በዳይሬክተሮች ቦርድ የዲሲፕሊን እርምጃ የተወሰደበት መሆኑ ወይም አባሉ በማንኛውም ምክንያት የምርት ገበያው አባልነቱ መቅረቱ ለክፍያ መፈፀሚያ ክፍሉ ወይም ለምርት ገበያው አባሉ ያለበትን ግዴታ ወይም በምርት ገበያው ደንቦችና ተፈፃሚ በሚሆኑ ህግጋት መሠረት አባሉ ለክፍያ መፈፀሚያ ክፍሉ ወይም ለምርት ገበያው የሚኖርበትን ማንኛውም ግዴታ አያስቀረውም።

## 13. የገበያ መረጃ ስርጭት

13.1 የገበያ መረጃ

13.1.1 ምርት ገበያው በእያንዳንዱ የንግድ ቀን የሚከተሉትን መረጃዎች መመዝገብ አለበት፡-

13.1.1.1 የግብይት መጠን፡- ጠቅላላ የግብይት መጠንና ለእያንዳንዱ ውል እና የምርት ክፍል የተደረገ ጠቅላላ ግብይት መጠን፣

13.1.1.2 የምርት ዋጋዎች ፡- በያንዳንዱ የምርት ግብይት ክፍለ ጊዜ ውስጥ የተደረጉ የመክፈቻ፣ዝቅተኛ፣ከፍተኛ፣እና የመዝጊያ ዋጋ ዓበይቶችን በትክክለኛው ጊዜ እና

13.1.1.3 ማናቸውንም ሌላ አግባብነት አላቸው ብሎ የሚያምናቸውን ነገሮች ።

13.1.2 የምርት ገበያው በየንግድ ቀኑ በገበያው የተከናወኑ ግብይቶችን፣ በመክፈቻውና በመዝጊያው የቀረቡ የጨረታ ወይም የሽያጭ ዋጋዎችን የሚያካትቱ ትዕዛዞችን፣ በምርት ገበያው የተዘገቡ ከፍተኛና ዝቅተኛ ዋጋዎች፣ የግብይት መጠን መረጃዎችን ያትማል፡-

13.1.2.1 በግብይት ወለሉ ላይ በሚገኝ ሰሌዳ ላይ ግብይቱ እየተፈፀመ እያለ አባላት እንዲያቁት

13.1.2.2 መረጃው ከተወሰደበት የንግድ ቀን ከአንድ ቀን በላይ ሳይዘገይ የዜና ሚዲያዎችና ሕዝቡ እንዲያውቀው እና

13.1.2.3 የምርት ገበያው ወደፊት የሚደረግን ግብይት ዋጋና መጠን የሚተነብይ መረጃ ማውጣት የለበትም።

13.2 የገበያ መረጃ ስርጭት ስርዓት በተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ ስለማፅደቅ

የምርት ገበያው የገበያ መረጃ ስርጭት ስርዓት ከማቋቋሙ በፊት ስለ መረጃው፣ ቅርፁና የስርጭት ሥነ-ሥርዓት ከተቆጣጣሪ ባለስልጣን ፈቃድ ማግኘት አለበት።

13.3 የኃላፊነት ማስወገጃ ማስታወሻዎች

የተጠቀሱትን የገበያ መረጃዎች የሚጠቀም ማንኛውም አባል ወይም ሰው የገበያ መረጃ ሲያገኝና ሲጠቀም የምርት ገበያውን፣ የዳይሬክተሮች ቦርዱ አባላትን፣ የምርት ገበያው የስራ ኃላፊዎችን፣ ሠራተኞችን፣ ህጋዊ ወኪሎችንና ተቋራጩችን የኃላፊነት ማስወገጃ ማስታወሻዎች ይቀበላል፤ ይስማማል።

## 14. የአባል የሥራ አካሄድ ደንብ

14.1 ከቢሮ ጋር የተያያዙ የሥነ ሥርዓት ደንቦች፤

14.1.1 ለምርት ገበያው ሙሉ አድራሻው እንዲሁም በቢሮው ሊከናወን የተፈለገው ሥራ ዝርዝር እና የታቀደው ሥራ በማን ክትትልና ቁጥጥር እንደሚካሄድ የሚያመለክቱ ዝርዝር ጉዳዮች ባልተገለፁበት ሁኔታ ማንኛውም አባል በየትኛውም ቢሮ ወይም ቅጥር ግቢ ከምርት ገበያ አባልነቱ ጋር የተያያዙ ወይም ግንኙነት ያላቸው ማናቸውንም ሥራዎች መሥራት አይችልም።

14.1.2 በምርት ገበያው የሚገበያይ ማንኛውም ቢሮ ወይም መምሪያ ባቋቋመው አባልና በዚህ ረገድ ይህ ሥልጣንና ኃላፊነት በውክልና በተሰጠው ክፍል ክትትል እና ቁጥጥር መሆን ይኖርበታል። እያንዳንዱ አባል በምርት ገበያው ወይም ከምርት ገበያው ጋር በተያያዘ ያሉትን ሥራዎች እሱን ወክለው በስሙ የሚሠሩ ሰዎች በሙሉ በማንኛውም ጊዜ ከፍተኛ የሙያ ብቃትና ታማኝነት ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት።

14.1.3 እያንዳንዱ አባል አገልግሎቱን ለደንበኞቹ በአጥጋቢ ሁኔታ መስጠት እንዲችል እንዲሁም በምርት ገበያው ደንብና በሌሎች አግባብነት ባላቸውና በወቅቱ በሥራ ላይ ባሉ የባለሥልጣኑ መመሪያዎች ላይ የተቀመጡት ድንጋጌዎች ይፈፀሙ ዘንድ አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ-ልማቶች፣ ሠራተኞች፣ የመገናኛ መሣሪያዎች እና ሪኮርዶች በማንኛውም ጊዜ ሊኖሩት ይገባል።

14.1.4 የምርት ገበያው ለሕዝብ ጥቅም ዓላማዎች አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በራሱ አነሳሽነት ወይም በሌላ አባል ወይም ደንበኛ በሚቀርብ አቤቱታ አማካኝነት ስለአባሉ ወይም

በሥሩ ስላለ ማንኛውም ሠራተኛ የአገልግሎት አሰጣጥ እና የሙያ ሥነ ምግባር ደረጃው፣ ከዚህ ጋር በተያያዘም አገልግሎቱ ወይም ሥነ ምግባሩ አጥጋቢ ሆኖ ካልተገኘ ወይም በምርት ገበያው ደንቦች፣ ወይም ማስታወቂያዎች ወይም መመሪያዎች ወይም እነርሱን መሠረት አድርገው በወጡ ሰርኩላሮች ላይ የተቀመጡ መርሆዎችን የሚቃረን ሆኖ ከተገኘ አባሉ መግለጫ እንዲያቀርብ ሊጠይቀው ይችላል።

14.2 ክትትልና ቁጥጥር

14.2.1 እያንዳንዱ አባል በምርት ገበያው ደንቦች እና ደንቦቹን መሠረት አድርገው በወጡ ሌሎች ማስታወቂያዎችና መመሪያዎች እንዲሁም በባለሥልጣኑ በወጡ መመሪያዎችና በሌላ አግባብነት ባለው የመንግሥት ደንብ ላይ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች ምክንያታዊነት በተከተለ ሁኔታ ለማስፈፀም እንዲቻል ሥራውንና የሰራተኞችን የሥራ ክንውን ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የሥነ-ሥርዓት ደንቦችን ያወጣል፣ ያስፈጽማል።

14.2.2 አንድ አባል በምርት ገበያው ለዚሁ ዓላማ በምርት ገበያው በተደነገገው መሠረት የአባሉን የፋይናንስ አቋም የሚመለከት መረጃ ሪኮርድ መያዝ እንዲሁም የምርት ገበያው ለሚያደርገው ክትትልና ቁጥጥር ዝግጁ ማድረግ አለበት።

14.2.3 እያንዳንዱ አባል፣የሚያከናውናቸው ሥራዎች የምርት ገበያው ደንቦችና የባለሥልጣኑ መመሪያዎች አለመጣሳቸውን ለማወቅ ወይም እንዳይጥሱ ለመከላከል እንዲሁም ከተጠቀሱት ደንቦችና መመሪያዎች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በሚረዳ መልኩ ቢያንስ ዓመታዊ ግምገማ ማካሄድ አለበት።

14.3 ከደንበኞች ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት

14.3.1 ማንኛውም አባል በደንበኛው ስም ትዕዛዞችን ከመስጠቱ ወይም ከመቀበሉ በፊት ከእያንዳንዱ ደንበኛ ጋር የአባልና ደንበኛ ውል ስምምነት /አደው/ መዋዋል አለበት። ውሉም ይህንን በተመለከተ በምርት ገበያው የተዘረዘሩትን ድንጋጌዎች ማካተት አለበት።

14.3.2 አባሉ ከአዲስ ደንበኛው ጋር ግንኙነት ሲመሠርት፣ የደንበኛውን የኋላ ታሪክ፣ሐቀኝነት፣ የፋይናንስ ብቃቱንና የኢንቨስትመንት ዕቅዶቹን በማጣራት ተገቢውን እርምጃ መውሰድ እንዲሁም በምርት ገበያው ከደንበኛው ጋር ባለው ግንኙነትወቅታዊውን የግብይት ተገቢ ዋጋ እና ግብይትን ወይም በምርት ገበያው የተሰጠውን የትዕዛዝ ብዛት ጨምሮ የምርት ገበያው ከተቀማጭ ሂሣብ፣ ከዋጋ ብዛት ጋር የተያያዙ የግብይት ገደቦችን የተመለከቱ አግባብነት ያላቸውን ጠቃሚ መረጃዎች በበቂ ሁኔታ ማሳወቅ አለበት።

14.3.3 ማንኛውም አባል በምርት ገበያው ወይም በባለሥልጣኑ ደንቦች ወይም በነዚህ ደንቦች ላይ በተደረጉ ማሻሻያዎች ላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች የተቀመጡ የአባላትንና የደንበኞችን ግዴታዎች የሚመለከቱ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች በመለየት ለደንበኞች ያለምንም ክፍያ መስጠት አለበት። አባሉ በገበያው ወይም በባለስልጣኑ የተወሰነበት ቅጣት፣የተጣለበት የገንዘብ መቀጮ ወዘተ ካለበት ለደንበኛው ማሳወቅ አለበት።

14.3.4 ማንኛውም አባል ወይም ከአባሉ ጋር በአባሉ ስር የሚሠራ ሌላ ሰው አባሉ ከደንበኛው ጋር ወይም ስለደንበኛው በፈፀመው የምርት ግብይት ኪሣራ ለደንበኛው ዋስትና መስጠት አይችልም።

14.3.5 አባሉ ለራሱ ጥቅም እንዲያገኝ በማሰብ፣ ደንበኛው በተወሰኑ ምርቶች ወይም ውሎች ግብይት እንዲፈጽም ለማድረግ ማንኛውንም ዓይነት የሐሰተኛ ወይም አሳሳች መረጃ ወይም ምክር ለደንበኛው መስጠት የለበትም።

14.3.6 አባሉ ከደንበኛው ማናቸውንም ዓይነት ትዕዛዝ ከመቀበሉ በፊት ስለመገበያያ መድረኩ፣ ስለደንቦቹ እና ስለትዕዛዝ የማስታረቅ ሂደቱ ለደንበኛው ማስረዳት አለበት።

14.3.7 አባሉ ደንበኛው ከፈለገ የትዕዛዝ ቲኬቱን ቅጂ እና ግብይቱን በሚፈፅምበት ጊዜ የተሰጠውን የግብይት ማረጋገጫ ሪፖርት ለደንበኛው መስጠት አለበት።

14.3.8 አባሉ በማናቸውም ጊዜ የደንበኛውን ገንዘብ በተለየ የባንክ ሂሣብ ማስቀመጥ ይኖርበታል። አባሉ በማናቸውም ጊዜ የደንበኛውን ገንዘብ በክፍያ መፈፀሚያ ባንኩ በአባል ደንበኛ የባንክ ሂሣብ ማስቀመጥ ይኖርበታል። አባሉ ይህንን ገንዘብ ለራሱ ወይም ለሌላ ደንበኛው መገበያያ ወይም ከተቀማጭ ሂሣቡ ዓላማዎች ውጪ እና ከተቀማጩ ከፋይ የሆነው ደንበኛ ከተቀማጩና ከክፍያው ጋር በተያያዘ ከሚያደርጋቸው ግብይቶች ውጪ መጠቀም እንዲሁም መክፈል አይችልም።

14.3.9 አባሉ ማናቸውንም ዓይነት ትዕዛዞች ከደንበኛው ከመቀበሉ በፊት ተቀማጭ የሚሆን በቂ ገንዘብ ከደንበኛው መቀበል አለበት።

14.4 የአገናኝነት ሥራ

የምርት ገበያው የምርት ግብይቱ አባላት ከደንበኞቻቸው ጋር በሚያደርጓቸው ግንኙነት መከተል የሚኖርባቸውን ከፍተኛና ዝቅተኛ የአገናኝነት /ድለላ/ ሥራ ክፍያ ተመኖችን ሊወስን ይችላል። የክፍያ ተመኖቹ ከአንድ ምርት ጋር ተያይዘው የተተመኑ የክፍያ አኃዞች ወይም የምርቱ ዓይነት ከግምት ሳይገባ የውሉን ዋጋ መሠረት በማድረግ በመቶኛ ሊገለፁ ይችላሉ። ይህ የአገናኝነት ሥራ /ድለላ/ የክፍያ መጠን አባላት ለደንበኞቻቸው በሚሰጧቸው የትዕዛዝ ትኬቶች ላይ መገለጽ አለበት። ለግዜው ከፍተኛ የአገናኝነት (ድለላ) ተመን 2% ወይም የምርት ገበያው አግባብ ሆኖ ያገኘው መጠን ይሆናል።

14.5 አጠቃላይ መመሪያዎች

14.5.1 አንድ አባል በምርት ገበያው ሥራውን ሲያካሂድ ከሚከተሉት ተገቢ ያልሆኑ የንግድ ድርጊቶች መታቀብ አለበት።

14.5.1.1 ከለላ ስለመስጠት ወይም ስለመርዳት፤ ማንኛውም አባል ሌላ የግብይቱ አባል የምርት ገበያውን ወይም የባለሥልጣኑን መመሪዎች መጣሱን ወይም አለማክበሩን እያወቀ ከለላ መስጠት ወይም መርዳት ወይም ይህንኑ ጥሰት ሪፖርት ሳያደርግ መቅረት የለበትም።

14.5.1.2 አሳሳች ግብይቶች፣ አንድ አባል የሚከተሉትን ማድረግ የለበትም።

ሀ. የተሳሳቱ ወይም ሀሰተኛ የገበያ ወይም የማናቸውንም ምርት ዋጋ ሁኔታ ለመፍጠር በማሰብ መጫረት እና /ወይም ምርቶችን ማቅረብ ፤

ለ. አባሉ ግብይቱ የተጠቃሚ ባለቤትነት ለውጥ የማያመጣ ስለመሆኑ የማያውቅ ካልሆነ በቀር፣ የተጠቃሚ ባለቤትነት ለውጥ የማያመጣ የምርቶች ግብይት መፈፀም ወይም የግዢ ወይም የሽያጭ ትዕዛዝ መስጠት።

14.5.1.3 በእምነት ወይም አደራ ላይ በተመሠረተ ግንኙነት የተገኘን መረጃ ስለመጠቀም፤ አንድ አባል በምርት ገበያ አባልነቱ ስለ ምርቶች ባለቤትነት ወይም ውሎች መረጃ ካገኘ፣ ይህንኑ መረጃ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ግዢና ሽያጭን ለመገፋፋት ዓላማዎች መጠቀም የለበትም።

14.6 ተገቢ ያልሆነ የመገበያየት ተግባር

ማንኛውም አባል

14.6.1 በተጭበረበረ ሁኔታ ምርቶችን/ ውሎችን መግዛት ወይም መሸጥ ወይም ተገቢ ያልሆኑ የግብይት ተግባሮችን መፈፀም የለበትም።

14.6.2 የምርቶችን ዋጋ ሕጋዊ ባልሆነ ሁኔታ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እንዲያሻቅብ ወይም እንዲወርድ የሚያደርግ ውጤት ሊኖራቸው በሚችሉ ድርጊቶች መሳተፍ የለበትም።

14.6.3 ትክክለኛ ወይም እውነተኛ ያልሆኑ ዋጋዎችን የመፍጠር ውጤት ያለው ሀሰተኛ ወይም አሳሳች የግብይት ሁኔታን የሚፈጥር ድርጊት መፈፀም የለበትም።

14.6.4 የደንበኛው ትዕዛዝ ሳይፈፀም በራሱ ስምም ሆነ ከእርሱ ጋር በሚሠራ ሰው ስም ምርቶችን/ ውሎችን መግዛትም ሆነ መሸጥ አይችልም።

14.6.5 የገበያውን ሁኔታ ለማዛባት በማሰብ የሂሣብ መዝገቦችን፣ የሂሣብ ሰነዶችን እና ሪኰርዶችን ወደ ሀሰትነት መለወጥ የለበትም።

14.6.6 በምርት ገበያው ከተገለፀበት ሁኔታ ውጭ ከደንበኛው ትዕዛዝ ተቃራኒ የሆነ አቋም ወይም ከሁለት ደንበኞቹ ሁለት ተቃራኒ የሆኑ ትዕዛዞችን መፈፀም የለበትም።

14.7 ሪኮርዶች ፣ ዓመታዊ የሂሣብ ሰነዶች እና ኦዲቶች

14.7.1 ሪኰርዶች

14.7.1.1 ማንኛውም አባል የሂሣብ መዝገቦችና ሪኮርዶችን አያያዝ በተመለከተ የባለሥልጣኑን አዋጆችና መመሪያዎች ጨምሮ አግባባነት ባላቸው የመንግሥት ደንቦች እና በፌዴራል መንግሥቱ እንዲሁም በማንኛውም ክልላዊ ወይም አካባቢያዊ ባለሥልጣን ወይም አካል ወይም በፌዴራል መንግሥቱ ሥልጣን በተሰጠው ወይም በሚመራ አካል በወጡ ማስታወቂያዎች፣ መመሪያዎች፣ የተመለከቱ ድንጋጌዎችን ማክበር አለበት።

14.7.1.2 ማንኛውም አባል ላይ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች ከተካተቱት ግዴታዎች በተጨማሪ በአባልነቱና ከምርት ግብይቱ ጋር በተያያዘ የሂሣብ መዝገቦችን፣ ሪኰርዶችንና ሰነዶችን አስመልክቶ የምርት ገበያው በየጊዜው የሚያሳውቃቸውን የሚከተሉትንና ሌሎች ግዴታዎችን መፈፀም አለበት።

14.7.1.3 ማንኛውም አባል አስር ዓመታት የሚሸፍኑ ሥራውን የሚመለከቱ የሚከተሉትን ሪኮርዶች በወረቀት ወይም በማይበላሽ የኤሌክትሮኒክ ዘዴ መያዝ አለበት።

ሀ. ከክፍያ መፈፀሚያ ተቋም የተቀበላቸው የተጣሩ የግዴታ መግለጫዎችና የርክክብ ማስታወቂያዎች ፣

ለ. ከአገናኝነት ሥራ/ድለላ/ ጋር የተያያዙ ከየደንበኛው ለየብቻ/በተናጠል የተሰበሰቡ/የተያዙ ሪኰርዶች እና

ሐ. የግብይቶች መዝገቦቹ (ወይም የትዕዛዝ ቲኬቶች ዋና ቅጂዎች የሆኑ ሌሎች ሪኮርዶች) የእያንዳንዱን የምርት/ውል የየዕለት ግዢና ሽያጭ ዝርዝር የያዙ ሆነው የእያንዳንዱን ግብይት የምርቱን ስምና ዓይነት፣

የምርቱን ዋጋ፣ የድለላውን ጥቅል እና የተጣራ የክፍያ መጠን እና የደንበኞችን ስም ማሳየት አለባቸው።

14.7.1.4 እያንዳንዱ አባል እንደ አባልነቱ ከሥራው ጋር የተያያዙ የሂሣብ መዝገቦች እንደአስፈላጊነቱ የሚከተሉትን የሚያሳዩና ለይተው በሚያመላክቱ ሁኔታ መያዝ አለበት።

ሀ. ከእያንዳንዱ ደንበኛ ወይም ስለደንበኛው የተቀበላቸው ወይም ለእያንዳንዱ ደንበኛ ወይም ስለ እያንዳንዱ ደንበኛ የከፈላቸውን ገንዘቦች፣

ለ. በአባሉ ስም /ሂሣብ መዝገብ የተቀበላቸውና የተከፈሉ ገንዘቦች።

14.7.1.5 እያንዳንዱ አባል የራሱንና የደንበኞችን ገንዘቦች በተለያዩ የባንክ ሂሣቦች የማስቀመጥ ግዴታ አለበት። አባሉ በራሱ ለሚያደርጋቸው ግብይቶች ከደንበኛው የባንክ ሂሣብ ክፍያ ሊፈጽም አይችልም።

14.7.1.6 ከደንበኛ የባንክ ሂሣብ ወደ አባሉ የባንክ ሂሣብ ገንዘብ እንዲተላለፍ የሚፈቀደው ከዚህ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ነው፤

ሀ. እያንዳንዱ አባል በምርት ገበያ ደንቦች መሠረት የተዘጋጁ የአባልና የደንበኛ ስምምነት ወይም ውል ቅጂዎች በቋሚነት መያዝ አለበት።

ለ. ማንኛውም አባል ከእያንዳንዱ የክፍያ መፈፀሚያ ባንክ ጋር የገባቸውን ውሎች ቅጂዎች በቋሚነት መያዝ አለበት።

ሐ. ማንኛውም አባል ሥራውን በሚመለከት የተቀበላቸውን የማናቸውንም ደብዳቤዎች ዋናዎቹን እንዲሁም አባሉ ራሱ የላካቸውን ደብዳቤዎች ቅጂዎቹን (የውስጥ ማስታወሻዎችንና ደብዳቤዎችን ጨምሮ) በቋሚነት መያዝ አለበት።

መ. ማንኛውም አባል ከምርት ገበያ ሥራው ጋር በተያያዘ የገባቸውን የጽሑፍ ውሎች / ወይም ቅጂዎቻቸውን/ መያዝ አለበት።

ሠ. እያንዳንዱ አባል የደንበኛው ሂሣብ ከተዘጋ በኋላ ከአስር ዓመታት ላላነሠ ጊዜ የደንበኛውን ሂሣብ በተመለከተ ከሂሣቡ አከፋፈትና አያያዝ ጋር የተያያዙ የውል ድንጋጌዎችንና ሁኔታዎችን የያዙ ሪኮርዶችን፣ ሰነዶችን፣ ከደንበኛው ጋር ውል የተገባበት ቀን፣ ውሉ የተሻሻለበት ቀን፣ ውሉ የተቋረጠበት/የተፈፀመበት ቀን እና በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ስለደንበኛው ሆኖ የፈረመው ተወካይን የያዘ ሪኮርድ ማስቀመጥ አለበት።

ረ. እያንዳንዱ አባል ለኦዲት /ምርመራ የተቀመጡትን ሪኮርዶች የት እንደሚገኙ ለምርት ገበያው ማሳወቅ አለበት።

ሰ. ማንኛውም አባል ደንበኛው ያቀረባቸውን የጽሑፍ አቤቱታዎች ሪኮርድ በሙሉ ይዞ ማቆየት አለበት። ሪኮርዱም የደንበኛውን መለያ ቁጥር፣ ቀኑን፣ የደንበኛውን ስም፣የአቤቱታዎቹ ዝርዝር ጉዳዮች፣ በአባሉ የተወሰደውን እርምጃ እንዲሁም ጉዳዩ ለሽምግልና ዳኝነት ወደ ምርት ገበያው ተመርቶ እንደሆነ ዝርዝሩን የያዘ መሆን አለበት።

ሸ. ማንኛውም አባል የአባሉ ንብረቶች የሆኑ የማናቸውንም ዋስትናዎች ዝርዝር መያዝ አለበት። ዝርዝሩም ዋስትናዎች ማን ዘንድ እንደቀመጡ፣ ከአባሉ ውጭ በሌላ ሰው የተያዙ እንደሆነ፣ ለብድሮች ወይም ቅድሚያ ክፍያዎች ዋስትናነት በመያዣነት ስለመሰጠታቸው ማመልከት አለበት።

ቀ. የሪኮርዶችን አያያዝ በተመለከተ ከላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት በአባሉ ዋና ቢሮ ሪኮርዶች ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ቅርንጫፍ ቢሮዎች/ ጽ/ቤቶች እና አባሉ ከምርት ግብይት ሥራው ጋር በተያያዘ የምርት ግብይት ሥራውን ለማከናወን በባለቤትነት በያዘው ወይም በሚቆጣጠረው ድርጅት ላይም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

14.8 ዓመታዊ ሂሣቦችና ኦዲት

14.8.1 ማንኛውም አባል በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት ማብቂያ በኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር እስከ ሰኔ 30 ቀን ያለውን በተመለከተ ወይም ለምርት ገበያው በሚቀርብ የሂሣብ ዓመት መሠረት በተወሰነ ሌላ ቀን ዓመታዊ የሂሣብ መግለጫ ማዘጋጀት አለበት።

14.8.2 የአባሉ የንግድ ሥራ ሀብቶችና ዕዳዎች በሂሣብ ሚዛን መግለጫው መያዝ ሲኖርባቸው፣ የሂሣብ ሚዛን መግለጫው በተዘጋጀበት ቀን ፣የንግድ ሥራው በአጠቃላይ ያለበትን ሁኔታ ትክክለኛና እውነተኛ ገጽታ ያንፀባርቁ ዘንድ ሂሣቦቹ መገለጽ አለባቸው።

14.8.3 ማንኛውም አባል የኦዲት ምርመራ የተደረገበትን የሂሣብ መግለጫ እና ሪፖርት የአባሉ የበጀት ዓመት በተጠናቀቀ ከሦስት ወራት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ለምርት ገበያው ማቅረብ ይኖርበታል። ሆኖም የምርት ገበያው የሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜውን ለማራዘም በቂ ምክንያቶች አሉ ብሎ ካመነ፣በቂ ነው ብሎ ለሚያስበው ጊዜ የሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜውን ማራዘም ይችላል።

# 15. ዲሲፕሊን እና አፈጻጸም

15.1 ስለ ግብይት አፈጻጸም ኮሚቴ መቋቋም

15.1.1 በደንብ ላይ የሚፈጸሙ ጥሰቶችን መርምሮ የዲሲፕሊን እርምጃ የሚወስድ የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

15.1.2 የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለዋና ስራ አስፈጻሚ ይሆናል፡፡

15.1.3 የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴው የሚከተሉትን አምስት አባላት ማካተት አለበት፡፡

15.1.3.1 ዋና የሕግ ማስከበሪያ የስራ ኃላፊ፣

15.1.3.2 በዋና ስራ አስፈጻሚ በየጊዜው የሚመረጡ ሁለት የስራ ኃላፊዎች እና

15.1.3.3 በምርት ገበያው አባላት ማህበር የሚመረጡ በመልካም ስማቸው የሚታወቁ እና ላለፉት ሁለት አመታት የዲሲፕሊን እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሁለት የምርት ገበያው አባላት፡፡

15.1.4 ዋና የሕግ ማስከበሪያ የስራ ኃላፊ የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴው ሰብሳቢ ሆኖ ያገለግላል፡፡

15.1.5 የምርት ገበያው የሕግ ማስከበሪያ መምሪያ የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴው ድምጽ የመስጠት መብት የሌለው ጽህፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፡፡

15.1.6 በግብይት አፈጻጸም ኮሚቴው ቢያንስ አንድ የምርት ገበያውን አባል ጨምሮ ሦስት አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

15.1.7 የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴ ውሳኔ የሚያልፈው በስብሰባ ላይ በተገኙ አባላት ድምጽ ብልጫ ይሆናል፡፡ ሆኖም ድምጽ እኩል በኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

15.1.8 ከዋና የሕግ ማስከበሪያ የስራ ኃላፊ በስተቀር የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን ሁለት አመት ይሆናል፡፡ ይሁንና ማንኛዉም አባል በድጋሚ መመረጥ ይችላል

15.1.9 የአባልነት ቦታ ከተለቀቀ በንዑስ አንቀጽ 15.1.3 በተመለከተው መሰረት ምትክ እንዲመረጥ ዋና ስራ አስፈጻሚ ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለበት፡፡

15.1.10 የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴው እንዳስፈላጊነቱ የራሱን የስብሰባ ሥነሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

15.2 የዲሲፕሊን ጥፋት ዓይነቶች

የጥፋቶቹን ክብደት ግምት ውስጥ በማስገባት ለዚህ ደንብ አፈጻጸም አራት ዓይነት የዲሲፕሊን ጥፋቶች ይኖራሉ፡፡

15.2.1 አንደኛ ደረጃ የዲሲፕሊን ጥፋቶች የሚባሉት የደንቡን ንዑስ አንቀፅ 4.7.1 በመተላለፍ የሚፈጸሙ ጥፋቶች ናቸው፡፡

15.2.2 ሁለተኛ ደረጃ የዲሲፕሊን ጥፋቶች የሚባሉት የደንቡን ንዑስ አንቀፅ 4.7.2 በመተላለፍ የሚፈጸሙ ጥፋቶች ናቸው፡፡

15.2.3 ሦስተኛ ደረጃ የዲሲፕሊን ጥፋቶች የሚከተሉትን ጥፋቶች ያጠቃልላል፡፡

15.2.3.1 ንዑስ አናቅፅ 4.5.5፣ 4.5.6፣ 4.5.11፣ 4.5.14፣ 4.11፣ 4.12.1፣ 4.12.5፣ 5.4.4.1፣ 5.4.6.1፣ 5.5.1.4፣ 5.5.5፣ 5.5.8.5፣ 5.5.8.6፣ 5.5.17፣ 6.3፣ 6.4፣ 6.6፣ 8.2.2፣ 10.5፣ 14.1፣ 14.2፣ 14.3፣ 14.4፣ 14.5፣14.6፣ 14.7፣ 14.8 ወይም 17.2.3 በመተላለፍ የተፈጸሙ ድርጊቶች ወይም

15.2.3.2 በምርት ገበያው ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም በምርት ገበያው ሰራተኞች ወይም ንብረት ላይ ተገቢ ያልሆነ ተግባር ወይም ጥቃት መፈጸም፡፡

15.2.4 አራተኛ ደረጃ የዲሲፕሊን ጥፋቶች የሚከተሉትን ጥፋቶች ያጠቃልላል፡፡

15.2.4.1 ንዑስ አናቅፅ 5.3.1.2፣ 5.3.1.3፣ 5.5.1.1፣ 5.5.1.6፣ 5.5.4፣ 5.5.7.4፣ 5.5.7.5 ወይም 5.5.8 በመተላለፍ የተፈጸሙ ድርጊቶች ወይም

15.2.4.2 በምርት ገበያው ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚደረጉ ግብይቶች በአግባቡ እንዳይከናወኑ ሊያደርግ በሚችል ሁኔታ መንቀሳቀስ፡፡

15.2.5 የምርት ገበያው ደንብን በመጣስ የሚፈጸሙ ተጨማሪ የዲሲፕሊን ጥፋቶችን ከጊዜ ወደ ጊዜ ከላይ በተጠቀሱት የዲሲፕሊን ጥፋቶች ደረጃዎች ስር ሊመድብ ይችላል፡፡

15.3 የዲሲፕሊን እርምጃዎች

15.3.1 በቦርድ መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አንደኛ ደረጃ የዲሲፕሊን ጥፋት የፈጸመ አባል እንደሚከተለው ይቀጣል፡፡

15.3.1.1 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.7.1 በተቀመጠው መሰረት ከምርት ገበያው አባልነት ወዲያውኑ በምርት ገበያው ይታገዳል እና/ወይም

15.3.1.2 የዲሲፕሊን ጥፋቱ ግብይት ነክ ጥሰት ከሆነ ከግብይቱ ዋጋ 10% ያልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ወይም ግብይት ነክ ጥሰት ካልሆነ ደግሞ ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺ.) ያልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ይከፍላል እና/ወይም

15.3.1.3 በምርት ገበያው የውሳኔ ሃሳብ መሰረት የምርት ገበያው አባልነት ይቋረጣል፡፡

15.3.2 በቦርድ መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሁለተኛ ደረጃ የዲሲፕሊን ጥፋት የፈጸመ አባል እንደሚከተለው ሊቀጣ ይችላል፡፡

15.3.2.1 በደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.7.2 በተቀመጠው መሰረት ከምርት ገበያው አባልነት ይታገዳል እና/ወይም

15.3.2.2 የዲሲፕሊን ጥፋቱ ግብይት ነክ ጥሰት ከሆነ ከግብይቱ ዋጋ 10% ያልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ወይም ግብይት ነክ ጥሰት ካልሆነ ደግሞ ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺ.) ያልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ይከፍላል እና/ወይም

15.3.2.3 በምርት ገበያው የውሳኔ ሃሳብ መሰረት የምርት ገበያው አባልነት ይቋረጣል፡፡

15.3.3 ማንኛውም አባል ሦስተኛ ደረጃ የዲሲፕሊን ጥፋት ከፈጸመ እንደሚከተለው ሊቀጣ ይችላል፡፡

15.3.3.1 የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል እና/ወይም

15.3.3.2 የዲሲፕሊን ጥፋቱ ግብይት ነክ ጥሰት ከሆነ ከግብይቱ ዋጋ 6% ያልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ይከፍላል እና/ ወይም

15.3.3.3 የዲሲፕሊን ጥፋቱ ግብይት ነክ ጥሰት ካልሆነ ደግሞ ከብር 20,000 (ሃያ ሺ.) ያልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ይከፍላል እና/ወይም

15.3.3.4 በራሱ ወጪ ስለምርት ገበያው ደንብ ስልጠና እንዲወስድ ሊደረግ ይችላል፡፡

15.3.4 ማንኛውም አባል አራተኛ ደረጃ የዲሲፕሊን ጥፋት ከፈጸመ እንደሚከተለው ሊቀጣ ይችላል፡፡

15.3.4.1 የጽሁፍ ተግሳጽ ይሰጠዋል እና/ወይም

15.3.4.2 ከብር 5,000 (አምስት ሺ.) የማይበልጥ መቀጮ እንዲከፍል ይታዘዛል፡፡

15.3.5 ለዚህ ንዑስ አንቀፅ ዓላማ የምርት ገበያው የዲሲፕሊን ጥፋቶችን ግብይት ነክ ወይም ግብይት ነክ ያልሆኑ በሚለው ውስጥ እንደመሰለው ሊመድብ ይችላል፡፡

15.3.6 ቦርዱ የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴን ሳያማክር በንዑስ አንቀፅ 4.6.5.5 እና 4.9.1 መሰረት አንደኛ ደረጃ የዲሲፕሊን ጥፋት የፈጸመን ሰው አባልነት ሊያቋርጥ ይችላል፡፡

15.3.7 ቦርዱ በንዑስ አንቀፅ 15.3.1.3 ወይም 15.3.2.3 ስር የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴ ያቀረበውን የአባልነት ማቋረጥ ሃሳብ ካልተቀበለ ጉዳዩ በድጋሚ እንዲታይ ለግብይት አፈጻጸም ኮሚቴ ሊመልሰው ይችላል፡፡ የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴ ጉዳዩ እንደደረሰው ተገቢ ሆኖ ያገኘውን የገንዘብ መቀጮ ሊወስን ይችላል፡፡

15.3.8 ማናቸውም አባል በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ከሁለት ጊዜ በላይ ሦስተኛ ደረጃ የዲሲፕሊን ጥፋት ከፈጸመ የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴው የጥፋቱን ባህሪ እና ቅጣትን ሊያከብዱ የሚችሉ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለሁለተኛ ደረጃ የዲሲፕሊን ጥፋት የተቀመጡ ቅጣቶችን ሊወስንበት ይችላል፡፡

15.3.9 ማናቸውም አባል በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ከሁለት ጊዜ በላይ አራተኛ ደረጃ የዲሲፕሊን ጥፋት ከፈጸመ የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴው የጥፋቱን ባህሪ እና ቅጣትን ሊያከብዱ የሚችሉ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለሦስተኛ ደረጃ የዲሲፕሊን ጥፋት የተቀመጡ ቅጣቶችን ሊወስንበት ይችላል፡፡

15.3.10 የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴ በደንቡ ውስጥ በአባላት ላይ ተፈጻሚ እንዲሆኑ የተቀመጡ ቅጣቶችን ደንቡን በተላለፉ የመድረክ ተወካዮች ወይም በደንበኞች ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን እንዳስፈላጊነቱ ሊወስን ይችላል፡፡

15.4 ስለ ምርመራ እና የዲሲፕሊን ጉዳዮችን ስለመወሰን

15.4.1 ስለ ምርመራ

15.4.1.1 የዲሲፕሊን ጥፋቶችን ሪፖርት ማድረግ እንዳለባቸው በደንቡ የተቀመጠው የአባላት ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ጉዳት ደርሶብኛል የሚልን ጨምሮ ማንኛውም ሰው የደንቡን መጣስ በተመለከተ የቃል ወይም የጽሁፍ አቤቱታ ለሕግ ማስከበሪያ መምሪያ ለማቅረብ ይችላል፡፡ የሕግ ማስከበሪያ መምሪያ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በዋና ስራ አስፈጻሚ ወይም በቦርድ ጥያቄ ምርመራ ሊጀምር ይችላል፡፡

15.4.1.2 የሕግ ማስከበሪያ መምሪያ የዲሲፕሊን ጥፋትን የሚመለከት ክስ፣አቤቱታ፣ጥቆማ ወይም ሪፖርት እንደደረሰው ቅድመ ምርመራ ማጣሪያዎችን በማድረግ ሙሉ ምርመራ ስለማስፈለጉ መወሰን አለበት፡፡

15.4.1.3 ሙሉ ምርመራ ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የሕግ ማስከበሪያ መምሪያ ከምርት ገበያው ግብይት ጋር የሚገናኙ ማናቸውንም መረጃ የምርት ገበያው ደንብ ተፈጻሚ ከሚሆንበት ማናቸውም ሰው በመጠየቅ ምርመራ ማከናወን አለበት፡፡ ማናቸውም አግባብነት ያለው ሰው ቀርቦ ቃሉን እንዲሰጥ የሕግ ማስከበሪያ መምሪያ ሊጠራው ይችላል፡፡

15.4.1.4 በሕግ ማስከበሪያ መምሪያ ተጠርቶ የቀረበ ሰው የምስክርነት ቃሉን እንዲሰጥ ማናቸውም ጥቅም እንደሚያገኝ የተስፋ ቃል ሊሰጠው አይገባም።

15.4.1.5 ከአራተኛ ደረጃ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ውጭ የሆነ ደንብ መጣስ ተፈጽሟል ብሎ የሕግ ማስከበሪያ መምሪያ ካመነ የምርመራ ሪፖርት እና ክስ ለግብይት አፈጻጸም ኮሚቴ ማቅረብ አለበት።

15.4.1.6 የሕግ ማስከበሪያ መምሪያ ተፈጽሟል ተብሎ የቀረበው ክስ በበቂ ማስረጃ አልተደገፈም ብሎ ከወሰነ ጉዳዩን በመዝጋት ለአቤቱታ አቅራቢው እና ለዋና ስራ አስፈጻሚ ያሳውቃል።

15.4.1.7 የሕግ ማስከበሪያ መምሪያ ጉዳዩን በመዝጋቱ ቅሬታ ያደረበት ሰው ውሳኔው በተሰጠ አስር የስራ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለግብይት አፈጻጸም ኮሚቴ ለማቅረብ ይችላል።

15.4.2 ለጉዳዩ የመጀመሪያ ውሳኔ ስለመስጠት

15.4.2.1 የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴ የምርመራ ሪፖርቱን ካየ በኋላ ደንቡ ስለመጣሱ የሚያመለክት በቂ ማስረጃ አልቀረበም ብሎ ካመነ ወይም ጉዳዩን የማየት ስልጣን ስለሌለው ሂደቱን መቀጠል አያስፈልግም ብሎ ከወሰነ ጉዳዩን በመዝጋት ውሳኔውን ለአቤቱታ አቅራቢው እና ለምርት ገበያው ማሳወቅ አለበት።

15.4.2.2 የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴ የምርመራ ሪፖርቱን ከተቀበለ በኋላ ጉዳዩን ለማየት በቂ ማስረጃ አለ ብሎ ካመነ ጉዳዩ የሚታይበትን ቀን በመወሰን እንዳስፈላጊነቱ የምርት ገበያው አባል እና/ወይም ማናቸውም ምስክር እንዲቀርብ ደብዳቤ ሊልክ ይችላል፡፡

15.4.3 ጉዳዩን ስለማየት

15.4.3.1 ከቀረበው ማስረጃ ምሉእነት በመነሳት የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴው በቀረበው ጉዳይ ላይ ሙሉ ውይይት ማድረግ አስፈላጊ እንዳልሆነ ካመነ በምርመራ ሪፖርቱ ላይ በመመስረት አባሉን በመቅጣት ጉዳዩን ሊዘጋው ይችላል፡፡

15.4.3.2 የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴው በጉዳዩ ላይ ሙሉ ውይይት ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ካመነ ስለደንቡ መጣስ ከመወሰኑ እና ቅጣት ከመጣሉ በፊት የምርመራ ሪፖርቱን ማየት እንዲሁም የአባሉን እና የምስክር ቃል ሊሰማ ይችላል፡፡

15.4.3.3 የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴው አባሉ የደንብ መጣስ አልፈጸመም ብሎ ካመነ ጉዳዩን መዝጋት አለበት፡፡

15.4.3.4 ጉዳዩ በሚታይበት ወቅት በግብይት አፈጻጸም ኮሚቴ ፊት እንዲቀርብ የተጠራው የተከሰሰ አባል ለሁለተኛ ጊዜ መቅረብ ካልቻለ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ መደረግ አለበት፡፡

15.4.3.5 የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴው የሰጠውን ውሳኔ ለዋና ስራ አስፈጻሚ ማስተላለፍ አለበት፡፡ዋና ስራ አስፈጻሚ በውሳኔው ከተስማማ እንዲፈጸም ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡ ውሳኔው በቦርድ መጽደቅ ያለበት ከሆነ ዋና ስራ አስፈጻሚ ለቦርዱ እንዲጸድቅ ማቅረብ አለበት፡፡

15.4.4 ውሳኔዎችን ስለማስፈጸም

15.4.4.1 የሕግ ማስከበሪያ መምሪያ የምርት ገበያውን የዲሲፕሊን ውሳኔ አፈጻጸም መከታተል አለበት፡፡

15.4.4.2 ማናቸውም አባል በዲሲፕሊን ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ በደንቡ መሰረት የተጣለበትን የገንዘብ መቀጮ ካልከፈለ ገንዘቡ ከአባሉ ሂሳብ እንዲቀነስ መደረግ አለበት፡፡

15.4.4.3 በዚህ ደንብ መሰረት በአንድ አባል ላይ የተጣለው የአባልነት እገዳ በደንቡ በተቀመጠው መሰረት ሊነሳ ይችላል፡፡

15.4.5 ስለ ይግባኝ

15.4.5.1 የምርት ገበያው ሶስተኛ ደረጃ የዲሲፕሊን ጥፋቶችን አስመልክቶ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አባል ውሳኔው በተሰጠ አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይግባኙን መጀመሪያ ለቦርድ ማቅረብ አለበት፡፡ ቦርዱ አቤቱታውን ከመረመረ በኋላ በግብይት አፈጻጸም ኮሚቴ በድጋሚ እንዲታይ ሊመራው ወይም እራሱ ውሳኔ ሊሰጥበት ይችላል፡፡

15.4.5.2 ምርት ገበያው በሰጠው ማናቸውም የዲሲፕሊን ውሳኔ ላይ የምርት ገበያው አባል ለባለስልጣኑ ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል፡፡

15.4.5.3 ቦርዱ ከአባል በሚቀርብለት ጥያቄ መሰረት የይግባኝ ሂደት እስኪጠናቀቅ ድረስ የምርት ገበያው ውሳኔ ታግዶ እንዲቆይ ትእዛዝ ለመስጠት ይችላል፡፡

## 16. የግልግል/የሽምግልና ዳኝነት፣ ዕርቅ እና የባለሙያ ውሳኔ

### 16.1 የግልግል/የሽምግልና ዳኝነት እና ዕርቅ

16.1.1 የግልግል ዳኝነትና የዕርቁ መቀመጫ

ምርት ገበያው ለተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች የተለያዩ የግልግል ወይም የእርቅ መቀመጫዎችን በአጠቃላይ ወይም በተለየ ሁኔታ ሊወሰን ሲችል፣ በዚህ ጊዜ የግልግል ዳኝነቱ ወይም የዕርቁ መቀመጫ በምርት ገበያው የሚወሰነው ይሆናል። ምርት ገበያው በተለየ ሁኔታ የሚወሰነው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የግልግል ዳኝነቱና የእርቁ መቀመጫ አዲስ አበባ ይሆናል።

16.1.2 የሥልጣን ክልል

ምርት ገበያው እራሱ ተከራካሪ ወገን ካልሆነ በስተቀር፣ ክርክሮች በሙሉ ለግልግል ዳኝነትና ለእርቅ ይቀርባሉ።

16.1.3 የይገባኛል ጥያቄዎችን፣ያለመግባባቶችን ወይም ክርክሮችን ስለማቅረብ

16.1.3.1 አመልካቹ በግልግል ዳኝነት ወይም በዕርቅ የሚታየውን ክርክር ወይም አለመግባባት ለምርት ገበያው ወይም ምርት ገበያው በየጊዜው በሚያሳውቃቸው ቦታዎች ማቅረብ አለበት።

16.1.3.2 በግልግል ዳኝነት እንዲታይ የሚቀርበው ማመልከቻ የምርት ገበያው አስፈላጊውን እንዲፈፅምና እንዲያፀድቀው የምርት ገበያው ባዘጋጃቸው ቅጾች መሠረት ተዘጋጅቶ ለምርት ገበያው መቅረብ አለበት። ምርት ገበያው አለመግባባቱ ወይም ክርክሩ በዕርቅ ይፈታ ዘንድ አስቀድሞ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ካደረገ በኋላ በዕርቁ ጉዳዩን ለመፍታት አለመቻሉን ካመነ ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት እንዲታይ ይመራዋል።

16.1.3.3 በተከራካሪ ወገኖች በተለየ ሁኔታ የሚወሰነው እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ማመልከቻው በቀረበበት ቀን ክርክሩ ወይም አለመግባባቱ የተነሳበት ጉዳይ በገንዘብ ሲተመን ከብር 50,000 /ሃምሣ ሺህ/ የሚበልጥ ከሆነ ሦስት የግልግል ዳኞች በሚሰየሙበት ጉባኤ እንዲታይ ይመራል። እንዲሁም ክርክሩ ወይም አለመግባባቱ የተነሳበት ጉዳይ በገንዘብ ሲተመን እስከ ብር 50,000 /ሃምሣ ሺህ/ የሚደርስ ከሆነ ጉዳዩ በአንድ የግልግል ዳኛ እንዲታይ ይመራል።

16.1.3.4 በተባባሪ አባሉና በተባባሪ አባሉ ደንበኛ መካከል ክርክር ከተነሣ ተባባሪ አባሉን የሚያሠራው አባል በተከራካሪነት ይገባል።

16.1.4 ዕርቅ

16.1.4.1 ምርት ገበያው በተከራካሪ ወገኖች ስምምነት መሠረት ጉዳዩ ለግልግል የዳኝነት ሥርዓት ከመመራቱና ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት ለዕርቅ ይመራዋል።

16.1.4.2 ተከራካሪ ወገኖች ብቸኛ አስታራቂ ወይንም የአስታራቂዎች ጉባኤ ይሾማሉ።ከዚህ በታች በንኡስ አንቀጽ 16.1.5 እና 16.1.6 የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው በአስታራቂና አስታራቂዎች አሿሿም ላይ ተፈፃሚዎች ይሆናሉ።

16.1.4.3 አስታራቂው ወይም አስታራቂዎች ተከራካሪ ወገኖች ክርክራቸውን በመግባባት ይፈቱ ዘንድ ነፃና ገለልተኛ ሆነው መርዳት አለባቸው።

16.1.4.4 የዕርቁ ዓላማ የተለያዩ አመለካከቶችን በማቀራረብ አከራካሪ ለሆኑት ጉዳዮች እልባት ሰጥቶ ወደ እርቅ ማሸጋገር ነው።

16.1.4.5 አስታራቂው/አስታራቂዎች የክርክሩን ዝርዝር ከመረመሩና ከተከራካሪዎቹም የሚሉትን ካዳመጡ በኋላ አግባብ ነው ብለው ያመኑበትን የማስታረቂያ ሃሳብ ሊያቀርቡ ይችላሉ።ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች በመግባባት ዕልባት ላይ ከደረሡ አስታራቂው ወይም አስታራቂዎች የተደረሰበትን ስምምነት በፅሑፍ በማቅረብ ሁለቱም ወገኖች በ7 ቀናት ውስጥ እንዲፈርሙበት በማድረግ ተግባራዊነቱን ይከታተላሉ።

16.1.4.6 የዕርቅ ሙከራው ያልተሳካ ከሆነ አስታራቂው ወይም አስታራቂዎች ተከራካሪ ወገኖች ስላለመታረቃቸው መግለጫ ያዘጋጃል፣ያዘጋጃሉ። በዚህ ጊዜ ተከራካሪ ወገኖች ሪፖርቱ ይፋ በሆነ በሰባት ቀናት ውስጥ የግልግል ሥርዓት ሂደቱን መጀመር ይኖርባቸዋል።

15.1.4.7 የእርቅ ሂደቱ ሳይሳካ ከቀረ፣ አስታራቂ ወይም አስታራቂዎች የነበሩ በዚሁ ተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የግልግል ዳኞች ሆነው ሊሾሙ አይችሉም።

16.1.5 የግልግል ዳኞች መመሪያዎች

16.1.5.1 የግልግል ዳኛውም ሆነ አስታራቂው በተጨባጭ ሁኔታ ላይ በተመሠረቱ፣ ሚዛናዊና ፍትሐዊ በሆኑ መርሆዎች መመራት የሚኖርባቸው ሲሆን በተለይም የተከራካሪ ወገኖችን መብትና ግዴታዎች፣ በሽምግልና ዳኝነት በክርክር ላይ ያለውን ጉዳይ በተመለከተ ቀደም ሲል የነበሩልማዶችንና አሠራሮችን ጨምሮ የክርክሩ ከባቢያዊ ሁኔታዎችን ከግምት ማስገባት አለበት።

16.1.5.2 ተከራካሪ ወገኖች በእኩልነት መታየት ያለባቸው ሲሆን ሃሳባቸውን በተሟላ ሁኔታ መግለፅ የሚችሉበት ዕድል መሰጠት አለበት።

16.1.6 የግልግል ዳኞች መምረጫ መስፈርትና ሥነ-ሥርዓት

16.1.6.1 ብቁነት

16.1.6.1.1 የግልግል ዳኞችን አሿሿም ለማቀላጠፍ ይረዳ ዘንድ የምርት ገበያው በየጊዜው የትምህርት ደረጃቸውን፣ ልምዳቸውን እና ዕውቀታቸውን መሠረት በማድረግ የግልግል ዳኞች ዝርዝር እያዘጋጀ ያቀርባል።

16.1.6.1.2 በዚህ አንቀጽ 16.1.6.1.1 ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ በግልግል ዳኞች ዝርዝር ውስጥ ሊካተት ይችላል።

ሀ. የንግድ ክርክሮችን በመፍታት ረገድ በቂ ልምድና ብቃት ያለው እና

ለ. ሥርዓቱን የጠበቀ የክርክር ሂደት መምራት የሚችል፣ ምስክሮችንና ማስረጃዎችን እና ኤግዚቢቶችን መረዳትና መተንተን የሚችል፣ የክርክሩን ሂደት ውጤቶች አጭርና ግልጽ በሆነ መንገድ ማዘጋጀት የሚችል እና ተገቢ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መወሰን የሚችል፡፡

16.1.6.1.3 ተከራካሪ ወገኖች የግልግል ዳኞችን ዝርዝር መቃወም አይችሉም፡፡ የምርት ገበያው በማንኛውም ጊዜ ቢሆን ከግልግል ዳኞች ዝርዝር ውስጥ የግልግል ዳኞችን የመሰረዝ ወይም በዝርዝሩ ውስጥ ሌላ የግልግል ዳኛ የመጨመር ሙሉ ሥልጣን አለው፡፡

16.1.7 የግልግል ዳኞች አሿሿም ሥነ ሥርዓት

16.1.7.1 አመልካቹና ክስ የቀረበበት ተጠሪ እያንዳንዳቸው በተመራጭነትደረጃ ከአንድ እስከ ሦስት በማስቀመጥ በምርት ገበያው ዝርዝር ከቀረቡት የግልግል ዳኞች መካከል እያንዳንዳቸው ሦስት የግልግል ዳኞችን እየቀነሰ በሚሄድ የፍላጎት ቅደም ተከተል በመምረጥ ለምርት ገበያው ያቀርባሉ። በአመልካቹና በተጠሪው የሚመረጡት ሰዎች ቁጥር ሦስት የግልግል ዳኞች ጉባኤ ይሆናሉ።

16.1.7.2 እያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን በተመራጭነት ደረጃ ከአንድ እስከ ሦስት ካስቀመጣቸው የግልግል ዳኞች መካከል አንድ የግልግል ዳኛ የመሾም መብት አለው። በተከራካሪ ወገኖች ካቀረቧቸው የግልግል ዳኞች ምርጫ ዝርዝር ውስጥ ሁለቱም በጋራ የመረጡት የግልግል ዳኛ ካለ ይኸው የግልግል ዳኛ ሰብሳቢ ሆኖ ይሾማል። የጋራ የግልግል ዳኛ በማይኖርበት ጊዜ ሰብሳቢው ከምርት ገበያው ዝርዝር ውስጥ በተከራካሪ ወገኖች ይሾማል። ተከራካሪ ወገኖች በሰብሳቢው አሿሿም ላይ መስማማት ካልቻሉ ሰብሳቢው በምርት ገበያው ይሾማል።

16.1.7.3 ብቸኛ የግልግል ዳኛ በሚሆንበት ጊዜ በአመልካቹና በተጠሪው ከፍተኛ ምርጫ ያገኘውን የግልግል ዳኛ የምርት ገበያው ይለያል። የምርት ገበያው የጋራ የግልግል ዳኛ ባልተገኘ ጊዜ በአመልካቹና በተጠሪው ከተመረጡት የግልግል ዳኞች ውጭ ካሉ የምርት ገበያው የግልግል ዳኞች ዝርዝር መካከል የግልግል ዳኛ ይመርጣል።

16.1.7.4 አመልካችም ሆነ ተጠሪው የግልግል ዳኞችን ዝርዝር ለምርት ገበያው ካላቀረቡ የምርት ገበያው ከዕጩ የግልግል ዳኞች ዝርዝር ውስጥ የግልግል ዳኞች ጉባዔን ወይም ብቸኛ የግልግል ዳኞችን ይመርጣል።

16.1.8 የግልግል ዳኞችን ሹመት ስለመቃወም

16.1.8.1 አንድ ዕጩ የየግልግል ዳኛ ከሹመቱ ጋር በተያያዘ ማንኛውም ነፃነቱን እና ገለልተኛነቱን አጠያያቂ የሚያደርጉና መስተባበል ለማይችሉ ጥርጣሬዎች መነሻ የሆኑ ሁኔታዎችን ካሉ መግለጽ አለበት።

16.1.8.2 አንድ ተከራካሪ የሾመውን የግልግል ዳኛ መቃወም የሚችለው ለተቃውሞው ምክንያት የሆኑትን ነገሮች ከሹመቱ በኋላ ካወቃቸው ብቻ ነው።

16.1.9 የሽምግልና ወጪ

16.1.9.1 ተከራካሪ ወገኖች የግልግል ዳኝነቱን ወጪ ይሸፍናሉ። ለዚሁም ዓላማ ሁለቱም የግልግል ዳኝነቱ ተከራካሪ ወገኖች በምርት ገበያው ለግልግል ዳኝነት ሂደቱ ወጪ መሸፈኛ የሚሆን ተቀማጭ ገንዘብ ያስቀምጣሉ። ሆኖም ተጠሪው የተጠቀሰውን ተቀማጭ ገንዘብ ሳያስቀምጥ ከቀረ፣ ወይም ችላ ካለ ወይም ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ አመልካቹ ይህንኑ ተቀማጭ ገንዘብ የማስቀመጥ ግዴታ አለበት። ሆኖም አመልካቹ ይህንን ያስቀመጠውን ተቀማጭ ገንዘብ በመጨረሻው ውሣኔ መሠረት ከተጠሪው የመቀበል መብቱ የተጠበቀ ነው።

16.1.9.2 አባሉ የሚፈለግበትን ተቀማጭ ገንዘብ ካላስቀመጠ፣ ምርት ገበያው ይህንኑ ተቀማጭ ገንዘብ ከአባሉ ገንዘብ ላይ ይወስዳል። ይህን ተቀማጭ ገንዘብ አመልካች ተከራካሪ ወገን ማስቀመጥ ካልቻለ ወይም በምርት ገበያው የሚገኘው የአባሉ ገንዘብ ከሚፈለገው ገንዘብ ያነሰ እንደሆነ የግልግል ዳኝነት ሂደቱ እስከ አሥራ አምስት ቀናት ያህል ታግዶ ሊቆይ ይችላል። ክፍያ ባለመፈጸሙ ምክንያት የተጣለው ዕገዳ ከተጠቀሰው ጊዜ በላይ ካለፈ ክሱ ወይም የመልስ ክሱ እንደነገሩ ሁኔታ ሂደቱ ወዲያውኑ ይቋረጣል።

16.1.9.3 ከዚህ በላይ በንኡስ አንቀጽ 16.1.9.1 የተመለከተው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አንድ ተባባሪ አባል ተከራካሪ ወገን በሆነበት ማንኛውም ክርክር

በምርት ገበያው ንኡስ አንቀጽ 16.1.9.1 መሰረት ተቀማጭ ገንዘቡን ካላስቀመጠ፣ አብሮት የሚሠራው አባል ይህንኑ ተቀማጭ ገንዘብ በምርት ገበያው ያስቀምጣል።

16.1.9.4 በተከራካሪዎች የሚቀመጠው የተቀማጭ ገንዘብ መጠን በየጊዜው በምርት ገበያው የሚወሰን ሲሆን፣ ይህን መጠን ለመወሰን ምርት ገበያው የክሱን ዋጋ ወይም ተመን እና የግልግል ዳኞችን ወጪ ከግምት ያስገባል። ይህን ተቀማጭ ሂሣብ ተከራካሪዎች በእኩል መጠን ለግልግል ዳኝነቱ ወጪ የሚያስቀምጡት ይሆናል ።

16.1.9.5 የግልግል ዳኝነቱ ወጪው ከተከፈለ በኋላ የሚተርፈው ቀሪ ገንዘብ ለተከራካሪው ወገን ወይም ለተከራካሪ ወገኖች ተመላሽ ይሆናል። ማንኛውም ለወጪዎችና ክፍያዎች የሚያገለግል ገንዘብ ተቀማጭ የሚሆነው ምርት ገበያው ዘንድ ነው። ተከራካሪ ወገኖች ለግልግል ዳኞች ማናቸውንም ክፍያዎች በቀጥታ ለመክፈል አይችሉም።

16.1.9.6 ከላይ በ ንኡስ አንቀጽ 16.1.9.3 ላይ የተመለከተው ቢኖርም ምርት ገበያው የተሰጡት ተቀማጭ ገንዘቦች የግልግል ዳኝነቱን ወጪ ለመሸፈን በቂ አይደሉም ብሎ በሚያምንበት ጊዜ ተጨማሪ ገንዘብ ተቀማጭ እንዲያደርጉ ሊያዝ ይችላል። ይህ ተጨማሪ ገንዘብ በተቀማጭ ገንዘብነት የሚታይና የሚስተናገድ ይሆናል።

16.1.10 የግልግል /የሽምግልና ዳኝነት ሥነ-ሥርዓት

16.1.10.1 አመልካቹ የግልግል ማመልከቻውን ምርት ገበያው ባዘጋጀው ቅጽ መሠረት አዘጋጅቶ ለምርት ገበያው (ለብቸኛየግልግል ዳኛ ሦስት ቅጂዎች ለግልግል ዳኞች ጉባኤ ደግሞ አምስት ቅጂዎች) ከሚከተሉት ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት።

ሀ. የክሱ መግለጫ (የተከራካሪ ወገኖችን ስም፣ አግባብነት ያላቸውን የክርክሩ ፍሬ ነገሮች እና የተፈለገው መፍትሔ ወይም ካሣ)፣

ለ. የሂሣብ መግለጫ፣

ሐ. አግባብነት ያላቸውን ውሎች፣ ደረሰኝ (ፋክቱር) ኢንቮይስ፣ ሌሎች ሰነዶች ቅጂዎች።

16.1.10.2 አመልካቹ ከማመልከቻው ጋር የሚከተሉትን ለምርት ገበያው በተጨማሪ ማቅረብ አለበት፣

ሀ. በግልግል ዳኝነቱ መቀመጫ ለምርት ገበያው ተከፋይ የሚሆን ተቀማጭ ቼክ /ክፈል ትዕዛዝ/ በዕይታ ለሦስተኛ ወገኖች የሚከፈል ድራፍት እና

ለ. የግልግል ዳኞች ሆነው ሊመረጡ የሚችሉ ሰዎች ስም ዝርዝር።

16.1.10.3 በማመልከቻው ላይ ጉድለት ከተገኘበት ምርት ገበያው አመልካቹ ይህን ጉድለት እንዲያስተካክል ያደርገዋል። አመልካቹም ከምርት ገበያው እንዲያስተካክል የተላለፈለት መረጃ በደረሰው በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ጉድለቱን ማስተካከል አለበት። አመልካቹ በተጠቀሱት ቀናት ውስጥ ጉድለቱን ማስተካከል ካልቻለ የምርት ገበያው ይህንኑ ጉድለት ያለበትን ማመልከቻ ለአመልካቹ ይመልስለታል። ሆኖም አመልካቹ የተሻሻለ ማመልከቻ የማቅረብ መብት አለው። ማመልከቻው ግን ለማናቸውም ዓላማ እንደ አዲስ ተቆጥሮ በአዲስነት ይስተናገዳል።

16.1.10.4 ምርት ገበያው ማመልከቻው እንደደረሰው፣ የክሱ መግለጫና ሌሎች ሰነዶችን ቅጂ ለተጠሪው ይልክለታል።

16.1.10.5 ተጠሪውም፣ የክስ መግለጫው በደረሰው ሰባት ቀናት ውስጥ ብቸኛ የግልግል ዳኛ ከሆነ ሦስት ቅጂዎችን፣ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ ከሆነ አምስት የመልስ ወይም መከላከያ መግለጫዎችን ከሚከተሉት ጋር አያይዞ ለምርት ገበያው ያቀርባል።

ሀ. የመልስ ወይም መከላከያ መግለጫ (ከቀረበው ክስ አንፃር ሊቀርቡ የሚችሉ መከላከያዎች ወይም መልሶች በሙሉ)፣

ለ. የውል ጽሑፎች፣ የደረሰኝ /ፋክቱር/ እና የርክክብ እና ሌሎች አግባብ ያላቸው ሰነዶች ቅጂዎች፣

ሐ. የመቻቻል ወይም የመልስ-ክስ መግለጫና ከዚሁ ጋርም የሂሣብ መግለጫዎች፣ የውል ጽሑፎች እና የሂሣብ መክፈያ ሰነዶች/ ቢል/ ቅጂዎች እና

መ. በግልግል መቀመጫ ቦታ ለምርት ገበያው ተከፋይ የሚሆን ተቀማጭ ቼክ (የክፍያ ትዕዛዝ) በዕይታ ለሦስተኛ ወገኖች የሚከፈል ድራፍት።

16.1.10.6 ተጠሪው በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መልስ ካልሰጠ የግልግል ዳኛው የግልግሉን ሂደት በመቀጠል ተጠሪው በሌለበት ፍርዱን መስጠት ይችላል።

16.1.10.7 ምርት ገበያው የተጠሪው መልስ እንደደረሰው የመልሱን አንድ ቅጂ ለአመልካቹ ይልክለታል። አመልካቹም የተጠሪው መልስ በደረሰው በአሥር ቀናት ውስጥ በአመልካቹ ማመልከቻ ተመሥርቶ የተነሣ የመልስ ክስ ካለ ምላሹን ለምርት ገበያው ያቀርባል። ምርት ገበያውም ይህንኑ ምላሽ ለተጠሪው ይልክለታል።

16.1.10.8 ከጉዳዩ ጋር ከተያያዙ ሁኔታዎች በመነሣትና ከግልግል ዳኛው ጋር በመመካከር የምርት ገበያው እዚህ ላይ የተገለጸውን የማመልከቻ ማቅረቢያ የጊዜ ወሰንን ሊያራዝመው ይችላል።

16.1.11 ለግልግል ዳኝነቱ መሰማት አስፈላጊ ነገሮች

16.1.11.1 የክርክሩ ዋጋ ተመን ብር 1000 /አንድ ሺህ/ እና ከዚያ ያነሠ እንደሆነ ለተከራካሪዎች የመሰማት ሥርዓት ማካሄድ አስፈላጊ አይሆንም። በዚህን ጊዜ የግልግል ዳኛው (ዳኞቹ) በተከራካሪ ወገኖች በቀረቡለት/ በቀረቡላቸው ሰነዶች መሠረት ጉዳዩን ይወስናል/ ይወስናሉ። ሆኖም የግልግል ዳኛው/ዳኞቹ/ ምክንያቱን በጽሑፍ በማስፈር ሁለቱንም ተከራካሪ ወገኖች ሊሰሙ ይችላል።

16.1.11.2 የክርክሩ ዋጋ ተመን ከብር ከ1000 /አንድ ሺህ/ የሚበልጥ ከሆነ ተከራካሪ ወገኖቹ የመስማት መብታቸውን መተዋቸውን በጽሑፍ ካልገለፁ በስተቀር የግልግል ዳኞቹ ተከራካሪዎች እንዲሰሙ ያደርጋሉ ።

16.1.12 ጊዜያዊ ትዕዛዞችን የመስጠት ሥልጣን

የተከራካሪ ወገኖችን መብቶችና የክርክሩን የመጨረሻ ውሳኔ በማይጐዳ ሁኔታ የግልግል ዳኛው /ዳኞች/ ጊዜያዊ ትዕዛዞች ሊሰጡ ይችላሉ። ይኸውም ጥበቃን፣ በጊዜያዊነት በአደራ ጥበቃ መስጠት፣ በጥንቃቄ ማስቀመጥን፣ መከላከልን፣ ማቆየትን የክርክሩ መነሻ የሆነውን ጉዳይ በሙሉ ወይም በከፊል መሸጥ ወይም ለዕይታ ወይም ምርመራ ወይም ለናሙና መስጠትን ያጠቃልላል።

16.1.13 የመሰማት ማስታወቂያ

በተለየ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር የምርት ገበያው ከግልግል ዳኛው ወይም ጉባኤው ጋር በመመካከር ጉዳዩ መሰማት የሚጀመርበትን ቀን፣ ጊዜና ቦታ ይወሰናል። ተከራካሪ ወገኖቹ በመስማማት ማስታወቂያ መስጠትን ለማስቀረት ካልተስማሙ በስተቀር፣ የመጀመያሪው መስሚያ ቀን ማስታወቂያ ቢያንስ ከመስሚያው ቀን አሥር ቀናት አስቀድሞ መሰጠት አለበት። በመቀጠል የግልግል ዳኛው ወይም ጉባኤው ጉዳዩ የሚሰማበትን ሰዓቱን፣ ጊዜንና ቦታውን ይወስናል። የምርት ገበያው ለሚመለከታቸው ተከራካሪ ወገኖች መጥሪያ እንዲደርሳቸው ያደርጋል።

16.1.14 ጉዳዩ በሚሰማበት ቀን ስለመገኘት

ከግልግል ዳኛው ወይም ከጉባኤው የተሰጡ መመሪያዎች በተከራካሪ ወገኖች ባይከበሩም፣ የግልግል ዳኛው ወይም ጉባኤው ጉዳዩን ሊያንቀሳቅስ፣ መስማቱን ሊቀጥል፣ ወይም ሊወስን ይችላል። መጥሪያ ደርሷቸው የግልግል ዳኛው ወይም ጉባኤው በወሰነው ቀን፣ ሰዓትና ቦታ ባይገኝ የቀረ፣ የቀሩ፣ ወይም ለመገኘት ፈቃደኛ ያልሆነ ወይም ያልሆኑ ተከራካሪ ወገን ወይም ተከራካሪ ወኖች ካሉ ጉዳዩ መሰማት ይቀጥላል።

16.1.15 የመሰማት ቀጠሮ

16.1.15.1 ጉዳዩ እንዲሰማ የተቀጠረበት ቀን እንዲተላለፍለት የሚፈልግ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን፣ ቀነ-ቀጠሮው እንዲተላለፍ የተፈለገበትን ምክንያት በግለጽ የምርት ገበያው ለግልግል ዳኛው ወይም ጉባኤው የመላኪያ እንዲኖረው አስቀድሞ ማመልከቻውን ለምርት ገበያው መላክ አለበት።

16.1.15.2 የግልግል ዳኛው አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በማስቀመጥ የተጠየቀውን ቀጠሮ ለመፍቀድ ይችላል።

165.1.15.3 በግልግል ዳኝነት ሂደት አንድን ተከራካሪ የሚወክል ሰው በተከራካሪው ወይም ወካዩ በአግባቡ የተፈፀመና በውልና ማስረጃ የተመዘገበ የውክልና ሥልጣን አቅርቦ መወከል ይችላል። አባል ከሆነ ግን አባሉ ራሱ ወይም ሥልጣን የተሰጠው ወኪሉ በመሰማቱ ጊዜ ሊቀርብ ይችላል። ለዚህ ደንብ ዓላማ ሥልጣን የተሰጠው ወኪል ማለት ፡-

ሀ. ግለሰብ - አባሉን የሚወክል ተቀጣሪ ወይም ሥልጣን የተሰጠው ሰው፣

ለ. የሽርክና ድርጅት- አንድ ሸሪክ ወይም ተቀጣሪ ወይም ሥልጣን የተሰጠው ሰው ወይም

ሐ. ድርጅት/ ኩባንያ- ማንኛውም ዳይሬክተር ወይም ተቀጣሪ፣ ወይም ሥልጣን የተሰጠው ሰው ማለት ነው።

16.1.16 በተከራካሪ ወገኖች ስምምነት መሠረት የተሰጠ የግልግል ዳኝነት ውሣኔ፤

የግልግል ዳኛው ከተሾመ በኋላ ተከራካሪ ወገኖች ክርክራቸውን ራሳቸው ቢፈቱ የግልግል ዳኛው ይህንን ስምምነት በተከራካሪዎች የስምምነት ቃሎች መሠረት የተሰጠ የሽምግልና ውሣኔ አድርጎ ይመዘግበዋል።

16.1.17 የግልግል ውሳኔ ስለመስጠት

16.1.17.1 ከአንድ በላይ የግልግል ዳኛ በሚኖርበት የግልግል ሂደት፣ ማንኛውም ውሣኔ በድምፅ ብልጫ ይወሰናል።

16.1.17.2 የግልግል ውሣኔው በጽሑፍ ሆኖ ሦስት ዋናዎች /ኦሪጂናሎች/ ተዘጋጅተው በሁሉም ላይ፣ ብቸኛ የግልግል ዳኛ ከሆነ ይኸው የግልግል ዳኛ፣ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ አባላት ከሆኑ ሦስቱም የግልግል ዳኞች ቀኑን ጽፈው መፈረም አለባቸው።

16.1.17.3 የግልግል ዳኛው ወይም ጉባኤው ሦስቱን ዋና ቅጂዎች ለምርት ገበያው ያስተላልፋል። ምርት ገበያውም አንድና ዋናውን ቅጂ ለራሱ በማስቀረት የተቀሩትን አንዳንድ ቅጂዎች ለያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን ያስተላልፋል።

16.1.18 የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ እና የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ መልስ

16.1.18.1 በግልግል ዳኝነት ተጠሪ የሆነው ወገን በከሳሹ ላይ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ማቅረብ የሚችል ሲሆን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ለዋናው/ለመጀመሪያው ክስ መነሻ ከሆነ ግብይት የመነጨ መሆን አለበት። ተጠሪው የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱን ከነሙሉ ዝርዝሮችና ደጋፊ ሰነዶች እንዲሁም የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ መነሻ መረጃዎችን በአሥር ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለበት። (ለመጀመሪያው/ዋናው ክስ የመከላከያ መልስ ለማቅረብ)

16.1.18.2 የመጀመሪያው ክስ አቅራቢ የግልግል ዳኛው /ጉባኤው በሚወስኑት ጊዜ ወይም ዳኛው ወይም ጉባኤው ለማራዘም በሚፈቅዱበት ጊዜ ውስጥ ለቀረበው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ መልሱን ያቀርባል። የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ የቀረበው መልስና ሌሎች የተያያዙ ሰነዶች ካሉ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ላቀረበው ተከራካሪ ወገን በመረጃነት ያገለግሉ ዘንድ ይላካሉ ።

16.1.18.3 በመጀመሪያው ክስ ላይ እንዲዳኙ የተሾሙት የግልግል ዳኛ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ የግልግል ጉባኤው ዳኞች በተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ላይ የመወሰን ሥልጣን ይኖራቸዋል። በመሆኑም የግልግል ዳኝነቱን እንዲያይ በተሾመው ዳኛ ወይም ዳኞች ላይ ሌላ ዳኛ አይጨመርም፣ የነበሩትም አይቀነሱም።

16.1.19 ወለድ

16.1.19.1 በሂሣቡ ውስጥ የግልግል ዳኛው ተገቢ ነው ብሎ የሚያስበውን የወለድ መጠንና የወለዱን ጊዜ በውሣኔው ላይ በተመለከተው ገንዘብ ላይ ሊጨምረው ይችላል።

16.1.19.2 በግልግል ዳኝነቱ ውሳኔው መሠረት የሚከፈለው ገንዘብ /ክፍያ/ በግልግል ውሣኔው በሌላ አኳኋን ካልተመለከተ በስተቀር የግልግል ውሣኔው ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ክፍያው እስከሚፈፀምበት ቀን ድረስ በወቅቱ ባለው ዓመታዊ የንግድ ወለድ መጠን መሠረት ወለድ ይታሰባል።

16.1.20 የግልግል ክፍያ ፣ ተከፋዮች እና ወጪዎች

16.1.20.1 ለግልግል ዳኛው ተከፋይ የሚሆኑ ክፍያዎችና ወጪዎች በምርት ገበያው በየጊዜው ይወሰናሉ፣

16.1.20.2 የግልግል ዳኞችን ለመሾምና ለግልግል ሂደቱ የወጡ ወጪዎች የግልግል ዳኛው/ዎቹ ተገቢ ነው ተብሎ በሚውሰነው መጠን በተከራካሪ ወገኖች እንዲሸፈን ካልተወሰነ በስተቀር ወጪው የሚሸፈነው በክርክሩ በተሸነፈው ወገን ይሆናል።

16.1.20.3 የግልግል ዳኝነቱን ለማካሄድ በተከራካሪዎቹ ወገኖች ከተሸፈኑ ክፍያዎች በተጨማሪ ለአንደኛው ተከራካሪ ወገን የሚከፈል ወጪ ካለ በግልግል ዳኛ መወሰን አለበት።

16.1.20.4 የግልግል ዳኛው በሌላ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር እያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን የራሱን የጉዞ ወጪዎችንና ሌሎች ወጪዎችን ራሱ ይሸፍናል።

16.1.21 ሌሎች ክፍያዎችና ወጪዎች

የግልግል ዳኛው የምስክሮችን ክፍያና ወጪ፣ ናሙናዎችን ለመምረጥና ለማጓጓዝ የወጣ ወጪን፣ የዕቃዎች ምርመራ ወጪ፣ የማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሰጪ ተቋማት ወጪንና ማጓጓዣ ፣ ኪራይ ፣ ከግልግል ጋር የሕግና የቴክኒክ ምክር ወጪ

ወይም ሌሎች ከግልግል ዳኝነቱ ውሣኔው ጋር የተያያዙ ወጪዎች እና ክፍያዎችን ለመፍቀድ ሥልጣን አለው።

16.1.22 ክሶችን ስለማጣመር

ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የሽምግልና ዳኝነት ማመልከቻዎች በሚኖሩበት ጊዜ እና የክርክሩ ጭብጦች መነሻ ጉዳዮች ተመሣሣይ ከሆኑ፣ ምርት ገበያው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውና በተከራካሪዎች ፈቃድ መሰማቱ እንዲጣመር ወይም ተከራካሪ ወገኖች ባልተስማሙ ጊዜ ማመልከቻዎቹ በተለያየ ጊዜ እንዲታዩ ሊመራቸው ይችላል። ማመልከቻዎቹ ተጣምረው ከታዩ ግን የእያንዳንዱ ክርክር ውሣኔ ለየብቻ ተለይቶ ይሰጣል።

16.1.23 በምርት ገበያው የሚሰጥ አስተዳደራዊ አገልግሎት

የምርት ገበያው፦

16.1.23.1 የማመልከቻዎችን መዝገብ ይይዛል፣

16.1.23.2 ከግልግል ሂደት በፊት ወይም በሂደቱ ወቅት ወይም ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከተከራካሪ ወገኖች የሚቀርቡ የሽምግልና ዳኝነት ማመልከቻዎችንና ሌሎች ጽሑፎችን ይቀበላል።

16.1.23.3 ማንኛውንም የወጪ፣ የክፍያ እና ሌሎች ወጪዎችን ክፍያዎች ይቀበላል፣

16.1.23.4 ከግልግልሂደት በፊት ወይም በሂደቱ ወቅት ወይም ከዚሁ ጋር በተያያዘ የመሰማት ማስታወቂያዎችንና ሌሎች ማስታወቂያዎችን ይሰጣል፣

16.1.23.5 የግልግል ዳኛውን መመሪያዎችና ትዕዛዞችን ለተከራካሪዎች ያስተላልፋል /ያሳውቃል/፣

16.1.23.6 ሰነዶችን በሙሉ እና ከማመልከቻው ጋር የተያያዙ ወረቀቶችን ይቀበላል፣ ይመዘግባል።እንዲሁም ተከራካሪ ወገኖች እንዲያስቀሯቸው/እንዲይዛቸው ከተፈቀደላቸው ውጭ ያሉትን እነዚህን ሰነዶችና ወረቀቶች ያስቀምጣል፣

16.1.23.7 በግልግል ዳኛ ስም ውሣኔዎችን ያሳውቃል እና

16.1.23.8 የግልግል ዳኛው ስራውን ለማከናወን የሚያግዙትን ሌሎች ነገሮችንና እርምጃዎችን ይወስዳል።

16.1.24 የተከራካሪዎች ግዴታ

16.1.24.1 ተከራካሪ ወገኖች የግልግል ዳኝነቱ ሥራውን በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲያካሂድና እንዲወስን ማንኛውንም አስፈላጊ ነገር መፈፀም አለባቸው። እንዲሁም የግልግል ሂደቱን የሚያጓትት ወይም የግልግል ዳኝነቱ በተቀላጠፈ ሁኔታ ውሣኔ እንዳይሰጥ ማድረግ ወይም ማስደረግ የለባቸውም። አንድ ተከራካሪ ወገን ይህን መጓተት የፈጠረ ወይም መጓተቱ እንዲፈጠር ያደረገ እንደሆነ የግልግል ዳኝነቱ ተገቢ ነው ብሎ ያሰበውን ወጪ እንዲከፍል ይደረጋል።

16.1.24.2 ተከራካሪ ወገኖች የመጨረሻ እና ይግባኝ የማይባልበትን የግልግል ዳኝነቱን ውሳኔ ማክበር አለባቸው።

16.1.25 የባለሙያ ምክር

የግልግል ዳኛው/ዳኞች የመጨረሻውን ውሣኔ ከመስጠቱ/ከመሰጠታቸው በፊት በማንኛውም ጊዜና በተከራካሪ ወገኖች ወጪ በክርክሩ የተመለከተውን በአንድ ኢንዱስትሪ፣ ምርት ወይም የንግድ ቅርንጫፍ ልዩ ዕውቀት ያለውን ሰው ወይም ማንኛውንም ልዩ ባለሙያ ወይም የሂሣብ አዋቂ የማማከርና አስተያየቱን የመቀበል ሥልጣን አለው/አላቸው። እንደዚሁም ከተከራካሪ ወገኖች ወጪ፣ ጠበቆችን፣ የሕግ ባለሙያዎችን እና የሕግ አማካሪዎችን ቴክኒካዊ የሕግ፣የማስረጃ የአሠራር እና የሥነ-ሥርዓት ጥያቄዎች ወይም ነጥቦች ላይ ማማከር ይችላል/ይችላሉ። የሽምግልና

ዳኛውበነዚህ ምክሮች ላይ በመመሥረት በዋና ጭብጦች ላይ ባለሙያው በቃል መሰማት ላይ እንዲሳተፍና በተያዙ ነጥቦች ወይም ጭብጦች ላይ የባለሙያ አስተያየቱ እንዲሰጥ ለመወሰን ይችላል።

16.1.26 ቋንቋ

የሽምግልናው ሂደትና ውሳኔ ቋንቋ አማርኛ ይሆናል። በተከራካሪ ወገኖች የቀረቡ ሰነዶች በአማርኛ ቋንቋ ካልሆኑ እነዚህን ሰነዶች ያቀረበው ተከራካሪ ወገን ከነዚሁ ሰነዶች ጐን ለጐን የአማርኛ ትርጓሜያቸውን ያቀርባል።

16.1.27 የመገናኛ ዘዴ

16.1.27.1 ተከራካሪ ወገኖች አልደረሰንም፣ አልተቀበልንም፣ ለመቀበል አልፈቀድንም የሚል ምላሽ ለምርት ገበያው ቢሰጡም በሚከተሉት መደበኛ የሥራ ቦታ አድራሻዎች፣ መደበኛ መኖሪያ ቦታ ወይም የተከራካሪ ወገን የመጨረሻው የታወቀ አድራሻውን ተከትሎ ወረድ ብሎ በተመለከቱት መንገዶች የተላከ ማንኛውም ጽሑፍ ወይም መላላክ በትክክለኛ መንገድ የተላከና የደረሰ እንደሆነ ይቆጠራል።

ሀ. በፋክስ፣

ለ. በፖስታ፣

ሐ. በቴሌግራም፣

መ. በእጅ በማድረስ፣

ሠ. ሀገር አቀፍ ሥርጭት ባለው በታወቀ አንድ ጋዜጣ ወይም በመጨረሻ በታወቀው የተከራካሪ ወገኖች አድራሻ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ በሚወጣ ማስታወቂያ ወይም

ረ. በመጨረሻ በታወቀው የሥራ ወይም የመኖሪያ አድራሻ በር ላይ በመለጠፍ፤

16.1.27.2 ተከራካሪ ወገኖች ለምርት ገበያው ከሚከተሉት የመገናኛ መንገዶች በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ በመጠቀም መላክ አለባቸው።

ሀ. በፋክስ፣

ለ. በፖስታ፣

ሐ. በቴሌግራም፣

መ. በእጅ በማድረስ፣

ሠ. ሀገር አቀፍ ሥርጭት ባለው በታወቀ ቢያንስ አንድ ጋዜጣ ወይም በመጨረሻ በታወቀው የተከራካሪ ወገኖች አድራሻ አካባቢ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ በሚወጣ ማስታወቂያ ወይም

ረ. በመጨረሻ በታወቀው የሥራ ወይም የመኖሪያ አድራሻ በር ላይ በመለጠፍ።

16.2 የባለሙያ ውሳኔ

16.2.1 ከቡና በስተቀር የሌሎች ምርቶች ደረጃ ምደባ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ ሥነ-ስርዓት

16.2.1.1 አስቀማጩ በምርት ገበያው ማከማቻ መጋዘን ውስጥ የሚቀመጠው ምርት በተሰጠው ደረጃ ላይ ያለውን ቅሬታ በይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

16.2.1.2 በደረጃ አመዳደብ ላይ የሚቀርብ የይግባኝ አቤቱታ የመጀመሪያው የምደባ መግለጫ በደረሰ በአንድ ቀን ጊዜ ውስጥ በምርት ገበያው በተዘጋጀ ይግባኝ ቅጽ መሰረት በጽሑፍ ሰፍሮ ለሚመለከተው ማከማቻ መጋዘን ስራ አስኪያጅ መቅረብ አለበት።

16.2.1.3 ተከራካሪ ወገኖች ባልተስማሙ ጊዜ፣ የኢተምድ ኢንስፔክተር ተከራካሪ ወገኖች እና ተወካዮቻቸው በተገኙበት የወሰደው ናሙና አስገዳጅ እንደሆነ ይቆጠራል። የመጀመሪያ ይግባኝ የማከማቻ መጋዘን ሥራ አስኪያጅ በያዘው ናሙና ላይ መሠረት አድርጎ መቅረብ ይኖርበታል።

16.2.1.4 ሥልጣን ያለው የኢተምድ ተወካይ ወዲያውኑ ናሙናውን መመርመርና የደረጃ ሰርተፊኬት መስጠት አለበት። በኢተምድ ተወካይ የተሰጠው ሰርተፊኬት መጀመሪያ ከተሰጠው የደረጃ ሠርተፊኬት ቀዳሚነት/ብልጫ ያለው ሆኖ የምርት ደረጃውን ይወስናል።

16.2.1.5 ይግባኙን ለመወሰን በምርቱ ላይ የሚደረግ ምርመራ የሚያስከትለው ወጪ በይግባኝ ክርክሩ በተረታው ተከራካሪ ወገን የሚሸፈን ይሆናል።

16.2.1.6 ምርቱ በምርት ገበያ ብቻ ግብይት እንዲካሄድበት በሕግ የሚጠበቅ ካልሆነ በስተቀር፣ የምርቱ ባለቤት ወይም ወኪሉ ከይግባኝ ውሳኔው በኋላ የተጠቀሰውን ምርት በምርት ገበያው መጋዘን ውስጥ እንዲያስቀምጥ አይገደድም፡፡ ሆኖም ባለቤቱ ምርቱን በማከማቻ መጋዘኑ ውስጥ ማስቀመጥ ከፈለገ በይግባኝ ውሳኔው በመጨረሻ በተሰጠው ደረጃ መሰረት መቀመጥ አለበት፡፡

16.2.2 በቡና ደረጃ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ ሥነ-ስርዓት

በግብርና ሚኒስቴር ስር የሚገኘው የቡና ጥራትና ቁጥጥር ማእከል(ከዚህ በኋላ የግብርና ሚኒስቴር የጥራት ቁጥጥር ክፍል ተብሎ በሚጠራዉ) ከቡና ጥራት ጋር በተያያዘ በምርት ገበያው እና በገዢ ወይም በአስቀማጭ መካከል የሚነሳ ክርክርን በሚከተሉት ድንጋጌዎች መሰረት ይወስናል።ቢሆንም የቡና ጥራት ደረጃ ወደ አገር ውስጥ ደረጃ ዝቅ እንዲደረግ በቡና አስቀማጭ ወይም ገዥ የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረዉም።

16.2.2.1 የቅሬታ አቀራረብ

16.2.2.1.1 ሁሉም ወገኖች ያለመግባባቶቻቸዉን ለባለሙያ ዉሳኔ ከማቅረባቸዉ በፊት በዉይይት/በድርድር ለመፍታት ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

16.2.2.1.2 ያለመግባባቶችን በቅድሚያ በዉይይት/በድርድር ለመፍታት የሚደረግ ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ; የቡና ጥራትን በተመለከተ በምርት ገበያዉ ላይ ቅሬታ ማቅረብ የሚፈልግ ማናቸዉም አስቀማጭ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ካላቃተዉ በስተቀር ቅሬታዉን ለቅሬታዉ ምክንያት የሆነዉን በምርት ገበያው የተሰጠውን ዉሳኔ ባወቀ በ24 ሰዓት ዉስጥ ለግብርና ሚኒስቴር ቡና ጥራት ቁጥጥር ክፍል ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ የቅሬታ አቤቱታው በምርት ገበያው የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ይቀርባል፡፡

16.2.2.1.3 የግብርና ሚኒስቴር የቡና ጥራት ቁጥጥር ክፍልም ቅሬታዉ በደረሰዉ በሦስት የስራ ቀናት ዉስጥ የሚከተሉትን ይፈጽማል።

ሀ. አስቀድሞ በምርት ገበያዉ ተይዞ የነበረዉን የምርቱን ዋቤ ናሙና ይወስዳል፣

ለ. ቅሬታዉን የሚፈታዉን የባለሙያዎች ቡድን ከራሱ ሰራተኞች ሦስት እንድሁም ከምርት ገበያዉ እና ከቅሬታ አቅራቢዉ ከእያንዳንዳቸዉ አንድ አንድ ባለሙያዎችን በመጥራት አምስት አባላት ያለዉ ጉባኤ ያደራጃል። በመሆኑም ቅሬታ አቅራቢዉ ወይም ምርት ገበያዉ ባለሙያ ለመመደብ

ካልቻለ ወይም ካልፈለገ እንደነገሩ ሁኔታ የግብርና ሚኒስቴር ቡና ጥራት ቁጥጥር ክፍል አንድ ወይም ሁለት ተጨማሪ ባለሙያ/ዎች በመመደብ ጎዶሎ ቁጥር ያለው የባለሙያዎች ጉባኤ ያደራጃል፣ እንዲሁም

ሐ. የባለሙያ ዉሳኔዉ አሰጣጥ ሂደቱን በመምራት የመጨረሻዉን ዉሳኔ በጽሁፍ ለምርት ገበያዉ እና ለቅሬታ አቅራቢዉ ያሳውቃል።

16.2.2.2 የግብርና ሚኒስቴር ቡና ጥራት ቁጥጥር ክፍልም ከላይ በንዑስ አንቀፅ 16.2.2.1.3(ሀ) መሠረት ናሙናዉ እንደደረሰዉ በተመደበው ሰራኛዉ አማካኝነት በናሙናዉ ላይ ያሉትን ምልክቶች'የከረጢቶች ቁጥር'የመኪና ታርጋ ቁጥር እና የመጠን ማመልከቻ ጽሁፎች ካሉ ጽሁፎቹን በማንሳት ከእራሱ ውጭ ሌላ ሰው የማይረዳውን ምልክት መስጠት አለበት። የዚህ ተግባር ዓላማ የቡናዉ ባለቤት ማንነት ለባለሙያዎቹ እንዳይታወቅ ለማድረግ ነዉ።

16.2.2.3 የጥራት ባለሙያዎች ጉባኤ

በንኡስ አንቀጽ 16.2.2.1.3 (ለ) በተገለጸዉ መሠረት ከምርት ገበያዉ እና ከቅሬታ አቅራቢዉ ከእያንዳንዳቸዉ አንድ አንድ ባለሙያዎች እና ከግብርና ሚኒስቴር ቡና ጥራት ቁጥጥር ክፍል ሦስት የጥራት ባለሙያዎች የተካተቱበት አምስት አባላት ያሉት ያለመግባባት በተነሳ ጊዜ የሚሰየም ጊዜያዊ የጥራት ባለሙያዎች ጉባኤ (ከዚህ በኋላ “ጉባኤዉ” እየተባለ የሚጠራ)ይኖራል።

16.2.2.4 ገዥ የዉሳኔ መሠረት

የናሙና ምርመራዉ የሚደረገዉ በምርት ገበያዉ የጥራት እና ደረጃ ምርመራ መመሪያ መሠረት ነዉ።

16.2.2.5 ሂደቱ

16.2.2.5.1 የግብርና ሚኒስቴር ቡና ጥራት ቁጥጥር ክፍል ያለመግባባት የተነሳበትን የቡና ናሙና ከሌሎች ሁለት ያለመግባባቱ ከተነሳበት ቡና ጋር አንድ አይነት ደረጃ ካላቸዉ ማስመሰያ የቡና ናሙናዎች ጋር በማሳጀብ ለጉባኤዉ ያቀርባል። የናሙናዎቹ ምርመራ በአንድ ላቦራቶሪ በአንድ ጊዜ በሦስት ሰዓታት ውስጥ ተደርጎ መጠናቀቅ ይኖርበታል።

16.2.2.5.2 እያንዳንዱ ባለሙያ በግሉ እና ሌሎችን ባለሙያዎች ሳያማክር የቡናዎቹን ደረጃ በጥሬ ግምገማ እና በቅምሻ ብቻ መወሰን ይኖርበታል።

16.2.2.5.3 ሁሉም የጉባኤዉ አባላት የጥሬ ግምገማቸዉን እና ቅምሻቸዉን ከጨረሱ በኋላ የጉባኤዉ ሰብሳቢ የእያንዳንዱን ባለሙያ ግኝት በማጠቃለል ውሳኔውን በአብላጫዉ ግኝት መሠረት ይጽፋል። አብላጫ ባልተገኘ ጊዜ ወይም ጉባኤዉ እኩል በተከፈለ ጊዜ ሰብሳቢዉ ያለበት ቡድን ግኝት የጉባኤዉ ዉሳኔ ይሆናል። በዚህ አንቀጽ ውስጥ አብላጫ ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ባለሙያዎች ግኝት አንድነት ማለት ነዉ።

16.2.2.6 የባለሙያዎቹ ሚና

16.2.2.6.1 እያንዳንዱ ባለሙያ የጥራት/ደረጃ ክርክሩን ለመፍታት የሚያደርገዉን ምርመራ በዚህ ደንብ እና የሚኖር ከሆነ አግባብነት ባለዉ ህግ መሠረት ማካሄድ ይኖርበታል።

16.2.2.6.2 ባለጉዳዮቹ (የምርት ገበያዉ እና አባሉ)፤

ሀ. የጥራት ባለሙያዎቹ ያለመግባባቱን የሚዳኙ የግልግል ዳኞች እንዳልሆኑ እንዲሁም እንደገላጋይ ዳኛ እንደማይታዩ፣

ለ. ሂደቱም በየትኛዉም የህግ ትርጉም የግልግል ዳኝነት ሂደት እንዳልሆነ ተስማምተዋል።

16.2.2.7 በባለሙያ ዉሳኔ ሂደት ወቅት የባለጉዳዮቹ ግዴታ

የምርት ገበያዉ እና የቅሬታ አቅራቢዉ ባለሙያዎች በጥራት ባለሙያዎች ጉባኤ የመሳተፍ መብታቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባኤዉ አንዴ ምርመራዉን ከጀመረ በኋላ ባለጉዳዮቹ ወደ ግብርና ሚኒስቴር ቡና ጥራት ቁጥጥር ክፍል መሄድ የለባቸዉም።

16.2.2.8 በክርክር ላይ ያለዉ ቡና አያያዝ

16.2.2.8.1 ክርክሩ በአቅራቢ እና በምርት ገበያዉ መካከል በሚሆንበት ጊዜ በቀረበው የጥራት/ደረጃ ክርክር ላይ የግብርና ሚኒስቴር ቡና ጥራት ቁጥጥር ክፍል ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ላለመግባባቱ መነሻ የሆነው ቡና በመኪናዉ ላይ እንደተጫነ የምርት ገበያዉ መጋዘን ባለበት ግቢ ዉስጥ እንደቆመ ይቆያል። በዚህ ጊዜ የግብርና ሚኒስቴር ቡና ጥራት ቁጥጥር ክፍል በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ የምርት ገበያዉ ቡናዉን መልሶ ማሸግ ይችላል።

16.2.2.8.2 ገዥው ቡናውን ተረክቦ ቡናው መኪና ላይ ከተጫነ በኋላ መኪናው የምርት ገበያውን መጋዘን ግቢ ከመልቀቁ በፊት ገዥው ወይም ተወካዩ እና የግብርና ሚኒስቴር የቡና ጥራት ቁጥጥር ክፍል ሰራተኛ በተገኙበት ከእያንዳንዱ መደብ አጠቃላይና ወካይ የሆነ ሶስት ኪግ የሚሆን ቡና ከያንዳንዱ ከረጢት ላይ የምርት ገበያው ናሙና መውሰድ አለበት:: ናሙናው በሶስት ተከፍሎ አንዱ በምርት ገበያው የሥራ ናሙና፣ ሁለተኛው ክፍል በምርት ገበያው ደህንነቱ በተጠበቀ እቃ በጥንቃቄ የሚቀመጥ ሆኖ በምርት ገበያውና በግብርና ሚኒስቴር የቡና ጥራት ቁጥጥር ክፍል የተመደበ ሰራተኛ በጋራ የሚይዙት ዋቤ ናሙና ሲሆን ሶስተኛው ለገዥው ወይም ለወኪሉ የሚሰጥ የጭነት ናሙና ይሆናል::

16.2.2.8.3 ቡናው በገዥው የንግድ ቦታ እንደደረሰ ገዥው በጭነት ናሙናው መሰረት ብቻ ቡናውን ከምርት ገበያው መጋዘን ካነሳበት ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት ቀናት ውስጥ የቡናውን የጥራት ደረጃ በተመለከተ ጉዳዩን ለግብርና ሚኒስቴር የቡና የጥራት ቁጥጥር ክፍል በማቅረብ ሊቃወም ይችላል::

16.2.2.8.4 አለመግባባቱ በገዥው እና በምርት ገበያው መካከል ከሆነ የባለሞያ ዉሳኔ አሰጣጡ በንዑስ አንቀፅ 16.2.2.8.2 ተወስዶ በምርት ገበያው ለግብርና ሚኒስቴር የቡና ጥራት ቁጥጥር ክፍል የተላለፈውን የመስሪያ ናሙና መሠረት በማድረግ የሚከናወን ይሆናል::

16.2.2.8.5 የጭነት ናሙናው ከመስሪያ ናሙናው የተለየ ሆኖ ከተገኘ የባለሞያ ውሳኔ አሰጣጡ በንዑስ አንቀፅ 16.2.2.8.2 ስር የተጠቀሰውን ዋቤ ናሙና መሰረት በማድረግ ይከናወናል::

16.2.2.8.6 የባለሙያ ዉሳኔዉ ሲጠናቀቅ የቡናዉ ደረጃ በባለሙያ ዉሳኔዉ የተገለጸው ደረጃ ይሆናል።

16.2.2.9 የይግባኝ መብትን ስለመተዉ

በክርክሩ ሂደት የቡናው ጥራት ደረጃ ወርዷል ለማለት የምርት ገበያው በቂ ምክንያት ሲኖረው እንደገና ለቡናው ደረጃ የመስጠት መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ ደንብ መሰረት በጥራት ክርክር ላይ የሚሰጥ የባለሙየዎች ዉሳኔ የመጨረሻ እና አስገዳጅ ነዉ። ባለጉዳዮቹ (የምርት ገበያዉ እና አባሉ) በማንኛዉም ሁኔታ ከግብርና ሚኒስቴር ቡና ጥራት ቁጥጥር ክፍል የባለሙያዎች ዉሳኔ ላይ ይግባኝ ወደየትም እንደማይወሰድ ተስማምተዋል።

16.2.2.10 ወጭ

16.2.2.10.1 የቡና ጥራት ቁጥጥር አስተዳደራዊ ወጪዎችን ለመሸፈን የሚውለው የባለሙያ ውሳኔ ወጪ በሰዓት አንድ ሺህ (1,000) ብር ሲሆን ይህም ከላይ በንዑስ አንቀጽ 16.2.2.5.1 ለተጠቀሰው ጊዜ ይሆናል።

16.2.2.10.2 የባለሙያ ውሳኔ ሂደቱን ወጭ በክርክሩ የተረታዉ ወገን ይከፍላል።

16.2.2.10.3 በባለሙያው ውሳኔ የምርት ገበያ የተረታ ከሆነ በንዑስ አንቀፅ 16.2.2.5 መሰረት የባለሞያ ውሳኔ አሰጣጥ ወጪውን ከመሸፈን ግዴታው በተጨማሪ በገዛው ቡና እና በቀረበለት ቡና መካከል ያለውን የዋጋ ልዩነት ለገዥው ይከፍላል:: የካሳ ክፍያው ያለመግባባት መንስኤ የሆነው ቡና በተገዛበት ቀን ለተመሳሳይ ቡና የተሰጠ አማካኝ ዋጋ መሰረት ተደርጎ መሰላት አለበት:: በዕለቱ የተጠቀሰው ተመሳሳይ ቡና ግብይት ካልተፈጸመ ከዚሁ ቀን ቀደም ብሎ በተካሄደ ቀን ያለውን የተመሳሳይ ቡና ዋጋ መነሻ በማድረግ ካሳው ይሰላል::

16.2.2.11 ናሙና

ለባለሙያ ዉሳኔ ሲባል ወደ ግብርና ሚኒስቴር ቡና ጥራት ቁጥጥር ክፍል ከተላከዉ የቡና ናሙና ዉስጥ ለቅምሻ ፍጆታ ያልዋለዉ የባለሙያ ዉሳኔ ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ወደ ምርት ገበያዉ መጋዘን ይመለሳል።

16.2.2.12 ሌሎች ተፈጻሚነት ያላቸዉ ሕጎች

የምርት ገበያዉ የግልግል ዳኞች የስነምግባር መመሪያ ፣ የምርት ገበያዉ ደንብ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸዉ ሕጎች ካሉ እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ ደንብ አማካኝነት በሚካሄደዉ የባለሙያ ዉሳኔ ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

16.2.2.13 የማታልለ ድርጊት

የምርት ገበያዉ በዲሲፒሊን እና ቅጣት ደንቡ መሠረት በአባላቱ ላይ ቅጣት ለመጣል ያለዉ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ ከባለሙያ ዉሳኔ ሂደት ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ የማታልለ ድርጊቶችን በተመለከተ ያለውን ጥርጣሬ ለአቃቤ ሕግ እና/ወይም ለባለሥልጣኑ የማስታወቅ ሥልጣን አለው።

## 17. ቁጥጥር

### 17.1 የመቆጣጠር ሥልጣን

17.1.1 የምርት ገበያው አስፈላጊ ነው ብሎ ባመነ ጊዜ በምርት ግብይቱ ደንብ ከተገለፁት ዓላማዎች አንፃር የአባላትን የሂሣብ መዝገቦችን፣ ሌሎች ሪኮርዶችን እና ሰነዶችን ሊመረምር ይችላል።

17.1.2 በደንቡ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. የሂሣብ መዝገቦችና ሌሎች ሠነዶች በሚፈለገው መንገድ እየታያዙ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

ለ. የባለሥልጣኑ የአዋጅ ድንጋጌዎች እየተከበሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

ሐ. በግብይት ደንቦቹ የተለያዩ ድንጋጌዎችና ደንቡን መሠረት በማድረግ የወጡ መመሪያዎችና ትዕዛዞች መከበራቸውን ማረጋገጥ፣

መ. ከደንበኞች፣ ከምርት ገበያው አባላት ወይም ከሌሎች ሰዎች የሚቀርቡና በአባሉ እንቅስቃሴ ላይ ተጽዕኖ ያላቸውን አቤቱታዎች ተቀብሎ መመርመር፣

ሠ. በራሱ አነሳሽነት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል በአባሉ ጉዳይ ላይ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ምርመራ ማካሄድ፣

ረ. የአባላት ምርት ግብይት እና ሌሎች እንቅስቃሴዎች ጋር በተያያዘ በየጊዜው በምርት ገበያው የሚወጡ ማስታወቂያዎች ፣ሰርኩለሮች፣ ትዕዛዞችና መመሪያዎች እየተከበሩ መሆናቸውን ለማወቅ እና

ሰ. የኢትዮጵያን መንግሥት ጨምሮ በባለሥልጣኑ ወይም በሌላ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የሚወጡ መመሪያዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ።

### 17.2 ማስታወቂያ

17.2.1 በዚህ ደንብ መሠረት ማንኛውም ምርመራ ከመደረጉ በፊት ስለ ምርመራው አላማ የምርት ገበያው ለአባሉ ተገቢ በሆነ መንገድ ማሳወቅ አለበት። በዚህ ደንብ የተደነገገው ቢኖርም፣ የምርት ገበያው የተጠቀሰው ማስታወቂያ መሰጠት የለበትም ብሎ ሲያምን ያለምንም ማስታወቂያ በአባሉ ላይ ምርመራ እንዲደረግ በጽሑፍ ሊያዝ ይችላል።

17.2.2 የምርት ገበያው ባለሥልጣናት ምርመራውን ያከናውናሉ። ምርመራው የሚካሄድበት አባልም ከዚህ በታች የተመለከቱትን ግዴታዎች መወጣት አለበት።

17.2.3 በምርመራ ወቅት የአባሉ ግዴታዎች

ሀ. ማንኛውም በምርመራ ላይ ያለ አባል ዳይሬክተር፣ ሠራተኛ እንዲሁም ተቀጣሪ በእጁ ወይም በይዞታው ወይም በቁጥጥሩ ሥር ያሉ መዛግብቶች፣ የሂሣብ መግለጫዎችን እና ሌሎች ሰነዶችን ለምርት ገበያው ባለሥልጣናት መስጠት አለበት ወይም ደግሞ እነዚህ መዝገቦች፣ የሂሣብ መግለጫዎችና ሰነዶች በሌሎች ሰዎች ይዞታ ወይም ቁጥጥር ሥር ያሉ እንደሆነ እነዚህን ለማቅረብ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። እንዲሁም የተጠቀሰው ምርት ገበያው ባለሥልጣን በሚፈልግበት ጊዜ አስፈላጊውን መግለጫና መረጃ ይሰጠዋል።

ለ. አባሉ ምርት ገበያው ባለሥልጣን በእርሱ ይዞታ ያለ ቦታን /ቤት ወይንም ስለእርሱ ሆነው ቦታ የያዙ ሰዎችን ቦታ/ ቤት ይመርምር ዘንድ ተገቢውን ፈቃድ ይሰጠዋል። እንደዚሁም በእርሱ ወይም በሌላ ሰው ይዞታ ያሉ መዛግብት፣ የሂሣብ መግለጫዎችን ሪኮርዶችን፣ እና የኮምፒዩተር ዳታዎችን ይመርመር ዘንድ አስፈላጊ መሣሪያዎችን ያቀርባል። በተጨማሪም በምርት ገበያው መርማሪ ባለሥልጣን እምነት አግባብነት አለባቸው የተባሉ ሰነዶችን እና ሌሎች ጽሑፎች ቅጂዎችን ይሰጣል።

ሐ. ምርመራ የሚያደርገው ምርት ገበያው ባለሥልጣን ምርመራውን በሚያደርግበት ወቅት የአባሉን፣ የዳይሬክተሩን የሠራተኛውን እና የተቀጣሪውን ቃሎች ለመመርመር ወይም ለመመዝገብ ይችላል።

መ. አባሉ በአግባቡ የሚጠበቅበትን ከምርመራው ጋር የተያያዘ ማንኛውንም ድጋፍ ዳይሬክተሩ፣ የሥራ ኃላፊዎች እና ቅጥር ሠራተኛው የመስጠት ግዴታ አለባቸው።

ሠ. የምርት ገበያው የምርመራ ባለሥልጣን አግባብነት ያላቸውን በአባሉ ደንበኛ ባንክ ወይም በሌላ ተቋም የተያዙ የፋይናንስ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ሪኮርዶችን የመመርመር መብት አለው።

ረ. የምርት ገበያው መርማሪ ባለሥልጣን የአባሉን የሂሣብ መዝገቦችንና ሪኮርዶችን የማየት መብት አለው።

17.3 ሪፖርት ስለማቅረብ

17.3.1 የምርት ገበያው መርማሪ ባለሥልጣን የምርመራውን ሪፖርት በተቻለው ፍጥነት ለምርት ገበያው ማቅረብ አለበት።

17.3.2 የምርት ገበያው መርማሪ አድራጊ ባለሥልጣን በምርት ገበያው ስም ሁሉንም የተሰጡትን ሰነዶች፣ ወረቀቶችና የተያያዙ ቅጂዎችን ለራሱ ሊያዛቸው ይችላል። የምርት ገበያው መርማሪ ባለሥልጣን በማናቸውም ጊዜ ሚስጥራዊነቱን መጠበቅ አለበት። ስለዚህም ለማንኛውም ሰው፣ ድርጅት፣ኩባንያ ወይም ባለሥልጣን በሥራ ላይ ባለ ሕግ ካልተገደደና በዚህ ረገድ ምርት ገበይው ካልፈቀደ በስተቀር ማንኛውንም መረጃ መስጠት አይችልም።

ሀ. የምርት ገበያው የምርመራውን ሪፖርት ከመረመረ በኋላ በምርመራ ሪፖርቱ መሠረት በአባሉ ላይ እርምጃ ከመወሰዱ በፊት አባሉ የመሰማት ዕድል እንዲያገኝ ሪፖርቱን ይሰጠዋል።

ለ. የምርት ገበያው አባሉ የሚሰጠው ማብራሪያ ወይም መግለጫ ካለ ይህንኑ ከተቀበለ በኋላ አባሉን ለሕዝብ ጥቅም ሲባል አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስድ ሊያዝዘው ይችላል።

ሐ. በዚህ ደንብ የተቀመጠው ቢኖርም በተወሰኑ ሁኔታዎች መሰማት አስፈላጊ ነው ብሎ ካላመነ፣ የመሰማት ዕድል ሳይሰጥ ወዲያውኑ እርምጃ ሊወሰድ ይችላል።

17.4 የመረጃ አሰባሰብና ሥርጭት

17.4.1 የምርት ገበያው ከደንቦች፣ ግብይቶች፣ ክርክር አፈታት፣ ሂሣብ አከፋፈል የሂሣብ መዝገቦችና ወይም ሌሎች ተያያዥ ነገሮችን በተመለከተ መግለጫ እና/ ወይም መረጃ እንዲሰጡት አባላትን መጠየቅ ይችላል።

17.4.2 የምርት ገበያው የአባላቱን ደንበኞች ዝርዝር ሁኔታ በሚስጥር ይይዛል። በሕግ ወይም በሌላ ባለሥልጣን ካልተፈቀደ በስተቀር በደንበኛው የምዝገባ ቅጽ ላይ የተመለከተውን የደንበኛውን መረጃ ወይም ሌላ የደንበኛውን መረጃ ለማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት መግለጽ የለበትም።

17.4.3 በደንቡ ላይ የተገለፁ ነገሮች ቢኖሩም ምርት ገበያው፣ ግብይትን የንግድ ውሎችን፣ የውሎችን አፈፃፀም፣የሂሣብ ሥራ በአባላት ላይ የተወሰዱ ወይም ከእርምጃው ጋር በተያያዘ የተጀመሩ ሂደቶች እና /ወይም ሌሎች ከአፈፃፀምና ከቁጥጥር ዓላማዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ጉዳዮች ጨምሮ ማናቸውንም መረጃ ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣን መ/ቤቶች ወይም ለሕዝቡ ይፋ ማድረግ ይችላል።

## 18. የኃላፊነት ወሰን

ምርት ገበያው ለአባላቶቹ ወይም በአባሉ ስም እንዲንቀሳቀሱ ለተፈቀደላቸው ወይም ላልተፈቀላቸው ሌሎች ሰዎች አድራጎት ኃላፊነት የለበትም።በተናጠል ወይም በጋራ ከመካከላቸው በአንዳቸው የተፈፀመ ድርጊት ወይም ያልተፈፀመ ድርጊት በማንኛውም ጊዜ ቢሆን የምርት ገበያው ወኪሎች በመሆን የፈፀሟቸው ወይም ያልፈፀሟቸው ድርጊቶች ሆነው መተርጐም የለባቸውም። በነዚህ የምርት ገበያ ደንቦች በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር በምርት ገበያው፣ በዳይሬክተሮች ቦርድ አባል/ ወይም ኮሚቴ እና በእሱ በተቋቋመው አመራር ወይም ሌላ በምርት ገበያው ስም የሚሠራ ሰው ላይ በአባሎቹ በኩል በተሰሩና በምርት ገበያው በተፈፀሙ ሥራዎች እና ሌሎች ከዚህ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ሆነው የምርት ግብይቱን ጉዳዮች የማስፋፋት፣ የማቀላጠፍ፣ የመርዳት፣ የመቆጣጠር ወይም የምርት ገበያውን ጉዳዮች የመምራት ዓላማዎች ያሏቸውና በምርት ገበያው አዋጅ ወይም በምርት ገበያው ደንቦች የተገለፁትን ዓላማዎች ለማሳካት የተሠሩት ላይ ማናቸውም ዓይነት ክስ ወይም ተዘዋዋሪ እርምጃ ሊወሰድ አይችልም።

## 19. የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች

19.1 ዋና ሥራ አስፈፃሚው ወይም በዋና ሥራ አስፈፃሚ የተሰየመ እና በዳይሬክተሮች ቦርድ ስያሜው የፀደቀ ሌላ ሰው የአስቸኳይ ሁኔታ አለ ብሎ ሲወሰን፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚው ወይም የተሰየመው ሰው እንደነገሩ ሁኔታ ወዲያውኑ ተፈፃሚነት ያለው ጊዜያዊ የአስቸኳይ ሁኔታ እርምጃ ወይም ደንብ ከባለሥልጣኑ ጋር በመመካከር ወይም በመተባበር ሊደነግግ ይችላል። ይህ አስቸኳይ ሁኔታ ለሃያ አራት ሰዓታት ሊቆይ ሲችል፣ ከሃያ አራት ሰዓታት በኋላ አስቸኳይ ሁኔታው ፀንቶ እንዲቆይ በዳይሬክተሮች ቦርድ መጽደቅ አለበት። ይህ የአስቸኳይ ሁኔታ ወይም ደንብ ምርት ገበያውን፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም በዚያ ውስጥ ያለ ሌላ ኮሚቴ ለአስቸኳይ ሁኔታው አስፈላጊ የሆኑና የሚከተሉትን እርምጃዎች ያካተተ እርምጃዎች እንዲወስዱ ሥልጣን ሊሰጥ ወይም ሊደነገግ ይችላል።

ሀ. የምርት ግብይቱን ማቋረጥ፣ወይም ማገድ፣

ለ. የውል መደቦችን /ዓይነቶች መሠረት በማድረግ የምርት ግብይቱን ማቋረጥ ወይም ማገድ፣

ሐ. ውሎችን መሰረዝ ወይም ማሻሻል፣

መ. የንግድ ግብይቱን በሙሉ ወይም በከፊል በካሽ ግብይት ደረጃ መወሰን፣

ሠ. በውል ውስጥ የሚደነገጉትን የርክክብ ጊዜያትን ማራዘም፣ የርክክብ ቦታዎችንና የርክክብ መንገዶችን መቀየር፣
ረ. አግባብ ያላቸው የካሣ ድንጋጌዎች እንዳሉ ሆነው በውል ከተገለፀው ምርት እኩል ወይም የበለጠ ጥራት ያለው አንድ ለግብይት የሚሆን ሸቀጥ እንዲጫረት ይቀርብ ዘንድ መፍቀድ፣
ሰ. በአንድ ውል አቋሞች/ሁኔታዎች ላይ ወይም የዋጋ ወሰኖች ላይ ለውጥ ማድረግ ወይም ማሻሻል፣
ሸ. ግልፅ አቋሞችን ጨምሮ ነገር ግን በእነሱ ብቻ ላይ ሳይወሰን አባላት አንድ የተከሰተ ሁኔታ ወይም አሠራርን እንዲያስተካክሉ ወይም እንዲቋቋሙ ያስችላቸዋል ብሎ ያሰበውን ማንኛውንም መመሪያ ለአባላት መስጠት፣
ቀ. በደንበኛው ስም በአባሉ የተያዙ ውሎችን ወይም ለነኚህ ውሎች መያዣ ወይም ዋስትና የሆኑ ገንዘቦችን ውሉን ለመፈፀም ፈቃደኛ ለሆኑ ወይም ግዴታ ላለባቸው ለአንድ ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ አባላት እንዲያስተላልፍ ማዘዝ፣
በ. የምርት ግብይት ሰዓታትን ማራዘም፣ በተወሰኑ ጊዜያት መገደብ ወይም መለወጥ፣
ተ. በአንዱ ወይም በሁሉም ውሎች የምርት ግብይቶችን ማቋረጥ ወይም ማገድ፣
ቸ. አባላት ወይም ደንበኞች የተለዩ ተቀማጭ ገንዘቦች እንዲያስዙ ማድረግ ወይም
ኀ. የምርት ግብይት ደንቦች ወይም የከፋይ ተቋሙ ደንቦች ድንጋጌዎችን ማሻሻል ወይም ማገድ።

19.2 ቀደም ሲል በተገለፀው ዐረፍተ ነገር መሠረት የተወሰደ ማንኛውም እርምጃ በይሬክተሮች ቦርድ በማንኛውም ጊዜ እንደገና ሊታይ፣ ሊሠረዝ፣ ሊታገድ ወይም ሊሻሻል ይችላል። ከላይ የተገለፀውን ዐረፍተ ነገር መሠረት በማድረግ ተግባራዊ የሆኑ ድንጋጌዎች በዳይሬክተሮች ቦርድ ሁኔታዎችን ከግምት በማስገባት በተቻለው ፍጥነት እንደገና ሊታዩ እንዲሁም ሊሰረዙ፣ ሊታገዱ ወይም ሊሻሻሉ ይችላሉ።

19.3 የአስቸኳይ ሁኔታ ትርጓሜ

19.3.1 የአስቸኳይ ሁኔታ ማለት ፍትሐዊ፣ ሥርዓት ያለውንና ግልፅ የሆነውን የምርት ግብይት፣ የካሽ ሂደት፣ ክፍያ ርክክብ እና የውል ዓይነቶች/ መደቦችን የሚያሰጋ ወይም ሊያሰጋ የሚችል አንድ ሁኔታ ወይም አሠራር ሲሆን፣ የዚህ ዐረፍተ ነገር ጠቅላላነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታነት ሊካተቱ ይችላሉ።

ሀ. አካባዊ አስቸኳይ ሁኔታ /ለምሣሌ እሳት ወይም ሌሎች ጉዳቶች፣ የቦምብ ሥጋት፣ የሽብር ተግባሮች፣ እጅግ አስቸጋሪ የአየር ጠባይ፣ የኃይል መቋረጥ፣ ወይም የትራንስፖርት አገልግሎት መቋረጥ/፣
ለ. የመገናኛ መንገዶች እና ዘዴዎች በመቋረጣቸው በምርት ገበያው ግብይት እና/ወይም ከክፍያ ሥርዓቶች ጋር አጠቃላይ የግንኙነት መቋረጥ፣
ሐ. ፍትሐዊ፣ ሥርዓት ያለው ግልጽ ገበያን ለማካሄድ ተቃራኒ የሆነ ሁኔታ ወይም አሠራር ሲኖር/ ለምሣሌ የገበያ ማዕዘን፣ የገበያ ማዛበትንና እና የንግድና ገንዘብ የመሰሉ ቀውሶች እና
መ. በመንግሥት፣ በመንግሥት መነሻነት፣ በምርት ገበያው ወይም በሌላ አካል ወይም ልዩ በሆኑ ወይም ባልተጠበቁ ሁኔታዎች እርምጃዎች ሲወሰዱ ወይም ሊወሰዱ ሲታቀዱና ከፍትሐዊ የግብይት መርሆዎች ወይንም ከሕዝብ ጥቅም ጋር ልዩነት ሲኖራቸው ወይም አስጊ ሲሆኑ ወይም ሊያሰጉ ሲችሉ።

19.4 ማስታወቅና መመዝገብ

በባለሥልጣኑ መመሪያ መሠረት በዚህ ደንብ የምርት ገበያው የወሰዳቸው ወይም ሊወስዳቸው ያሰባቸውን እርምጃዎች ለባለሥልጣኑ ያስታውቃል። ይህ ማስታወቂያ ከተቻለ እርምጃውን ከመውሰዱ ጥቂት ቀደም ብሎ ወይም እርምጃውን በመውሰድ ላይ እንዳለ ወይም እርምጃው እንደተወሰደ ወዲያውኑ መሰጠት አለበት። ይህ እርምጃ ሲወሰድ የውሣኔ አሰጣጥ ሂደቱ እና ምክንያቶቹ በጽሑፍ ተመዝግበው መያዝ አለባቸው። ለዚህ አንቀጽ ዓላማ ማስታወቂያ ማለት የስልክ ጥሪ ሆኖ ከጥሪው በኋላ በጽሑፍ ማስታወቂያ፣ በፋክስ ወይም በኤሌክትሮኒክ መልዕክት መፃፍ ማለት ነው።

19.5 የጥቅም ግጭቶች

በዚህ ደንብ የዋና ሥራ አስፈፃሚው ወይም የእሱ ወይም የእሷ ተሻዕሚዎች እርምጃ ይወሰዱ ዘንድ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ መሠረት እንደአግባብነታቸው አስፈላጊው ማሻሻያና ለውጦች ተደርገው የእነዚህ ደንቦች ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ሰነዶች ድንጋጌዎች ተፈፃሚዎች ይሆናሉ።

## 20. ሚስጢር ስለመጠበቅ

20.1 ማንኛውም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ወይም በዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም በምርት ገበያው ደንቦች መሠረት የተቋቋመ ኮሚቴ አባል በቦርዱ ወይም በኮሚቴ አባልነቱ የሥራ ግዴታውን ለመወጣት ካልሆነ በስተቀር በቦርዱ ወይም በኮሚቴ አባልነቱ ተሳትፎ የሚያገኛቸውን ለሕዝብ ይፋ የማይሆኑ መረጃዎች ሊጠቀም ወይም ይፋ ሊያደርግ አይችልም።

20.2 ማንኛውም ሠራተኛ፣ ተቀጣሪ ወይም የምርት ገበያው ወኪል /ሀ/ ስለ አንድ ምርት ወሣኝ የሆነና ለሕዝብ ይፋ የማይሆን መረጃ ካለው ከዚህ ምርት ጋር በተያያዘ መገበያየት አይችልም /ለ/ ወይም ይህ የሥራ ኃላፊ፣ ቅጥር ሠራተኛ ወይም ወኪል መረጃው ቢገለጽ ምክንያታዊ በሆነ አስተሳሰብ መረጃው ቢገለፅ በዚህ ምርት የሚገበያይ ሌላ ሰውን ይረዳል ወይም ይጠቅመዋል ብሎ ካመነ፣ ይህ የሥራ ኃላፊ፣ቅጥር ሠራተኛ ወይም ወኪል ከቅጥሩ በተያያዘ ያገኘውን ወሣኝ ለሕዝብ-የማይገልጽ ወይም ይፋ የማይሆን መረጃ ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት የለበትም።

20.3 ለዚህ ደንብ ዓላማ "ተቀጣሪ" "ወሣኝ መረጃ" "ለሕዝብ ይፋ የማይሆን መረጃ' "ከምርት ጋር የተያያዘ ወለድ" እና "የምርት ወለድ" የሚሉት ቃላቶች ወይም ሐረጐች ትርጓሜ በባለሥልጣኑ መመሪያ ላይ የተሰጣቸው ትርጓሜ ይሆናል።

20.4 የምርት ገበያው እያንዳንዱ አባል ያለበትን ግዴታ በተመለከተ የምርት ገበያውን ታሪክ እና ለሕዝብ ክፍት ወይም ነፃ ከሆነው መረጃ ውጭ በደንበኞች የምዝገባ ቅጽ የተመለከተው የአባላት ደንበኞች መረጃ ወይም ሌላ መረጃ በአባሉ በምሲጢር የሚያዝ መሆኑን ያውቃል። የመረጃው ምንጭ ከየትም ቢሆን ምርት ገበያው በሚቀበላቸው መረጃዎች ላይ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

ሀ. ምርት ገበያው ኃላፊነቱን ለመወጣት ወይም በሕግ፣ በመመሪያ፣ በደንብ፣ በባለሥልጣኑ ደንብ ወይም መመሪያ በምርት ገበያው ላይ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ወይም የመንግሥት አካል የተሰጡትን ግዴታዎች ለመፈፀም እነዚህን ሚስጥራዊነታቸው የሚጠበቁ መረጃዎችን በውስጥ ሊጠቀምባቸው ይችላል፣ እንዲሁም

ለ. ምርት ገበያው እነዚህን ምስጢርነታቸው የሚጠበቁ መረጃዎችን በምርት ገበያው ላይ ምርት ጥቅም ያለው ዳይሬክተር/ሮች/ ተቀጣሪ/ዕዎች/ አማካሪዎች ሦስተኛ ወገንን ጨምሮ ለሦስተኛ ወገኖች ወይም ለእነሱ ጥቅም፣ መጠቀም፣ ማሰራጨት፣ ማቅረብ፣ መስጠት፣ እንዲያገኙ ማድረግ፣ ወይም መሸጥ አይችልም።

# 21. ደንብ ስለማሻሻል

21.1 ምርት ገበያው ይህን ደንብ በየጊዜው ያሻሽላል፤ አባላቱን ስለተደረገው ማሻሻያ በማሻሻያ ማስታወቂያ ያሳውቃቸዋል።በዚህ ሁኔታ የተደረገ ማሻሻያ በባለሥልጣኑ በፀደቀ በ14ኛው ቀን ሕጋዊ ውጤት ይኖረዋል።

21.2 በማሻሻያ ማስታወቂያው መገዛት የማይፈልግ ማንኛውም አባል ማሻሻያው በወጣ በአሥራ አራት ቀናት ውስጥ ከምርት ገበያው አባልነቱ መውጣቱን ወይም መልቀቁን በጽሑፍ ለምርት ገበያው ያሳውቃል።

# 22. የደንቡ ድንጋጌዎች በተናጠል የሚታዩ ስለመሆናቸው

በማናቸውም ሁኔታና ረገድ የዚህ ደንብ የትኛውም ክፍል/ድንጋጌ ፈራሽ ወይም ሊፈጸም የማይችል ቢሆን የተቀረው የደንቡ ክፍል/ድንጋጌ በምንም መልኩ አይነካም/አይታገድም።

## 23. ማስታወቂያዎች

23.1 ማስታወቂያዎች በሚከተሉት መንገዶች መላክ አለባቸው ፡-

ሀ. በፋክስ ወይም

ለ. በፖስታ ወይም

ሐ. በቴሌግራም ወይም

መ. በእጅ ማድረስ ወይም

ሠ. ኤሌክትሮኒክ መንገድ -ዲጂታል ኢንኮድ ተደርጎ የሚተላለፍ ኤሌክትሮኒክ መረጃ ነው፡

ረ. ሀገር አቀፍ ሥርጭት ባለው በታወቀ ቢያንስ አንድ ጋዜጣ ወይም በመጨረሻ በታወቀው የተከራካሪ ወገኖች አድራሻ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ በሚወጣ ማስታወቂያ።

23.2 በማስታወቂያው ላይ ተቀባይ ተብሎ አድራሻው የተገለፀው ሰው ማስታወቂያው እንዳልደረሰው ካላረጋገጠ በስተቀር በዚህ አንቀጽ መሠረት እንደደረሰው ተቆጥሮ በማስታወቂያው ውስጥ የተካተቱን ጉዳዮች ይፈፅማል።

## 24. ስለ ደንቡ ተፈጻሚነት

ይህ የተሻሻለ ደንብ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን አዋጅ ቁጥር 551/2000 አንቀጽ 6(3) መሰረት በባለሥልጣኑ እንደጸደቀ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

**በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን ቦርድ ጥቅምት 13 ቀን 2007 ዓ.ም**
**በአዲስ አበባ ጸደቀ፡፡**